
መፅሐፍቅዱስ ቁርአን

# እውነቱን በፍቅር መግለፅ
(Amharic)

**By**
**Adnan Sileshi**

# ማውጫ

1. አስገራሚ የአላህ መሀላዎች.......................................4
2. የመሀመድን ነቢይነት የማልቀበልባቸው 12 ምክንያቶች.............25
3. ስለ መሀመድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተተንብዮአል?..............34
4. የጀነት በር ተከፍቷል...............................................38
5. ኢደል አድሃ በኢንጂል...............................................44
6. ሴቶች በቁርዓን በሀዲስ እና በመጽሐፍ ቅዱስ.......................50
7. የቁርዓን ምዕራፎች ስያሜ ትርጉም.....................................53
8. ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ መሆኑን ተናግሯል?........................62
9. ኢንጂል ተበርዟልን?....................................................75
10. የደህንነት ማረጋገጫ (ክፍል 1 እና 2)..............................91
11.የኢየሱስና የአብ አንድነት የዓላማ ብቻ ወይንስ የባህሪም ጭምር?.96
12. የሴቶች ምስክርነት በእስልምና.......................................97
13. ኢየሱስ ያህዌ ነው................................................ 101

## አስገራሚዎቹ የአላህ መሐላዎች

ሰዎች የሚምሉት የተናገሩት ቃል እውነት መሆኑን ወይንም የገቡት ቃል እንደማይለወጥ ማረጋገጫ ለመስጠት ነው። ስለዚህ በመሐላቸው የሚጠሩት ማንኛውም ነገር ወይንም አካል ከቃላቸው የሚበልጥ ዋጋ ሊኖረው ይገባዋል፡፡ በመሐላ የምንጠራው ስም ከፍ ባለ ቁጥር የቃላችንም ክብደት በዚያው መጠን ይጨምራል። ሰዎች ሊምሉበት የሚችሉት የመጨረሻው ትልቅ ስም የፈጣሪያቸው ስም ነው። ይህ መሐላ እጅግ ከባዱ ነው።

እግዚአብሔር አምላካችን ከእርሱ የሚበልጥ ምንም ነገር ባለመኖሩ ሲምል በራሱ ይምላል እንጂ በፍጡራን አይምልም። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡-

“ቃሌ ከአፌ በጽድቅ ወጥታለች፥ አትመለስም፦ ጕልበት ሁሉ ለእኔ ይንበረከካል፥ ምላስም ሁሉ በእኔ ይምላል ብዬ በራሴ ምያለሁ።” (ኢሳ. 45፡23)

“እናንተ በግብጽ ምድር የምትኖሩ ይሁዳ ሁሉ፥ ስለዚህ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ፤ በግብጽ ምድር ሁሉ በሚኖር በይሁዳ ሰው ሁሉ አፍ ስሜ ከእንግዲህ ወዲህ፦ ሕያው እግዚአብሔርን! ተብሎ እንዳይጠራ፥ እነሆ፥ በታላቅ ስሜ ምያለሁ፥ ይላል እግዚአብሔር።” (ኤር. 44፡26)

“እግዚአብሔርም ለአብርሃም ተስፋ በሰጠው ጊዜ። በእውነት እየባረክሁ እባርክሃለሁ እያበዛሁም አበዛሃለሁ ብሎ፥ ከእርሱ በሚበልጥ በማንም ሊምል ስላልቻለ፥ በራሱ ማለ።” (ዕብ 6፡13-14)

እግዚአብሔር አምላክ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በገዛ ራሱ ስምና ክብር እንጂ በሌላ ፍጥረት ሲምል አይታይም። የዚህ ምክንያቱ ከመሐላ ትርጉም ጋር የተያያዘ ነው። ይህም ቀደም ሲል እንደገልጽነው መሐላ ቃላችን የማይለወጥ መሆኑን ማረጋገጫ ለመስጠት ከቃላችን የሚበልጥ ስም የምንጠራበት የመጨረሻው ንግግር በመሆኑ ነው።

“ሰዎች ከእነርሱ በሚበልጠው ይምላሉና፥ ለማስረዳትም የሆነው መሐላ የሙግት ሁሉ ፍጻሜ ይሆናል” (ዕብ. 6፡16)።

እግዚአብሔር አምላክ በፍጡራን የሚምል ከሆነ የቃሉን ክብር ወደ ፍጡራን ደረጃ አውርዶታል ማለት ይሆናል። ይህ ደግሞ ከክብሩና ከግርማ ሞገሱ ጋር የማይሄድ በመሆኑ እግዚአብሔር አምላክ በፍጡራን አይምልም።

የእስልምና ሃይማኖት መመርያ የሆነው ቁርኣን ግን ከቃሉ ክብደትና ከግርማው ጋር በማይመጣጠን ሁኔታ አላህ በፍጥረታት መማሉን ይነግረናል። አላህ ከማለባቸው ፍጥረታት መካከል የሚበዙቱ እንኳንስ ለፈጣሪ ይቅርና ለሰው ልጆች እንኳ የማይመጥኑ ለመሐላ ቃል የማይበቁ ሆነው እናገኛቸዋለን። በቁርኣን ከተጠቀሱት የአላህ መሐላዎች መካከል የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያህል፡-

በሙሐመድ ዕድሜ፡- 15:72 “በዕድሜህ እንምላለን”

በብዕር፡- 68:1 “በብርዕ እምላለሁ በዚያም መልአኮች በሚጽፉት”

በመካ ከተማ፡- 90:1 “በዚህ አገር በመካ እምላለሁ”

በፈረሶች፡- 100:1 “እያለከለኩ ሩዋጮች በኾኑት ፈረሶች እምላለሁ”

በወጋገን፡- 84:16 “በውጋገኑ እምላለሁ”

በፕላኔቶች፡- 81:15 “ተመላሾቹም በሆኑት ዐዋድያት እምላለሁ”

በረፋድ፡- 93:1 “በረፋዱ እምላለሁ”

በሌሊት፡- 92:1 “በሌሊቱ እምላለሁ በጨለማው በሚሸፍን ጊዜ”
በፀሐይ 91:1 “በፀሐይና በብርሃኗ እምላለሁ”
በጎህ፡- 89:1 “በጎህ እምላለሁ”
በሌሊት ሰማይ፡- 86:1 “በሰማዩ፣ በሌሊት መጪውም እምላለሁ”
በከዋክብት መጥለቂያዎች፡- 56:75 “በከዋክብትም መጥለቂያዎች እምላለሁ”
በሰማይ፡- 86:11 “የመመለስ ባለቤት ብሆነችው ሰማይም እምላለሁ”፤ 85:1 “የቡርጆች ባለቤት በሆነችው ሰማይ እምላለሁ”፤ 51:7 “የከዋክብት መንገዶች ባለቤት በሆነችው ሰማይ እምላለሁ”
በኮከብ፡- 53:1 “በኮከብ እምላለሁ በገባ ጊዜ”
በጨረቃ፡- 74:32 “ከክሕዱት ይከልከሉ፤ በጨረቃ እምላለሁ”
በጡር ጋራ፡- 52:1 “በጡር ጋራ እምላለሁ”
በበለስና በዋይራ፡- 95:1 “በበለስና በዘይት ወይራ፣ እምላለሁ”
በሰው ነፍስ፡- 75:2 “ራሷን ወቃሽ በሆነች ነፍስም እምላለሁ”
በዕለተ ትንሣኤ፡- 75:1 “አይደለም፤ በትንሣኤ ቀን እምላለሁ”
በጊዜያት፡- 103:1 “በጊዜያቱ እምላለሁ”
በመላእክት፡- 77:6 “ምክንያትን ለማስወገድ፣ ወይም ለማስፈራራት፣ ጣይዎች በሆኑት መላእክት እምላለሁ”፤ 79:5 ነገርንም አስተናባሪዎች በሆኑት መላእክት እምላለሁ”
በቁርኣን፡- 50:1 “በተከበረው ቁርኣን እምላለሁ”፤ 38:1 “የክብር ባለቤት በሆነው ቁርኣን እምላለሁ”
በራሱ፡- 15:92 “በጌታህም እንምላለን”፤ 92:3 “ወንድና ሴትን በፈጠረውም አምላክ እምላለሁ”፤ 16:63 “በአላህ እንምላለን”
አላህ በነዚህ ሁሉ ነገሮች ከማለ በኋላ አንድም ነገር እንዳይቀረው የፈለገ ይመስል በሚታዩትና በማይታዩት ነገሮች ሁሉ ሲምል ይገኛል፡- 69:38-39 “በምታዩትም ነገር እምላለው፡፡ በማታዩትም ነገር፡፡”
የቁርአኑ አላህ ሲምል አይመርጥም፡፡ የራሱን ስም ጨምሮ ለመሐላ የማይገለገልበት ስም የለም፡፡ በሰማይና በምድር ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ሊያዩት የሚችሉትም ሆነ የማይችሉት የትኛውም ፍጥረት አይቀረውም፡፡ እንዲህ ያለ መሐላ ለፈጣሪ ቃል ክብር የማይሰጥ፣ ቃል ተቀባዩን የማያስተማምንና የመሐላን ትክክለኛ ትርጉም የሳተ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡
ይህ የቁርአኑ አላህ መሐላ ከእስላማዊ የተውሒድ አስተምሕሮ ጋር ይጋጫል፡፡ በእስላማዊ የተውሒድ አስተምሕሮ መሠረት በአላህ ስም ካልሆነ በስተቀር በሌላ ፍጥረት ስም መማል ይቅርታ የሌለው የሺርክ ኃጢአት ነው፡-
ዑመር እንዳወራው ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡- “አንድ ሰው የሚምል ከሆነ በአላህ ስም ብቻ ይማል፡፡” ቁረይሾች በአባቶቻቸው ይምሉ ነበር ነገር ግን ነቢዩ “በአባቶቻችሁ አትማሉ” ብለዋል፡፡ (Sahih Al-Bukhari, Volume 5, Book 58, Number 177)
ለምንድነው ይህ የተባለው? በሙሐመድ እምነት መሠረት ለመሐላ ብቁ የሆነው የአላህ ስም ብቻ በመሆኑ ነው፡፡ ነገር ግን የሰው ልጆች በአላህ ስም ብቻ በመማል ክብርን እንዲሰጡትና በሌላ ቢምሉ ከኃጢአት እንደሚቆጠርባቸው የደነገገው ሙሐመድ በቁርኣን ውስጥ አላህ ከግዑዛን ፍጥረታት ጀምሮ በሚታዩትና

በማይታዩት ፍጥረታት ሁሉ እንደማለ በመግለፅ ይህንን መርህ እንደጣሰ ይነግረናል፡፡ ምናልባት ሙስሊም ሰባኪያን ይህ መርህ ለሰው እንጂ ለአምላክ እንደማይሠራ ይነግሩን ይሆናል፡፡ ነገር ግን ለመሐላ ብቁ የሆነው የአምላክ ስም ብቻ ከሆነ አላህ ከራሱ ውጪ ባሉት ፍጡራን ሲምል ፍጡራን ለመሐላ ብቁ የሚሆኑበት አመክንዮ የለም፡፡ ሰዎች በስሙ ብቻ ምለው ለቃላቸው ክብደት እንዲሰጡ ያዘዘው አምላክ መልሶ ደግሞ በፍጡራን በመማል ቃሉን አያቃልልም፡፡

አንዳንድ ሙስሊም ሰባኪያን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ በመጥቀስ እግዚአብሔር አምላክ በፍጡራን እንደማለ ለማሳየት ሞክረዋል፡፡ የሚጠቅሱት ጥቅስ እንደሚከተለው ይነበባል፡-

"እግዚአብሔር በያዕቆብ ክብር እንዲህ ብሎ ምሎአል፡- ሥራቸውን ሁሉ ለዘላለም ምንም አልረሳም፡፡" (አሞፅ 8፡7)

"The Lord hath sworn by the excellency of Jacob, Surely I will never forget any of their works." (KJV)

በዚህ ስፍራ "ክብር" ተብሎ የተጠቀሰው ቃል የእብራይስጥ አቻ "ገዖን" የሚል ሲሆን "ክብር፣ ግርማ፣ ሞገስ፣ ትምክህት፣ ትዕቢት፣ ኩራት" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል፡፡ ይህ ቃል የእግዚአብሔርን ክብር ለማመልከት በተደጋጋሚ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጥቅም ላይ ውሏል (ዘጸ. 15፡7፣ ኢዮብ 37፡4፣ ኢሳ. 2፡10፣ 2፡19፣ 2፡21፣ 24፡14፣ ሚክ. 5፡4)፡፡ ከዚህም በመነሳት በዚህ ቦታ የያዕቆብ ክብር፣ ግርማ፣ ሞገስ፣ ኩራት፣ የተባለው ራሱ እግዚአብሔር እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት በአንድ ድምፅ የሚስማሙበት እውነታ ነው፡፡

"The Lord hath sworn by the excellency of Jacob — That is, by himself" (Benson Commentary)

"By the excellency of Jacob – that is, by Himself who was its Glory, as Samuel calls Him "the Strength" 1 Samuel 15:29 or the Glory of Israel. Amos had before said, "God sware by His Holiness" and "by Himself" or "His soul." (Barnes' Notes on the Bible)

"Lord hath sworn by the excellency of Jacob—that is, by Himself, in whom Jacob's seed glory [Maurer]. Rather, by the spiritual privileges of Israel, the adoption as His peculiar people [Calvin], the temple, and its Shekinah symbol of His presence. Compare Am 6:8, where it means Jehovah's temple (compare Am 4:2)." (Jamieson-Fausset-Brown Bible Commentary)

"By the excellency of Jacob; by himself, for God cannot swear by any greater, and he is called the excellency of Jacob, Psalm 47:4." (Matthew Poole's Commentary)

"The Lord hath sworn by the excellency of Jacob,... Not by the ark, as R. Japhet; nor by the temple, as Kimchi; but by himself; which sense Kimchi also mentions, and Aben Ezra; the God of Jacob and his glory, the most excellent of all Jacob's enjoyments, and of whom he had reason to boast and glory; see Amos 6:8." (Gill's Exposition of the Entire Bible)

"The pride of Jacob may be Jehovah Himself (cf. 1 Samuel 15:29)" (Cam-

bridge Bible for Schools and Colleges)
“The Excellency of Jacob. This is a title of God himself, as in Hosea 5:5; Hosea 7:10, where it is rendered “pride.” Thus the Lord is said to swear by his holiness (Amos 4:2), by his soul (Amos 6:8; comp. 1 Samuel 15:29). So here he swears by himself, who is the Glory and Pride of Israel; as truly as he is this, he will punish.” (Pulpit Commentary)
ስለዚህ ይህ ጥቅስ እግዚአብሔር በፍጡራን ስለመማሉ ማሳያ ሊሆን አይችልም፡፡
አንዳንድ ሙስሊም ሰባኪያን ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ በራሱ ስለማለ አላህ በፍጡራን ቢምል ምን ችግር አለው? የሚል አስቂኝ ጥያቄ አንስተዋል። የሚጠቅሷቸው ጥቅሶች የሚከተሉት ናቸው፡-
“በጌታችን በክርስቶስ ኢየሱስ ባለኝ በእናንተ ትምክህት እየማልሁ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ዕለት ዕለት እሞታለሁ።” (1ቆሮንቶስ 15፡31)
“እናንተ ደግሞ ትምክህታችን እንደምትሆኑ እንዲሁ ትምክህታችሁ እንድንሆን፥ በከፊል ስለ እኛ እንዳስተዋላችሁ ፈጽማችሁ ታስተውሉት ዘንድ ተስፋ አደርጋለሁ። (2ቆሮንቶስ 1፡14)
ሁለቱን ጥቅሶች በማገጣጠም “ጳውሎስ ‹ትምክህታችሁ እኛ ነን› ብሎ ተመልሶ ‹በእናንተ ትምክህት እየማልሁ› በማለት በራሱ ምሏል” ይላሉ። ይህ በሦስት ምክንያቶች ስህተት ነው። አንደኛ ጳውሎስ ፍጡር በሆነው በራሱ ማንነት ስለማለ አላህ በፍጡራን ቢምል ችግር የለውም የሚለው አመክንዮ ተቀባይነት የለውም። ሁለተኛ ጳውሎስ በራሱ ምሎ ከሆነ ለገዛ ንግግሩ የሰጠውን ዋጋ የሚያሳይ ነው። ቢያንስ ከራሱ ባነሰ ነገር አልማለም። አላህ ቃሉ ከፍጡራን በላይ እንደሆነ የሚገነዘብ ከሆነ በፍጡራን መማል የለበትም ምክንያቱም ቃሉ ከፍጡራን በላይ ነውና። ሦስተኛ በትርጉም ችግር ምክንያት እንጂ 1ቆሮንቶስ 15፡31 ላይ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አልማለም። በቦታው የተጠቀሰው የግሪክ ቃል “ኔ” የሚል ሲሆን “ማረጋገጥ” ተብሎ ቢተረጎም ይበልጥ ትክክል ይሆናል። አዲሱ መደበኛ ትርጉም “አረጋግጣለሁ” በማለት ተርጉሞታል።
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዕለት ተዕለት መግባቢያችን ውስጥ ቃላችን “አዎን” እና “አይደለም” እንዲሆን እንጂ መሐላ አስፈላጊ አለመሆኑን አስተምሯል፡-
“ደግሞ ለቀደሙት፦ በውሸት አትማል ነገር ግን መሐላዎችህን ለጌታ ስጥ እንደተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፦ ከቶ አትማሉ፤ በሰማይ አይሆንም የእግዚአብሔር ዙፋን ነውና፤ በምድርም አይሆንም የእግሩ መረገጫ ናትና፤ በኢየሩሳሌምም አይሆንም የታላቁ ንጉሥ ከተማ ናትና፤ በራስህም አትማል፥ አንዲቱን ጠጉር ነጭ ወይም ጥቁር ልታደርግ አትችልምና። ነገር ግን ቃላችሁ አዎን አዎን ወይም አይደለም አይደለም ይሁን፤ ከነዚህም የወጣ ከክፉው ነው።” (ማቴ. 5፡33-36)
ጌታችንኢየሱስክርስቶስበእግዚአብሔርፍጥረትናግዛትውስጥባለበማንኛውም ነገር መማል ትክክል አለመሆኑን አስተምሯል። ይህ ማለት ግን በምንም ሁኔታ መማል አይቻል ማለት አይደለም። እርሱ ራሱ ሊቀ ካህኑ በመሐላ በጠየቀው ጊዜ መሐላውን በማክበር ምላሽ ሰጥቷል (ማቴ. 26፡63-64)። ቅዱሳንም የጌታን ስም ጠርተው ሲምሉ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ታይተዋል (ሐዋ. 21፡23-26፣ ሮሜ 9፡1፣

ገላ. 1፡20፤ ራዕይ 10፡5-6)።
መሐላ በክርስትና እጅግ ጥብቅ ጉዳይ ነው። በሁሉም አጋጣሚ የእግዚአብሔርን ስም በመጥራት ማቃለል በአሥርቱ ትዕዛዛት ከተከለከሉት ተግባራት መካከል አንዱ ነው፡-
“የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፤ እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነጻውምና” (ዘጸአት 20፡7)።
እስልምና በመሐላ ላይ ያለው አቋም በእጅጉ የላላ ነው። ሙስሊሞች የአምላካቸውን ስም ጠርተው መተማመን እንኳ እስከማይችሉ ድረስ “ወላሂ (በአላህ እምላለሁ)” እያሉ በእንቶ ፈንቶ ጉዳዮች መማል የባሕላቸው አካል ነው፡፡ ከአንድ ደካማ ክርስቲያን ይልቅ አንድ ጠንካራ የሚባል ሙስሊም በሆነው ባልሆነው በአምላኩ ስም እየማለ የአምላኩን ስም ሲያቃልል ይውላል። ሙሐመድ በብዙ ሐዲሳት ውስጥ መሐላ በማያስፈልግባቸው ጉዳዮች በመማል መጥፎ ምሳሌ ሆኗቸዋል። አምላካቸው አላህም ግርማ ሞገሱን በማይመጥኑ በግዑዛንና በጥቃቅን ፍጥረታት በመማል ቃሉን አቃሏል። አላህ የተባለው ይህ የሙሐመድ አምላክ በራሱ ብቻ ከሚምለው የነቢያት አምላክ ከያሕዌ እግዚአብሔር ምንኛ የተለየ ነው!

## ሙሐመድን ነቢይነት የማልቀበልባቸው 12 ምክንያቶች

ሙስሊም ወገኖች ክርስቲያኖች ሙሐመድን እንደ እውነተኛ ነቢይ ለምን እንደማይቀበሉ በመገረም ይጠይቃሉ። ምናልባትም ክርስቲያኖች “የተሳሳቱ ህዝቦች በመሆናቸው” እውነትን ለመቀበል ዝግጁዎች አይደሉም ብለው ያስቡ ይሆናል። ነገር ግን እኔ በግሌ እንደ አንድ ክርስቲያን ሙሐመድ በሙሴና በሌሎች ነቢያት አምላክ እንደተላከ የሚያረጋግጥልኝን ማስረጃ ባገኝ ኖሮ ነቢይነቱን የማልቀበልበት ምክንያት አልነበረም። እውነቱን ለመናገር ግን በእስልምና የመጨረሻው ነቢይ እንደሆነ የሚታመንበት ሙሐመድ እንኳንስ በመጽሐፍ ቅዱስ የነቢይነት መስፈርት ተመዝኖ ይቅርና በእስልምና መጽሐፍት ውስጥ በሰፈረው የግል ታሪኩ እንኳ ነቢይነቱን አምኜ እንዳልቀበል የሚያስገድዱኝ ብዙ ዘገባዎች አሉ። በዚህ ጽሑፍ ሙሐመድን እንደ እውነተኛ ነቢይ የማልቀበልባቸውን ምክንያቶች በዝርዝር አቀርባለሁ።

### 1. ለነቢይነቱ ተጨባጭ ማስረጃ አለመስጠቱ

የሙሐመድን ነቢይት የማልቀበልበት መሠረታዊው ምክንያት ለነቢይነቱ የሚሆን የረባ ማስረጃ አለማቅረቡ ነው። ሙሐመድ በመካ ከተማ ስብከቱን ሲጀምር ለነቢይነቱ ማረጋገጫ የሚሆን ምልክት እንዲያሳይ በተደጋጋሚ ቢጠየቅም ጠያቂዎቹን በገሃነም ከማስፈራራትና ጥያቄዎቻቸውን በዘዴ ከማለፍ በዘለለ ምንም ዓይነት ምልክት ማሳየት አልቻለም ነበር። በሐዲስ መጻሕፍት የተመዘገቡ ብዙ የተዓምራት ታሪኮች ቢኖሩም በቁርኣን ውስጥ ሙሐመድ እንዳደረገው የተመዘገበ ምንም ዓይነት ማስረጃ አለመኖሩ በሐዲሳት የተመዘገቡት ታሪኮች ከክፍለ ዘመናት በኋላ የተጻፉ ተረታ ተረቶች መሆናቸውን ያስገነዝበናል። በቁርኣን ውስጥ ሙሐመድ ተዓምር ማድረጉን የሚገልፅ ምንም ዓይነት ማስረጃ ካለመኖሩም በላይ ተዓምራትን ማድረግ መቻሉ በገሃድ ተስተባብሏል። ለአብነት ያህል፡-

ሱራ 2:118 “እነዚያም የማያውቁት (አንተ መልክተኛ ስለመኾንህ) አላህ አያናግረንም ኖሮአልን? ወይም (ለእውነተኛነትህ) ታምር አትመጣልንም ኖሮአልን? አሉ። እንደዚሁ እነዚያ ከነሱ በፊት የነበሩት እንደ ንግግራቸው ብጤ ብለዋል። ልቦቻቸው (በክሕደት) ተመሳሰሉ። ለሚያረጋግጡ ሕዝቦች አንቀጾችን በእርግጥ አብራርተናል።”

ሙሐመድ የመጨረሻውና ታላቁ የፈጣሪ ነቢይ አድርጎ ራሱን ከማቅረቡ አንፃር የአድማጮቹ ጥያቄ ተገቢና ትክክል ነበር። ከፈጣሪ ነቢያት ሁሉ የላቀ ደረጃና አስፈላጊነት እንዳለው የተናገረ ሰው ቢያንስ ከእነርሱ ጋር የሚስተካከል ተዓምራትን እንዲያደርግ መጠበቅ በከሃዲነት አያስፈርጅም። ከነቢያት ሁሉ የላቀ ደረጃ አለኝ፣ የመጨረሻው ነቢይ ነኝ፣ ገነት እንድትገቡ ተከተሉኝ፣ ከገዛ ነፍሳችሁ ይልቅ ውደዱኝ፣ ለእኔ ተጋደሉ፣ ለእኔ ሙቱ፣ እኔን መታዘዝ ማለት ፈጣሪን መታዘዝ ማለት ነው፣ ወዘተ. እያለ ራሱን ከፍጥረት በላይ ከፈጣሪ ጥግ አድርሶ የሚጓደድ ጀብራሬ “እንደ ቀደሙት ነቢያት ተዓምር ባለማድረጌ ካላመናችሁብኝ ከሃዲያን ናችሁ” ብሎ ማለቱ ትዝብት ላይ ይጥለዋል።

ሱራ 6:37 “«ከጌታውም በእርሱ ላይ ለምን ተዓምር አልተወረደም» አሉ። «አላህ ተአምርን በማውረድ ላይ ቻይ ነው» በላቸው። ግን አብዛኞቻቸው አያውቁም።”

ጠያቂዎቹ እውነተኛው አምላክ ለነቢያቱ ተዓምራትን የማድረግ ኃይል ሊሰጣቸው እንደሚችል ባያምኑ ኖሮ ሙሐመድ ተዓምራትን እንዲያደርግ ባልጠየቁት ነበር። ስለዚህ “አብዛኞቻቸው አያውቁም” የሚለው የሙሐመድ ወቀሳ ተራ ውንጀላ ነው።

ሱራ 6:109 “ተዓምርም ብትመጣላቸው በእርሷ በቁርጥ ሊያምኑ ጥብቅ መሐሎቻቸውን በአላህ ማሉ። «ተዓምራት ሁሉ አላህ ዘንድ ናት» በላቸው። እርሷ በመጣች ጊዜም አለማመናቸውን (ወይም ማመናቸውን) ምን አሳወቃችሁ።”

ሱራ 13:27 “እነዚያም የካዱት፤ በርሱ ላይ ከጌታው ታምር ለምን አልተወረደም ይላሉ፤ አላህ የሚሻውን ያጠማል፤ የተመለሰውንም ሰው ወደርሱ ይመራል፤ በላቸው።”

ሱራ 17:59 “ታምራቶችንም ከመላክ የቀድሞዎቹ ሰዎች በርሷ ማስተባበልና (መጥፋት) እንጂ ሌላ አልከለከለንም፤ ለሠሙድም ግመልን ግልጽ ታምር ሆና ሰጠናቸው፤ በርሷም በደሉ፤ታምራቶችንንም ለማስፈራራት እንጂ አንልክም።”

በዚህ ጥቅስ ደግሞ አላህ በሙሐመድ በኩል ተዓምር ከማድረግ የታቀበበትን ምክንያት ሲገልፅ የቀድሞ ሰዎች ክደው ስለጠፉ ነው የሚል ሰበብ ይሰጣል። ፈጣሪ በነቢያቱ በኩል ተዓምራትን እየሠራ ብዙ ክፍለ ዘመናትን ካሳለፈ በኋላ “የመጨረሻው፣ ታላቁና የነቢያት አለቃ” ጋር ሲደርስ ማቆሙ አስገራሚ ነው። ለነዚያ ሁሉ ክፍለ ዘመናት ተዓምራትን እየላከ “ሰዎችን እያጠፋ መኖሩን” ልክ የሙሐመድ ዘመን ላይ ሲደርስ ተገንዝቦት ይሆን? ምን የሚሉት ስላቅ ነው!

ሱራ 28:48 “እውነቱም ከእኛ ዘንድ በመጣላቸው ጊዜ «ለሙሳ የተሰጠው ብጤ አይስሰጠውም ኖሯልን» አሉ። «ከዚህ በፊት ሙሳ በተሰጠው አልካዱምን የተረዳዱ ሁለት ድግምቶች ናቸው» አሉ። «እኛ በሁሉም ከሓዲዎች ነንም» አሉ።”

ሙሐመድ ተዓምራትን ማሳየት ባለመቻሉ ምክንያት የሙሴን ተዓምራት አስፈላጊነት አሳንሶ ለማሳየት ሲጣጣር ይታያል። ሙሴ ያንን ሁሉ ተዓምር ባያሳይ

ኖሮ እስራኤላውያንን ከባርነት ነፃ ማውጣት ባልቻለ ነበር። ሙሐመድም የእውነተኛ ነቢያት ምልክቶችን ማሳየት ቢችል ኖሮ አረቦችን ለማስለም ሰይፍ መምዘዝ ባላስፈለገው ነበር።
ከላይ የተጠቀሱት ጥቅሶች ሁሉ እንደሚያሳዩት ሙሐመድ ተዓምራትን እንዲያደርግ በተጠየቀ ጊዜ ሁሉ ጠያቂዎቹን ከመውቀስ በዘለለ ለጥያቄዎቻቸው ተገቢውን ምላሽ መስጠት አልቻለም። ከዚህም አልፎ ሙሐመድ ተዓምር ማድረግ እንደማይችልና አስፈራሪ (በቃላት የሚያስፈራራና የሚያስጠነቅቅ) ሰው ብቻ መሆኑን ቁርኣን እንዲህ ሲል የማያወላዳ ማረጋገጫ ይሰጣል፡-
ሱራ 13:7 "እነዚያም የካዱት፣ በርሱ ላይ ከጌታው ታምር ለምን አልተወረደለትም ይላሉ፤ አንተ አስፈራሪ ብቻ ነህ ለሕዝብም ሁሉ መሪ አላቸው።"
ሙሐመድ ተዓምራትን ማድረግ የማይችልበት ምክንያት አስፈራሪ ብቻ ስለሆነ መሆኑን ይህ ጥቅስ በግልፅ ይናገራል። ቁርኣን እንዲህ በግልፅ ሙሐመድ ተዓምር የመሥራት ምንም ዓይነት መንፈሳዊ ችሎታ እንደሌለው በተናገረበት ሁኔታ ሐዲሳትና ሌሎች እስላማዊ መጻሕፍት ሙሐመድ ብዙ ተዓምራትን ማድረጉን መናገራቸው ትክክል አይደለም።
ሌላው የእውነተኛ ነቢያት መታወቂያ ትክክለኛና ጊዜያቸውን ጠብቀው የሚፈፀሙ ትንቢቶችን መናገር ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በትክክል የተፈፀሙ እጅግ በርካታ ትንቢቶች ተመዝግበዋል። ነገር ግን በቁርኣንም ሆነ በእስላማዊ ትውፊቶች ውስጥ የረባ ትንቢታዊ መልእክት አይደገኝም። አንዳንድ ሙስሊሞች እንደ ትንቢት የሚጠቅሷቸው ይዘቶች እጅግ አሻሚና አንዳንዶቹ እንዲያውም የሐሰት ትንቢቶች መሆናቸው የተረጋገጡ ናቸው።
ሙስሊም ወገኖች ለሙሐመድ ነቢይነት ማረጋገጫ አድርገው በዋናነት የሚያቀርቡት ቁርኣንን ነው። ሥነ ጽሑፋዊ ውበቱ እጅግ የላቀ መሆኑ የፈጣሪ መጽሐፍ መሆኑን ያረጋግጣል ይላሉ። ዳሩ ግን ውበት እንደ ተመልካቹ በመሆኑ እንዲህ ካለው ግላዊ መመዘኛ በመነሳት የዘላለም መኖርያዬን የሚወስነውን እርምጃ መውሰድን ከሞኝነት እቆጥረዋለሁ።
የሙሐመድን ነቢይነት ለመቀበል ሰበብ የሚሆን አዎንታዊ ነገር አለመኖሩ እውነተኛ ነቢይ አለመሆኑን ለማረጋገጥ በራሱ ብቻውን በቂ ቢሆንም በማስከተል ደግሞ ነቢይነቱን እንዳልቀበል ምክንያት የሆኑኝን አሉታዊ ምክንያቶች አቀርባለሁ።

2. ከቀደሙት ነቢያት ጋር የሚጋጭ ትምሕርት ማስተማሩ

ከብሉይ ኪዳን ነቢያት ጀምሮ እስከ ጌታ ሐዋርያት ድረስ የሚገኙትን ቅዱሳን ሰዎች ስንመለከት መልእክታቸው ተያያዥና ተደጋጋፊ መሆኑን እናስተውላለን። አንዱ በሌላው ላይ የተገነባ ከመሆን ባለፈ አንዱ የሌላውን መልእክት ሲጣረስና ሲያፈርስ አይታይም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ገዢ የሆነው ትራኬ የእግዚአብሔር ፍጥረቱን የመዋጀት ሒደት ሲሆን ከዘፍጥረት መጽሐፍ ጀምሮ የዓለም ፍፃሜን እስከሚያሳየው እስከ ራዕይ መጽሐፍ ድረስ ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ በዚህ ሰንሰለት እርስ በርሳቸው ተሳስረውና ተጋምደው እንመለከታለን። ይህንን ገዢ ትራኬ የነገረ መለኮት ሊቃውንት The Crimson Thread በማለት የሚጠሩት ሲሆን እግዚአብሔር አንድያ ልጁን በመላክ ከእርሱ ተለይቶ የወደቀውን ፍጥረት ከራሱ ጋር ለማስታረቅ ያቀደውን ዕቅድና ፍጻሜውን የሚያመለክት በቅዱሳት

መጻሕፍት ውስጥ ከመጀመርያው አንስቶ እስከ መጨረሻ ድረስ የተዘረጋ የታሪክና የአስተምሕሮ ሰንሰለት ነው።

የሙሐመድ ቁርኣን ይህንን የነቢያት ሁሉ መልእክት የሚጻረርና ዓላማውንም የክርስቶስን መልእክትና ተልዕኮ መቀልበስ ያደረገ ነው። የሙሐመድ ቁርኣን ይህንን የቅልበሳ ግብ ከዳር ለማድረስ የተጠቀመው ዘዴ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ ወደ ክርስቶስ የሚያመለክቱ ክስተቶችን፣ ስብዕናዎችን፣ ሥርዓቶችንና አስተምህሮዎችን ከእንደገና መተርጎም ነው። ቁርኣን ይህንን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሰንሰለት (የክሪምሰን ሰንሰለት) ለማስወገድ የነቢያትን መልእክት በመከለስና አቅጣጫን በማስለወጥ አማራጭ እስላማዊ ሰንሰለትን አዘጋጅቷል። ይህም የቅዱሳን ነቢያት ሁሉ መልእክት ሙሐመድ የመጨረሻው ነቢይ መሆኑን መጠቆም ነው የሚል ነው።[1] ይህ ግን ፍፁም ሐሰትና የነቢያትን መልእክት የሚጻረር ነው።

ሙሐመድ የፈጠረው ሃይማኖት የአንድ አምላክ ካባን የለበሰና የነቢያትን ታሪኮች የሚጠቃቅስ እንዲሁም የቀደሙትን ቅዱሳት መጻሕፍት የሚያረጋግጥ መሆኑን የሚለፍፍ ቢሆንም ቅሉ የቅዱሳት መጻሕፍት ዋና መልእክት የሆነውን የክርስቶስን ተልእኮ ስለሚክድ ፈፅሞ ከእግዚአብሔር ሊሆን አይችልም። ሙሐመድ እውነተኛ ነቢይ እንደሆነ ከተቀበልን የቀደሙት ነቢያት ሁሉ ሐሰተኞች ይሆናሉ። የቀደሙት ነቢያት እውነተኞች ከሆኑ ደግሞ ሙሐመድ እውነተኛ ነቢይ የሚሆንበት ምንም ዓይነት ዕድል ሊኖር አይችልም።

ይህንን ርዕሰ ጉዳይ በማንሳት ከሙስሊም ወገኖቼ ጋር በምወያይበት ጊዜ ሁሉ የሚሰጡኝ የተለመደ ምላሽ "የቀደሙት ቅዱሳት መጻሕፍት በሙሉ ስለተበረዙ እንጂ የሙሐመድ መልእክት ከቀደሙት ነቢያት መልእክት ጋር አንድ ነው" የሚል ነው። ነገር ግን ቅዱሳት መጻሕፍት ስለመበረዛቸው ማስረጃዎችን እንዲሰጡኝ በምጠይቅበት ጊዜ ሁሉ የረባ ምላሽ አግኝቼ አላውቅም። ይህ ምላሽ ለምን እንደማያስኬድና የሙስሊሞች ብሒል እውነት ከሆነ እስልምና ሐሰት መሆኑን ከማረጋገጥ የዘለለ ፋይዳ እንደሌለው ለማወቅ እስላማዊ አጣብቂኝ በሚል ርዕስ ያዘጋጀሁትን ጽሑፍ ታነቡ ዘንድ እጋብዛለሁ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዳልተበረዘ የሚያረጋግጡ የጥንታውያን መዛግብት ማስረጃዎችን ለማየት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥንታውያን የእጅ ጽሑፎች በሚል ርዕስ ያሰባሰብኳቸውን መረጃዎች ትመለከቱ ዘንድ አበረታታችኋለሁ።

3. የክርስቶስን ስቅለት መካዱ

የክርስቶስን ስቅለት በተመለከተ ቁርኣን እንዲህ ይላል፦

"እኛ የአላህን መልክተኛ የመርየምን ልጅ አልመሲህ ዒሳን ገደልን በማለታቸው (ረገምናቸው)፡ አልገደሉትም አልሰቀሉትምም ነገር ግን ለነሱ (የተሰቀለው ሰው በዒሳ) ተመሰለ። እነዝያ በሱ ነገር የተለያዩት ከርሱ (መገደል) በመጠራጠር ውስጥ ናቸው። ጥርጣሬን ከመከተል በስተቀር በሱ ነገር ምንም እውቀት የላቸውም። በእርግጥም አልገደሉትም። ይልቁንስ አላህ ወደርሱ አነሳው። አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው።" (አል-ኒሳ 4፡157-158)

የክርስቶስ ስቅለት ከነገረ መለኮታዊ ሙግት በመለስ የታሪክ ሃቀኝነት ጉዳይ ነው። ሙስሊም ወገኖች የክርስቶስን ስቅለት በተመለከተ የሚያቀርቧቸው ነገረ መለኮታዊ ሙግቾ ክርስቲያኖች ለክርስቶስ ስቅለት የሰጡትን ትርጓሜ

ለማስተባበል ያገለግል ይሆናል፤ ነገር ግን ክርስቶስ እንዳልተሰቀለ በማስተባበል ቁርኣንን ከታሪካዊ ስህተቱ መታደግ አይቻልም። ለዚህም ምክንያቱ የክርስቶስ ስቅለት ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ በሚገኙ ዓለማውያንና መንፈሳውያን መዛግብት ውስጥ የሰፈረ መሆኑ ነው። የኢየሱስን ስቅለት በተመለከተ ከአራቱ ወንጌላት በተጨማሪ በዘመኑ በነበሩት የታሪክ ምሑራን የተጻፉ ብዙ ማስረጃዎች አሉ። ለምሳሌ ያህል፡-

1. ሮማዊው ጸሐፊ ታሪክ ቆርኖሌዎስ ታሲተስ የኢየሱስን ስቅለት ጽፏል።[2]
2. አይሁዳዊው ጸሐፊ ታሪክ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን የኢየሱስን ስቅለት በማያሻማ ቃል ጽፏል።[3]
3. የባቢሎናውያን ታልሙድ ኢየሱስ በፋሲካ ዋዜማ መሰቀሉን ይናገራል።[4]
4. ኢስጦኢክ ፈላስፋ የነበረው ማራ በር ሰራፒዮን ለልጁ በጻፈው ደብዳቤ ውስጥ የኢየሱስን ሞት ጠቅሷል።[5]
5. ሉሺያን የተሰኘ ግሪካዊ ጸሐፊ ኢየሱስ መገደሉን ጽፏል።[6]
6. ፍሌጎን የተሰኘ ሮማዊ ጸሐፊ ስለ ኢየሱስ መሰቀል ብቻ ሳይሆን በስቅለቱ ወቅት በምድር ላይ ስለወደቀው ጨለማና ስለ ምድር መናወጥ እንዲሁም ስለ ትንሣኤው ጽፏል።[7]

ከነዚህ በተጨማሪ ከአዲስ ኪዳን ውጪ የኢየሱስ ሞት ተዘግቦ የምናገኘው በጥንት የቤተ ክርስቲያን አበው ጽሑፎች ውስጥ ነው። የሐዋርያው ዮሐንስ ደቀ መዝሙር የነበረው ፖሊካርፕ የክርስቶስን ሞት ደጋግሞ የጻፈ ሰው ነው። ለምሳሌ ያህል ከጽሑፎቹ መካከል በአንዱ ውስጥ “ስለ ኃጢአታችን እስከ ሞት ድረስ መከራን የተቀበለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ…” በማለት አስፍሯል። የፖሊካርፕ ወዳጅ የነበረው የእስክንድርያው ኢግናጢዎስ በበኩሉ “በእውነት መከራን ተቀብሎ ከሞተ በኋላ ተነስቷል… ጌታችንን የሰቀሉት ፈሪሃ እግዚአብሔር የሌላቸው ሰዎች ነበሩ” በማለት ጽፏል።[8] የመጀመርያው ክፍለ ዘመን ክርስቲያን ጸሐፊ የነበረው ዮስቶኒዮስ ሰማዕትም ትሪፎ ለተሰኘ አይሁዳዊ በሰጠው ምላሽ በእርሱ ዘመን የነበሩት አይሁድ ኢየሱስን “የተሰቀለ ገሊላዊ” በማለት ይጠሩት እንደነበር ጽፏል።[9]

እነዚህ ሁሉ ታሪካዊ ማስረጃዎች በአንደኛው ክፍለዘመንና በሁለተኛው ክፍለዘመን መጀመርያ ላይ የተጻፉ ናቸው። በተጨማሪም ጌታችን ከመወለዱ ከብዙ ክፍለ ዘመናት በፊት ስለ ስቅለቱ ቅዱሳን ነቢያት ተንብየዋል (ኢሳ. 53፡ 1-12፤ ዳን. 9፡24-25፤ መዝ. 22፡12-18)።

ይህ ሁሉ ስፍር ቁጥር የሌለው ማስረጃ ባለበት ሁኔታ ከ600 ዓመታት በኋላ፣ ከምድረ እስራኤል ቢያንስ በ1000 ኪሎሜትሮች ርቆ ይኖር የነበረ አረብ ነጋዴ ወደ ዋሻ ገብቶ በመውጣት ክርስቶስ እንዳልተሰቀለ መልአክ እንደነገረው ተናገረ። የነጋዴው ንግግር ግልፅ ባለመሆኑም ምክንያት ሙስሊም ተርጓሚዎች ከሰማይ ወረደ የተባለውን ቃል ትርጉም እንዲሰጥ ለማድረግ የግል ማብራርያዎቻቸውን በቅንፍ ለማስገባት ተገድደዋል። በክርስቶስ ምትክ ተሰቅሏል የተባለው ሰው ማንነትም ስላልተጠቀሰ ሙስሊም ሊቃውንት ለክፍፍል ተዳርገዋል። አንዳንዶች ከአይሁድ መካከል አንዱ ተሰቅሏል በማለት ሲናገሩ ሌሎች ደግሞ የተሰቀለው

ከሮማውያን ወታደሮች መካከል አንዱ ነው ይላሉ። ከዒሳ ተከታዮች መካከል አንዱ በፍቃደኝነት መሞት ስለፈለገ አላህ የዒሳን መልክ ሰጥቶት ተሰቀለ የሚሉም አሉ። "የበርናባስ ወንጌል" በሚል ስም በመካከለኛው ዘመን በአንድ ሙስሊም የተጻፈ መጽሐፍ ደግሞ በምትኩ የሞተው የአስቆሮቱ ይሁዳ ነው ይላል።
በዚህ ዘመን የሚገኙት የታሪክ ሊቃውንት በክርስቶስ ስቅለት ዙርያ አንዳች ልዩነት የላቸውም። የክርስቶስን ስቅለት ለማስተባበል መሞከር በዓለም የታሪክ ሊቃውንት ፊት መሳቂያና መሳለቂያ የሚያደርግ በመሆኑ በዘመናችን የሚገኙት የተማሩ ሙስሊሞች የቁርአኑን ቃል በተለየ መንገድ በመተርጎም የክርስቶስን ስቅለት ወደ መቀበል እየመጡ ነው። ዒሳ እንደተሰቀለ ነገር ግን በመስቀል ላይ በነበረ ጊዜ እንዳልሞተና ራሱን እንደሳተ የሚናገር ትወራ በአሁኑ ወቅት በተለይም በተማሩት ሙስሊሞች ዘንድ በስፋት ተቀባይነት እያገኘ መጥቷል። ይህ አስተሳሰብ "ራስን የመሳት ትወራ" (Swoon Theory) በመባል የሚታወቅ ሲሆን ቬንቱሪኒ በተሰኘ ሰው በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ አካባቢ የተጀመረ ነው። ግንባር ቀደም ሙስሊም ዐቃቤ እምነት የነበሩት ሼኽ አሕመድ ዲዳት እና የዘመናችን ስመጥር ተሟጋች የሆኑት ዶ/ር ሻቢር አሊን የመሳሰሉት ሙስሊሞች ያቀነቅኑታል። ከእስላማዊ ቡድኖች መካከል የኔሽን ኦፍ ኢስላም (NOI) እና የአሕመዲያ ጎራዎች እንደ እምነት አቋም ይዘውታል።
እንግዲህ የተማሩት ሙስሊሞች ሙሐመድ ስለ ክርስቶስ ስቅለት የፈፀመው የታሪክ ቅጥፈት አሳፍሯቸው ከስህተቱ ራሳቸውን እያሸሹ በሚገኙበት ዘመን እንዴት ብዬ እንደ እውነተኛ ነቢይ ልቀበለው? የክርስቶስን ስቅለት በተመለከተ ሙሐመድ የፈፀመውን ስህተት በስፋት ያብራራሁበትን እስልምናና የመሲሁ ስቅለት በሚል ርዕስ የተጻፈውን ጽሑፍ አንብባችሁ የራሳችሁን ፍርድ ስጡ።

4. የብሉይ ኪዳንን ሕግጋት መተላለፉ

እግዚአብሔር አምላክ በሲና ተራራ ላይ ለሙሴ የሰጣቸው ትዕዛዛት ከሞላ ጎደል ሁሉም ሊባል በሚቻልበት ሁኔታ በሙሐመድ ተጥሰዋል። እነዚህ ትዕዛዛት በዘጸአት 20 ላይ ይገኛሉ። እስኪ አንድ በአንድ እንመልከት።
የመጀመርያው ትዕዛዝ፦ "ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ያወጣሁህ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ። ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ። በላይ በሰማይ ካለው፥ በታችም በምድር ካለው፥ ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ፥ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ። አትስገድላቸው፥ አታምልካቸውምም..."
ሙሐመድ አንዱና እውነተኛ የሆነውን የእስራኤልን አምላክ ሰብኳልን? በፍፁም! የሙሐመድ አምላክ ከአረብ ጣኦታውያን የተኮረጀ እንጂ ለአብረሃምና ለሙሴ የተገለጠው ያሕዌ እግዚአብሔር አይደለም። የዚህ አምላክ ማንነት የጣዖታት ከተማ ከነበረቻው ከመካ ጋር በእጅጉ የተቆራኘ መሆኑ ከቁርኣንና ከሌሎች እስላማዊ ጽሑፎች ግልፅ ነው። ሙሐመድ የእውነተኛው አምላክ የግል ስም የሆነውን ያሕዌ የሚለውን ስም ከመጠቀም ይልቅ አረብ ጣዖታውያን ሲጠቀሙበት የነበረውን አላህ የሚለውን ቃል የፈጣሪ ትክክለኛ ስም በማስመሰል አቅርቧል። ከሙሴ ዘመን ጀምሮ የነበሩት እውነተኛ ነቢያት ሁሉ ያሕዌ በሚለው የእግዚአብሔር የግል ስም የተናገሩና ያስተማሩ ቢሆንም ሙሐመድ ግን ይህንን ስም ጭራሽ አያውቀውም።

በተጨማሪም በመጀመርያው ትዕዛዝ ውስጥ ያሕዌ እግዚአብሔር የተቀረፀ ምስሎችን በመስራት ለእነርሱ መስገድን አጥብቆ ቢከለክልም ሙሐመድ ግን አረብ ጣዖታውያን ሲሰግዱለት ለኖሩት ጥቁር ድንጋይ በመስገድ፣ እርሱን በመሳምና በመተሻሸት በመላው ዓለም የሚገኙት ሙስሊሞች የእርሱን ፈለግ በመከተል አምልኮተ ጣዖትን እንዲለማመዱ ምክንያት ሆኗል።[10] ሙስሊም ወገኖች ጥቁሩን ድንጋይ እንደማያመልኩትና እንደማይሰግዱለት ቢናገሩም በተግባር ግን ወደ ድንጋዩ ዞረው በመስገድ፣ ድንጋዩን በመዞር፣ በመሳምና በመተሻሸት አምልኮተ ጣዖትን ይለማመዳሉ። ይህንን ጥያቄ ለሙስሊም ወገኖቼ ሳቀርብ ተግባራቸው በብሉይ ዘመን ሰዎች ወደ ኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ ዞረው ከመጸለያቸው ጋር አንድ እንደሆነና የሚፈፅሙትም ሥርኣት በመጽሐፍ ቅዱስ ድጋፍ ያለው መሆኑን ይገልጹልኛል። ዳሩ ግን አይሁድ ወደ ኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ ዞረው የሚጸልዩበት ምክንያት እግዚአብሔር አምላክ በገሃድ ክብሩን በቤተመቅደሱ ውስጥ ስለገለጸ የእግዚአብሔር ክብር መገኛና መገለጫ ቦታ መሆኑን ስለሚያውቁ ነው (1ነገሥት 8፡10)። ነገር ግን የመካ ካዕባ ቀደም ሲል በ360 ጣዖታት የተሞላ አረማውያን ብዙ ርኩስ ተግባራትን የሚፈፅሙበት የረከሰ ቦታ እንጂ የእግዚአብሔር ክብር የተገለጠበት ቦታ አይደለም። የሚገርመው ነገር ሙሐመድ መጀመርያ አካባቢ እንደ አይሁድ ሁሉ ወደ ኢየሩሳሌም ዞሮ ይሰግድ የነበረ ቢሆንም ኋላ ላይ ግን አይሁድ ስለ ተዘባበቱበት በመበሳጨት የስግደት አቅጣጫውን ወደ መካ እንዲዞር አድርጓል። በጊዜው ደግሞ 360 ጣዖታት በቦታው ይመለኩ ነበር (ሱራ 2፡150)።

ሁለተኛው ትዕዛዝ፡- "የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፤ እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነጻውምና።"

ሙሐመድ እውነተኛ አምላክ ብሎ የሚጠራውን የአላህን ስም በከንቱ በመጥራት ይህንን ትዕዛዝ በተደጋጋሚና በተለያዩ መንገዶች ተላልፏል፤ ሙስሊሞችም እንዲተላለፉ ምክንያት ሆኗል። የመጀመርያው የጣሰበት መንገድ በአላህ ስም የማላቸውን መሀላዎች ማፍረስ እንደሚቻል በማስተማር ነው።

ሱራ 66:1-2 "አንተ ነቢዩ ሆይ አላህ ለአንተ የፈቀደልህን ነገር ሚስቶችህን ማስወደድን የምትፈልግ ስትሆን (ባንተ ላይ) ለምን እርም ታደርጋለህ፤ አላህ እጅግ መሐሪ አዛኝ ነው። አላህ ለናንተ የመሐሎቻችሁን መፍቻ ደነገገላችሁ፤ አላህም ረዳታችሁ ነው፤ እርሱም ዐዋቂው ጥበበኛው ነው።"

"Allah has already ordained for you [Muslims] the dissolution of your oaths. And Allah is your protector, and He is the Knowing, the Wise."

ሙስሊም ሊቃውንት ይህ ጥቅስ ለምን "እንደ ወረደ" ሲናገሩ ሙሐመድ የሚስቶቹን ተራ ላለማጠፍ በመሀላ ቃል የገባ ቢሆንም የአይሻን ወይንም የሐፍሷን ተራ በማጠፍ ግብፃዊቷ መርየም ከተሰኘችው ሚስቱ (የጭን ገረዱ) ጋር ወሲብ በመፈፀሙ ምክንያት አላህ ከመሀላው ነፃ መሆኑን ለመግለፅ ያወረደለት መገለጥ ነው ይላሉ። ይህ ፍፁምና ቅዱስ በሆነው አምላክ ላይ መሳለቅ አይደለምን?

ሌላው ሙሐመድ የአምላክን ስም በከንቱ በመጥራት ያቀለለበት መንገድ ሙስሊሞች በረባው ባልረባው በአላህን ስም በመጥራት እንዲምሉ ምሳሌ በመሆን ነው። በእስላማዊ ሐዲሳት ውስጥ ብዙ ጊዜ ሙሐመድ "ወሏሂ" (በአላህ እምላለሁ) የሚለውን አባባል የንግግሩ ማጀቢያ አድርጎት እንመለከታለን። ዛሬም

ሙስሊሞች በትንሽ በትልቁ “ወሏሂ” እያሉ ሲምሉ መስማት የተለመደ ነው፡ ፡ ሃይማኖታቸውን እንደሚያውቁ የሚናገሩ ብዙ ሙስሊሞች ለሃይማኖታቸው ግድ ከሌላቸው ደካማ ክርስቲያኖች በከፋ ሁኔታ የአምላካቸውን ስም በረባው ባልረባው እየጠሩ በመማልና በመገዘት ሲያቃልሉት ማየት የተለመደ ነው።
ሦስተኛው ትዕዛዝ፡- “የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ። ስድስት ቀን ሥራ ተግባርህንም ሁሉ አድርግ፤ ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር ለአምላክህ ሰንበት ነው፤ አንተ፥ ወንድ ልጅህም፥ ሴት ልጅህም፥ ሎሌህም፥ ገረድህም፥ ከብትህም፥ በደጆችህም ውስጥ ያለ እንግዳ በእርሱ ምንም ሥራ አትሥሩ።”
ሙሐመድ እግዚአብሔር ለክብሩ ከመረጠው ዕለተ ሰንበት ይልቅ የመዲና የገበያ ቀን የሆነውን ዕለተ አርብን በመምረጥ የእስልምና ቅዱስ ቀን እንዲሆን አድርጓል፡ ፡ በዚህም እስልምና ከቀደሙት ነቢያት ጋር ተያያዥነት እንደሌለውና የአረቦችን ሁኔታ ብቻ ያገናዘበ መሆኑን አረጋግጧል።[11]
የሆነው ሆኖ ሰንበትን ማክበር ከሥርዓታዊ ሕግጋት የሚመደብና ግብረ ገባዊ ሕግ ባለመሆኑ በዚህ ጉዳይ ላይ ማጥበቅ አልሻም። እስኪ ቀጣዩን ትዕዛዝ እንመልከት።
አራተኛው ትዕዛዝ፡- “አባትህንና እናትህን አክብር፤ እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ እንዲረዝም።”
የሙሐመድ አባት ከልደቱ በፊትና ወላጅ እናቱ በህፃንነቱ በመሞታቸው ምክንያት ይህንን ትዕዛዝ የመተግበር ዕድል አላገኘም። ሆኖም ሙሐመድ በዕድሜ ከእርሱ የሚበልጡትን ንፁህን ወንዶችና ሴቶችን መዝረፉ፣ መግደሉና ማሳደዱ እናትና አባቱን ካለማክበር ይቆጠራል። እናም ይህንንም ትዕዛዝ እንዳልጠበቀ መናገር ይቻላል።
አምስተኛው ትዕዛዝ፡- “አትግደል።”
ስድስተኛ ትዕዛዝ፡- “አታመንዝር።”
ምንዝርና ከሕጋዊ ጋብቻ ውጪ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈፀም ነው። ሙሐመድ ምንዝርናን ከመፈፀሙም በላይ አመንዝራነትን ፈቅዷል። ቁርኣን ከጋብቻ ውጪ ከሴት ባርያዎች ጋር ወሲብ መፈፀም እንደሚቻል እንዲህ ይናገራል፡-
ሱራ 70፡29-30 “እነዚያም እነሱ ብልቶቻቸውን ጠባቂዎች የሆኑት። በሚስቶቻቸው ወይንም እጆቻቸው በያዙዋቸው (ባሮች)፣ ላይ ሲቀር። እነሱ (በነዚህ) የማይወቀሱ ናቸውና።”
ሱራ 23፡5-6 “እነዚያም እነርሱ ብልቶቻቸውን ጠባቂዎች የሆኑት (አገኙ)፡ ፡ በሚስቶቻቸው ወይም እጆቻቸው በያዟቸው (ባሪያዎች) ላይ ሲቀር። እነርሱ (በነዚህ) የማይወቀሱ ናቸውና።”
እነዚህ ጥቅሶች ሙስሊም ወንዶች በጋብቻ ከተጣመሯቸው ሚስቶቻቸውና ከሚያገለግሏቸው ሴት ባርያዎቻቸው ጋር ወሲብ ቢፈፅሙ ወቀሳ እንደሌለባቸው ይናገራሉ። በሐዲስ መጻሕፍት ውስጥ ሙስሊም ወንዶች ይህንን ተግባር በሙሐመድ ይሁንታ ይፈፅሙ እንደነበር ተጽፏል፡-
…አቡ ሲርማ ለአቡ ሰዒድ አል-ኹድሪ እንደነገረው፡ “አቡ ሰዒድ ሆይ የአላህ መልእክተኛ ስለ አዝል (የዘር ፈሳሽ ሳይፈስስ ብልትን ከሴት ማህፀን ስለማውጣት) ሲናገር ሰምተህ ታውቃህን?” ብሎ ጠየቀው። “አዎን” በማለት መለሰ፤ እንዲህ ሲልም አከለ “ከአላህ መልእክተኛ ጋር ወደ አል ሙስጠሊቅ በዘመትን ጊዜ ውብ

የሆኑ የአረብ ሴቶችን ማርከን ነበር፤ ሚስቶቻችን ከኛ ጋር ስላልነበሩ የፍትወት ፍላጎት እጅግ አይሎብን የነበረ ቢሆንም በተመሳሳይ እነርሱን የማስለቀቂያ ወጆ መቀበልም ፈልገን ነበር። ስዚህ አዝል እያደረግን (እንዳይፀንሱ የዘር ፈሳሻችንን ውጪ በማፍሰስ) ከእነርሱ ጋር ወሲብ ለመፈፀም ወሰንን። ነገር ግን እንዲህ አልን፡ ‹‹የአላህ መልእክተኛ ከኛ ጋር እያለ ይህንን ነገር እየፈፀምን ነው። ለምን አንጠይቀውም?›› ስለዚህ የአላህን መልእክተኛ በጠየቅነው ጊዜ እንዲህ ሲል መለሰልን፡ “እስከ ዕለተ ትንሣኤ ድረስ የሚወለዱ ነፍሶች ሁሉ መወለዳቸው ስለማይቀር እንደርሱ ባታደርጉ ምንም ችግር የለውም።”[12]

ከዚህ ሐዲስ እንደምንረዳው ሙሐመድ ወታደሮቹ ከጋባቻ ውጪ እንዲዘሙቱ ከመፍቀዱም በላይ እነዚህ ምርኮኛ ሴቶች መፀነሳቸው የወታደሮቹን ያህል አላሳሰበውም። እንዲህ ያለውን ሰው ነቢይ ብሎ መከተል ምንኛ መታወር ነው!

ሙሐመድ እራሱ ግብፃዊቷ መርየም ከተሰኘች ባርያው ጋር ወሲብ ይፈፅም እንደነበር እስላማዊ መጻሕፍት ይናገራሉ።[13]

የሙሐመድ የወሲብ ፍላጎት እጅግ ከፍ ያለ ከመሆኑ የተነሳ በአንድ ሌሊት ከ 9 ሚስቶቹ ጋር ወሲብ ይፈፅም እንደነበር እስላማዊ ሐዲሳት ይዘግባሉ።[14] በሌላ የሐዲስ ዘገባ ደግሞ በአንድ ቀን 11 ሚስቶቹን ይጎበኝ እንደነበርና የ30 ወንዶች ያህል የወሲብ ጉልበት እንደነበረው ተነግሮለታል።[15] ይህ ልማዱ እንደ ጀግንነት ቢነገርለትም ሴሰኝነት ጀግንነት ሳይሆን ደካማነት መሆኑን አእምሮው በትክክል የሚያስብ ሰው ሁሉ የሚያውቀው እውነታ ነው።

ከዚህም በተጨማሪ ቁርኣን ሙስሊም ወንዶች በሰማይ ቤት ከደናግላን ጋር ወሲብ እንደሚፈፅሙ ይናገራል፡-

ሱራ 44፡54 “(ነገሩ) እንደዚሁ ነው፤ ዓይናሞች የሆኑን ነጫጭ ሴቶች እናጠናዳቸዋለን።”

ሱራ 55፡56 “በውስጣቸው ከበፊታቸው (ከባሎቻቸው በፊት) ሰውም ጅንም ያልገሠሣቸው ዓይኖቻቸውን (በባሎቻቸው ላይ) አሳጣሪዎች (ሴቶች) አልሉ።”

ሱራ 55፡70-74 “በውስጣቸው ጠባየ መልካሞች መልከ ውቦች (ሴቶች) አልሉ። ከጌታቸሁም ጸጋዎች በየትኛው ታስተባብላላችሁ? በድንኳኖች ውስጥ የተጨጐሉ፥ የዓይኖቻቸው ጥቁረትና ንጣት ደማቅ የሆኑ ናቸው። ከጌታቸሁም ጸጋዎች በየትኛው ታስተባብላላችሁ? ከነሱ በፊት፥ ሰውም ጃንም አልገሠሣቸውም።”

ሱራ 56፡34-37 “ከፍ በተደረጉ ምንጣፎችም፣ (ሴቶችም፣ መካከል)። እኛ አዲስ ፍጥረት አድርገን (ለነሱ) ፈጠርናቸው። ደናግሎችም አደረግናቸው። ለባሎቻቸው ተሽሞርሟሪዎች፣ እኩያዎች (አደረግናቸው)።”

ሱራ 78፡31-33 “ለጥንቁቆቹ መዳኛ ስፍራ አላቸው። አትክልቶችና ወይኖችም። እኩያዎች የሆኑ ጡተ ጉቻማዎችም።”

ሙሐመድ ሙስሊም ወንዶች በገነት 72 ደናግላንን እንደሚሸለሙ መናገሩ በሐዲስ መጻሕፍት ተዘግቧል።[16] ሙሐመድ አመንዝራነት በምድር ብቻ ሳይሆን በሰማይም እንደተፈቀደ በማስተማር በእውነተኛው አምላክ ላይ የተሳለቀ ሰው ነው።

ሰባተኛው ትዕዛዝ፡- “አትስረቅ።”

የሙሐመድን ዘራፊነት ማስተባበል አይቻልም። ከመካ ወደ መዲና ከተሰደደ

በኋላ ያደረገው የመጀመርያው ነገር ሽምቅ ተዋጊዎችን በመላክ የመካ ነጋዴያንን ማስገደልና ማስዘረፍ እንደነበር ከእስላማዊ ጽሑፎች መረዳት ይቻላል።
በቁርኣን ውስጥ ሱረቱ አል-አንፋል (የጦር ዘረፋዎች ምዕራፍ) ተብሎ በተሰየመው ምዕራፍ የመጀመርያው ቁጥር ላይ እንዲህ ተብሏል፡-
ሱራ 8:1 "ከጦር ዘረፋ ገንዘቦች ይጠይቁሃል፤ የዘረፋ ገንዘቦች የአላህና የመልክተኛው ናቸው፤ ስለዚህ አላህን ፍሩ፤ በመካከላቸሁ ያለችውንም ሁኔታ አሳምሩ፤ አማኞችም እንደሆናችሁ፣ አላህንና መልክተኛውን ታዘዙ በላቸው።"
ሙሐመድ ተከታዮቹ በትጋት በመሥራት የገዛ እንጀራቸውን እንዲበሉና ሃይማኖታቸውን እንዲጠቅሙ ከማስተማር ይልቅ ዝርፍያን በማበረታታት ራሱና ተከታዮቹ የግፍ ሐብትን እንዲያከማቹ አድርጓል። በሙሐመድ ዘመን የነበሩት አረቦች ወደ እስልምና በብዛት እንዲጎርፉ ካደረጓቸው ነገሮች መካከል አንዱ በአላህ መንገድ እየተጋደሉ ቢሞቱ ገነትን እንደሚወርሱና በሕይወት ቢተርፉ ደግሞ በዘረፋ ገንዘብ እንደሚበለፅጉ የተሰጣቸው ተስፋ ነበር።[17]
ስምንተኛው ትዕዛዝ፡- "በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር።"
ሙሐመድ በመዋሸትና ውሸትን በመፍቀድ ይህንን አምላካዊ ትዕዛዝ አፍርሷል። በዚህ ዝርዝር 7ኛው ቁጥር ላይ እናየዋለን።
ዘጠነኛው ትዕዛዝ፡- "የባልንጀራህን ሚስት ... አትመኝ።"
ሙሐመድ ይህንን ትዕዛዝ በመተላለፍ የማደጎ ልጁን ሚስት አግብቷል። ይህንንም በተራ ቁጥር 9 ላይ እንመለከተዋለን።
አሥረኛው ትዕዛዝ፡- "የባልንጀራህን ቤት አትመኝ፤ የባልንጀራህን ሚስት ሎሌውንም ገረዱንም በሬውንም አህያውንም ከባልንጀራህ ገንዘብ ሁሉ ማናቸውንም አትመኝ።"
ሙሐመድ የኸይበር አይሁድ ብዙ ያከማቹት ኃብት መኖሩን በመስማቱ ምክንያት ወረራ እንደፈፀመባቸው እስላማዊ ምንጮች ይናገራሉ። የኃብት ክምችታቸው የት እንደሚገኝ ለማውጣጣት የጎሣ መሪውን በሚዘገንን ሁኔታ አሠቃየው። በአል-ጠበሪ የተጻፈው ታሪክ እንዲህ ይላል፡-
"ነቢዩ ኪናና የተባለውን ሰው በተመለከ ለዙባይር እንዲህ የሚል ትእዛዝ ሰጡ ‹በውስጡ የደበቀውን ሁሉ እስኪያወጣ ድረስ አሰቃየው።› ስለዚህ ዙባይር ኪናና ለሞት እስኪቃረብ ድረስ ደረቱ ላይ እሳት አስቀመጠበት። ከዚያም ነቢዩ ለመስለማህ አሳልፈው ሰጡት። እርሱም አረደው።"[18]
ከዚህ ታሪክ እንደምንረዳው ሙሐመድ የጎረቤቶቹን ኃብት መመኘቱ አሣቃቂ ግድያዎችን እንዲፈፅም አድርጎታል። እናም የጎረቤቶቻችንን ኃብት እንዳንመኝ የሚከለክለውን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ከመተላለፋም በተጨማሪ ንፁህ ደምን ማፍሰስን የሚከለክለውን ትዕዛዝ ተላልፏል።

5. የአምላኩን ስም የግል ጥቅሞቹን ለማስከበር መጠቀሙ

ሙስሊሞች ሙሐመድ የአላህ መልእክተኛና አገልጋይ እንደሆነ ያምናሉ። ዳሩ ግን ቁርኣንንና ሌሎች እስላማዊ መጻሕፍትን ያነበብን እንደሆን እውነታው የተገላቢጦሽ ነው። አላህ የሙሐመድ አገልጋይና ጉዳይ አስፈፃሚ፣ ቁርኣንም ደግሞ የሙሐመድ የግል ሰነድ ሆነው እናገኛቸዋለን። ሙሐመድ የግል ምኞቱን ለማሳካት የአላህን ስም ሲጠቀምና ዘላለማዊ የአላህ ቃል እንደሆነ የሰበከውን ቁርኣንን እንደ መሣርያ ሲጠቀም እናስተውላለን።

ለምሳሌ ያህል ሙሐመድ ብዙ ሴቶችን የማግባት ፍላጎቱን ከግብ ለማድረስ በአላህ ሽፋን እንዲህ ሲል ተናግሯል፡-
ሱራ 33:50 “አንተ ነቢዩ ሆይ! እኛ እነዚያን መህሮቻቸውን የሰጠሃቸውን ሚስቶችህን፣ አላህ ባንተ ላይ ከመለሰልህም እነዚያን እጅህ የጨበጠቻቸውን ምርኮኞች፣ እነዚያንም ከአንተ ጋር፣ የተሰደዱትን የአንጎትህን ሴቶች ልጆች፣ የአክስቶችህንም ልጆች፣ የየሹማህንም ሴቶች ልጆች ፣ የየሹሜዎችሕንም ሴቶች ልጆች(ማግባትን)ለአንተ ፈቅደንልሃል፤የአመነችንም ሴት ነፍሷን(ራሷን)ለነቢዩ ብትሰጥ ነቢዩ ሊያገባት የፈለገ እንደ ሆነ፣ ከምእምናን ሌላ ላንተ ብቻ የጠራች ስትሆን፣ (ፈቀድንልህ)፤ በነርሱ (በምእምናን) ላይ በሚስቶቻቸውና እጆቻቸውም በጨበጧቸው (ባሮች ነገር) ግዴታ ያደረግንባቸው በእርግጥ አውቀናል፤ ባንተ ላይ ችግር እንዳይኖር፣ (ያለፉትን ፈቀድንልህ)፤ አላህም መሐሪ አዛኝ ነው፡፡”
ሙሐመድ መልከ መልካም እንደሆኑ ያሰባቸውን ዘመዶቹን ጨምሮ በዙርያው የሚገኙትን ሴቶች አግበስብሶ የማግባት ምኞት ስላደረበት እንጂ ከአላህ ዘንድ ሰምቶ እንዳልተናገረ እርግጠኛ ሆኖ መናገር ይቻላል፡፡ እውነተኛና ቅዱስ የሆነው አምላክ የአንድን ሰው የፍትወት ጥማት ለማርካት እንዲህ ያለውን ትዕዛዝ የዘላለማዊ ቃሉ አካል አድርጎ ምድር ከመፈጠሯ በፊት ጽፎ አስቀምጧል ማለት ትልቅ የስድብና የክህደት ንግግር ነው፡፡
በአንድ ወቅት ደግሞ ሙሐመድ ሰዎች ሳያስፈቅዱ ወደ ቤቱ ዘው ብለው በመግባታቸው ምክንያት ተበሳጨ፤ የሚስቶቹንም ልብ እንዳይሰርቁ ሰጋ፤ እናም አገልጋዩ አላህን እንዲህ ሲል አናገረው፡-
ሱራ 33:53 “እላንተ ያመናችሁ ሆይ መድረሱን የማትጠባበቁ ስትሆኑ ወደ ምግብ ካልተፈቀደላችሁ በስተቀር የነቢዩን ቤቶች (በምንም ጊዜ) አትግቡ፤ ግን በተጠራችሁ ጊዜ ግቡ በተመገባቹ ሁም ጊዜ ወዲያውኑ ተበተኑ፤ ለወግ የምትጫወቱ ኾናችሁም (አትቆዩ) ፤ ይሃችሁ ነቢዩን በእርግጥ ያስቸግራል፤ ከናንተምያፍራል፤ግንአላህከውነትአያፍርምዕቃንም(ለማዋስ)በጠየቃችኋቸው ጊዜ፣ ከመጋረጃ ኋላ ኾናችሁ ጠይቋቸው፤ ይሃችሁ በልቦቻችሁ፤ ለልቦቻቸውም የበለጠ ንጽሕናን ነው፤ የአላህም መልክተኛ ልታስቸግሩ ሚስቶቹንም ከርሱ በኋላ ምንጊዜም ልታስቡ ለናንተ አይገባቸ ሁም፤ ይሃችሁ አላህ ዘንድ ከባድ (ኀጢአት) ነው፡፡”
በአንድ ወቅት ደግሞ ሙሐመድ የቤቱ ደጅ ላይ ሆነው ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በሚጠሩት ሰዎች ምክንያት ተበሳጨ፤ እናም አገልጋዩ አላህ እንዲህ ሲል እንዲናገርለት አደረገ፡-
ሱራ 49:4 “እነዚያ ከክፍሎቹ ውጭ ሆነው የሚጠሩህ አብዛኞቻቸው አያውቁም፡፡ ወደነርሱም እስክትወጣ ድረስ እነርሱ በታገሡ ኖሮ ለነርሱ በላጭ በሆነ ነበር፤ አላህም እጅግ መሐሪ አዛኝ ነው፡፡”
ሙሐመድ የአምላኩን ስም የግል ጥቅሙን ለማስከበር በእንቶ ፈንቶ ጉዳዮች ሲጠቀም የሚያሳዩ ብዙ ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ እንዲህ ያሉ የአንድን ግለሰብ ጊዜያዊና ግላዊ ጥቅም ለማስከበር የታለሙ መንፈሳዊ ርባና የሌላቸውን ነገሮች ፈጣሪ በዘላለማዊ ቃሉ ውስጥ እንዲካተቱ አድርጓል ብሎ ለማመን በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ዐይንን ጨፍኖ በዚያ ላይ በወፍራም ጨርቅ ተሸፍኖ ለማየት ከመሞከር ጋር ሊነፃፀር የሚችል ጭፍንነት ይጠይቃል፡፡

6. ባስተማረው ትምሕርት አለመኖሩ

ማራ በር ሰራፒዮን የተሰኘ ፈላስፋ በ70 ዓ.ም. ገደማ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲጽፍ እንዲህ አለ፡-

“ሶቅራጥስን በመግደል የአቴንስ ሰዎች ምን አተረፉ? ድርቅና ወረርሽኝ ለሰሩት ወንጀል እንደ መቀጣጫ መጣባቸው፡፡ የሳሞስ ሰዎች ፓይታጎረስን በማቃጠላቸው ምን አተረፉ? በቅጽበት መሬታቸው በአሸዋ ተሸፈነ፡፡ አይሁድ ጥበበኛ ንጉሣቸውን በመግደላቸው ምን አተረፉ? ልክ ከዚያ በኋላ መንግሥታቸው አከተመለት፡፡ አምላክ ለነዚህ ሦስት ሰዎች በትክክለኛ ፍረድ ተበቀለላቸው፡፡ አቴናውያን በረሃብ ሞቱ፡፡ ሳሞሳውያን በባህር ሰጠሙ፡፡ አይሁድ ተፍረክርከው ከምድራቸው ላይ በመባረር ሙሉ በሙሉ ተበትነው ኖሩ፡፡ ነገር ግን ሶቅራጥስ መሞቱ ለበጎ አልሆነም፡፡ በፕላቶ ትምህርት ኖሯልና፡፡ ፓይታጎረስ መሞቱ ለበጎ አልሆነም፡፡ በሄራ ሐውልት ውስጥ ኖሯልና፡፡ ጥበበኛውም ንጉሥ መሞቱ ለበጎ አልሆነም፡፡ ራሱ ባስተማረው ትምህርት ኖሯልና፡፡”[19]

የእውነተኛ የእግዚአብሔር ሰው አንዱ መገለጫ ባስተማረው ትምሕርት መኖሩ ነው፡፡ ነገር ግን ሙሐመድ ቀደም ሲል ከአምላኩ ዘንድ እንደተሰጡ ያስተማራቸውን ትዕዛዛት በመተላለፍ የወደደውን ሲያደርግ እንመለከታለን፡፡ ለምሳሌ ያህል ቁርኣን ለአንድ ሙስሊም ወንድ እንዲያገባ የሚፈቅደው እስከ አራት ሚስቶች ብቻ ነው (ሱራ 4፡3)፡፡ ነገር ግን በታሪክ እንደሚታወቀውና ሙስሊም ምሁራን እንደተስማሙበት ከሆነ ሙሐመድ ወደ አሥራ ሦስት ሚስቶችን በማግባት በቁርኣን ከተፈቀደው ከሦስት እጥፍ በላይ ሚስቶች ነበሩት፡፡ ታዲያ ሙሐመድ ይህንን ትዕዛዝ ተላልፎ ነው ይህን ያደረገው ወይስ ትእዛዙ እርሱን የማይመለከት ሆኖ ነው? ይህ ትዕዛዝ እርሱን አይመለከትም ካልን ለምን? የሚል ጥያቄ ማስከተል ተገቢ ነው፡፡ አንድ ነቢይ እውነተኛነቱ የሚታወቀው በተናገረው መልዕክት መኖር ሲችል ነው፡፡ እርሱ ያላደረገውን (ማድረግ የማይችለውን) ትዕዛዝ በሌላው ላይ የሚጭን መምህር ጥሩ ሞዴል ተደርጎ ሊወሰድ አይገባውም፡፡ ሙሐመድ ለራሱ አሥራ ሦስት ሚስቶችን አግብቶ ሌሎችን ግን “አላህ የፈቀደላችሁ እስከ አራት ማግባት ብቻ ነው” ማለቱ የሚናገራቸውን መገለጦች ሲፈልግ ለራሱ ጥቅም እንደሚገለገልባቸው ማሳያ ነው፡፡

7. ውሸትን መፍቀዱ

በዓለም ላይ ከሚገኙት ታላላቅ ሃይማኖታት መካከል እስልምና ውሸትን የሚፈቅድ ብቸኛው ሃይማኖት ነው፡፡ በእስልምና ውስጥ ብዙ የተፈቀዱ የውሸት ዓይነቶች አሉ፡፡ የሱኒ ሙስሊሞች “ሙደራት” የተሰኘ የአታላይነት አስተምህሮ አላቸው፡፡ በሺኣ ሙስሊሞች ዘንድ ደግሞ “ታቂያ” በመባል ይታወቃል፡፡ ከኡላማ (ከእስልምና ሊቃውንት) ክበብ ውጪ የሚገኙ ብዙ ሰዎች ስለዚህ አስተምህሮ ብዙም አያውቁም፡፡ “ሙደራት” ማለት ማደናነቅ፣ የግብዝነት አድናቆት፣ ማታለል፣ ቆዳን ማስወደድ፣ ማጭበርበር፣ እኩል መራመድ፣ መሸፈን፣ መደበቅ ወይንም መሰወር ማለት ነው፡፡ ይህ የማታለል ጠባይ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ሰዓት ሁሉ በማንም ላይ ተግባራዊ ሊደረግ ይችላል፡፡ ነገር ግን የሱኒ ምሑራን በቋሚነት የሙደራት ዒላማ ውስጥ መግባት አለባቸው ያሏቸውን አሥር ዓይነት ሰዎች ለይተው አስቀምጠዋል፡፡ ካፊር (ሙስሊም ያልሆነ ሰው)፣ “ክፉ” የሆነ መሪ፣ አዲስ የሰለሙ ሰዎች፣ ከእስልምና ልቡ ያፈነገጠውን ሰው ወደ እስልምና ለመመለስ፣ አማኞች

ያልሆኑትን በመምሰል የሳተን ሙስሊም ለመመለስ፣ የተማረን ሰው ወይንም ሳይንቲስት ከዕውቀቱ ለመጠቀም፣ ጓደኛን ለማስደሰት፣ ከጠላት ለማምለጥ ወይም ለመጉዳት፣ የትዳር አጋርን ለማስደሰት፣ የታመመ ሰው (ለምሳሌ ያህል ደህና እንደሚሆን ወይንም ደህና መምሰሉን በመንገር)። የሱኒ ሊቃወንት ይህንን አመለካከት ለማፅደቅ የተለያዩ የቁርአን ጥቅሶችን ይጠቅሳሉ።[20]
ሙሐመድ አንድ ሙስሊም በአደጋ ውስጥ በሚሆንበት ሰዓት ሃይማኖቱን እስከ መካድ የሚደርስ ውሸትን መዋሸት እንደሚችል በማስተማር ሙስሊም መሆንን ርካሽ አድርጎታል (16፡106)። ነገር ግን እውነተኛ አማኞች የሆኑት ሲድራቅ፣ ሚሳቅና አብድናጎ አምላካቸውን ክደው ለጣዖት እንዲሰግዱ በንጉሥ ናቡከደነፆር በታዘዙ ጊዜ እንዲህ የሚል ምላሽ በመስጠት እሳት ውስጥ መጣልን መርጠዋል፡-
“ናቡከደነፆርም፦ ሲድራቅና ሚሳቅ አብደናጎም ሆይ፥ አምላኬን አለማምለካችሁ፥ ላቆምሁትም ለወርቁ ምስል አለመስገዳችሁ እውነት ነውን? ሲድራቅና ሚሳቅ አብደናጎም መለሱ ንጉሡንም፦ ናቡከደነፆር ሆይ፥ በዚህ ነገር እንመልስልህ ዘንድ አስፈላጊያችን አይደለም። የምናመልከው አምላካችን ከሚነድደው ከእሳቱ እቶን ያድነን ዘንድ ይቻላል፤ ከእጅህም ያድነናል፥ ንጉሥ ሆይ! ነገር ግን፥ ንጉሥ ሆይ፥ እርሱ ባያድነን፥ አማልክትህን እንዳናመልክ ላቆምኸውም ለወርቁ ምስል እንዳንሰግድለት እወቅ አሉት።” (ዳንኤል 3፡16-18)
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቃልም ሆነ በተግባር በእምነት ፀንቶ ስለመገኘት እንዲህ ብሏል፡-
“ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ፤ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፉ የሚቻለውን ፍሩ። ሁለት ድንቢጦች በአምስት ሳንቲም ይሸጡ የለምን? ከእነርሱም አንዲቱ ያለ አባታችሁ ፈቃድ በምድር ላይ አትወድቅም። የእናንተስ የራሳችሁ ጠጉር ሁሉ እንኳ ተቈጥሮአል። እንግዲህ አትፍሩ ከብዙ ድንቢጦች እናንተ ትበልጣላችሁ። ስለዚህ በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ፤ በሰው ፊትም የሚክደኝን ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እክደዋለሁ።” (ማቴዎስ 10፡28-33)
ክርስትና የሕይወት መንገድ ስለሆነ ክርስቲያን መሆን ውድ ነው። እስልምና ሰው ሰራሽ ሃይማኖት ስለሆነ ሙስሊም መሆን ቀላልና ርካሽ ነው። ነገሮች ሲከብዷችሁ ትክዱታላችሁ፤ ሲመቻችሁ አብራችሁ ትጎርፋላችሁ።
ሙሐመድ በአንድ ወቅት ከኣብ ኢብን አል-አሽራፍ የተሰኘውን ሰው ለመግደል የእርሱ ወዳጅ የነበረው ሙሐመድ ቢን መስለማ የተሰኘ ሰው ውሸትን እንዲጠቀም ፈቃድ ሰጥቶት ነበር።[21]
በእስልምና የሸሪኣ መጽሐፍ ውስጥ እንዲህ ተብሏል፡- it is permissible to lie if attaining the goal is permissible. የሚፈለገው ግብ የተፈቀደ ከሆነ (ትክክል ከሆነ) መዋሸት የተፈቀደ ነው እንደ ማለት ነው።[22] ስለዚህ በዚህ ረገድ ያለው እስላማዊ አስተምሕሮ “የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው” ዓይነት ነው። እስልምና በምንም መስፈርት እውነተኛና ቅዱስ ከሆነው አምላክ ዘንድ ሊሆን አይችልም።

8. ከ 9 ዓመት ህፃን ጋር መተኛቱ

ሙሐመድ ከፈፀማቸው አስደንጋጭ ተግባራት መካከል አንዱ አይሻ የተሰኘችውን ጨቅላ ሚስቱን በ6 ዓመቷ አጭቷት በ9 ዓመቷ አብሯት መተኛቱ ነው። ይህ ጉዳይ ማስተባበል በማይቻልበት ሁኔታ በእስላማዊ ሐዲሳትና የሙሐመድ ግለ-ታሪኮች ውስጥ በግልፅ የሰፈረ ሲሆን ሙስሊም ወገኖች ድርጊቱን ለማፅደቅ እንጂ ለማስተባበል ሲጨነቁ እምብዛም አይታዩም።[23] ድርጊቱ ትክክል መሆኑን ለማሳየት ሙስሊሞች የሚጠቅሷቸው ምክንያቶች በሙሉ ለምን ሊያስኬዱ እንደማይችሉ ሙሐመድ ለአቅመ ሔዋን ያልደረሰችውን አይሻን ስለ ማግባቱ – ለሙስሊሞች ምላሽ የተሰጠ ምላሽ በሚል ርዕስ በጻፍኩት ጽሑፍ በቂ ምላሽ ሰጥቻለሁ።

ሙሐመድ ለጨቅላ ህፃናት ፆታዊ ፍላጎት እንደነበረው የሚያሳዩ ሌሎች ታሪኮች በእስላማዊ መጻሕፍት ውስጥ ይገኛሉ። ለምሳሌ ያህል ሙስናድ አህመድ ኢብን ሐንበል ሐዲስ ቁጥር 25636 ላይ እንዲህ ተፅፏል፡-

“የአባስ ልጅ ኡም ሐቢባ ጡት በመጥባት ዕድሜ ላይ ሳለች በዳዴ ስትሄድ ተመልክቷት ነቢዩ እንዲህ አለ፡- ወሏሂ እኔ በሕይወት እያለሁ የምታድግ ከሆነ አገባታለሁ።”[24]

እንዲህ ያለውን ሰው እንደ እውነተኛ ነቢይ መቀበል እንደ እውነቱ ከሆነ የጤና ምልክት አይደለም። ብዙ ሙስሊሞች ይህንን ሚስጥር ካወቁ በኋላ ሙሐመድን ከመከተል እንደሚመለሱ ጥርጥር የለኝም።

9. የማደጎ ልጁን ሚስት መንጠቁ

ሙሐመድ “የባልንጀራህን ሚስት አትመኝ” የሚለውን አምላካዊ ትዕዛዝ በመተላለፍ የማደጎ ልጁ የዘይድ ሚስት የነበረችውን ዘይነብን ተመኝቷታል፤ ስለ ውበቷም ባልተገባ መንገድ በመናገር ትዳሯን ካናጋ በኋላ አግብቷታል። ይባስ ብሎ ይህንን አስነዋሪ ተግባሩን ለማፅደቅ በቁርኣን ውስጥ አገልጋዩ አላህን እንዲህ ሲል እንዲናገርለት አድርጎታል፡-

ሱራ 33:37 “ለዚያም አላህ በርሱ ላይ ለለገሰለትና (አንተም ነጻ በማውጣት) በርሱ ላይ ለለገስክለት ሰው (ለዘይድ)፡ አላህ ገላጩ የኾነን ነገር በነፍስህ ውስጥ የምትደብቅና አላህ ልትፈራው ይልቅ የተገባው ሲኾን፣ ሰዎችን የምትፈራ ሆነህ ፦ ሚስትህን ባንተ ዘንድ ያዝ፤ (ከመፍታት) አላህንም ፍራ፤ በምትል ጊዜ፡ (አስታውስ) ዘይድንም ከርሷ ጉዳይን በፈጸመ ጊዜ በምእምናኖች ላይ፣ ልጅ አድርገው ባስጠጉዋቸው (ሰዎች) ሚስቶች፡ ከነሱ ጉዳይን በፈጸሙ ጊዜ (በማግባት) ችግር እንዳይኖርባቸው፡ እርሷን አጋባንህ፤ የአላህም ትእዛዝ ተፈጻሚ ነው።”

በዚህ የቁርኣን ጥቅስ መሠረት ሙሐመድ ዘይነብን ተመኝቷት ነበር። ነገር ግን ሰዎች ምን ይሉኛል በሚል እፍረት ዘይድ ሚስቱን እንዳይፈታ ግብዛዊ በሆነ መንገድ ይመክረው ነበር። ዳሩ ግን አላህ ጉዳዩን አደባባይ በማውጣት ዘይነብን ዳረለት። ለዚህም ሙስሊሞች የማደጎ ልጆቻቸውን ሚስቶች ከፍቺ በኋላ ማግባት እንደሚችሉ ምሳሌ ለመሆን ነው የሚል ደካማ ምክንያት ቀርቧል። ነገር ግን ሙሐመድ ዘይነብን የተመኛት ባለትዳር በነበረችበት ጊዜ በመሆኑና ስለ ውበቷ ባልተገባ መንገድ መናገሩ ለትዳሯ መናጋትና ለፍቺ ምክንያት መሆኑ በእስላማዊ ሐዲሳት ውስጥ በግልፅ ተጽፎ ስለሚገኝ “ምሳሌ ለመሆነ ነው” የሚለው ሰበብ አሳማኝ አይደለም።[25]

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ አለ፡-

“አታመንዝር እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፣ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል።” (ማቴዎስ 5፡27-28) ሙሐመድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የላቀ የሥነ ምግባር ልኬት መሠረት አመንዝራ ነው።

10. ለጥቁሮች የነበረው ዝቅተኛ አመለካከት

ሙሐመድ ለጥቁሮች ከፍተኛ ንቀት እንደነበረውና የሰዎችን ሰብዓዊ ዋጋ በቆዳ ቀለም የሚለካ ሰው እንደነበር እስላማዊ መጻሕፍት ያሳያሉ። ለምሳሌ ያህል ሙሐመድ እንዲህ በማለት ሰይጣንና ጥቁር ሰውን አመሳስሏል፦

“ነቢዩ እንዲህ አሉ፦ ‹‹ሰይጣንን ማየት የሚፈልግ ሰው ነብጣል ኢብን አል-ሐሪሥን ይመልከተው!›› ጥቁር ሰው ሲሆን የተንጨባረረ ረጅም ፀጉርና ጥቁር መንጋጋዎች አሉት።”[26]

የጥንት ሙስሊሞች ሙሐመድ ጥቁር መሆኑን የሚናገር ሰው ይገድሉ ነበር፦

“የሰህኑን ወዳጅ የነበረው አሕመድ ኢብን አቢ ሱለይመን እንዲህ አለ፦ ‹‹ማንኛውም ነቢዩ ጥቁር እንደሆኑ የሚናገር ሰው ይገደላል። ነቢዩ ጥቁር አልነበሩም››።”[27]

ሙሐመድ ጥቁር ባርያዎች እንደነበሩት በብዙ እስላማዊ ትውፊቶች ውስጥ በተደጋጋሚ ተዘግቧል።[28] ጥቁር ባርያዎችንም በስጦታ ይቀበል እንደነበር ተነግሯል።[29]

በአንድ ወቅት አንድ ባርያ በሁለት ጥቁር ባርያዎች እንደለወጠ እስላማዊ ትውፊቶች ውስጥ ተጽፏል፦

“ጃቢር ኢብን አብዱላህ እንዳስተላለፈው፦ አንድ ባርያ ወደ አላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) በመምጣት ቃል ኪዳን ያዘ። ነቢዩም ባርያ መሆኑን አላወቁም ነበር። አሳዳሪው በመምጣት ባርያው እንዲመለስለት በጠየቀ ጊዜ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ‹‹ሸጥልኝ›› አሉት? በሁለት ጥቁር ባርያዎችም ገዙት።”[30]

ለኢትዮጵያውያን ያለውን ንቀትና ዘረኛ አመለካከት እንዲህ በማለት ገልጧል፦

“የእናንተ መሪ ዘቢብ (የደረቀ የወይን ፍሬ) የመሰለ ጭንቅላት ያለው ኢትዮጵያዊ ቢሆን እንኳ ታዘዙት።”[31]

እንዲህ ያለ የዘረኝነት አመለካከት የነበረው ሰው እውነተኛ የእግዚአብሔር ነቢይ ሊሆን አይችልም።

11. ፍቺን መፍቀዱ

እንደ እስልምና ፍቺን ያቀለለ ሃይማኖት ያለ አይመስለኝም። ሙሐመድ የፈለገውን እንዲፈታና የፈለገውን እንዲያስጠጋ አላህ ፈቃድ እንደሰጠው ቁርኣን እንዲህ ሲል ይናገራል፦

ሱራ 33:51 “ከነሱ የምትሻትን ታቆያለህ፤ ይምንሻትንም ወደ አንተ ታስጠጋለህ፤ (በመፍታት) ከአራቅሃትም የፈለግሃትን፣ (በመመለስ ብታስጠጋ)፣ በአንተ ላይ ሐጢያት የለብህም፤ ይህ ዓይኖቻቸው ወደ መርጋት፣ ወደ አለማዘናቸውም፣ ለሁሉም በሰጠሃቸው ነገር ወደ መውደዳቸውም በጣም የቀረበ ነው፤ አላህም በልቦቻችሁ ውስጥ ያለውን ሁሉ ያውቃል፤ አላህም ዐዋቂ ታጋሽ ነው።”

የፍቺ ነፃነት ለሙሐመድ ብቻ ሳይሆን ለሙስሊም ወንዶች ሁሉ የተሰጠ ነው፦

ሱራ 4፡20 “በሚስትም ስፍራ ሚስትን ለመለወጥ ብትፈልጉ፣ ለአንደኛዪቱ (ለምትፈታው) ብዙን ገንዘብ የሰጣችኋት ስትሆኑ ከርሱ ምንንም አትውሰዱ።

በመበደልና ግልጽ በሆነ ኃጢያት ትወስዱታላችሁን?"
በዚህ ጥቅስ መሠረት ሙስሊም ወንዶች ሚስት መለወጥ ቢፈልጉ ማድረግ ያለባቸው ለተፈቺዋ ብዙ ገንዘብ መስጠት ነው። ፍቺ ያን ያህል ቀላል ነው። ነገር የእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡-
"ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ ሌላይቱንም የሚያገባ ያመነዝራል። ከባልዋም የተፋታችውን የሚያገባ ያመነዝራል።" (ሉቃስ 16፡18)
"ሚስትህ ባልንጀራህና የቃልኪዳንህ ሚስት ሆና ሳለች እርስዋን አታለሃታልና እግዚአብሔር ባንተና በልጅነት ሚስትህ መካከል ምስክር ስለሆነ ነው። እግዚአብሔር የህይወትን መንፈስ አንድ አዱርጎ ጠብቆልን የለምን? እርሱም የሚፈልገው ምንድ ነው? ዘር አይደለምን? ስለዚህ መንፈሳችሁን ጠብቁ፡ ፡ ማንም የልጅነት ሚስቱን አያታልል። መፋታትን እጠላለሁ ይላል የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር። ልብሱንም በግፍ ስራ የሚከድነውን ሰው እጠላለሁ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር። ስለዚህ እንዳታታልሉ መንፈሳችሁን ጠብቁ፡ ፡" (ሚልክያስ 2፡14-16)
ሙሐመድ በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላውን ተግባር ያፀደቀና አቅልሎ ያቀረበ ሰው በመሆኑ እውነተኛ ነቢይ ሊሆን አይችልም።

12. በድግምት ቁጥጥር ስር መውደቁ

አይሻ እንደዘገበችው ላቢድ ቢን አል-አስማ የተባለ ሰው በሙሐመድ ላይ ድግምት በመሥራቱ ሳብያ ሙሐመድ ሚስቶቹ በሌሉበት ከሚስቶቹ ጋር እየተኛ እንደሆነ ይመስለው ነበር። እንኳንስ በእግዚአብሔር ነቢይ ላይ ይቅርና በእግዚአብሔር በእውነት ባመነ በማንኛውም ሰው ላይ አስማት እንዴት ሊሠራ ይችላል? የበለአም አስማት እንኳንስ በሙሴ ላይ ሊሠራ ይቅርና በሙሴ ከሚመራው ህዝብ መካከል በአንዱ ላይ እንኳ ሊሠራ አልቻለም። ይልቅስ ይህንን የተረዳው አስማተኛው በለአም "በያዕቆብ ላይ አስማት የለም በእስራኤልም ላይ ሟርት የለም" በማለት መስክሯል (ዘኁልቁ 23፡23)።
በአዲስ ኪዳን ውስጥ ደግሞ ጌታ ኢየሱስ የአጋንንት ኃይል በስሙ ባመኑት ሰዎች ላይ እንደማይሠራና ይልቁኑ በስሙ አጋንንትን ከሰዎች ውስጥ እንዳሚያስወጡ ተናግሯል። ይህ ተስፋ በሐዋሪያት ዘመን ሲሠራ ነበር። ዛሬም ቢሆን እየሠራ እንደሆነ ማንም አይቶ መመስከር ይችላል (ማርቆስ 16፡17-18)።
ማጠቃለያ
እኔ እንደ አንድ ሰው ከላይ በተጠቀሱትና ወደፊትም በተከታታይ በማቀርባቸው በሌሎች ብዙ ምክንያቶች ሙሐመድን እንደ እውነተኛ ነቢይ ልቀበለው ከቶ አልችልም። ብዙ ሙስሊም ሰባኪያን እነዚህ የነቢያቸው እውነተኛ ገፅታዎች አደባባይ እንዲወጡባቸው አይፈልጉም። ይህ ሀቀኝነት የጎደለው አካሄድ ነው፡ ፡ አሁን ግን ይህ አካሄዳቸው ፊፅሞ እንደማያዋጣቸው ሊያውቁት ይገባል። ምክንያቱም እያንዳንዱ ሰው ከመቼውም ጊዜ በላቀ ሁኔታ ለመረጃ ቅርብ ሆኗልና፡ ፡ ስለዚህ የሚያዋጣቸው እውነትን መደበቅ ሳይሆን ተጋፍጠው ምክንያታዊ በሆነ መንገድ መልስ መስጠት አለበለዚያ ደግሞ ለእውነት እጅ ሰጥቶ አቅጣጫን ማስተካከልና ሌሎችንም ማስተማር ነው።
ጌታ እግዚአብሔር የሙስሊም ወገኖቼን የልብ ዓይኖች በመክፈት ወደ ልጁ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃን ይመራቸው ዘንድ የዘወትር ጸሎቴ ነው።

________________________

[1] ሳም ሰለሞንና አጢፍ ዴብስ፣ ያሕዌ እግዚአብሔርና አላህ  አንድ ናቸውን? ገፅ 10
[2] Josh McDowell, Evidence that Demands a Verdict, New and Revised, 1999, pp. 122-123
[3] Ibid., p. 125
[4] Ibid., pp. 123-124
[5] Ibid., p. 123
[6] Norman L. Geislere, Encyclopedia of Christian Apologetics, 1999, p. 128
[7] Ibid.
[8] Ibid.
[9] Ibid.
[10] (Sahih al-Bukhari, Volume 2, Book 26, Number 673)
[11] https://www.answering-islam.org/Books/MW/friday.htm
[12] Sahih Muslim, volume 2, #3371
[13] Kitab al-Tabaqat al-Kabir, p. 151
[14] Bukhari, volume 7, # 142
[15] Bukhari, volume 1, #268
[16] Sunan Ibn Majah, Zuhd (Book of Abstinence) 39
[17]  Sahih Al-Bukhari, # 2787
[18] Al-Tabari; Vol. 8, p. 122
[19] Josh McDowell, Evidence that Demands a Verdict, New and Revised, 1999, p. 123
[20] Sam Solomon & E. Al-Maqdisi. Al-Hijra, Islamic Migration: Accepting Freedom or Imposing Islam?; 2009, pp. 72-79
[21] Bukhari Vol 5 Book 59 Num 369
[22] Ahmad ibn Naqib al-Misri, The Reliance of the Traveller, translated by Nuh Ha Mim Keller, amana publications, 1997, section r8.2, page 745
[23] Sahih Al-Bukhari, Volume 5, Book 58, Number 234; Volume 5, Book 58, Number 236; Volume 9, Book 87, Number 140; see also Number 139; Volume 7, Book 62, Number 64; see also Numbers 65 and 88; Sahih Muslim, Book 008, Number 3309; see also 3310; Book 008, Number 3311; Sunan Abu Dawud, Number 2116; Book 41, Number 4915; Book 13, Number 2380;
[24] Musnad Ahmed, Number 25636
[25] Sahih Muslim, Book 008, Number 3330
[26] Ibn Ishaq, Sirat Rasulallah, translated as, The Life of Muhammad by A. Guillaume, page 243
[27] Qadi 'Iyad Musa al-Yahsubi, Muhammad Messenger of Allah (Ash-Shifa of Qadi 'Iyad), translated by Aisha Abdarrahman Bewley [Madinah

Press, Inverness, Scotland, U.K. 1991; third reprint, paperback], p. 375 & 387
[28] Sahih Bukhari, Volume 9, Book 91, Number 368
[29] Malik's Muwatta, Book 21, Number 21.13.25
[30] Sahih Muslim, Book 10, Number 3901
[31] Sahih al-Bukhari Book Number 89 Hadith Number 25

## ስለሙሐመድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተተንብዮአልን?

ቁርኣን ስለሙሐመድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተተነበየ ይናገራል (ሱራ 7፡157-158፤37፡6)። ሙስሊም ዐቃቤ እምነታውያን እነዚህን ትንቢቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዳገኙ በርግጠኝነት እየተናገሩ ይገኛሉ። ክርስቲያኖችና አይሁዶችም ሆነ ብለው ትንቢቶቹን እንደሚደብቁ በማስመሰል ወቀሳ ሲሰነዝሩ እያደመጥን ነው። ነገር ግን እነዚህ ወገኖች ስለሙሐመድ የተነገሩ ትንቢቶች ናቸው በማለት የሚያቀርቧቸውን ጥቅሶች በትክክል ብንመረምራቸው የሙሐመድን ነቢይነት በመጽሐፍ ቅዱስ ለማረጋገጥ መሞከራቸው "ላም ባልዋለበት…" እንደሚባለው ምሳሌ ዓይነት ከንቱ ምኞት መሆኑን በቀላሉ መረዳት እንችላለን።

ሙስሊም ዐቃቤ እምነታውያን የመጽሐፍ ቅዱስን ጥቅሶች ሲጠቅሱ የራሳቸውን ሐሳብ እንዲደግፉላቸው ከሚጠቀሟቸው ዘዴዎች መካከል በጣም የተለመደው ጥቅሱን ከአጠቃላይ የመጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ ብሎም ከተጻፈበት አውድ ገንጥሎ ማውጣት ነው። ነገር ግን ከጥቅሱ ጋር አብረው የተቀመጡትን ከላይና ከታች ያሉትን ሐሳቦች ብናነባቸው እነርሱ ከሚፈልጉት አላማ ጋር ፈፅሞ የማይሄዱ መሆናቸውን በቀላሉ መረዳት እንችላለን። ሌላው የተሳሳተ ዘዴያቸው በቦታው ላይ የሌለን እንግዳ ሐሳብ ወደ ጥቅሱ በመጨመር ማንበብ ሲሆን የራሳቸውን አላማ እስከደገፈ ድረስ በግድየለሽነት የሚፈልጉትን ትርጓሜ ሲሰጡ እየታዘብን ነው። ይህ ዓይነቱ ታማኝነትና ሚዛናዊነት የጎደለው አካሄድ ትዝብት ላይ የሚጥልና በእግዚአብሔር ዘንድም የሚያስጠይቅ ነው። በእርግጥ ሙስሊም ዳዒዎች በእንዲህ ዓይነቱ ከእውነት የራቀና ደካማ መሠረት ላይ አስተምህሮአቸውን መትከላቸው ለኛ ለክርስቲያን ዐቃቤ እምነታውያን እስልምና መሠረት የለሽ ሃይማኖት መሆኑን ለማሳየት ጥሩ አጋጣሚን በመፍጠር ሥራችንን አቅልሎልናል።

ሙስሊም ሰባክያን ስለሙሐመድ እንደተተነበዩ በማስመሰል የሚከራከሩባቸው ሁለት አበይት ጥቅሶች አሉ። እነርሱም ዘዳግም 18:18 እና የዮሐንስ ወንጌል 14:16 ናቸው። ጥናታችንን ከነዚህ በመጀመር መለስተኛ ግምት ወደሚሰጧቸው ጥቅሶች እንዘልቃለን፡

ማሳሰብያ፦ የሙስሊም ወገኖች የመከራከርያ ነጥቦች የተወሰዱት በዑመር አርሲ "ታላቅ ምክር ለአዲሱ ትውልድ" በሚል ርዕስ ተፅፎ በ 1999 ዓ.ም. በሱና አሳታሚ ድርጅት ከታተመው ሦስተኛ ዕትም መጽሐፍ ላይ ነው። በመሆኑም ድግግሞሽ እንዳይኖር ከመጽሐፉ የተወሰዱ ሐሳቦች ሲኖሩ ገፁን ብቻ በመጥቀስ እናልፋለን፡
፡

ሙሴን የሚመስለው ነቢይ ማን ነው?
ዘዳግም 18፡18 “እግዚአብሔር አለኝ ፦ የተናገሩት መልካም ነው። ከወንድሞቻቸው መካከል እንደአንተ ያለ ነቢይ አስነሳላቸዋለሁ። ቃሌንም በአፉ አደርጋለሁ። ያዘዝሁትንም ቃል ሁሉ ይነግራቸዋል። በስሜም የሚናገረውን ቃሌን የማይሰማውን ሰው እኔ እበቀልለታለሁ።”
ሙስሊም ዐቃቤ እምነታውያን ከዚህ ጥቅስ በመነሳት እንደ ዋና መከራከርያ የሚያቀርቡት ነጥብ አረቦችና እስራኤላውያን “ወንድማማች ሕዝቦች” በመሆናቸው ሳብያ “ከወንድሞቻቸው መካከል” የሚለው ቃል በቀጥታ የሚመለከተው ሙሐመድን ነው የሚል ነው። ነገር ግን ፈጥነን ወደ ድምዳሜ ከመድረሳችን በፊት የዘዳግም መጽሐፍ “ወንድሞች” የሚለውን ቃል በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሚጠቀምበት ማየቱ ተገቢ ነው።
የዘዳግም መጽሐፍ “ወንድሞች” የሚለውን ቃል አሥራ ሁለቱን የእስራኤል ነገዶች ለማመልከት ይጠቀማል። ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል፦
ዘዳ. 17፡14-15 “... አምላክህ እግዚአብሔር የመረጠውን በላይህ ታነግሳለህ ከወንድሞችህ የሆነውን በአንተ ላይ ንጉስ ታነግሳለህ። ወንድምህ ያልሆነውን ከሌላ ወገን ሰው በላይህ ንጉሥ ታደርግ ዘንድ አይገባህም ።”
ዘዳ. 18፡1-2 “ለሌዋውያን ካህናት ለሌዊም ነገድ ሁሉ ከእስራኤል ጋር ድርሻና ርስትአይሆንላቸውም። በእሳት ለእግዚአብሔር የሚቀርበውን መስዋእቱንና ርስቱን ይበላሉ።በወንድሞቻቸውም መካከል ርስት አይሆንላቸውም። እርሱ እንደተናገራቸው ርስታቸውእግዚአሔር ነው።”
ዘዳ. 15፡7 “አምላክህ እግዚአብሔር በሰጠህ በአገርህ ደጅ ውስጥ ከሚኖሩ ከወንድሞችህ አንዱ ቢደኸይ ልብህን አታፅና። በድሃው ወንድምህ ላይ እጅህን አትጨብጥ።”
ከላይ በተጠቀሱት ጥቅሶች ውስጥ ወንድሞች ተብለው የተጠሩት የእስራኤል ነገዶች መሆናቸው ግልፅ ነው። ስለዚህ ዘዳ. 18፡18 በዙርያው ካሉት ከነዚህ ጥቅሶች በተለየ ሁኔታ ወደሌላ ወገን ያመለክታል ተብሎ መታሰብ የለበትም።
ሌላው ይህ ጥቅስ ወደ ሙሐመድ እንደሚያመለክት የሚናገሩት ሙስሊሞች ቆርጠው የሚያስቀሩትና ክርክራቸውን ሁሉ ከስር መሠረቱ የሚንድ ሐሳብ እዚያው ምዕራፍ 18 ቁጥር አስራ አምስትና አስራ ስድስት ላይ ይገኛል።
“አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ መካከል ከወንድሞችህ እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሳልሃል።”
አሁን ሙስሊም ሰባኪያን ይህንን ጥቅስ ለምን ቆርጠው ከወገቡ መሃል ማንበብ እንደሚጀምሩ ግልፅ ነው። ይኸውም “ከአንተ መካከል ከወንድሞችህ” የሚለውን ቃል መስማትም ሆነ ማየት ስለማይፈልጉ ነው። ፈለጉም አልፈለጉም እውነቱ ይኸው ነው! “ከአንተ መካከል” የሚለው ቃል ሌላ ምንም አማራጭ ሳያስቀር ወደ እስራኤላውያን ብቻ የሚያመለክት መሆኑን የሚክድ በእኩለ ቀን ሜዳ ላይ ቆሞ ፀሐይ አይታየኝም እንደሚል የታወረ ሰው ነው!
ሌላው ሙስሊም ዐቃቤ እምነታውያን ሊጠቅሱት የማይወዱት የቃሉ ተከታይ ክፍል እንዲህ ይነበባል፦
ዘዳ18፡20-22 “ነገር ግን ይናገር ዘንድ ያላዘዝሁትን ቃል በድፍረት የሚናገር ወይም በሌላ አማልክትስም የሚናገር ነቢይ እርሱ ይገደል። በልብህም፦ እግዚአብሔር

ያልተናገረውን ቃል እናውቅ ዘንድእንዴት ይቻለናል? ብትል ነቢዩ በእግዚአብሔር ስም በተናገረ ጊዜ የተናገረው ነገር ባይሆን ባይመጣም ያ ነገር እግዚአብሔር ያልተናገረው ነው። ነቢዩ በድፍረት ተናግሮታል እርሱን አትፍራው።"
ሙሐመድ ይህንን መለኪያ ያልፍ ይሆን? "ሰይጣናዊ ጥቅሶች" በመባል ስለሚታወቁ መገለጦች በጥንታዊያን እስላማዊ ድርሳናት ውስጥ እናነባለን፡፡ ሙሐመድ እስልምናን በጀመረበት ወቅት ለረጅም ዘመናት ሲመለኩ የኖሩ አል-ላት፤ አል-ኡዛ እና አል-መናት በመባል የሚታውቁ ጣዖታትን ትቶ የርሱን ትምህርት መከተል ለብዙዎች ፈተና ሆኖ ነበር። ስለዚህ ሙሐመድ እነዚህ ጣዖታት እንደሚያማልዱ እንደ ተገለጠለት በመናገር ቁረይሾችን አስደሰተ፤ ብዙ ተከታዮችንም አገኘ። ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ እንዲተሳሳተ ገባው። እናም መገለጡ ከአላህ ዘንድ ሳይሆን ከሰይጣን ዘንድ እንደነበር ተናገረ። (ይህ ታሪክ በኢብን ኢስሃቅና በአልጠበሪ በተጻፉ የሙሐመድ ግለ-ታሪኮች ውስጥ በስፋት የተዘገበ ሲሆን ኢማም ቡኻሪ በከፊል ጽፈውታል።የበለጠ ለማወቅ እዚህ ጋ ጠቅ ያድርጉ)። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ግን ከእውነተኛ ነቢያት መካከል መገለጥ ተናግሮ መልሶ ደግሞ መገለጡ ከሰይጣን ዘንድ እንደሆነ የተናገረ ነቢይ የለም!
ሙስሊሞች ሙሴና ሙሐመድ እንደሚመሳሰሉ ለማሳመን ብዙ ጥረቶችን አድርገዋል። ነገር ግን ይመሳሰሉባቸዋል በማለት የሚያነሱአቸው ነጥቦች ማንኛውም ተራ ሰው ሊመሳሰልባቸው የሚችላቸው ናቸው። ለምሳሌ ያህል ዑመር አርሲ ከአሕመድ ዲዳት በመቅዳት የወሠዷቸውን "መመሳሰሎች" እንደሚከተለው በመጽሐፋቸው ውስጥ አስፍረዋል፡-
"- ሁለቱም እናትና አባት ነበሯቸው
– አግብተው ልጆች ወልደዋል
– ተፈጥሮአዊ ሞት ሞተዋል
– ተዋግተዋል
– በሕዝባቸው ላይ መሪዎች ነበሩ" (ገፅ 59)
እነዚህ ተራ "መመሳሰሎች" ዋጋ የሚሠጣቸው ከሆነ አቶ ዑመርን ለመርዳት ያህል ጥቂት ነጥቦችን መጨመር እንችላለን፡-

- ሁለቱም ሰዎች መሆናቸው
- ሁለቱም ወንዶች መሆናቸው
- ሁለቱም ጢም ያላቸው መሆናቸው
- የሁለቱም ስም "M" በሚለው የእንግሊዘኛ ፊደል መጀመሩ ወዘተ.

ደቡብ አፍሪካዊው አሕመድ ዲዳት በተለያዩ ጽሑፎቻቸውና የቪዲዮ ሰበካዎቻቸው ሙሴና ሙሐመድ እንደሚመሳሰሉ ለማሳየት በዑመር አርሲ የተጠቀሱትን ነጥቦች ከኢየሱስ ጋር በማያያዝ በእነዚህ ነገሮች ሙሴና ኢየሱስ እንደማይመሳሰሉ በመግለጽ ሙሐመድና ሙሴ ይመሳሰላሉ ለሚለው ነጥባቸው ጥንካሬን ለመስጠት ይታገላሉ። አሕመድ ዲዳት ። ሙሴና ሙሐመድን ብቻ ማመሳሰል ሚዛን የማይደፋ ከንቱ ልፋት መሆኑን የተረዱ ይመስላል። እንደ አሕመድ ዲዳት ብልጠትና ማጭበርበርን ያልተካኑት የአገራችን ጸሐፊ ዑመር አርሲ ግን ኢየሱስን ከሁለቱ በመነጠል የሙሴና የሙሐመድ መመሳሰል ተራ መሆኑን በበቂ ሁኔታ አሳይተዋል። ግሩም ሥራ ነው።
መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ሙሴን የሚመስለው ነብይ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን

ይናገራል (ሐዋ. 3፡17-26)፡፡
ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው መመሳሰል የጠለቀና መንፈሳዊ ገፅታ ያለው እንጂ ከላይ የተጠቀሰው ዓይነት ተራ መመሳሰል እንዳልሆነ መረዳት ተገቢ ነው፡፡
ሙሴና ኢየሱስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ንፅፅር (ከብዙ በጥቂቱ)

1. ሙሴና ኢየሱስ የተወለዱት ወገኖቻቸው በባዕድ አገዛዝ ሥር በነበሩበት ጊዜ ነበር፡፡ ዘጸ. 1፡9-14፣ ሉቃ. 2፡1
2. ሁለቱም በተወለዱ ጊዜ የሞት አዋጅ ታውጆባቸው ነበር፡፡ ዘጸ. 1፡15-16 ማቴ. 3፡13-18
3. ሁለቱም በመለኮታዊ ጣልቃ ገብነት ከሞት ተርፈዋል፡፡ ዘጸ. 2፡ 2-10 ማቴ. 2፡13-18
4. ሁለቱም በግብፅ ተጠልለው ኖረዋል፡፡ ዘጸ 2፡10 ማቴ. 2፡14-15
5. ሁለቱም በድንቅና በተአምራት ተገልጠዋል፡፡ ዘጸ. ም. 7፤8፤14፤17 ማቴ 8፡14-17ሉቃ 7፡11
6. ሁለቱም አርባ ቀንና ሌሊት ፆመዋል፡፡ ዘጸ. 32፡ 31 ማ ቴ. 4፡2
7. ውሃ ለሁለቱም ሥልጣን ተገዝቷል፡፡ ዘጸ. 14፡21 ማቴ. 14፡ 22-23
8. ሙሴ የብሉይ ኪዳን መካከለኛ ሲሆን ኢየሱስ ደግሞ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ነው፡፡ ዘጸ. ም. 19-20 ዕብ 12፡24
9. ሙሴ እስራኤላዊያንን ከግብፅ ባርነት ነፃ እንዳወጣ ሁሉ ኢየሱስም በስሙ ያመኑትን ከኃጥያት ባርነት ነፃ ያወጣል፡፡ ኢሳ. 53 ዮ ሐ 8፡32-36 ሉቃ 4፡17-19
10. ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር በቀጥታ ተነጋግሯል፡፡ ኢየሱስም እንዲሁ፡፡ ዘጸ. 33፡11 ማቴ. 17፡3
11. ሁለቱም ሕዝብ እየሠማ እግዚአብሔር ተናግሯቸዋል፡፡ ዘጸ. 19:19 ዮሐ 12:28
12. በሲና ተራራ ላይ በነበረው ክብር ምክንያት የሙሴ ፊት ሲያበራ በተራራው ሕብረት ምክንያት እንዲሁ የክርስቶስ ሁለንተና አብርቷል፡፡ ዘጸ 34፡29 ማቴ 17፡2
13. ሁለቱም ተከታይ ለማግኘት ሰይፍ አላነሱም፡፡ ዘጸ. 7፡8፤ 14፡25 ማር 1፡21-25
14. የሙሴ መቃብር በመላእክት ይጠበቅ እንደነበረ ሁሉ የክርስቶስም እንዲሁ ነበር፡፡ ይሁዳ 1፡9 ማቴ 28፡2
15. ሙሴ ከሞተ በኋላ ለነ ጴጥሮስ ታይቷል፡፡ ኢየሱስም እንደዚሁ ከሙታን ተነስቶ ለነ ጴጥሮስ ታይቷል፡፡ ማቴ 17፡1-5፣ ዮሐ 20፡19

ክርስቲያኖች ሙሴና ኢየሱስ ይመሳሰላሉ በማለት ሲናገሩ ከላይ በቀረበው መልኩ ነው፡፡ ከላይ በተጠቀሱት በአብዛኞቹ ነጥቦች ላይ ሙሴና ሙሐመድ ይቃረናሉ እንጂ አይመሳሰሉም፡፡ ስለዚህ ሙስሊሞች ከላይ የተጠቀሱት ዓይነት የጠለቀ አንድምታ ያላቸው መመሳሰሎች በሙሴና በሙሐመድ መካከል መኖራቸውን ሊያረጋግጡልን ይችላሉን?
አፅናኙ ሙሐመድ ነውን?
ዮሐንስ 14፡16 "እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እን ዲኖር ሌላ

አፅናኝይሰጣችኋል”
በቁርአን 61፡6 ላይ እንዲህ የሚል ቃል ተፅፎ እናገኛለን “የመርየም ልጅ ኢሳም፡ – የእስራኤል ልጆችሆይ እኔ ከተውራት በፊቴ ያለውን የማረጋገጥና ከኔ በኋላ የሚመጣው መልክተኛ ስሙ አሕመድበሆነው የማበስር ሲሆን ወደእናንተ (የተላክሁ) የአላህ መልክተኛ ነኝ።” ይህንን ቃል የሚደግፍ ሐሳብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለማግኘት ካላቸው ጉጉት የተነሳ ሙስሊም ሰባኪያን ስለ አፅናኙ የተተነበየውን ትንቢት ስለ ሙሐመድ ነው የሚል መከራከርያ ያቀርባሉ። እነዚህ ወገኖች ክርስቲያኖች ይህንን እውነታ በማጣመም መንፈስ ቅዱስ ነው በማለት እንደሚያስተምሩ በማማረር ይወነጅላሉ። እንደሌሎቹ እስላማዊ ክርክሮች ሁሉ ይህኛውም ፍፁም የተሳሳተና መሠረተ ቢስ መሆኑን እንደሚከተለው እንገልጣለን።
ሙስሊም ዳዒዎች አሕመድ የሚለው የአረብኛ ቃል በግሪክ ቋንቋ “ፔሪክሉቶስ” (በአማርኛ አነባበብ ጴሪቅሉጦስ) እንደሆነና ክርስቲያኖች “ፐራክሊቶስ” (በአማርኛ አነባበብ ጰራቅሊጦስ) ወደሚለው እንደቀየሩት ይናገራሉ። “ፐራክሊቶስ” በግሪክ ቋንቋ አፅናኝ ማለት ሲሆን ወደ “ፔሪክሉቶስ” ሲቀየር “የተመሰገነ” (በአረብኛ አሕመድ) የሚል ትርጓሜን ይሰጣል። ነገር ግን ሙሐመድ ከመወለዱ በፊት ብዙ ዘመናትን ካስቆጠሩ በሺዎች ከሚቆጠሩ የአዲስ ኪዳን መዛግብት መካከል አንዱም እንኳ “ፔሪክሉቶስ” የሚለውን ቃል ይዞ አይገኝም፡ ፡ ነገር ግን ሁሉም ላይ ተፅፎ የሚገኘው “ፐራክሊቶስ” የሚለውና አፅናኝ የሚል ትርጉም ያለው ቃል ነው። በመሆኑም ይህ የሙስሊም ሰባኪያን ክስ መሠረተ ቢስ አሉባልታ ብቻ መሆኑ መታወቅ አለበት።
ብዙ ጊዜ ሙስሊም ወገኖቻችን ሊያነቡ የማይወዱትና ክርክራቸው ትክክል እንዳልሆነ የሚገልጥ የክፍሉ ቀጣይ ቁጥር እንዲህ ይላል፦
“እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለሆነ ሊቀበለው የማይችለው የእውነት መንፈስ ነው። ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር በውስጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቁታላችሁ” ዮሐ. 14፡17።
ኢየሱስ ይህንን ቃል የተናገረው ለሐዋርቱ ነበር። አፅናኙም ይመጣል እያለ ያለው ወደ እነርሱ ነው። በማስከተል ደግሞ እንዲህ በማለት የአፅናኙን ማንነትና ይሥራ ድርሻ ግልፅ አድርጓል፦
“አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አፅናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔምየነገርኳችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል” ዮሐ. 14፡26
“እኔ ግን እውነት እነግራችኋለሁ እኔ እንድሄድ ይሻላችኋል። እኔ ባልሄድ አፅናኙ ወደ እናንተአይመጣምና። እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ ። እርሱም መጥቶ ስለኃጢዓት ስለፅድቅምስለፍርድም ዓለምን ይወቅሳል። ስለኃጢዓት በኔ ስለማያምኑ ነው፤ ስለፅድቅም ወደ አብ ስለምሄድከዚህ በኋላ ስለማታዩኝ ነው ስለፍድም የዚህ ዓለም ገዢ ስለተፈረደበት ነው። የምነግራችሁ ብዙነገር አለኝ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም። ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደእውነት ሁሉ ይመራችኋል። የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይናገርምና የሚመጣውንምይነግራችኋል። እርሱ ያከብረኛል ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና። ለአብ ያለው ሁሉ የእኔ ነው ።ስለዚህ ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋል አልሁ” ዮሐ. 16፡8-16።

አፅናኙ ሙሐመድ ነው ከተባለ ተከታዮቹን ነጥቦች ሙስሊም ዐቃቤ እምነታውያን እንዴት ይመለከቱአቸዋል?

1. አፅናኙን ዓለም ሊያየው ሊያውቀውና ሊቀበለው አይችልም። ሙሐመድ ግን ሥጋ ለባሽ እንጂ መንፈስ ስላልነበረ በዓለም ታይቷል ፤ ማንነቱም በታሪክ ይታወቃል።
2. አፅናኙ "የእውነት መንፈስ" እንጂ ሰው አይደለም።
3. አፅናኙ ከኢየሱስ ሐዋርያት ዘንድ ስለሚኖርና በውስጣቸውም ስለሚሆን እነርሱ ያውቁታል። ሙሐመድ ግን የመጣው እነዚህ ሰዎች ከሞቱ ከብዙ አመታት በኋላ ስለሆነ ከእነርሱ ጋር መኖር አይችልም፤ መንፈስ ስላልሆነም በውስጣቸው ሊያድር አይችልም።
4. አፅናኙ መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ በግልጥ ተፅፏል።
5. አፅናኙ የሚመጣው በኢየሱስ ስም ነው። ሙሐመድ ግን በማን ስም ነው የመጣው?
6. አፅናኙ ለኢየሱስ ሐዋርያት ሁሉን ያስተምራቸዋል ኢየሱስ የነገራቸውንም ሁሉ ያሳስባቸዋል። ሙሐመድ ግን በእነርሱ ዘመን ስላልነበረ ይህን ሁሉ ነገር ማድረግ አይቻለውም።
7. አፅናኙ ኢየሱስን ያከብረዋል፡ ከኢየሱስ ካለውም ወስዶ ለሐዋርያቱ ይነግራቸዋል። ምክንያቱም የአብ የሆነው ሁሉ የኢየሱስ ነውና። ሙስሊሞች የአብ የሆነው ሁሉ የኢየሱስ መሆኑን ያምናሉን?
8. አፅናኙን ወደ ሐዋርያቱ የሚልከው ራሱ ኢየሱስ ነው። ሙስሊሞች ሙሐመድ በኢየሱስ እንደተላከ ያምናሉን? አፅናኙ ሙሐመድ ነው ከተባለ ተከታዩ አመክንዮአዊ ድምዳሜ አይቀሬ ነው፦

- ሙሐመድን የላከው አላህ ነው።
- ሙሐመድ አፅናኙ ነው።
- አፅናኙን የላከው ኢየሱስ ነው።
- ስለዚህ አፅናኙ ሙሐመድን የላከው አላህ ኢየሱስ ራሱ ነው።

በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ላይ እንደምናነበው ጌታ ኢየሱስ ስለ መንፈስ ቅዱስ ወደ ሐዋርያቱ መምጣት በድጋሜ የተስፋ ቃሉን አጽንቷል (ሐዋ. 1፡5)። ይህም የተስፋ ቃል በጥቂት ቀናት ውስጥ ፍፃሜን አግኝቷል። (የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ሁለትን ያንብቡ።)

ሙስሊሙ ጸሐፊ ዑመር አርሲ "ታላቅ ምክር ለአዲሱ ትውልድ" በሚለው መጽሐፋቸው ገፅ 57 እና 58 ላይ ዮሐ. 16፡5-8 ላይ ያለውን ቃል ሲጠቅሱ "እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ" የሚለውን ዐረፍተ ነገር በግልፅ ይዘሉታል። ይህ የኢየሱስ ንግግር አፅናኙ ሙሐመድ ነው የሚለውን ነጥባቸውን የእምቧይ ካብ እንደሚያደርግባቸው ስለሚገነዘቡ እንደ አቶ ዑመር ሁሉ ሙስሊም ሰባኪያን በንግግሮቻቸውና በጽሑፎቻቸው ውስጥ ይህንን ቃል ላለመጥቀስ ይጠነቀቃሉ።

አቶ ዑመር በመጽሐፋቸው ውስጥ መንፈስ ቅዱስ "ዓለምን ሲወቅስ አልታየም" በሚል ልፍስፍስ ምክንያት አፅናኙ እርሱ እንዳልሆነ ለማሳመን ይጥራሉ (ገፅ 57)። ነገር ግን በሐዋርያት ውስጥ ሆኖ ዓለምን ሲወቅስ የነበረው ማን ነበር? ራሱ መንፈስ ቅዱስ አልነበረምን? መንፈስ ቅዱስ ዓለም ባያየው፣ ባያውቀውና

ባይቀበለው እንኳ በሐዋርያት ውስጥ ሆኖ ሥራውን ሲሠራ ነበር። በእርሱ ምሪት በተጻፈልን በቅዱስ ቃሉም አማካይነት ሥራውን ቀጥሏል። ዛሬም ቢሆን በእውነት በክርስቶስ ኢየሱስ ባመኑት ክርስቲያኖች ውስጥ ይኖራል።
መንፈስ ቅዱስ በሁሉ ስፍራ በመገኘት ቾሎታው ከሐዋርያት ጋር ነበር። ነገር ግን ከዚያ ባለፈ ሊጠቀምባቸውና ሥራውን ሊሠራ በውስጣቸውም ሊኖር በታላቅ ክብር ወደ እነርሱ የመጣው ኢየሱስ የተስፋ ቃሉን ለሐዋርያቱ ካፀናላቸው ከጥቂት ቀናት በኋላ ነበር። ዑመር አርሲ "መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር አብና ከእግዚአሔር ወልድ ጋር እኩል ከሆነ ከማነው የሚሰማውን የሚናገረው?" የሚል ጥያቄ ይሰነዝራሉ (ገፅ 58)። በእግዚአብሔር አካላት (በሥላሴ) መካከል እኩልነት መኖሩ እንደይከባበሩ እንዳይደማመጡና አንዱ ለአንዱ እንዳይታዘዝ አያደርግም። መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ የሚሰማውን መናገሩ፤ ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ ለአብ መገዛቱና በመንፈስ ቅዱስ መመራቱ፤ አብ ኢየሱስን ማክበሩ ለኛ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን የፍቅርና የትህትና መገለጫ እንጂ የበላይነትና የበታችነትን አያሳይም። አቶ ዑመርና ሌሎች ሙስሊም ተሟጋቾች የክርስቲያኖች አምላክ በቁርኣን ውስጥ ከተገለጠው አምላካቸው ፈፅሞ የተለየ መሆኑን ሊረዱልን ይገባል።
አምስቱ ጥቅሶች
በማስከተል ሙስሊም ዐቃቤ እምነታውያን ስለሙሐመድ እንደተተነበዩ በማስማሰል የሚጠቅሷቸውንና መለስተኛ ግምት የሚሰጧቸውን አምስት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እንመለከታለን።
1. ዘዳ. 33፡2-3 "እግዚአብሔር ከሲና መጣ ከሴይርም ተገለጠ ከፋራን ተራራ አበራላቸውከአእላፋትም ቅዱሳኑ መጣ፡ በስተቀኙ የእሳት ህግ ነበረላቸው ። ህዝቡንም ወደዳቸውቅዱሳኑ ሁሉ በእጅህ ናቸው።"
ሙስሊም ዐቃቤ እምነታውያን ለዚህ ጥቅስ ማብራሪያ ሲሰጡ "እግዚአብሔር ከሲና ሲመጣ በሙሴ በኩል መጣ ከሴይር ሲገለጥ በኢየሱስ በኩል ተገለጠ ከፋራን ተራራ ሲያበራ በሙሐመድ በኩል አበራ" በማለት ነው። ነገር ግን "እግዚአብሔር" የሚል እንጂ "ነቢይ" የሚል አንድም ቃል በቦታው ላይ አይገኝም። ሙስሊሞች ይህንን ቃል ለነቢያቸው እንደተነገረ ትንቢት የሚቆጥሩበት ምክንያት የፋራን ተራራ መካ አጠገብ ይገኛል ከሚል የተሳሳተ ግምት በመነሳት ነው። የፋራን ተራራ የሚገኘው በሰሜን ምዕራብ ሲና በሚገኘው በፋራን ምድረበዳ ውስጥ ነው። ይህም ከመካ ቢያንብ 1000 ኪሎሜትሮች ርቀት ላይ ይገኛል። እስራኤላውን በጉዟቸው ወቅት በፋራን ምድረበዳ ውስጥ እንዳለፉ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልፅ ሰፍሯል (ዘኍ. 10፡12፤ 12፡16፤ 13፡3፤13፡26 ዘዳ. 1፡1)። መቼም እስራኤላውያን ወደ መካ እንዳልተጓዙ ይታወቃል። ስለዚህ ለራስ ዓላማ ሲባል የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል እንደፈለጉ መተርጎም ትክክለኛ አካሄድ እንዳልሆነ ለማሳሰብ እንወዳለን።
2. ራዕይ 19፡11 "ሰማይም ተከፍቶ አየሁ እነሆም አምባላይ ፈረስ የተቀመጠበትም የታመነናእውነተኛ ይባላል፡ በፅድቅም ይፈርዳል ይዋጋልም። "
ሙስሊም ዐቃቤ እምነታውያን ስለነቢያቸው እንደተተነበዩ በማስመሰል በድፍረት ከሚያቀርቧቸው ጥቅሶች መካከል በጣም አስገራሚው ይኸኛው ነው። ሙስሊሙ ጸሐፊ ዑመር አርሲ የዚህን ጥቅስ ቀጣይ ክፍል ቆርጠው

በማስቀረት ከላይ የተጠቀሰውን ብቻ በመውሰድ ለሙሐመድ የተነገረ ነውና እመኑ ይሉናል (ገፅ 58)። ምናልባት የሳቸውን መጽሐፍ የሚያነቡ አብዛኞቹ ሙስሊሞች ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ለማመሳከር እድሉ እንደሌላቸው ስለሚያውቁ እነርሱን ለማታለል ካልሆነ በስተቀር መጽሐፍ ቅዱስ በእጁ እያለለት የሚታለል ክርስቲያን እንደማይኖር ልቦናቸው ሳያውቅ ቀርቶ አይመስለንም። ቀጣዩ ክፍል እንዳህ ይነበባል፡-

“ዓይኖቹ እንደ እሳት ነበልባል ናቸው። በራሱ ላይም ብዙ ዘውዶች አሉ።ከእርሱ በቀር አንድስንኳየማያውቀው የተፃፈ ስም አለው። በደምም የተረጨ ልብስ ተጎናፅፎል ስሙም የእግዚአብሔርቃል ተብሎአል። … በልብሱና በጭኑ ላይ የተፃፈበት፡– የነገስታ ንጉስና የጌታዎች ጌታ የሚል ስምአለው።” ራዕ. 19፡12-16

በቁርኣንም ሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ “የእግዚአብሔር ቃል” መሆኑ የተመሠከረለት ኢየሱስ ብቻ ነው። (ዮሐ. 1፡11 ከሱራ 4፡171 ጋር ያነፃፅሩ።)

አቶ ዑመር የክርስትና መመርያ መዋጋትን ስለሚከለክል ይህ ጥቅስ ኢየሱስን አይመለከትም ይሉናል። ነገር ግን ጌታችን ኢየሱስ በዳግም ምፅዓቱ ጊዜ ለሁሉም እንደየሥራው ዋጋን እንደሚሰጥና በፅድቅ እንደሚፈርድ እንዲሁም የሰይጣንን ኃይል እንደሚደመስስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጥ ተጽፏል (ራዕ. 22፡12 ፤19፡19-21)። ኢየሱስ መጀመርያ የመጣው ሰዎችን ለማዳን ሲል ራሱን ዝቅ አድርጎ ክብሩን ጥሎ ቢሆንም ነገር ግን በዳግም ምፅዓቱ ጊዜ በታላቅ ግርማና ሞገስ ጠላቶቹን ለመደምሰስና በፅድቅ ሊፈርድ ይገለጣል። ዮሐንስም በራዕዩ ያየው ይህንኑ ነው።

3. ዕንባቆም 3፡3 “እግዚአብሔር ከቴማን ቅዱሱም ከፋራን ተራራ ይመጣል። ክብሩም ሰማያትንከድኗል። ምስጋናውም ምድርን ሞልቷል።”

አሁንም የሙስሊም ጸሐፊያን ግራ መጋባት የመነጨው ቴማን መዲና ፋራን ደግሞ መካ ነው ከሚል የተሳሳተ ግምት ነው። የመጽሐፍ ቅዱሱ ፋራን ከመካ ርቆ የሚገኝ ቦታ እንሆነ ቀደም ሲል ገልፀናል። ቴማን ደግሞ ከመካ ቢያንስ በ400 ኪሎ ሜትሮች ርቀት ወደ ሰሜን አቅጣጫ የሚገኝበታ ነው።

ይህ ቃል የሚናገረው እግዚአብሔር በታላቅ ግርማ እንደሚገለጥ ነው። ይመጣል የተባለውም ራሱ እግዚአብሔር ሲሆን ወደ ሌላ ወደ ማንኛውም ነቢይ አያመለክትም። ይህ ዓይነቱ አነጋገር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተለመደ፤ የእግዚአብሔርን ክብር እንዲሁም ቁጣውን ለመግለጥ የሚነገር ተምሳሌታዊ ንግግር ነው። መካና መዲና ከቴማንና ፋራን ጋር በፍፁም አንድ ስላልሆኑ ይህ የሙስሊሞች መከራከርያ ስፍራ የሚሰጠው አይደለም።

4. ኢሳያስ 21፡7 “በከብት የሚቀመጡትን ሁለት ሁለት እየሆኑ የሚሄዱት ፈረሰኞች በአህዮችየሚቀመጡትንና በግመሎች የሚቀመጡትን ባየ ጊዜ በፅኑ ትጋት አስተውሎ ተግቶም ያዳምጥ”

ሙስሊም ጸሐፊያን በግመሎች የሚቀመጡት ነቢዩ ሙሐመድና ተከታዮቹ ሲሆኑ በአህዮች የሚቀመጡት(!?) ደግሞ ኢየሱስ እንደ ሆነ ይነግሩናል። እኛ ደግሞ በፈረሶች የሚቀመጡትስ እነማን ሊሆኑ ይችላሉ? ብለን እንጠይቃቸዋለን፡ ፡ ኢየሱስ በክብር ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ ብቻውን በአህያ ውርንጫ ላይ ተቀምጦ እንጂ ሌሎች ሰዎች ከርሱ ጋር በአህዮች ተቀምጠው አላጀቡትም ሉቃ. 19፡ 28-40። ይህ ጥቅስ የሚናገረው ስለ ነቢያት ሳይሆን ስለባቢሎን መጥፋት ነው፡

፡ ይህንንም እዚያው ላይ ከተጻፈው ቃል መረዳት ይቻላል። “ባቢሎን ወደቀች ...” (ቁ. 9)። የባቢሎንን መጥፋት የሚያውጁ መልእክተኞች በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሚመጡ የሚገልጥ ትንቢት መሆኑን ከአውዱ ንባቡ መገንዘብ እንችላለን። ስለዚህ ይኸኛውም የሙስሊም ጸሐፊያን የመከራከሪያ ነጥብ እንደሌላው ሁሉ ሚዛን የሚደፋ አይደለም።

5. ኢሳያስ 21፡13-17 “ ስለ ዓረብ የተነገረ ሸክም፡– የድዳው ያን ነጋዴዎች ሆይ በአረብ ዱር ውስጥታድራላችሁ። በቴማን የምትኖሩ ሆይ ወደ ተጠሙ ሰዎች ውሃ አምጡ እንጀራ ይዛችሁየሸሹትን ሰዎች ተቀበሏቸው።ከሰይፍ ከተመዘዘው ሰይፍ ከተለጠጠውም ቀስት ከፅኑምሰይፍ ሸሽተዋልና። ጌታ እንዲህ ብሎኛልና፡– እንደምንደኛ ዓመት በአንድ ዓመት ውስጥ የቄዳርክብር ሁሉ ይጠፋል ከቀስተኞች ቁጥር የቀሩት የቄዳር ልጆች ኃያላን ያንሳሉ። የእስራኤልአምላክ እግዚአብሔር ተናግሯልና።”

ከላይ የተጠቀሰው ጥቅስ የሙሐመድን ከመካ ወደ መዲና መሰደድ የሚያመለክት እንደሆነ ሙስሊም ሰባኪያን ይነግሩናል። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጠው ቴማን መዲና እንዳልሆነ ቀደም ሲል ተመልክተናል። ቄዳር ተብለው የሚታወቁት ደግሞ የእስማኤል ዝርያዎች ናቸው። (ሙሐመድ የእስማኤል ዘር ስለመሆኑ እስላማዊ ምንጮች እርስ በርሳቸው የሚጣረሱ መርጃዎችን ያቀርባሉ። ገሚሶቹ የእስማኤል ዘር እንደሆን የሚናግሩ ሲሆን ገሚሶቹ ግን ይህንን ሐሳብ ያፈርሳሉ። ሙሐመድን ከእስማኤል ጋር ማያያዝ ከአብርሃም ጋር እርሱን በማገናኘት ለነቢይነቱ ሕጋዊ መሠረት ለመስጠት በኋለኞቹ ሙስሊሞች የተፈጠረ የፈጠራ ታሪክ እንጂ ማስረጃ ያለው አይደልም። ለበለጠ መረጃ እዚህ ጋር ጠቅ ያድርጉ።)

ኢሳይያስ በትንቢቱ ውስጥ እየተናገረ ያለው ሕዝቦች ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ ስለሚሰደዱበት ሁኔታ ነው። በዚሁም መሠረት ኢሳይያስ ትንቢቱን በተናገረ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በ732 ዓ.ዓ ላይ አሦራውያን መካከለኛውን ምስራቅ በመውረር ብዙ ሕዝቦችን ፈጅተዋል። በዚህም ወረራ በአረብና በሲና በረሃ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ህዝቦች ከአንዱ ወደ ሌላው ቦታ ለመሰደድ ተገደዋል። ነቢዩ ኢሳይያስ በትንቢቱ ውስጥ በግልፅ እንደተናገረው የመፈፀምያ ጊዜው በአንድ አመት ውስጥ ነው። ትንቢቱም በትክክል ተፈጽሟል።

ዑመር አርሲ ሙሐመድ ከመካ ወደ መዲና ከተሰደደ ከአንድ ዓመት በኋላ የመካን ክብርስላጠፋትንቢቱበዚያተፈጽሟልበማለትጽፈውልናል(ገፅ46)።ይህ ፍጹም ሀሰት ነው። ሙሐመድ መካን ለመቆጣጠር ድፍን ስምንት ዓመት ፈጅቶበታል። “የበድር ጦርነት የተካሄደውና ሙሐመድና ተከታዮቹ የመካን ነዋሪዎች ያሸነፉት ከስደቱ በኋላ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ነበር” የሚለው የአቶ ዑመር አባባል ዐይን ያወጣ ቅጥፈት ነው። እኚህ ጸሐፊ “አንድ ዓመት” የሚለውን የትንቢት ቃል ከሙሐመድ ታሪክ ጋር ለማገናኘት የበድር ጦርነት የተደረገው በ 623 ዓ.ም. እንደነበር ነግረውናል። ነገር ግን ሙሐመድ ከመካ ወደ መዲና የተሰደደው በ622 እ.ኤ.አ ሲሆን የበድር ጦርነት ደግሞ የተካሄደው በ624 እ.ኤ.አ (በሁለተኛው ሂጅራ) ነው። በድር ላይ ካሸነፈ ከአንድ ዓመት በኋላ በ625 ዓ.ም በኡሁድ ጦርነት ላይ ከባድ የሆነ ሽንፈት ገጥሞታል። በዚህ ጦርነት ላይ አጎቱ ሐምዛ የሞተ ሲሆን ሙሐመድ እራሱ ከጠላት ወገን በተወረወረ ድንጋይ ከንፈሩ ተሰንጥቆ ሁለት የፊት ጥርሶቹ ረግፈዋል። የሙሐመድ እንደሆኑ የሚነገርላቸው ሁለት ጥርሶች

ዛሬ በኢስታንቡል ሙዚየም ውስጥ ተቀምጠው ይገኛሉ። (Paul Fregosi, Jihad in the West, 1998, p. 53 ይመልከቱ።)
ሙስሊሞች መካን ከተቆጣጠሩ በኋላም ቢሆን የመካ ክብር ጠፍቷል የሚያስብል ምንም ምክንያት የለም። የመካ ነዋሪዎች ለሙሐመድ እጅ መስጠታቸው በብዙ መልኩ ጥቅማቸውን አስጠብቆላቸዋል። ከካዕባ ያገኙ የነበሩትም ገቢ ቀደም ሲል ቢቀዛቀዝም ነገር ግን ለአምልኮ ወደዚያ በሚመላለሱ ሙስሊሞች ሳቢያ ተፈላጊነታቸው ጨመረ እንጂ አልቀነሰም። ከሙሐመድ ሞት በኋላም ቢሆን በኸሊፋዎች አማካይነት የመሪነቱን ስፍራ በመቆናጠጥ የበላይነታቸውን አረጋግጠው ኖረዋል። ታዲያ የመካና የነዋሪዎቿ የቁረይሾች ክብር ሁሉ ጠፍቷል የሚያስብል ምን ሁኔታ ተፈጠረ? ሙስሊሙ ጸሐፊ ዑመር አርሲ የሙሐመድን ነቢይነት በመጽሐፍ ቅዱስ ለማረጋገጥ ያላቸው ጉጉት ታሪክን እንኳ እንዲጠመዝዙ ምክንያት ሆኗቸዋል።
እግዚአብሔር አምላካችን የሙስሊም ወገኖቻችንን የልብ ዐይኖች በመክፈት እውነትን ወደማወቅ ይመራቸው ዘንድ የዘወትር ጸሎታችን ነው።

## የጀነት በር ተከፍቷል!

ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች የሰው ልጆች ከፈጣሪያቸው ተለይተው ለጥፋት እንደተዳረጉ ያምናሉ። ትክክለኛ መኖርያችን የነበረው ተድላና ደስታ የተሞላበት ገነት ቢሆንም አዳምና ሔዋን (አደምና ሐዋ) በሠሩት ኃጢአት ምክንያት ከገነት ስለተባረርን በሰቆቃ በተሞላው ምድር እንድንኖር ተወስኖብናል። ነገር ግን ቸርና አዛኝ የሆነው ፈጣሪ አምላካችን ከእርሱ ተለይተን ለዘላለም እንድንጠፋ ስላልወደደ የገነትን በር ድጋሜ ከፍቶታል፤ የመመለሻ መንገዱንም እጅግ አቅልሎልናል። በቁርአንም ሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ ታሪኮችን ስናጠና ፈጣሪ አምላካችን ሩቅ ሆኖ መመርያዎችን ከመላክ ይልቅ ወደ ሰው ልጆች ቀርቦ ከእርሱ ጋር መኖር የሚያስችላቸውን ከእነርሱ የሚጠበቁትን መስፈርቶች ራሱ ባዘጋጀው መንገድ ሲያሟላ እንመለከታለን።
ከተከታዮቹ አምስት ታሪኮች መካከል አራቱ በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ በቁርአን ውስጥ ተመዝግበዋል። ውዱ ሙስሊም ወዳጄ! እነዚህ ታሪኮች እግዚአብሔር ካንተ የሚጠበቁትን መስፈርቶች አሟልቶልህ ወደ ገነት ሊመልስህ የሠራውን ሥራ የሚያሳዩ ናቸውና እባክህን በጥንቃቄ አጥናቸው።
በኃጢአታቸው ምክንያት የደረሰባቸውን ራቁትነታቸውን ለመሸፈን እግዚአብሔር አምላክ ለአዳምና ለሔዋን ልብስ አዘጋጀላቸው። ለቃኤልና ለአቤል እግዚአብሔር ትክክለኛውን የመሥዋዕት መንገድ አዘጋጀ። ለአብርሃም ልጁን ለመታደግ ታላቅ መሥዋዕትን አዘጋጀለት። ለሙሴና ለእስራኤላውያን ለተወሰኑ ኃጢአቶች ስርየት የሚሆን የመሥዋዕት ስርአትን በካህናትና በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ አማካይነት አቋቋመላቸው። ለሰው ልጆች በሙሉ ደግሞ የመሥዋዕት ስርአቶችን ወደ ፍጻሜ የሚያመጣ ቤዛ ቅዱስ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ሰጠ። ያለፉት የእንስሳት መሥዋዕቶች በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የኃጢአት ይቅርታንና ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ሕብረት ለማደስ የተደረገልንን ቤዛነት ትዕምርታዊ በሆነ መንገድ የሚያሳዩ ናቸው።

ይህንን ወሳኝ እውነታ በመዘንጋት በእግዚአብሔር ማመን፣ መልካም ሥራዎችን መሥራትና መልካም ነገርን መመኘት ብቻ በቂ እንደሆነ የሚያስቡ ወገኖች ለእግዚአብሔርና እርሱ ላዘጋጀው መንገድ ክብርን ባለመስጠታቸው ምክንያት ከስኬት ይጎድላሉ። ስለዚህ እባክህን ከላይ የተጠቀሱትን አምስቱን ታሪኮች በጥንቃቄ አጥናቸው።

አዳምና ሔዋን (አደምና ሐዋ)

አዳምና ሔዋን ኃጢአትን ከሠሩ በኋላ ራቁታቸውን ሆኑ፤ እፍረትና ፍርሃትም ሕይወታቸውን ተቆጣጠረ። በገዛ ፈጣሪያቸው ላይ ማመጻቸው ለውርደት ዳረጋቸው። የገዛ ራቁትነታቸውን ለመሸፈን የሞከሩት በቅጠል ነበር። በኃጢአታቸው ምክንያት የመጣባቸውን ይህንን እፍረትና ውርደት ለመሸፈን ያደረጉት ጥረት በእግዚአብሔር ዕይታ በቂ አልነበረም። ከሁሉ አስቀድሞ ከተከለከሉት ዛፍ ቢበሉ ሞትን እንደሚሞቱ ነግሯቸው ነበር። ይህ ሞት መንፈሳዊ ሞት ሲሆን ከገነት በመባረራቸው ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን የግል ሕብረት በማጣት የሚመጣባቸው ነው። አካላዊ ሞት ደግሞ እርሱን ተከትሎ የሚመጣ ነው። አንድ ሰው የሞት ፍርደኛ ከሆነ አክትሞለታል፤ ሟች ነው! ስለዚህ እግዚአብሔር ጣልቃ በመግባት እፍረታቸውን የሚሸፍኑበትን የእንስሳን ቆዳ ሰጣቸው። ይህም አጥፊ ለሆነው የኃጢአት ውጤት የሚቀርበውን መሥዋዕት የሚያመለክት ነው። (ተውራት፣ ዘፍጥረት 3፡7፣ 21)። በቁርአን ውስጥም አላህ ራቁትነታቸውን የሚሸፍኑበት ልብስ እንደሰጣቸው ተነግሯል (ሱራ 7፡26)።

ተውራት፣ ዘቡርና ኢንጂል "ኃጢአት" የሚለውን ቃል በስህተት መጥፎ ሥራን ከመሥራት የዘለለ ትርጉም እንዳለው ይናገራሉ። በሰው ልጆች ሁሉ ልብ ውስጥ ከሚገኝ አመፀኛ አስተሳሰብ የተነሳ መጥፎ ሐሳቦችን በማሰብ ጭምር የሚፈፀም ክፉ ነገር ነው። እግዚአብሔር ፍፁም ቅዱስ በመሆኑ ምክንያት ኃጢአት ከእርሱ ዕይታ አኳያ በጣም ከባድ ነገር ነው። የሰው ልጆች በሙሉ ኃጢአተኞች በመሆናቸው ፍርድ ይገባቸዋል (ሱራ 16፡1)።

እፍረት የኃጢአት ውጤት ነው። በልብ የታሰበ ኃጢአት በሌለበት ቦታ እፍረት የለም። ለዚህ ነው ህፃናት ራቁታቸውን ቢሆኑ የማያፍሩት። በክርስትና የውርስ ኃጢአት ማለት ሰው ኃጢአትን ከመሥራት ዝንባሌ ጋር ይወለዳል ማለት እንጂ ራሱን ከማወቁ በፊት ኃጢአት ሠርቷል ማለት አይደለም። ሁሉም ሰው በፍጥረቱ የቁጣ ልጅ ነው፤ ለዚህም ምክንያቱ ከተጨባጭ ኃጢአት ጋር መወለዱ ሳይሆን ኃጢአትን ከመሥራት ዝንባሌ ጋር በመወለዱ ነው (ኤፌሶን 2፡3)። የሰው ዘር ሁሉ ወኪል የሆነው አዳም ኃጢአትን በመሥራቱ ምክንያት ሁላችንም ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ነን (ሮሜ 5፡12)። ስንወለድ ከተጨባጭ ኃጢአት ጋር አልተወለድንም። ነገር ግን ኃጢአትን ከመሥራት ዝንባሌ ጋር ስለተወለድን ኃጢአተኞች የመሆናችን ጉዳይ አጠያያቂ አይደለም። ስለዚህ ከእግዚአብሔር ፍርድ ማምለጥ አይቻለንም።

ቃኤልና አቤል (ቃቢልና ሀቢል)

ስለ ቃኤልና አቤል መሥዋዕት በቁርአን ውስጥ በዝርዝር አልተነገረም (ሱራ 5፡27)። ተውራትና ኢንጂል እንደሚነግሩን ከምድር ዘር የነበረውን የቃኤልን መሥዋዕት እግዚአብሔር ያልተቀበለ ሲሆን የእንስሳ መሥዋዕት የሆነውን የአቤልን መሥዋዕት ተቀብሏል (ዘፍጥረት 4፡3-7)። ደግሞም አቤል መሥዋዕቱን

በእምነት ስላቀረበ ተቀባይነትን እንዳገኘ ተነግሯል (ዕብራውያን 11፡4)። አቤል ለምንድን ነበር የእንስሳን መሥዋዕት ማቅረብ አስፈላጊ እንደሆነ ያመነው? አዳምና ሔዋን በሠሩት ኃጢአት ምክንያት ከእፍረት እንዲተርፉ የእንስሳን ቆዳ በማልበሱ ምክንያት ለእግዚአብሔር ምስጋና ለማቅረብ ፈልጎ ይሆንን? የሙሴን ታሪክ ስንመለከት ይህ ይበልጥ ግልፅ ይሆናል።

አብረሃም (ኢብራሂም)

አብረሃም ልጁን እንዲሠዋ ከታዘዘ በኋላ በልጁ ፈንታ የሚቀርብን የበግ መሥዋዕት እግዚአብሔር ራሱ አዘጋጀ (ሱራ 37፡107፣ ተውራት ዘፍጥረት 22)፡ ፡ ያ የእንስሳ መሥዋዕት እንደ ቀላል የአምልኮ ተግባር ብቻ የሚቆጠር አይደለም፤ ምክንያቱም ቁርአን ክብደቱን ሲገልፅ "በታላቅ እርድ (መሥዋዕትም) ተቤዠነው" ይላልና። ልጅ ከእንስሳ እጅግ የላቀ ዋጋ አለው። እንስሳው "ታላቅ" የተባለው ሌላ ፍፁም የሆነን መፃዒ መሥዋዕት ትዕምርታዊ በሆነ መንገድ ስለሚያሳይ ይሆን?

ሙሴ (ሙሳ)

ሙሴ ለእስራኤል ሕዝብ ኃጢአት ማስተሰርያ ይሆኑ ዘንድ በእግዚአብሔር የተፈጠሩትን እንስሳት እንዲሠዋ ታዘዘ (ተውራት ዘኁልቁ 19፡1-10፣ ሌሎችም ብዙ ጥቅሶች)።

እንደ ዩሱፍ አሊና መውዱዲ ያሉ ሙስሊም ሐታቾች ሱራ አል-በቀራ 2፡67-74 ላይ የሚገኘው ይህንን አስደናቂ ታሪክ የሚያስታውስ መሆኑን ይናገራሉ። የአይሁድ ካህናትና ቤተ መቅደሱም ሱራ 17፡1-7፣ 5፡44 ላይ ተጠቅሰዋል። ለኃጢአት ሥርየት በቤተ መቅደሱ ውስጥ የሚቀርቡት የእንስሳት መሥዋዕቶች የተውራት ማዕከላዊ ጉዳዮች ናቸው። የአዳምና የሔዋን እፍረት እንደተሸፈነላቸው ሁሉ ያለ ደም መሥዋዕት የሚሸፈን እፍረት የለም። ተውራት ሌዋውያን 17፡11 ላይ እንዲህ ይላል፡-

"የሥጋ ሕይወት በደሙ ውስጥ ነውና፤ ደሙም ከሕይወቱ የተነሣ ያስተሰርያልና በመሠዊያው ላይ ለነፍሳችሁ ማስተስረያ ይሆን ዘንድ እኔ ለእናንተ ሰጠሁት።"

መሲሁ ኢየሱስ

ብዙ መሥዋዕቶች በተደጋጋሚ ቢቀርቡም ለሰው ልጆች የኃጢአት ችግር ግን ዘላቂ መፍትሄ ሊሆኑ አልቻሉም። ችግሩ ደግሞ እንስሳት የሰው ልጆችን ሰብዓዊ ዋጋ የሚመጥኑ አለመሆናቸው ነው። ፍፁምና ኃጢአት አልባ የሆነውን መፃዒ መሥዋዕት የሚያመለክቱ ብቻ ነበሩ። ልክ እንደ ባንክ ቼክ ዓይነት ናቸው። የባንክ ቼክ ለገንዘብ እንደ መያዣ ያገለግላል ነገር ግን አንዴ ገንዘቡ እጃችሁ ከገባ ቼኩ አያስፈልጋችሁም።

የእንስሳት መሥዋዕት የላቀውን መሥዋዕት አመላካች ነው። ያ መሥዋዕት አንዴ ከተፈፀመ የእንስሳት መሥዋዕት አያስፈልጋችሁም። መጥምቁ ዮሐንስ (የሕያ) ኢየሱስን "የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ" ሲል ነበር የጠራው (ኢንጂል ዮሐንስ 1፡29)። ኢየሱስ የዓለምን ኃጢአት፣ እፍረት፣ ፍርሃትና ወቀሳ ለማስወገድ በሰልጆች ምትክ ሆኖ የሞትን ፅዋ ተቀብሏል (ኢንጂል ማርቆስ 10፡45)።

ኢንጂል ሉቃስ 24፡44-47 እንዲህ ይላል፡-

እርሱም፦ ከእናንተ ጋር ሳለሁ በሙሴ ሕግና በነቢያት በመዝሙራትም ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይገባል ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው አላቸው።

በዚያን ጊዜም መጻሕፍትን ያስተውሉ ዘንድ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው፤ እንዲህም አላቸው፦ ክርስቶስ መከራ ይቀበላል በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሣል፥ በስሙም ንስሐና የኃጢአት ስርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል ተብሎ እንዲሁ ተጽፎአል።

እግዚአብሔር ኢየሱስን በሦስተኛው ቀን ከሙታን በማስነሣትና በአርባኛው ቀን ወደ ራሱ በማንሳት ለሥራው መስክሯል (ኢንጂል፣ የሐዋርያት ሥራ 1፡3፣ 1ቆሮንቶስ 15)። ይህ ፍፁማዊ ይቅርታን የማግኛ መንገድ ከገዛ መንገዳቸው ተመልሰው እግዚአብሔር ያዘጋጀላቸውን መንገድ ለመቀበል ፈቃደኛ ለሆኑት ሰዎች ሁሉ የተዘጋጀ መሆኑን ተውራት፣ ዘቡርና ኢንጂል ይናገራሉ። ቁርአንም ሙስሊሞች በነዚህ መጻሕፍት ማመን እንደሚገባቸው ይናገራል (ሱራ 5፡46-48)።

ከእግዚአብሔር ዕይታ አኳያ እኛ በኃጢአታችን ምክንያት የተራቆትንና እፍረት ውስጥ ያለን ነን። ነገር ግን በፈሰሰልን በልጁ ቅዱስ ደም አማካይነት ጽድቅን መጎናጸፍ እንችላለን። ይህ የምሥራች ከአዳም ዘመን ጀምሮ ተገልጧል። በመሲሁ ኢየሱስ በኩል ደግሞ እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ ለሰው ልጆች ሁሉ ዝግጁ ሆኖ ቀርቧል። ከዚህ ተሽሎ ሊሸረው የሚችል ምንም ነገር የለም። ብቸኛው ለሰው ልጆች ሁሉ በቂ፣ አስተማማኝና ፍፁም የሆነ የመዳኛ መንገድ ነው።

---

እንዲያው ይሁን እንኳ ብንል የሚከተሉትን በረከቶች ሊተካ የሚችል ምን የተሻለ መንገድ ይገኛል?

- ፍፁም የሆነ የኃጢአት ይቅርታ
- ከእፍረት ወደ ክብር መመለስ
- ከፍርሃትና የኅሊና ክስ ነፃ መሆን
- የተሟላ ሕይወት
- እንደ እግዚአብሔር ሐሳብና ፈቃድ ለመመላለስ የሚያስችል የመንፈስ ቅዱስ ኃይል

---

ኢየሱስ ነቢያት አስቀድመው የተነበዩለት የዓለም አዳኝ ነው፤ ይህንን የማድረግ ብቃት ያለው እርሱ ብቻ ነው (ኢንጂል ማርቆስ 2፡6፣ ሉቃስ 24፡44-47፣ ዮሐንስ 11፡25-26)። የእርሱ መልእክት የተለየ ነው። በአጭሩ የሚከተለውን ይመስላል፡- እግዚአብሔር ጻድቅ ነው፣ እኛን ይወደናል – ሁላችንም ኃጢአተኞች በመሆናችን ከእርሱ ተለይተን ጠፍተናል – ሃይማኖታት አቅጣጫቸውን ስተዋል፣ መልካም ሥራዎቻችንም እኛን ለማዳን በቂ አይደሉም – ብቃት ያለውና ለችግራችን መፍትሄው ኢየሱስ ብቻ ነው! እርሱ ቅጣታችንን ተቀብሎልናል – ንስሐ ግቡ – እርሱን ተከተሉ! ውዱ ወዳጄ፣ እውነተኛና ፍፁም የሆነውን መሥዋዕት፣ ዘላለማዊና ሕያው የእግዚአብሔር ቃል የሆነውን ኢየሱስን ልትታመነው ትሻለህን?

...

## ፈጣሪ ያዘጋጀው ትክክለኛ የመዳን መንገድ

በመላው ዓለም የሚገኙት ሙስሊሞች በየዓመቱ የአል-አድሃን በኣል ያከብራሉ፡፡ ይህ በኣል በሙስሊሞች የጨረቃ አቆጣጠር መሠረት ዙል ሒጃ በመባል በሚታወቀው ወር 10ኛ ቀን ላይ ይውላል፡፡

አድሃ የሚለው ቃል ዳሂያ ወይንም መሥዋዕት ከሚለው የአረብኛ ሥረወ ቃል የተገኘ ነው፡፡ የአል-አድሃ በኣል የመሥዋት በኣል ወይንም ታላቁ በኣል፣ ዒድ አል ከቢር በመባል ይታወቃል፡፡ በቱርክ ዓለም ውስጥ የአድሃ በኣል ቁርባኒ በመባል ይታወቃል፡፡

በአል-አድሃ በኣል ዕለት ሙስሊሞች ፈጣሪ የአብርሃምን ልጅ የዋጀበትን ክስተት ለማስታወስ በግ ይሠዋሉ፡፡ ይህ ክስተት በቁርአን ውስጥ ሱራ 37፡99-111 ላይ ተዘግቧል፡፡

የአይሁድ ሃይማኖት ተከታዮችም እግዚአብሔር የአብርሃምን ልጅ በበግ የዋጀበትን ይህንን ክስተት ያምናሉ፡፡ አብርሃም ልጁን ሊሠዋ ሲል የእግዚአብሔር ቅዱስ መልአክ አስቆመው፡፡ አብርሃምም ቀንዱ በዕፀ ሳቤቅ የታሰረ በግ ተመለከተ፡፡ በጉን በመውሰድ የሚቃጠል መሥዋዕት አድርጎ አቀረበው፡፡ የዚህ ታሪክ ሙሉ ዘገባ በተውራት ውስጥ ዘፍጥረት 22፡1-19 ላይ ይገኛል፡፡

የአይሁድ ሃይማኖት ይህንን ክስተት እንደ በኣል ባያስብም በነቢዩ ሙሴ በተሰጣቸው የፋሲካ በኣል ውስጥ ተመሳሳይ ሐሳብ ይገኛል፡፡ አይሁድ እግዚአብሔር የበኩር ልጆቻቸውን እንዳይሞቱ ከግብፃውያን የለየበትን በኣል ያከብራሉ፡፡ የሞት መልአክ በበራቸው መቃን ላይ የበጉን ደም የቀቡትን የበኩር ልጆቻቸውን ሳይጎዳ ያልፋቸው ነበር፡፡ ፋሲካ በተውራት ውስጥ ዘጸአት 12፡1-14 ላይ ተመዝግቧል፡፡

የክርስቲያን አድሃ ወዴት አለ?

ክርስቲያኖች በአይሁድ ፋሲካም ሆነ በአድሃ (የአብርሃም ልጅ በበግ የተዋጀበትን ክስተት)የሚያምኑ ቢሆኑም እንደ በኣል ሲያከብሯቸው የማይታየው ለምንድነው? የክርስቲያን ፋሲካና አድሃ አለን? ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት አዲስ ኪዳንን በማጥናት የእግዚአብሔርን ባሕርይና ለሰው ልጆች ያዘጋጀውን ዕቅድ መመልከት ያስፈልገናል፡፡

የኢንጂል አስተምሕሮ

1. እግዚአብሔር ፍቅር ነው

እግዚአብሔር አፅናፈ ዓለምን የፈጠረ ሲሆን ከፍጥረቱ ጋር ሕብረት ማድረግ ይፈልጋል፡፡ እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር ሕብረት በማድረግ ይደሰታል፡፡ የፍጥረቱ ቁንጮዎች ሲሆኑ አእምሮና ፈቃድ የተሰጣቸው ብቸኛ ፍጥረታት ናቸውና፡፡

ኢንጂል እንዲህ ይላል፡-

“እኛም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር አውቀናል አምነንማል፡፡ እግዚአብሔር ፍቅር ነው፥ በፍቅርም የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል እግዚአብሔርም በእርሱ ይኖራል፡፡” (1ዮሐንስ 4፡16)

“በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድ ያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና፡፡”(ዮሐንስ 3፡16)

እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ጋር ሕብረት ማድረግ የሚፈልግ ከሆነ ዓለማችን

ከእግዚአብሔር የራቀቸው ለምን ይሆን? ሰዎች ከእግዚአብሔር የተለዩ እንዲሆኑ ስለምን ይሰማቸዋል? የእግዚአብሔርን ፍቅር እንዳናጣጥም ትልቅ ባሕር የከፈለን ይመስላል።

2. እግዚአብሔር ቅዱስ ነው

እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ሲሆን ሰዎች ግን ኃጢአተኞች ናቸው። በሁሉም ቦታ የሰዎችን ኃጢአተኝነት እናያለን። ተግባሮቻቸው የኃጢአት በሽታ ምልክቶች ናቸው። ኃጢአት በእግዚአብሔር ላይ ማመፅ ነው።

ሁሉም የሰው ልጆች ኃጢአትን ሠርተዋል። ኃጢአት የእግዚአብሔርን መንገድ ከመምረጥ ይልቅ የገዛ ራሳችንን መንገድ መምረጥ ነው። ሁሉም የሰው ልጆች የእግዚአብሔርን ሕግ ከመከተል ይልቅ በገዛ መንገዳቸው ነጉደዋል።ኢንጂል ኃጢአት ብሎ የሚጠራው ይህንን አለመታዘዝነው።

ሁላችንም በሃያሉ ፈጣሪያችን ላይ ኃጢአትን የሠራን ቢሆንም ወንጀላችንን ማስወገድ አይቻንም። ጻድቅ የሆነው እግዚአብሔር ቅዱስ በመሆኑ ኃጢአተኛ ከሆኑ ሰዎች ጋር ሕብረት የለውም።

ኢንጂል ሁሉም ሰዎች በቅዱሱ እግዚአብሔር ላይ ኃጢአት መሥራታቸውን ይናገራል፦

“ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ፤ አስተዋይም የለም፤ እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም፤ ሁሉ ተሳስተዋል።” (ሮሜ 3፡10-12)

“ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል” (ሮሜ 3፡ 23)

አፍቃሪና ቅዱስ ከሆነው ፈጣሪያችን የለየን ኃጢአት መሆኑን ኢንጂል ይናገራል። የእግዚአብሔር ቅድስና ኃጢአትን ይቃወማል። የእግዚአብሔር ቅዱስ የሆነ ባሕርይ ኃጢአትን መቀበል አይችልም። ስለዚህ ሰውና እግዚአብሔር ኃጢአት በተባለ ትልቅ ባሕር ተለያይተዋል።

ይህ ከእግዚአብሔር መለየት መንፈሳዊ ሞትን ያስከትላል።

ኢንጂል እንዲህ ይላል፦

“የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው።” (ሮሜ 6:23)

የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው ነገር ግን ሌላኛውን ሃጢአተኛ ሞቶ ሊዋጅ የሚችል ሃጢአተኛ የለም። ይህ ደግሞ በቅዱሱ እግዚአብሔርና በሰዎች መካከል ትልቅ ባሕር ሆኖዋል።

አምፖል የኤሌክትሪክ ኃይል እንደሚያስፈልገው ሁሉ ሰዎችም እግዚአብሔር ያስፈልጋቸዋል። አምፖል ያለ ኤሌክትሪክ ኃይል የሞተ፣ ሕይወት አልባና ዓላማ የለሽ ነው። ኃጢአት እኛን ከእግዚአብሔር በመለየት በመንፈስ ሙታን፣ ሕይወት አልባና ዓላማ የለሽ እንድንሆን አድርጎናል።

3. እግዚአብሔር ፍትሃዊ ነው

የእግዚአብሔርፍትሃዊባሕርይኃጢአትንእንዲቀጣናእንዲያጠፋያስገድደዋል። በሃያሉ ፈጣሪያችን ላይ ኃጢአትን ስለሠራን ቅጣቱ ሞት ነው። አንድ ኃጢአተኛ የኃጢአት ዕዳው እስኪከፈል ድረስ እግዚአብሔር ይቅር ሊለው አይችልም። ፆምና ድኾችን መርዳትን የመሳሰሉት መልካም ሥራዎች የእግዚአብሔርን ቸሮታ በማስገኘት ዕዳችንን መክፈል አይችሉም። በጣም መልካም የምንለው ተግባር እንኳ የእግዚአብሔርን ፍፁማዊ ቅድስናና ፍትህ ሊስተካከል አይችልም።

ስለዚህ ከኛ መካከል ምርጥ የምንለው ሰው እንኳ ፍፁም የሆነውን ፈጣሪያችንን ለማስደሰት የማይበቃ በመሆኑ ኃጢአተኛ ነውና ቅጣት ይገባዋል፡፡
ወንጀለኛ ወንጀለኛን ሊዋጅ አይችልም፡፡ በቀላል አባባል፤ ከሰው ልጆች መካከል ኃጢአት የሌለበትና ከእግዚአብሔ ጸጋ ያልጎደለ ማንም የለም፡፡ የእግዚአብሔር ፍትሃዊ ባሕርይ ይህ ታላቅ ዕዳ ሳይከፈል ይቅር እንዲባል አይፈቅድም፡፡ የገዛ መንገዳችንን በመምረጥ የእግዚአብሔርን ተዕዛዛት ስለተላለፍን ቅጣታችንን መክፈል ይኖርብናል፡፡ ያ ቅጣት ደግሞ ከፈጣሪያችን መለየት ነው፡፡

4. እግዚአብሔር መሓሪ ነው

የእግዚአብሔር ምሕረት ለዚህ ችግር ምላሽ ይሰጠናል፡፡ እግዚአብሔር ፍጥረቱ ከሆንነው ከእኛ ጋር ሕብረት ማድረግ ቢፈልግም የኃጢአት ባሕር ግን ለይቶናል፡፡ ባሕሩን ተሻግሮ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ የሚችለው ጻድቅ የሆነ ሰው ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን ሁሉም ሰው ኃጢአት መሥራቱንና አለመብቃቱን ቀደም ሲል አረጋግጠናል!
ሁሉም ሰው፤ ከኢየሱስ በስተቀር፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ በሆነው እግዚአብሔርና ኃጢአተኛ በሆኑት የሰው ልጆች መካከል የሚገኝ ድልድይ መሆኑን ኢንጂል ያስተምራል፡፡

ለምን ኢየሱስ ብቻ? ለምን ሌላ ሰው አልሆነም?

ተዓምራዊ ልደት

ኢንጂል እንደሚያስተምረው ኢየሱሰ ሰው የሆነ አባት የሌለውና በመንፈስ ቅዱስ ሃይል የተጸነሰ ነው፡፡ ከድንግል የተወለደ ብቸኛው ሰው ነው፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በሰው ፈቃድ ሳይሆን በእግዚአብሔር ፈቃድ የተከናወነ ነበር፡፡
ኢየሱስ ክርስቶስ በተዓምራዊ ልደቱ ለየት ያለ ነበር፡፡ ከድንግል የተወለደ መሪ ወይንም ነቢይ የለም፡፡ ሁሉም ነቢያት ሰዎች ብቻ መሆናቸውን የተናገሩ ሲሆን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ ቃል፣ ከሊመት አላህ ነው፡፡ ይህንን ተዓምር የሠራው የእግዚአብሔር ሃይል ነው፡፡
“መልአኩም እንዲህ አላት፦ ማርያም ሆይ፣ በእግዚአብሔር ፊት ጸጋ አግኝተሻልና አትፍሪ፡፡ እነሆም፣ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፣ ስሙንም ኢየሱስ ትዩዋለሽ፡፡ እርሱ ታላቅ ይሆናል የልዑል ልጅም ይባላል፣ ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፤ በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘለላም ይነግሣል፣ ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም፡፡ ማርያምም መልአኩን፦ ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል? አለቻው፡፡ መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት፦ መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፣ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል፡፡ እነሆም ዘመድሽ ኤልሳቤጥ፣ እርስዋ ደግሞ በእርጅናዋ ወንድ ልጅ ፀንሳለች፣ ለእርስዋም መካን ትባል ለነበረቻው ይህ ስድስተኛ ወር ነው፤ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና፡፡ ማርያምም፦ እነሆኝ የጌታ ባሪያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ አለች፡፡ መልአኩም ከእርስዋ ሄደ፡፡” (ሉቃስ 1:30-37)

ተዓምራዊ የሆነ ሕይወት

ኢየሱስ ክርስቶስ የቅድስናና የቅንነትን ሕይወት ኖረ፡፡ በሕይወት ዘመኑ በሙሉ ለእግዚአብሔር ሕግ ታዛዥ ነበር፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ከማንም በተለየ ሁኔታ ያስተማረ ሲሆን በሰዎች ላይ የነበሩትን ድካሞችና ህመሞች ሁሉ ፈወሰ፡፡ ከልደቱ

አንስቶ ኃጢአት የሌለበትና በምድር ላይ ከኖሩት መምህራን ሁሉ የላቀው ነው። "ኢየሱስም በምኩራቦቻቸው እያስተማረ የመንግሥትንም ወንጌል እየሰበከ በሕዝብም ያለውን ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ በገሊላ ሁሉ ይዞር ነበር። ዝናውም ወደ ሶርያ ሁሉ ወጣ፤ በልዩ ልዩ ደዌና ሥቃይም ተይዘው የታመሙትን ሁሉ አጋንንትም ያደሩባቸውን በጨረቃም የሚነሣባቸውን ሽባዎችንም ወደ እርሱ አመጡ፥ ፈወሳቸውም። ከገሊላም ከአሥሩ ከተማም ከኢየሩሳሌምም ከይሁዳም ከዮርዳኖስም ማዶ ብዙ ሕዝብ ተከተሉት።" (ማቴዎስ 4:23-25)

ተዓምራዊ አሟሟት

ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር የመጣው ጥሩ አስተማሪ ወይንም ፈዋሽ ብቻ ለመሆን ሳይሆን የእግዚአብሔር መሥዋዕት ለመሆን ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ ከልደቱ አንስቶ ጻድቅና ኃጢአት የሌለበት በመሆኑ ሞቱ ብቻ የኃጢአትን ቅጣት ሊከፍል ይችላል። የሰው ልጆችን ከውድቀት ሊያድን ነው የመጣው። ሁሉም በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን መሥራታቸውንና ደህንነት እንደሚያስፈልጋቸው ኢንጂል በግልፅ ይናገራል። ደህንነት ማለት እኛ መክፈል የማንችለውን ዕዳ ሌላ ሰው ስለከፈለልን በእግዚአብሔር ይቅርታን ማግኘት ማለት ነው።

ብቸኛ ጻድቅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ እኛ መክፈል የማንችለውን ዕዳ ከፈለልን። የሰው ልጆች በኃጢአት ሙታን ነበሩ። ኃጢአት እኛንና እግዚአብሔርን የለየ ባሕር ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ የሆነ መሥዋዕት በመሆን ለሰው ዘር በሙሉ ሞቷል። አብርሃም በልጁ ፋንታ በግ እንደሰዋው ሁሉ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ሞትም የሰው ልጆችን የኃጢአት ዕዳ ከፍሏል።

የአብርሃም ልጅ ነፃ ይሆን ዘንድ በጉ ሞተ። ልክ እንደዚሁ እኛ ነፃ እንሆን ዘንድ ኢየሱስ ሞተ። እግዚአብሔር የአብርሃምን ልጅ በበግ እንደዋጀው ሁሉ ዓለምንም በኢየሱስ ክርስቶስ ዋጅቷል።

ሙስሊሞች በዒድ አል-አድሃ ዕለት እንዲሁም እስራኤላውያን ከግብጽ መውጣታቸውን አስመልክቶ በግ እንደሚሰውት ሁሉ፣ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን ስለ እኛ ፍጹም መሥዋዕት አደረገው።

ኢየሱስ እውነተኛው አድሃ ሆነ። የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ እርሱ ነው። መጥምቁ ዮሐንስ (ነቢዩ ያህያ) ኢየሱስን ባየ ጊዜ እንዲህ ሲል ትንቢት ተናገረ፦

"እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ።" (ዮሐንስ 1:29)

እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከእርሱ በለየን ባሕር ላይ ድልድይን ሠራ። "ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል። ነገር ግን የሆነው ሁሉ፥ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን፥ ከእግዚአብሔር ነው።" (2ቆሮንቶስ 5:18)

የኃጢአት ዕዳ ስለተከፈለ የእግዚአብሔር ፍትህ ረካ። የሰው ልጆች ቤዛን ስላገኙ የእግዚአብሔር ምህረት ተፈፀመ።

ተዓምራዊ ትንሣኤ

ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት ይኖረን ዘንድ ኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢአት ዕዳችንን ከፈለ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ጻድቅ በመሆኑ ሞት የሚገባው አልነበረም። ኢየሱስ ክርስቶስ

ስለ እኛ ጼህንነት መሥዋዕት ይሆን ዘንድ ሥጋ በመሆን የመጣ የእግዚአብሔር ቃል ነው።
አስቀድሞ በተተነበየው መሠረት ክርስቶስ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተነስቷል። የክርስቶስ ትንሣኤ መስዋዕትነቱ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ማግኘቱን አረጋገጠ።
እኔ ደግሞ የተቀበልሁትን ከሁሉ በፊት አሳልፌ ሰጠኋችሁ እንዲህ ብዬ፦ መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ፤ ተቀበረም፤ መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሣ፤ ለኬፋም ታየ በኋላም ለአሥራ ሁለቱ፤ ከዚያም በኋላ ከአምስት መቶ ለሚበዙ ወንድሞች በአንድ ጊዜ ታየ፤ ከእነርሱም የሚበዙቱ እስከ አሁን አሉ አንዳንዶች ግን አንቀላፍተዋል፤ ከዚያም በኋላ ለያዕቆብ ኋላም ለሐዋርያት ሁሉ ታየ…” (1ቆሮንቶስ 15:3-6)
በመላው ዓለም የሚገኙት ክርስቲያኖች አድሃንና ፋሲካን የክርስቶስን ስቅለትና ትንሣኤ አስመልክተው በአንድ ላይ እንደ ታላቅ በኣል ያከብሩታል። ይህም በአማርኛ ፋሲካ፣ በእንግሊዘኛ ኢስተር፣ በአረብኛ ደግሞ ዒድ አል-ቂያማ በመባል ይታወቃል። ይህ አድሃና ፋሲካ የተገናኙበትና የተፈፀሙበት ነው!
እነዚህ ሁለቱ ክስተቶች ትክክለኛውን ቤዛነት መረዳት እንችል ዘንድ እግዚአብሔር የተጠቀማቸው ተምሳሌቶች ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው የበጎችና የሌሎች እንስሳት መሥዋዕት ሃጢአታችንን ማንፃት አይችልም። ጽድቃችንም ፍፁም ከሆነው የእግዚአብሔር ጽድቅ ጋር ሲስተያይ እንደ ቆሻሻ ጨርቅ ነው። በኛ ላይ የነበረውን ታላቅ የእግዚአብሔር ዕዳ መክፈል የሚችል ማንም የለም። ደስ የሚያሰኘው የምሥራች ግን እግዚአብሔር የዓለምን ኃጢአት ያስወግድ ዘንድ ኢየሱስ ክርስቶስን መላኩ ነው።
ኢየሱስ ክርስቶስ የኛ እውነተኛው አድሃ ነው!
አንድ ወዳጄ ለሥራ ወደ ሩቅ ሀገር በሄደበት ሰዓት ቤቱን እንድጠብቅለት በአደራ ሰጥቶኝ እኔ ግን ድንገት የቤቱን ቁሳቁስ ሰበርኩ እንበል። ነገር ግን እርሱ ከመመለሱ በፊት መኪናውን አጠብኩለት። ይህ የተሰበረውን ዕቃ ለመተካት የሚያስችለውን ወጪ ይሸፍናልን? አይሸፍንም!
ጓደኛዬ መኪናውን ስላጠብኩለት የሰበርኩትን ንብረት ይቅር እንዲለኝ ብጠይቀው ትክክል ይሆናልን? አይሆንም!
ጓደኛዬ ይቅር ቢለኝ እንኳ አዲስ ዕቃዎቸን ለመግዛት ገንዘቡን መክፈል ያስፈልገዋል። ልክ እንደዚሁ የኛ መልካም ሥራ ከእግዚአብሔር ጽድቅ ጋር ሲስተያይ በቂ አይደለም። የኛ መልካም ሥራዎች ኃጢአታችንን ማስወገድ አይችሉም ምክንያቱም መልካም መሥራትና ሁሉንም የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት መጠበቅ ይኖርብናልና።
ኃጢአታችን የእግዚአብሔርን ጽድቅ የሚፃረር ነው፤ ብቃት ያለው የኢየሱስ ቤዛዊ መሥዋዕት ብቻ ነው። የኃጢአታችንን ዕዳ በመክፈል ልዩነቱን ማስወገድ የሚችለው የክርስቲያን አድሃ ብቻ ነው።
የክርስቲያን አድሃ ለሁሉም ሰው የተዘጋጀ ነው። ምክንያቱም ክርስቶስ ሁሉንም የሰው ዘር ሊያድን መጥቷልና። በክርስቶስ በኩል ተሻግረን ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት ማድረግ እንዲሁም ፍቅሩንና ማዳኑን ማጣጣም እንችላለን።

5. እግዚአብሔር ይቅር ባይ ነው

እግዚአብሔር ለኃጢአት የሚሆን አድሃ ማዘጋጀቱን ማወቅ ብቻ በቂ አይደለም። እያንዳንዳችን ይህንን አድሃ በግልና በትህትና ልንቀበል ያስፈልገናል።
የእግዚአብሔርን ይቅርታ በሕይወታችን ውስጥ የምናገኘው በሚከተለው መንገድ ነው። የእግዚአብሔርን ፍቅርና ይቅርታ በሕይወታችን ውስጥ ለመለማመድ ከኃጢአታችን ንስሐ ገብተን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ጌታና አዳኝ በሕይወታችን ውስጥ ልንቀበል ይገባናል።
ንስሐ ከኃጢአተኛ መንገዳችን በመመለስ በክርስቶስ የመስቀል ሥራ (የክርስቲያን አድሃ) በኩል የተገኘውን የእግዚአብሔርን የይቅርታ ስጦታ መቀበል ነው።
ኢንጂል እንዲህ ይላል፦
“በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለንና ከአመፃም ሁሉ ሊያናፃን የታመነና ጻድቅ ነው።” (1ዮሐንስ 1:9)

- እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ብንናዘዝ ይቅር የሚለን ክርስቶስ ዕዳችንን ስለከፈለ ነው።
- ፍጹም የሆነው የእግዚአብሔር ፍትሃዊ ባሕርይ ቅጣትን ይጠይቃል።
- የእግዚአብሔር ምህረት በክርስቲያን አድሃ ውስጥ ታይቷል።
- የእግዚአብሔር ፍትህ ስለረካ ይቅርታ ተሰጥቷል።
- ክርስቶስ ዕዳችንን ስለከፈለ ንስሐ የሚገቡ ኃጢአተኞች ይቅርታን ያገኛሉ።

ኃጢአት በሁሉም የሰው ልጆች ልብ ውስጥ ይገኛል። የሰው ልጆች “የልብ ቅያሬ” ያስፈልጋቸዋል። ይህም ደግሞ ኃጢአተኛን ወደ ጻድቅ ሰው ይለውጣል። ኢንጂል እንዲህ ይላል፦
“የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው።” (ሮሜ 6:23)
የክርስቲያን አድሃ ከመንፈሳዊ ሞት በማውጣት የዘላለምን ሕይወት ሰጥቶናል። የእግዚአብሔር የዘላለም ሕይወት ስጦታ የክርስቶስን መሥዋዕትነት በመቀበል ይገኛል። የክርስቶስን መሥዋዕትነት የምንቀበለው በእምነት ነው።
የክርስቶስ መሥዋዕትነት ነፃ ቢሆንም በገንዘብ የሚተመን ግን አይደለም። በእምነት ልንቀበለው ይገባል። ከዚህ ያለፈ እርሱን ለማግኘት በራሳችን የምንሠራው ምንም ነገር የለም።
“ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም።” (ኤፌሶን 2:8-9)
የእግዚአብሔርን ስጦታ ማጣጣም የምንችለው ስንቀበለው ነው። ክርስቶስንና የመሥዋዕትነት ሥራውን መቀበል የምንችለው ልባችንን ሙሉ በሙሉ በመስጠት ነው።
“ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤ እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም።” (ዮሐንስ 1:12-13)
ክርስቶስ ወደ ሕይወታችን በመግባት ከኃጢአት ሊያንጻንና ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን የተበላሸ ሕብረት ሊያስተካክል ይፈልጋል። ክርስቶስ ጌታችንና አዳኛችን ሊሆን ይፈልጋል። ኢየሱስ ኢንጂል ውስጥ እንዲህ አለ፦
“እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ። ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ

ወደ እርሱ እገባለሁ።” (ራዕይ 3:20)

ጸሎት ለእግዚአብሔር መናገር ማለት ነው። በየትኛውም ቦታ ሆነን በየትኛውም ሰዓት ለእግዚአብሔር መናገር እንችላለን። የክርስቶስን መሥዋዕትነት (የክርስቲያን አድሃ) ለመቀበል ወደ እግዚአብሔር እንጸልያለን፤ ደህንነት መቀበላችንንም በእምነት እናውቃለን።

እንዲህ ብላችሁ ወደ እግዚአብሔር መጸለይ ትችላላችሁ፦

ጌታ ሆይ ለኔ ስላለህ ፍቅር አመሰግንሃለሁ። ከክርስቶስ መሥዋዕትነት የተነሳ ይቅርታህን እጠይቃለሁ። የሕይወቴን በር በመክፈት ክርስቶስን እንደ ጌታዬና አዳኜ እቀበላለሁ። አዲስ ሰው አድርገኝ። የዘላለምን ሕይወት ስለሰጠኸኝ አመሰግንሃለሁ። በኢየሱስ ስም፤ አሜን።

ይህንን ጸሎት በመጸለይ ክርስቶስ ወደ ሕይወታችሁ እንዲገባ፣ ኃጢአታችሁን ይቅር እንዲል እንዲሁም ከእግዚአብሔር ጋር ያላችሁን ሕብረት እንዲያድስ ጠይቁት። በእውነት ከልባችሁ ሆናችሁ ክርስቶስ ወደ ሕይወታችሁ እንዲመጣ ከጠየቃችሁት ወደ ሕይወታችሁ እንደመጣ እርግጠኞች ሁኑ።

የእግዚአብሔር ተስፋዎች እውነት እንደሆኑ ማወቅ ወሳኝ ነው። ራዕይ 3:20 ላይ ክርስቶስ እንዲህ አለ፦

“እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ። ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ ወደ እርሱ እገባለሁ።”

የሕይወታችሁን ደጅ በመክፈት ክርስቶስ እንደ ጌታና አዳኝ እንዲገባ ብትጠይቁት አያታልላችሁም። ክርስቶስ ታማኝ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ለቃሉ ታማኝ መሆኑን ኢንጂል ይናገራል፦

“በእኔ ብትኖሩ፣ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ የምትወዱትን ሁሉ ጠይቁ ይሆንላችሁማል።” (ዮሐንስ 15:7)

“አልተውህም አልጥልህም።” (ዕብራውያን 13:5)

“ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትናም ዛሬም እስከ ለዘላለምም ያው ነው።” (ዕብራውያን 13:8)

“ያመንሁትን አውቃለሁና፤ የሰጠሁትንም አደራ እስከዚያ ቀን ድረስ ሊጠብቅ እንዲችል ተረድቼአለሁ።” (2ጢሞቴዎስ 1:12)

“በእናንተ መልካምን ሥራ የጀመረው እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ድረስ እንዲፈፅመው ይህን ተረድቼአለሁና።” (ፊልጵስዩስ 1:6)

## ሴቶች በቁርኣን በሐዲስና በመጽሐፍ ቅዱስ

### 1. ሴቶች በቁርኣን

ቁርኣን ሴቶችን በተመለከተ ግልፅና ማብራርያ የማይሻ አስተምህሮ አለው። አጠቃላይ ሐሳቡም ሴቶች ከወንዶች እንደሚያንሱና ወንዶች የሴቶች የበላይ እንደሆኑ ነው። ከዚህም አልፎ የሴቶችን ፍጥረት ከሰው ደረጃ ዝቅ በማድረግ ለጥቃት ያጋልጣቸዋል። ጥቂቶቹን እንደሚከተለው እናያለን፡-

ባሎች በሚስቶቻቸው ላይ ብልጫ አላቸው፡- 2፡228 “... ለነርሱም (ሴቶች) የዚያ በነሱ ላይ ያለባቸው (ግዴታ) ብጤ በመልካም አኗኗር (በባሎቻቸው ላይ መብት) አላቸው። ለወንዶችም (ጣጣቸውን ስለሚሸከሙ) በነሱ ላይ ብልጫ አላቸው።

አላህ አሸናፊ ጥበበኛ ነው፡፡”
በዚህ ስፍራ ላይ “ጣጣቸውን ስለሚሸከሙ” የሚለው ንግግር በአረቢኛው ቁርኣን ውስጥ የሌለ ሲሆን በተርጓሚዎቹ የተጨመረ ማብራሪያ ነው፡፡ ይህንንም ሀሳብ በመጨመር ይህ ጥቅስ ሊያስከትላቸው የሚችላቸውን ችግሮች ለመቀነስ ሞክረዋል፡፡ ይህ እንዲያውም ችግሩን ያከረዋል እንጂ በፍፁም አያለዝበውም፡ ፡ “ጣጣ” የተባለው ባሎች ለሚስቶቻቸው የሚያወጡት ወጪ ከሆነ በእጅጉ ያስገርማል፡፡ እውነተኛው አምላክ በእንዲህ ዓይነት እንቶ ፈንቶ ምክንያቶች ላይ ተመስርቶ ደረጃ የሚመድብ አምላክ አይደለም፡፡ በብዙ ማሕበረሰቦች ውስጥ እንዲያውም ከወንዶች ይልቅ ብዙ “ጣጣ” የሚሸከሙት ሴቶች በመሆናቸው በዚህ ደረጃ እንመድብ ከተባለ የበላይነቱ የሚገባው ለሴቶች እንጂ ለወንዶች አይደለም፡፡1
ሴቶች ለባሎቻቸው እርሻ ስለሆኑ በፈለጉበት ሁኔታ “ሊደርሷቸው” ይችላሉ፡- 2፡ 223 “ሴቶቻችሁ ለናንተ እርሻ ናቸው፡፡ እርሻችሁን በፈለጋችሁት ሁኔታ ድረሱ” ጋብቻ ክቡር መኝታውም ቅዱስ መሆኑ እሙንና ቅቡል ነው፡፡ ታድያ ይህ ሊሆን የሚችለው የሴቷም ፍላጐትና ስሜት ጭምር ከተጠበቀ ብቻ ነው፡፡ ባል ሚስቱን እንደ ግል እርሻው በመቁጠር በፈለገው ሁኔታ ልድረስ ቢል በሴቷ ስነ ልቦና ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል፡፡ ሴቶችን ከእርሻ ጋር ማመሳሰልና “በፈለጋችሁት ሁኔታ ድረሱ” የሚለው አባባል ለሰው ህሊና ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡
ባሎች ሚስቶቻቸውን በመምታት መቅጣት ይችላሉ፡- 4፡34 “እነዚያም ማመጣቸውን የምትፈሩትን ገስፁዋቸው በመኝታዎቻችም ተለዩዋቸው (ሳካ ሳታደርሱ) ምቱዋቸውም፡፡ ቢታዘዟችሁም (ለመጨቆን) በነርሱ ላይ መንገድን አትፈልጉ አላህ የበላይ ታላቅ ነውና፡፡”
አሁንም እንደተለመደው የቁርኣን ተርጓሚዎች ቃላትን በቅንፍ ውስጥ በመጨማመር የመጽሐፋቸውን ገመና ለመሸፈን ሞክረዋል፡፡ “ሳካ ሳታደርሱ (አካላዊ ጉዳት ሳታደርሱ)” የሚለውን ሀሳብ መጨመራቸው “ምቱዋቸው” የሚለው የቁርኣን ትዕዛዝ ከህሊናቸው ጋር ግጭትን እንደፈጠረ ያሳያል፡፡ በትዕግስትና በፍቅር መምከር እየተቻለ መደብደብ ለምን ያስፈልጋል? ምድራዊ መንግሥታት እንኳ ሚስቶችን መምታት ኀልጻፋ ተግባር መሆኑን በመገንዘብ የዜጎቻቸውን መብት የሚያስከብሩ ህግጋትን አውጥተዋል፡፡ ሴትን ልጅ መምታት ኢ-ሞራላዊ የሆነ ኋላ ቀር ተግባር ነው፡፡ እንዲህ አይነቱ ትዕዛዝ ሊመነጭ የሚችለው ለሴት ልጅ ዝቅተኛ ግምት ካለው አዕምሮ እንጂ ቅዱስ ከሆነው አምላክ ዘንድ ከቶ ሊሆን አይችልም፡፡ ማንም ሰብኣዊነት የሚሰማው ሰው እንዲህ አይነቱን ኀጂ ልማድ መቃወምና መታገል ይኖርበታል፡፡
ከባሏ ለሦስተኛ ጊዜ የተፋታች ሴት የመጀመሪያ ባሏን መልሳ ማግባት የምትችለው ሌላ ወንድ አግብታ ከፈታች ብቻ ነው፡- 2፡230 “(ሦስተኛ) ቢፈታትም ከዚህ በኋላ ሌላን ባል እስከምታገባ ድረስ ለርሱ አትፈቀድለትም፡፡ (ሁለተኛው ባል) ቢፈታተም የአላህን ህግጋት መጠበቃቸውን ቢያውቁ በመማለሳቸው በሁለቱም ላይ ኃጢአት የለባቸወም፡፡”
ለሦስተኛ ጊዜ መፋታት ጥሩ ባይሆንም ነገር ግን መልሶ መታረቅ ደግሞ ሊበረታታ የሚገባው ተግባር ነው፡፡ ከፍቺ በኋላ ከቀድሞ ባሏ ጋር የመታረቅ እድል ያገኘች ሴት ይህንን እርቅ ከመፈፀሟ በፊት ሌላ ወንድ አግብታ መፍታት ለምን ያስፈልጋታል?

ከቀደሞ ባሏ ጋር መታረቅ እየፈለገች ነገር ግን እርሷ ሳትፈልግ “ሌላ ባል አግብተሽ ካልፈታሽ በስተቀር ከቀድሞ ባልሽ ጋር መታረቅ አትችይም” ማለትስ ምን የሚሉት መፍትሄ ነው?
የአንድ ወንድ ምስክርነት ከሁለት ሴቶች ምስክርነት ጋር እኩል ነው፡- 2፡282 “ከወንዶቻችሁም ሁለትን ምስክሮች አስመስክሩ፡፡ ሁለትም ወንዶች ባይሆኑ ከምስክሮች ሲሆኑ ከምትወዷቸው የሆኑን አንድ ወንድና አንድኛዋ ስትረሳ አንደኛዋን ታስታስውሳት ዘንድ ሁለት ሴቶች (ይመስክሩ)፡፡”
የዚህ ጥቅስ አውደ ንባብ የሚናገረው ስለ ብድር እዳ ውል ነው፡፡ አንድ ሰው ለሌላ ሰው ገንዘብ ማበደሩን አይቶ ለመመስከር የአንዷት ሴት ምስክርነት ከአንድ ወንድ ምስክርነት እኩል ተቀባይነት የማይኖረው ምን ስለሆነ ነው? ይህ ጥቅስ የሴቶች የማስታወስ ችሎታ ከወንዶች ያነሰ መሆኑን ለመግለፅ ያለመ መሆኑን ብዙ ሐዲሳት ያሳያሉ፡፡
በገነት ውስጥ ለሙስሊም ወንዶች የስሜት ማርኪያ እንዲሆኑ የተፈጠሩ ሴት ፍጥረታት ይገኛሉ፡- 78፡30-33 “ለጥንቁቆቹ መዳኛ ስፍራ አልላቸው፡ ፡ አትክልቶችና ወይኖችም፡፡ እኩያዎች የኾኑ ጡተ ጉቻማዎችም፡፡ የተሞሉ ብርጭቆዎችም፡፡”
44፡51-54 “ጥንቁቆቹ በእርግጥ በጸጥተኛ መኖሪያ ውስጥ ናቸው፡፡ በአትክልቶችና በምንጮች ውስጥ ናቸው፡፡ ፊት ለፊት የተቅጣጩ ኾነው ከስስ ሐርና ከወፍራም ሐር ይለብሳሉ፡፡ (ነገሩ) እንደዚሁ ነው፤ ዓይናማዎች የኾኑን ነጫጭ ሴቶችም እናጠናዳቸዋለን፡፡”
56፡34-36 “ከፍ በተደረጉ ምንጣፎችም (ሴቶችም መካከል)፡፡ እኛ አዲስ ፍጥረት አድርገን (ለእነርሱ) ፈጠርናቸው፡፡ ለባሎቻቸው ተሽሞርሟሪዎች እኩያዎች (አደረግናቸው)፡፡ ለቀኝ ጓዶች (አዘጋጀናቸው)፡፡”
አንድ ሙስሊም ወንድ በገነት ውስጥ የ100 ወንዶች ጉልበት እንደሚያገኝ ቲርሚዚ መዘገቡን ሚሽካት አል መሳቢህ የተሰኘው የሐዲሳት ስብስብ መጽሐፍ ይጠቅሳል፡፡[1]
ሴት የነካ ወንድ ልክ እንደሰከረ ሰው፣ እንደታመመ ሰው እና ከዓይነ ምድር እንደመጣ ሰው ሁሉ ታጥቦ ከርክሰቱ ካልነፃ መጸለይ አይችልም፡- 4፡43 “እናንተ ያመናችሁ ሆይ! እናንተ የሰከራችሁ ኾናችሁ የምትሉትን ነገር እስከምታውቁ የረከሳችሁም ስትኾኑ መንገድን አላፊዎች ካልኾናችሁ በስተቀር (አካላታችሁን) እስከምትታጠቡ ድረስ ስግደትን አትቅረቡ፡፡ በሽተኞች ወይም በጉዞ ላይ ብትኾኑም፤ ወይንም ከእናንተ አንዱ ከዓይነምድር ቢመጣ፤ ወይንም ሴቶችን ብትነካኩና ውሃን ባታገኙ፣ ንጹሕ የኾነን የምድር ገጽ አስቡ፡፡ ፊቶቻችሁንና እጆቻችሁንም (በርሱ) አብሱ፡፡ አላህ ይቅር ባይ መሓሪ ነውና፡፡”
ዕድሜያቸው ለአቅመ ሔዋን ያልደረሱትን ሴቶች ማግባት ይቻላል፡- 65፡4 “እኒያም ከሴቶቻቸው ከአደፍ ያቋረጡት (በዒዳቸው ሕግ) ብትጠራጠሩዒዳቸው ሦስት ወር ነው፡፡ እኒያም ገና አደፍን ያላዩት (ዒዳቸው እንደዚሁ ነው)፡፡ የእርግዝና ባለቤቶችም ጊዜያቸው እርጉዛቸውን መውለድ ነው፡፡አላህንም የሚፈራ ሰው ከነገሩ ሁሉ ለርሱ መግራትን ያደርግለታል፡፡”
ይህንን ጥቅስ ግልፅ ለማድረግ ያህል፡- አንድ ሙስሊም ወንድ አንዲትን የወር አበባዋ የተቋረጠ ሴት ለመፍታት ቢፈልግ ለሦስት ወር ያህል የግብረ ሥጋ

ግንኙነት ሳይፈፅምይቆያል። ለአቅመ ሔዋን ባለመድረሷ ምክንያት የወር አበባ ያላየችን ሴት ለመፍታት ቢፈልግ እንዲሁ ሦስት ወር ያህል የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሳይፈፅም ይጠብቃል። ይህ የቁርኣን ሐታቸች የሚስማሙበት እስላማዊ መመርያ ነው። ሰይድ አቡል ዓላማውዱዲ የተሰኙ ፓኪስታናዊ ሙስሊም ሊቅ ይህንን ጥቅስ በተመለከተ እንዲህ ይላሉ፡- "ገና አደፍን ያላዩትን (የወር አበባ ያላዩትን) መፍታት የሚቻልበትን መመርያየሚሰጠው ይህ የቁርኣን ጥቅስ እንዲህ አይነት ሴቶችንም ማግባት እንደሚቻል በግልፅ የሚያሳይ ነው፤ በመሆኑም ቁርኣን ያፀደቀውን ይህንን ተግባር ማንም የመከልከል መብት የለውም።"[2] ማውዱዲ በሙስሊሙ ዓለም እጅግ የተከበሩ ዕውቅ የቁርኣን ተንታኝ የነበሩ ናቸው።

በአጠቃላይ ቁርኣን ሴቶችን በተመለከተ ያለው አስተምህሮ የሴቶችን ተፈጥሮና ስብዕና በእጅጉ ዝቅ የሚያደርግ ነው። በመጽሐፉ ውስጥ ከማርያም ስም በስተቀር የአንዲት ሴት ስም እንኳ አልተጠቀሰም።[3] በእስልምናም ውስጥ ሴት ነቢያት አይታወቁም። እድሜ ልካቸውን በጥቁር ጨርቅ ተጀቡነው እንዲኖሩ ተፈርዶባቸዋል። ወንዶች እስከ አራት እንዲያገቡና ከዚያም አልፈው ቁባቶችን እንዲይዙ ሲፈቀድላቸው ሴቶች ግን ከወንዱ መልካም ፈቃድ ውጭ ምንም መወሰን እንዳይችሉ በአስጨናቂ ህግጋት ታጥረዋል (ሱራ 4፡3)።

2. ሴቶች በሐዲስ መጻሕፍት

በተለያዩ ሐዲሳት ውስጥ ሰፍረው የሚገኙ ትዕዛዛትና ህግጋትም እንዲሁ የሙስሊም ሴቶችን ስቃይ ከፍ የሚያደርጉ ናቸው። ለአብነት ያህል ጥቂቶቹን እንመለከታለን፡-

ሴቶች ለባሎቻቸው እንደ ባርያ ናቸው፡-

"ባርያ የጌታው ንብረት ጠባቂ ሲሆን ሚስት ደግሞ የባሏ ቤትና ልጆች ጠባቂ ናት።"[4]

ባሎች ሚስቶቻቸውን መምታት ይችላሉ፡-

"ዑመር እንዳስተላለፈው ነቢዩ እንዲህ ብለዋል፡-‹ባል ሚስቱን ለምን እንደመታት መጠየቅ የለበትም።›" አቡዳውድና ኢብን ማጃህ ዘግበውታል።[5]

የገሃነም አብዛኞቹ ነዋሪዎች ሴቶች ናቸው፡-

"ሴቶች ሆይ ምፅዋት ስጡ የገሃነም አብዛኞቹ ነዋሪዎች ሴቶች መሆናቸውን አይቻለሁና። ‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ ለምንድነው?› ብለው ጠየቁት። ‹ብዙ ጊዜ ትሳደባላችሁ፤ ለባሎቻችሁም ምስጋና ትነፍጋላችሁ። በዕውቀትና በሃይማኖት ከእናንተ በከፋ ሁኔታ ጎደሎ የሆነ አላየሁም›... ሴቶቹም እንዲህ ብለው ጠየቁ፡- ‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ በዕውቀትና በሃይማኖት ጎደሎዎች የሆንነው እንዴት ነው?› እርሱም ‹የሁለት ሴቶች ምስክርነት ከአንድ ወንድ ምስክርነት ጋር እኩል አይደለምን?› በማለት ጠየቃቸው። እነርሱም በአዎንታ መለሱ። ‹ይህ በዕውቀት ጎደሎዎች መሆናችሁን ያሳያል። ሴት በወር አበባ ጊዜዋ መጸለይም ሆነ መፆም አለመቻሏ እውነት አይደለምን?› ብሎ ጠየቃቸው። ሴቶቹም በአዎንታ መለሱ። ‹ይህ በሃይማኖት ጎደሎ መሆናችሁን ያሳያል› በማለት መለሱላቸው።"[6]

ሴት መሪ መሆን አትችልም፡-

"አቡበከር እንዳስተላለፉት በአል ጀመል (ግመል) ዘመቻ ወቅት አላህ (ነቢዩ ሲናገር በሰማሁት ቃል) አጣቀመኝ። ነቢዩ የፋርስ ሰዎች የኾስራውን ሴት ልጅ እንዳነገሷት ሲሰሙ እንዲህ ብለው ነበር፡- ‹በሴት የሚመራ ሕዝብ ፈፅሞ

ስኬታማ አይሆንም።›”[7]
ሙሐመድ ለአቅመ ሔዋን ያልደረሰችን ሕፃን አግብተዋል፡-
“የሐሺም አባት እንዳስተላለፉት፡- ከዲጃ ነቢዩ ወደ መዲና ከመሄዳቸው ከሦስት ዓመታት በፊት ነበር ሕይወቷ ያለፈው። ወደዚያ በሄዱ በሦስት ዓመታት ውስጥ አይሻን አገቧት። ጋብቻውንም ያሟሉት እርሷ ዘጠኝ ዓመት ሲሆናት ነበር።”[8]
ሙሐመድ የሴት ግርዛትን አፅድቀዋል፡-
“ኡም አቲያ አል አንሳርያ እንዳስተላለፉት፤ አንዲት ሴት በመዲና ውስጥ ግርዛትን ትፈፅም ነበር። ነቢዩ (ሰላም በእሳቸው ላይ ይሁንና) እንዲህ አሏት ‹በጣም አድርገሽ መቁረጥ የለብሽም ምክንያቱም እርሱ ለሴት የተሻለ ነው፤ ባልም ይበልጥ የሚወደው ነገር ነው።›”[9]
በዚህ ሐዲስ መሠረት ሙሐመድ አገራረዝ እንዴት መሆን እንዳለበት አስተያየት በመስጠት ድርጊቱን አፀደቁ እንጂ ግርዛት ትክክል አለመሆኑን አልተናገሩም።
ጸሎት በሴት ምክንያት ይቋረጣል፡-
“አቡ ዘር እንዳስተላለፈው፡- የአላህ መልእክተኛ (ሰላም በእሳቸው ላይ ይሁንና) እንዲህ ብለዋል፡- ከመካከላችሁ አንድ ሰው ለጸሎት በሚቆምበት ሰዓት… ከፊት ለፊቱ የኮርቻ ያህል መጠን ያለው ነገር የማይኖር ከሆነ ጸሎቱ (በፊቱ በሚያልፍ) አህያ፣ ሴት እና ጥቁር ውሻ ይቋረጣል። እኔም አቡ ዘር ሆይ ጥቁር ውሻን ከቀይ ወይም ከቢጫ የሚለየው ምንድነው? ብዬ ጠየቅሁት። እርሱም የወንድሜ ልጅ ሆይ አንተ እንደጠየቅኸኝ ሁሉ እኔም የአላህን መልእክተኛ (ሰላም በእሳቸው ላይ ይሁንና) ጠይቄያቸው ነበር፤ ‹ጥቁር ውሻ ዲያብሎስ ነው› በማለት ነበር የመለሱልኝ።”[10]
3. ሴቶች በመጽሐፍ ቅዱስ
እስኪ እነዚህን እስላማዊ ትምህርቶች እውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል ከሆነው ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ያነፃፅሩ።
ባሎች ሚስቶቻቸውን መውደድና ማክበር ይጠበቅባቸዋል።
“ባል ለሚስቱ የሚገባትን ያድርግላት፥ እንደዚሁም ደግሞ ሚስቲቱ ለባልዋ፡ ፡ ሚስት በገዛ ሥጋዋ ላይ ሥልጣን የላትም፥ ሥልጣን ለባልዋ ነው እንጂ፤ እንዲሁም ደግሞ ባል በገዛ ሥጋው ላይ ሥልጣን የለውም፥ ሥልጣን ለሚስቱ ነው እንጂ። ለጸሎት ትተጉ ዘንድ ተስማምታችሁ ለጊዜው ካልሆነ በቀር፥ እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ፤ ራሳችሁን ስለ አለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈታተናችሁ ደግሞ አብራችሁ ሁኑ።” (1ቆሮንቶስ 7፡3-5)።
“ባሎች ሆይ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤ እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ። እንዲሁም ባሎች ደግሞ እንደ ገዛ ሥጋቸው አድርገው የገዛ ሚስቶቻቸውን ሊወዱአቸው ይገባቸዋል። የገዛ ሚስቱን የሚወድ ራሱን ይወዳል፤ ማንም የገዛ ሥጋውን የሚጠላ ከቶ የለምና፥ ነገር ግን የአካሉ ብልቶች ስለሆንን፥ ክርስቶስ ደግሞ ለቤተ ክርስቲያን እንዳደረገላት፥ ይመግበዋል ይከባከበውማል። ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። ይህ ምሥጢር ታላቅ ነው፥ እኔ ግን ይህን ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ

ክርስቲያን እላለሁ። ሆኖም ከእናንተ ደግሞ እያንዳንዱ የገዛ ሚስቱን እንዲህ እንደ ራሱ አድርጎ ይውደዳት፥ ሚስቱም ባልዋን ትፍራ።" (ኤፌሶን 5፡25-33)።
"ባሎች ሆይ፥ ሚስቶቻችሁን ውደዱ መራራም አትሁኑባቸው።" (ቆላስይስ 3፡19)።
"እንዲሁም፥ እናንተ ባሎች ሆይ፥ ደካማ ፍጥረት ስለ ሆኑ ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ፤ ጸሎታችሁ እንዳይከለከል አብረው ደግሞ የሕይወትን ጸጋ እንደሚወርሱ አድርጋችሁ አክብሩአቸው።" (1ጴጥሮስ 3፡7)።
"ደካማ ፍጥረት" (Weak Vessels) የሚለው ሴቶች በስሜት እና በአካል ከወንድ አንፃር ደካሞችና እንክነብካቤ የሚያሻቸው መሆናቸውን እንጂ በመንፈስና በአዕምሮ ደካማ መሆናቸውን አያሳይም። ወንዶች ሴቶችን ካላከበሩ ጸሎታቸው እግዚአብሔር ዘንድ እንደማይደርስ መነገሩ ሴቶች በእግዚአብሔር ፍጥረት ውስጥ ያላቸውን ከፍተኛ ደረጃና በእግዚአብሔር ልብ ውስጥ ያላቸውን ቦታ የሚገልፅ ነው።
ወንዶችና ሴቶች እኩል ናቸው፡-
"አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፥ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፥ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና።" (ገላቲያ 3፡28)።
እኩል በአምሳለ እግዚአብሔር ተፈጥረዋል፡-
"እግዚአብሔርም አለ፦ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር፤ የባሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፥ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፥ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ። እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው።" (ዘፍጥረት 1፡26-27)።
"የአዳም የትውልዱ መጽሐፍ ይህ ነው። እግዚአብሔር አዳምን በፈጠረ ቀን በእግዚአብሔር ምሳሌ አደረገው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው፥ ባረካቸውም፡፡ ስማቸውንም በፈጠረበት ቀን አዳም ብሎ ጠራቸው።" (ዘርጥረት 5፡1-2)።
ከላይ ያየናቸው ጥቅሶች ሴቶች ከወንዶች እኩል መሆናቸውን የሚያረጋግጡ ሲሆኑ ቀደም ሲል ከተመለከትናቸው እስላማዊ መመርያዎች በተፃራሪ የቆሙ ናቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሴት ነቢያት በብዛት ተጠቅሰዋል (ዘጸአት 15፡20፣ መሣፍንት 4፡4፣ 1ዜና 34፡22፣ የሐዋርያት ሥራ 21፡9)። ከሐዋርያት ጋር ሲያገለግሉ የነበሩ ሴት አገልጋዮች ነበሩ (ሮሜ 16፡1፣ 7)። የኢየሱስ ትንሳኤ የመጀመርያዎቹ ምስክሮች ሴቶች ነበሩ (ማቴዎስ 28፡1-9፣ ማርቆስ 16፡1-8፣ ሉቃስ 24፡1-11፣ ዮሐንስ 20፡1-10)። ሴቶች ለምስክርነት በማይቀርቡበት በመጀመርያው ክፍለ ዘመን የክርስትና መሠረት የሆነውን የክርስቶስን ትንሣኤ ለመመስከር መመረጣቸው ምንኛ አስደናቂ ነገር ነው!
ውድ ሙስሊም ወገኖቻችን፤ ከላይ ከተረዘሩት እውነታዎች አንፃር ትክክለኛው የአምላክ መንገድ የትኛው ይመስላችኋል? እግዚአብሔር የልብ ዓይኖቻችሁን በመክፈት የእውነትና የነፃነት መንገድ ወደ ሆነው፣ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ተመሠረተው ትክክለኛ መንገድ ይመራችሁ ዘንድ የዘወትር ጸሎታችን ነው።

ማጣቀሻዎች

[1] Mishkat Al-Masabih: vol. 3, p. 1200

[2] Sayid abul A'La maududi. The meaning of the Qur'an, Vol. 5 pp. 599 & 617
[3] በአማርኛው ትርጉም ውስጥ በቅንፍ ተቀምጠው የምናያቸው በተርጓሚዎቹ የተጨመሩ እንጂ በአረብኛው ውስጥ የሚገኙ አይደሉም።
[4] Sunan Abu Dawud vol.2 no.2922, p.827
[5] Mishkat Al-Masabih: vol. 2, p. 693
[6] Sahih Al-Bukhari vol.1 no.301 p.181. See also Sahih Muslim vol.2 book 4 no.1982,1983 p.432
[7] Sahih Al-Bukhari vol.9 no.219 p.170-171
[8] Bukhari: vol. 5, bk. 58, no. 236, Khan
[9] Sunan Abu-Dawud: bk. 41, no. 5251. "Reliance of the Traveller – A Classic Manual of Islamic Sacred Law" የተሰኘ በአልአዝሃር ዩኒቨርሲቲ አፅዳቂነት የታተመ የሸሪኣ ሕግ መጽሐፍ ገፅ 59 ላይ የሴት ልጅ ግርዛት በእስልምና ግዴታ (Obligatory) መ ሖሕይገልፃል።
[10] Sahih Muslim, Book 004, Number 1032

## አስቂኝ የቁርአን ምዕራፎች ስያሜ

በነገራችን ላይ ቁርአንን ውድቅ ለማድረግ ውስጡን ማንበብም አይጠበቅብህም ። እንዲሁ ከላይ አይተህ የአምላክ ቃልነቱ ቀርቶ የጀማሪ ፀሀፊ እንኳ ፅሁፍ ፈፅሞ ሊሆን እንደማይችል ትረዳለህ ። በእነዚህ ርእሶች የተሰየመ ፅሁፍ እንኳን ልታምነው እንዴት ልታነበው ትችላለህ ??

1ሱረቱ አል-ፋቲሃ --------------------የመክፈቻይቱ ምእራፍ
2 ሱረቱ አል-በቀራህ ------------------የላሚቱ ምዕራፍ
3 ሱረቱ አል-ኢምራን--------------- የአቶ ኢምራን ምዕራፍ
4 ሱረቱ አል-ኒሳዕ-------------------- (ሴቶች) ምዕራፍ
5 ሱረቱ አል ማኢዳህ----------------- የምግብ ማዕድ ምዕራፍ
6 ሱረቱ አል-አንዓም ------------------የቤት እንስሳ ምዕራፍ
7 ሱረቱ አል-አዕራፍ ------------------የርዝማኔይቱ (የርቀቲቱ ) ምዕራፍ
8ሱረቱ አል-አንፋል -------------------የጦር ዘረፋዎች ምዕራፍ
9 ሱረቱ አል-ተውባህ -----------------የንስሀ ምዕራፍ
10 ሱረቱ ዩኑስ -----------------------የአቶ የኑስ ምዕራፍ
11 ሱረቱ ሁድ------------------------የሁድ ከተማ ምዕራፍ
12 ሱረቱ ዩሱፍ ----------------------የአቶ ዩሱፍ ምዕራፍ
13 ሱረቱ አል-ረዕድ------------------ የነጎድጓድ ምዕራፍ
14 ሱረቱ ኢብራሂም ----------------የጋሽ ኢብራሂም ምዕራፍ
15 ሱረቱ አል ሒጅር----------------- የአለታማ ከተማ ምዕራፍ
16 ሱረቱ አን-ነሕል -------------------የንቢቱ ምዕራፍ
17 ሱረቱ አል ኢስራዕ---------------- የሌሊት ጉዞ ምዕራፍ
18 ሱረቱ አል ከህፍ ------------------የዋሻ ምዕራፍ

19 ሱረቱ መርየም------------------ የወይዘሪት መርየም ምዕራፍ
20 ሱረቱ ጣሃ----------------------- የአቶ ጣሀ ምዕራፍ
21 ሱረቱ አል አንቢያ ------------------የነቢያት ምዕራፍ
22 ሱረቱ አል ሐጅ ----------------------የመንፈሳዊ ጉዞ ምዕራፍ
23 ሱረቱ ሙዕሚኑን -----------------የምእመናን ምዕራፍ
24 ሱረቱ አል ኑር-------------------- የብርሀን ምዕራፍ
25 ሱረቱ አልፉርቃን ------------------እውነትን ከውሸት የመለየት ምዕራፍ
26 ሱረቱ አል አሹዐራዕ---------------- የገጣሚዎች ምዕራፍ
27 ሱረቱ አል ነምል-------------------- የጉንዳን ምዕራፍ
28 ሱረቱ አል ቀሶስ --------------------የትረካ ምዕራፍ
29 ሱረቱ አል ዓንከቡት-------------------የሸረሪት ምዕራፍ
30 ሱረቱ አል ሩም ----------------------የሮም ግዛት ምዕራፍ
31 ሱረቱ አል ሉቅማን ------------------የአቶ ሉቅማን ምዕራፍ
32 ሱረቱ አል ሰጅዳህ------------------- የመስገድ ምዕራፍ
33 ሱረቱ አል አሕዛብ-------------------- የአህዛብ ምዕራፍ
34 ሱረቱ ሰበእ ----------------------------የሰብእ ከተማ ምዕራፍ
35 ሱረቱ ፋጢር ------------------------የፈጣሪይቱ ምዕራፍ
36 ሱረቱ ያሲን------------------------- የአቶ ያሲን ምዕራፍ
37 ሱረቱ አል ሷፋት --------------------የተሰላፊዎች ምዕራፍ
38 ሱረቱ ሷድ----------------------------የሷድ ፊደል ምዕራፍ
39 ሱረቱ አዥ ዙመር------------------ የጭፍራዎች ምዕራፍ
40 ሱረቱ ጋፊር------------------------ የይቅር ባዩ ምዕራፍ
41 ሱረቱ ፉሲለት--------------------- የመብራራት ምዕራፍ
42 ሱረቱ አሽ ሹራ-------------------- የመመካከር ምዕራፍ
43 ሱረቱ አዥ ዙኽሩፍ---------------- የጌጣጌጥ ምዕራፍ
44 ሱረቱ አድ ዱኻን------------------- የጭስ ምዕራፍ
45 ሱረቱ አል ጃሲያህ-------------------የተንበርካኪ ምእራፍ
46 ሱረቱ አል አህቃፍ-----------------የአሸዋዎች ምዕራፍ
47 ሱረቱ ሙሀመድ-------------------የአቶ ሙሀመድ ምዕራፍ
48 ሱረቱ አል ፈትህ -------------------ሀገር የመክፈት ምእራፍ
49 ሱረቱ አል ሑጅራት--------------- የቤት ክፍሎች ምዕራፍ
50 ሱረቱ ቃፍ------------------------ የቃፍ ምዕራፍ
51 ሱረቱ አዥ ዛሪያት---------------- የበታኞች ምዕራፍ
52 ሱረቱ አጥ ጡር -----------------የጡር ጋራ ምዕራፍ
53 ሱረቱ አን ነጅም----------------- የኮከብ ምዕራፍ
54 ሱረቱ አል ቀመር---------------- የጨረቃ ምዕራፍ
55 ሱረቱ አል ረሕማን--------------- የሩህሩህ ምዕራፍ
56 ሱረቱ አል ዋቂዓህ ----------------የመከራይቱ ቀን ምዕራፍ
57 ሱረቱ አል ሐዲድ------------------ የብረት ምዕራፍ
58 ሱረቱ አል ሙጃደላ ----------------የመከራከር ምዕራፍ
59 ሱረቱ አል ሐሽር -------------------ከሀገር የማባረር ምዕራፍ

60 ሱረቱ አል ሙምተሀና-------------የፈታኚቱ ምዕራፍ
61 ሱረቱ አስ ሶፍ-----------------------የሰልፍ ምዕራፍ
62 ሱረቱ አል ጁሙዓህ----------------የአርብ ምዕራፍ
63 ሱረቱ አል ሙናፊቁን---------------የመናፍቃን ምዕራፍ
64 ሱረቱ አል ተጋቡን----------------- የመጎዳዳት ምዕራፍ
65 ሱረቱ አል ጠላቅ------------------- የፍቺ ምዕራፍ
66 ሱረቱ አል ተህሪም------------------የማውገዝ ምዕራፍ
67 ሱረቱ አል ሙልክ------------------የንግስና ምዕራፍ
68 ሱረቱ አል ቀለም-------------------የእስኪቢርቶ(ብእር) ምእራፍ
69 ሱረቱ አል ሓቃህ------------------- የአረጋጋጪቱ ምዕራፍ
70 ሱረቱ አል መዓሪጅ---------------- የመሰላሎች ምዕራፍ
71 ሱረቱ ኑህ-------------------------- የአባባ ኑህ ምዕራፍ
72 ሱረቱ አል ጂን---------------------የጂኒ ምዕራፍ
73 ሱረቱ አል ሙዘሚል---------------የተከናናቢው ምዕራፍ
74 ሱረቱ አል ሙደሲር---------------- የልብስ ደራቢው ምዕራፍ
75 ሱረቱ አል ቂያማህ------------------የትንሳኤ ምዕራፍ
76 ሱረቱ አል ኢንሳን------------------- የዘመናት ምዕራፍ
77 ሱረቱ አል ሙርሰላ ------------------የተላኪዎች ምዕራፍ
78 ሱረቱ አል ነበእ -----------------------የወሬ ምዕራፍ
79 ሱረቱ አል ናዚዓት-------------------- የአውጪዎቹ ምዕራፍ
80 ሱረቱ ዐበሰ--------------------------- የማጨፍገግ ምዕራፍ
81 ሱረቱ አት ተክዊር-------------------- የመጠቅለል ምዕራፍ
82 ሱረቱ አል ኢንፊጣር----------------- የመሰንጠቅ ምዕራፍ
83 ሱረቱ አል ሙጠፊፉን ---------------የሰላቢዎች ምዕራፍ
84 ሱረቱ አል ኢንሺቃቅ------------------ የመቀደድ ምዕራፍ
85 ሱረቱ አል ቡሩጅ--------------------- የህብረ-ክዋክብት ምዕራፍ
86 ሱረቱ አል ጣሪቅ--------------------- የሌሊት መጪው ምዕራፍ
87 ሱረቱ አል አዕላ-----------------------የአሸናፊው ምዕራፍ
88 ሱረቱ አል ጋሺያህ--------------------የሸፋኟቱ ምዕራፍ
89 ሱረቱ አል ፈጅር ---------------------የጎህ ምዕራፍ
90 ሱረቱ አል በለድ----------------------የሀገር ምዕራፍ
91 ሱረቱ አል ሸምስ-------------------- የፀሐይቱ ምዕራፍ
92 ሱረቱ አል ለይል--------------------- የሌሊት ምዕራፍ
93 ሱረቱ አል ዱሓ----------------------ረፋድ ምዕራፍ
94 ሱረቱ አሽ ሸርህ --------------------ልብ መስፋት ምዕራፍ
95 ሱረቱ አል ቲን ----------------------የሾላ ምዕራፍ
96 ሱረቱ አል ዐለቅ--------------------የረጋ ደም ምዕራፍ
97 ሱረቱ አል ቀድር --------------------የውሳኔ ምእራፍ
98 ሱረቱ አል-በይናህ------------------ግልፅ አድራጊይቱ ምዕራፍ
99 ሱረቱ አል ዘልዘላህ -----------------የምድር መንቀጥቀጥ ምዕራፍ
100 ሱረቱ አል ዓዲያት---------------የሯጮች ምዕራፍ

101 ሱረቱ አል ቃሪዓሕ--------------- የቆርቋሪቱ ምዕራፍ
102 ሱረቱ አል ተካሱር----------------በጣም የመፎካከር ምዕራፍ
103 ሱረቱ አል ዓስር------------------የጊዜይቱ ምዕታፍ
104ሱረቱ አል ሁመዛህ---------------- የሀሜተኞች ምዕራፍ
105 ሱረቱ አል ፊል --------------------የዝሆን ምዕራፍ
106 ሱረቱ ቁረይሽ --------------------የቁረይሽ ጎሳ ምዕራፍ
107 ሱረቱ አል ማዑን----------------- እቃ የመዋዋስ ምዕራፍ
108 ሱረቱ አል ከውሰር-----------------የበጎ ነገሮች ምዕራፍ
109 ሱረቱ አል ካፊሩን -----------------የከሀዲዎች ምዕራፍ
110 ሱረቱ አን ነስር---------------------የእርዳታ ምእራፍ
111 ሱረቱል ለሀብ----------------------የመንቀልቀል ምእራፍ
112 ሱረቱ አል ኢኽላስ -----------------የፍፁምነት ምዕራፍ
113 ሱረቱ አል ፈለቅ------------------- የተፍለቅላቂዎች ምዕራፍ
114 ሱረቱል አል ናስ -----------------የሰዎች ምዕራፍ

ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ መሆኑን ተናግሯልን?

ሙስሊም ወገኖች ከሚያነሷቸው ጥያቄዎች መካከል "ኢየሱስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እኔ አምላክ ነኝና አምልኩኝ በማለት የተናገረበትን ቦታ አሳዩን" የሚለው አንዱና ዋነኛው ነው። ይህ አግባብ የሆነ ጥያቄ ቢመስልም ነገር ግን የኢየሱስ ክርስቶስን ተልዕኮ በትክክል ካለመረዳትና የመጽሐፍ ቅዱስን ቋንቋ በትክክል ካለማወቅ የመነጨ ጥያቄ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ለመሆን የግድ እኔ አምላክ ነኝና አምልኩኝ በማለት መናገር ያስፈልገዋል የሚለው እሳቤ ምክንያታዊ አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኢየሱስ የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ስለመሆኑ፣ ስለስቅለቱ፣ ስለሞቱና ስለትንሳኤው የተናገረባቸው በርካታ ቦታዎች ይገኛሉ። ሙስሊም ወገኖች እነዚህን እውነታዎች አለመቀበላቸው ኢየሱስ "አምላክ ነኝና አምልኩኝ" ያለበትን ቦታ ብናሳያቸው ሊቀበሉ እንደማይችሉ ያሳያል። ታድያ የጥያቄቸው ትክክለኛው ነጥብ ምንድነው?
ሙስሊም ወገኖች በብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር እርሱ እውነተኛ አምላክ መሆኑን የተናገረባቸውን ቦታዎችበመጥቀስ ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ በተመሳሳይ መንገድ መናገር ነበረበት ይሉናል። ነገር ግን የብሉይ ኪዳን እና የአዲስ ኪዳን ዘመናት ልዩነት እንዳላቸው አይገነዘቡም። እግዚአብሔር በሁሉም ዘመናት በተመሳሳይ መንገድና ሁኔታ ራሱን መግለጥ የግድ አያስፈልገውም። ጥያቄያችን ሊሆን የሚገባው ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነቱን በምን ዓይነት መንገድ ነው የገለጠው? የሚል እንጂ "እኛ በምንፈልገው መንገድ ስላልተናገረ አምላክ አይደለም" በማለት መደምደም ትክክል አይደለም።
በአዲስ ኪዳን ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ ገልጧል። ነገር ግን ይህ መንገድ "አምላክ ነኝና አምልኩኝ" የሚሉትን እነዚህን ቃላት በመናገር ላይሆን ይችላል። ስለዚህ "እኔ ባልኩት መንገድ ካልተናገረ በስተቀር አምላክነቱን አልቀበልም" በማለት ሌሎች ማስረጃዎችን መካድ ጠያቂው መልስ ፈላጊ ሳይሆን ክርክር ፈላጊ መሆኑን ያሳያል።

ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ይመላለስ በነበረበት ዘመን "አምላክ ነኝና አምልኩኝ" የሚሉትን እነዚህን ቃላት መናገር ያላስፈለገበትን የተወሰኑ ምክንያቶች መጥቀስ ይቻላል። ይህንን ስንል ግን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነቱን ክዷል፣ ሸሽጓል ወይንም ደግሞ በምንም አይነት መንገድ አልተናገረም ማለታችን አይደለም።

ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር የመጣው አምላክነቱንና ጌትነቱን ለማወጅ አልነበረም። የኢየሱስ ተልዕኮ ራሱን በማዋረድ ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ አድርጎ መስጠት እንጂ መለኮታዊ ክብሩን በማወጅ ሰዎች እንዲያውቁት ባለመሆኑ በየስፍራው እየዞረ አምላክነቱን ቢያውጅ ከተልዕኮው ጋር የሚጣጣም አይሆም። ጌታችን የራሱን ክብር ፍለጋ እንዳልመጣ በተደጋጋሚ ተናግሯል (ዮሐንስ 8:50፣ ማቴዎስ 20:28)። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ይህንን ሐሳብ ልብን በሚነካ መንገድ ገልፆታል (ፊልጵስዩስ 2፡5-10)።

ኢየሱስ በእርሱና በአብ መካከል ያለውን የአካል ልዩነት ግልፅ ሳያደርግ ‹አምላክ ነኝና አምልኩኝ› የሚሉትን ቃላት ቢናገር አይሁዶች ግራ ይጋቡ ነበር። አይሁዶች ስለ እግዚአብሔር ሦስቱ አካላት፣ ማለትም ስለ ሥላሴ ግንዛቤ ስላልነበራቸው ኢየሱስ ‹አምላክ ነኝና አምልኩኝ› የሚሉትን ቃላት ቢናገር ‹አብ ነኝ› የሚል ስለሚመስላቸው እንዲህ ብሎ መናገሩ ግርታን ከመፍጠርና በእርሱ ላይም ተቃውሞን ከማስነሳት የዘለለ ጠቀሜታ ሊኖረው አይችልም ነበር። ስለዚህ ሁልጊዜ አምላክነቱን የሚያሳዩ ስራዎችን እየሰራ እና በትምህርቶቹም ውስጥ ጥበብን በተሞላ መንገድ እየነገራቸው ሰዎች አምላክ መሆኑን ወደማወቅ ደረጃ እንዲመጡ መርቷቸዋል። ነገር ግን ይህንን ሲያደርግ ሁል ጊዜ ከአብ ጋር ያለውን የአካል ልዩነት ግልፅ በማድረግ ነበር።

ኢየሱስ በምድር ላይ ይመላለስ በነበረበት ዘመን ከሌሎች ሰዎች የተለየ መልክ አልነበረውም። ዛሬ አንድ ሰው ወደ እኛ መጥቶ ‹አምላክ ነኝና አምልኩኝ› ቢለን እንደማንቀበለው ሁሉ ኢየሱስም በዘመኑ ይህንን ቢል ኖሮ ተቃውሞን ከማትረፍ ውጪ ምንም ጠቀሜታ አይኖረውም ነበር። ‹አምላክ ነኝና አምልኩኝ› ከሚለው መንገድ ይልቅ በተግባር አምላክ መሆኑን መግለጥ የተሻለ በመሆኑ ይህንኑ አድርጓል። ሰዎች ደግሞ ሥራውን በማየት አምላክነቱን ወደ ማወቅ ሲመጡና ለአምላክ የሚገባውን ክብር ሲሰጡት በመስማማት ሲያረጋግጥላቸው እንጂ አንድም ጊዜ ሲቃወማቸው አልታየም (ዮሐንስ 20:24-29)።

ኢየሱስ አምላክ መሆኑን የገለጠባቸው መንገዶችና ንግግሮች

መሲህ መሆኑን (ክርስቶስ መሆኑን) በመናገር፡-

ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን ትንቢት የተነገረለት መሲህ መሆኑን በተደጋጋሚ ተናግሯል (ማቴዎስ 16፡13-17፣ ዮሐንስ 4፡25-26፣ 26፡1-3 ማርቆስ 14፡1-2፣ 12:35-37፣ 13፡26-27 ሉቃስ 24፡13-15፣ 24፡25-27፣ 24፡44-49 ይመልከቱ)።

የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች መሲሁ አምላክ መሆኑን ይናገራሉ፡-

"ሕፃን ተወልዶልናልና፣ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ መካር፣ ኃያል አምላክ፣ የዘለዓለም አባት፣ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል። ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘለዓለም ድረስ በፍርድና በጽድቅ ያጸናውና ይደግፈው ዘንድ በዳዊት ዙፋንና በመንግሥቱ ላይ አለቅነቱ ይበዛል፣ ለሰላሙም ፍፃሜ የለውም። የእግዚአብሔር ቅንዓት ይህን ያደርጋል።" ትንቢተ ኢሳይያስ 9፡ 6-7

“የጭፍሮች ሴት ልጅ ሆይ፥ ጭፍሮችሽን አሁን ሰብስቢ ከብቦ አስጨንቆናል የእስራኤልን ፈራጅ ጕንጬን በበትር ይመታሉ። አንቺም ቤተ ልሔም ኤፍራታ ሆይ፥ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘለዓለም የሆነ፥ በእስራኤልም ላይ ገዥ የሚሆን ይወጣልኛል፡፡” ትንቢተ ሚክያስ 5፡1-2

“እነሆ፥ መልእክተኛዬን እልካለሁ፥ መንገድንም በፊቴ ያስተካክላል እናንተም የምትፈልጉት ጌታ በድንገት ወደ መቅደሱ ይመጣል የምትወዱትም የቃል ኪዳን መልእክተኛ፥ እነሆ፥ ይመጣል፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፦ ነገር ግን እርሱ እንደ አንጥረኛ እሳትና እንደ አጣቢ ሳሙና ነውና የሚመጣበትን ቀን መታገሥ የሚችል ማን ነው? እርሱስ በተገለጠ ጊዜ የሚቆም ማን ነው? እርሱም ብርን እንደሚያነጥርና እንደሚያጠራ ሰው ይቀመጣል፥ የሌዊንም ልጆች ያጠራል፥ እንደ ወርቅና እንደ ብርም ያነጥራቸዋል እነርሱም ለእግዚአብሔር በጽድቅ ቍርባንን የሚያቀርቡ ይሆናሉ።” ትንቢተ ሚልክያስ 3፡1-3

“አምላክ ሆይ፥ ዙፋንህ ለዘለዓለም ነው የመንግሥትህ በትር የቅንነት በትር ነው፡፡ ጽድቅን ወደድህ ዓመፃንም ጠላህ ስለዚህ ከባልንጀሮችህ ይልቅ እግዚአብሔር አምላክህ የደስታ ዘይትን ቀባህ።” መዝሙረ ዳዊት 45

ከላይ የተጠቀሱትን ሁለት ነጥቦች አመክንዮአዊ በሆነ መንገድ ስናስቀምጣቸው እንደሚከተለው ይሆናል፡-

- ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን ትንቢት የተነገረለት መሲህ መሆኑን ተናግሯል
- በብሉይ ኪዳን ትንቢቶች መሠረት መሲሁ አምላክ ነው
- ስለዚህ ኢየሱስ አምላክ መሆኑን ተናግሯል።

ይህ ቀላል ሲሎጂዝም (የአመክንዮአዊ አረፍተ ነገሮች ድርደራ) ኢየሱስ አምላክ መሆኑን እንደተናገረ በግልፅ ያሳያል።

በሰማይ ደመና የሚመጣው “የሰው ልጅ” መሆኑን በመናገር፡-

ኢየሱስ ክርስቶስ በተደጋጋሚ “የሰው ልጅ” የሚለውን ማዕርግ ሲጠቀም እናያለን (ማርቆስ 13፡23-27፣ 14፡60-64)፡፡

“የሰው ልጅ” የሚለውን ስያሜ ሚስጥር የምናገኘው በትንቢተ ዳንኤል 7፡13-14 ላይ ነው፡-

“በሌሊት ራእይ አየሁ እነሆም፥ የሰው ልጅ የሚመስል ከሰማይ ደመናት ጋር መጣ በዘመናት ወደ ሸመገለውም ደረሰ ወደ ፊቱም አቀረቡት። ወገኖችና አሕዛብ በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገሩ ሁሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትና ክብር መንግሥትም ተሰጠው ግዛቱም የማያልፍ የዘለዓለም ግዛት ነው፥ መንግሥቱም የማይጠፋ ነው፡፡”

በዚህ ጥቅስ መሠረት ይህ የሰው ልጅ የተባለው አካል ህዝቦችን ሁሉ የሚገዛ፤ የማያልፍ የዘለዓለም ግዛት ያለው እና የማይጠፋ መንግሥት ያለው ነው፡፡ ከአምላክ በስተቀር ህዝቦች ሁሉ ሊገዙት የሚገባ እና ዘለዓለማዊ ግዛትና መንግሥት ሊኖረው የሚችል ማነው? ኢየሱስ “የሰው ልጅ” የሚለውን ማዕርግ መጠቀሙ ስጋ ለብሶ የመጣ አምላክ መሆኑን ለማሳየት እንደነበር ከዚህ ትንቢት እንረዳለን።

አምላክ ብቻ ሊያደርጋቸው የሚችላቸውን ነገሮች በማድረግ፡-

ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን ኢየሱስ ኃጢዓትን ይቅር የማለት ችሎታ እንዳለው

ማሳየቱ ነው (ማርቆስ 2፡1-12)፡፡
ከአምላክ በስተቀር ኃጢዓትን ይቅር ሊል የሚችል ማነው?
ለአብ የሚገባው ክብር ሁሉ ለእርሱም እንደሚገባ በመናገር፡-
“ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድን ያከብሩት ዘንድ፥ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ በአንድ ሰው ስንኳ አይፈርድም። ወልድን የማያከብር የላከውን አብን አያከብርም፡፡” (ዮሐንስ 5፡22-23)
አብን የምናከብረው እርሱን በማምለክ ነው። ኢየሱስንም አብን እንደምናከብረው ማክበር የምንችለው ለአብ የምንሰጠውን ክብር ሁሉ ስንሰጠው ነው፡፡
ወደ እርሱ እንድንጸልይ እና እርሱም ደግሞ የምንለምነውን በሙሉ እንደሚያደርግልን በመናገር፡-
“እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፤ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል፥ እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና፤ አብም ስለ ወልድ እንዲከበር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ። ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ፡፡” (ዮሐንስ 14)፡፡
ኢየሱስ የሁሉን ሰው ጸሎት ለመስማት በሁሉም ስፍራ መገኘት እና ሁሉን ማወቅ መቻል አለበት፤ የምንለምነውን ሁሉ ለማድረግ ደግሞ ሁሉን ቻይ መሆን አለበት፡፡ ከአንዱ አምላክ በስተቀር ፀሎታችንን ሰምቶ የምንለምነውን ሁሉ ማድረግ የሚችል ማነው? ኢየሱስ ግን ይህንን ማድረግ እንደሚችል ነግሮናል ስለዚህ አምላክ መሆኑን ተናግሯል።
በሁሉም ስፍራ መገኘት እንደሚችል በመናገር፡-
“ደግሞ እላችኋለሁ፥ ከእናንተ ሁለቱ በምድር በማናቸውም በሚለምኑት ነገር ሁሉ ቢስማሙ በሰማያት ካለው ከአባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል። ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና፡፡” (ማቴዎስ 18፡19-20)፡፡
“እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ፡፡” (ማቴዎስ 28፡19-20)፡፡
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምንሰበሰብበት ስፍራ ሁሉ በመካከላችን መገኘት የሚችለው እና እስካለም ፍፃሜ ድረስ ከእኛ ጋር መሆን የሚችለው በሁሉም ስፍራ የመገኘት ችሎታ ካለው ብቻ ነው። ስለዚህ ኢየሱስ ይህን ማድረግ እንደሚችል መናገሩ በሌላ ቋንቋ አምላክ መሆኑን መናገሩ ነው፡፡
ሰዎች በስሙ የኃጢዓት ይቅርታን እንደሚያገኙ በመናገር፡-
“በዚያን ጊዜም መጻሕፍትን ያስተውሉ ዘንድ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው፤ እንዲህም አላቸው፦ ክርስቶስ መከራ ይቀበላል በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሣል፥ በስሙም ንስሐና የኃጢአት ስርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል ተብሎ እንዲሁ ተጽፎአል። እናንተም ለዚህ ምስክሮች ናችሁ፡፡” የሉቃስ ወንጌል 24፡45-48
ከአምላክ ስም በስተቀር የኃጢዓትን ይቅርታ የሚያስገኝ ስም የማን ስም ነው?
በስሙ በሽተኞች እንደሚፈወሱና አጋንንት እንደሚወጡ በመናገርና አማኞች ይህንን ማድረግ እንዲችሉ ስልጣን በመስጠት፡-

“ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፤ እባቦችን ይይዛሉ፥ የሚገድልም ነገር ቢጠጡ አይጎዳቸውም፤ እጃቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ እነርሱም ይድናሉ። ጌታ ኢየሱስም ከእነርሱ ጋር ከተናገረ በኋላ ወደ ሰማይ ዐረገ በእግዚአብሔርም ቀኝ ተቀመጠ። እነርሱም ወጥተው በየስፍራው ሁሉ ሰበኩ፥ ጌታም ከእነርሱ ጋር ይሠራ ነበር፥ በሚከተሉትም ምልክቶች ቃሉን ያጸና ነበር።” የማርቆስ ወንጌል 16፥ 17-20

“ሰብዓውም በደስታ ተመልሰው ጌታ ሆይ፥ አጋንንት ስንኳ በስምህ ተገዝተውልናል አሉት። እንዲህም አላቸው ሰይጣንን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ፡ ፡ እነሆ፥ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ፥ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፥ የሚጐዳችሁም ምንም የለም። ነገር ግን መናፍስት ስለ ተገዙላችሁ በዚህ ደስ አይበላችሁ፥ ስማችሁ ግን በሰማያት ስለ ተጻፈ ደስ ይበላችሁ።” የሉቃስ ወንጌል 10፡17-20

አጋንንትን ማስወጣት የሚችልና በሽተኞችን መፈወስ የሚችል ከአምላክ ስም በስተቀር የማን ስም ሊሆን ይችላል? ሰዎች ይህንን ማድረግ እንዲችሉ ስልጣን መስጠት የሚችል ከአምላክ በስተቀር ማነው?

መላእክትን ማዘዝ እንደሚችል እና የእርሱ እንደሆኑ በመናገር:-

“ከዚያች ወራትም መከራ በኋላ ወዲያው ፀሐይ ይጨልማል፥ ጨረቃም ብርሃንዋን አትሰጥም፥ ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ፥ የሰማያትም ኃይላት ይናወጣሉ። በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ይታያል፥ በዚያን ጊዜም የምድር ወገኖች ሁሉ ዋይ ዋይ ይላሉ፥ የሰው ልጅንም በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል፤ መላእክቱንም ከታላቅ መለከት ድምፅ ጋር ይልካቸዋል፥ ከሰማያትም ዳርቻ እስከ ዳርቻው ከአራቱ ነፋሳት ለእርሱ የተመረጡትን ይሰበስባሉ።” (ማቴዎስ 24፡ 29-30)።

ከአምላክ በስተቀር ቅዱሳን መላዕክትን እንደራሱ አገልጋዮች ማዘዝና መላክ የሚችል ማነው?

በመጨረሻው ቀን ሙታንን የሚያስነሳው እርሱ እንደሆነ በመናገር:-

“ፈቃዴን ለማድረግ አይደለም እንጂ የላከኝን ፈቃድ ለማድረግ ከሰማይ ወርጃለሁና። ከሰጠኝም ሁሉ አንድንስንኳ እንዳላጠፋ በመጨረሻው ቀን እንዳስነሣው እንጂ የላከኝ የአብ ፈቃድ ይህ ነው። ልጅንም አይቶ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወትን እንዲያገኝ የአባቴ ፈቃድ ይህ ነው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።” (ዮሐንስ 6፡38-40)።

ከአምላክ በስተቀር በፍርድ ቀን ሙታንን ማስነሳት የሚችል ማነው?

በመጨረሻው ቀን በሁሉም ላይ የመፍረድ ስልጣን ያለው እርሱ መሆኑን በመናገር:-

“የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላእክቱ ሁሉ፥ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል፤ አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፤ እረኛም በጎቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርስ በርሳቸው ይለያቸዋል፥ በጎችን በቀኙ ፍየሎችንም በግራው ያቆማቸዋል። ንጉሡም በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል። እናንተ የአባቴ ቡሩካን፥ ኑ፤ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ። ተርቤ አብልታችሁኛልና፥ ተጠምቼ

አጠጥታችሁኛልና፣ እንግዳሆኜ ተቀብላችሁኛልና፣ ታርዤ አልብሳችሁኛልና፣ ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፣ ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና። ጻድቃንም መልሰው ይሉታል። ጌታ ሆይ፥ ተርበህ አይተን መቼ አበላንህስ? ወይስ ተጠምተህ አይተን መቼ አጠጣንህ? እንግዳ ሆነህስ አይተን መቼ ተቀበልንህ? ወይስ ታርዘህ አይተንመቼ አለበስንህ? ወይስ ታመህ ወይስ ታስረህ አይተን መቼ ወደ አንተ መጣን? ንጉሡም መልሶ፦ እውነት እላችኋለሁ፤ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት ይላቸዋል። በዚያንጊዜ በግራው ያሉትን ደግሞ ይላቸዋል። እናንተርጕማን፣ ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘለዓለም እሳት ከእኔ ሂዱ። ተርቤ አላበላችሁኝምና፣ ተጠምቼ አላጠጣችሁኝምና፣ እንግዳሆኜ አልተቀበላችሁኝምና፣ ታርዤ አላለበሳችሁኝምና፣ ታምሜ ታስሬም አልጠየቃችሁኝምና ...” (ማቴዎስ 25፡31-43)።

“ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድን ያከብሩት ዘንድ፣ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ በአንድ ሰው ስንኳ አይፈርድም። ወልድን የማያከብር የላከውን አብን አያከብርም።” የዮሐንስ ወንጌል 5፡22-23

ከአምላክ በስተቀር በመጨረሻም ቀን በህያዋንና በሙታን የመፍረድ ሥልጣን ያለው ማነው?

የዘለዓለምን ሕይወት መስጠት እንደሚችል በመናገር:-

“በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ እኔም አውቃቸዋለሁ ይከተሉኝማል፤ እኔም የዘለዓለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ፣ ለዘለዓለምም አይጠፉም፣ ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም። የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል፣ ከአባቴም እጅ ሊነጥቃቸው ማንም አይችልም። እኔና አብ አንድ ነን። አይሁድ ሊወግሩት ደግመው ድንጋይ አነሡ።” (ዮሐንስ 10፡27-31)።

ከአምላክ በስተቀር የዘለዓለምን ሕይወት መስጠት የሚችል የለም!

ለአምላክ ብቻ የሚገባውን ስግደትና አምልኮን በመቀበል:-

“እነሆም፣ ሲሄዱ ነጹ። ከእነርሱም አንዱ እንደ ተፈወሰ ባየ ጊዜ በታላቅ ድምፅ እግዚአብሔርን እያከበረ ተመለሰ፣ እያመሰገነውም በእግሩ ፊት በግንባሩ ወደቀ፤ እርሱም ሳምራዊ ነበረ። ኢየሱስም መልሶ፦ አሥሩ አልነጹምን? ዘጠኙስ ወዴት አሉ? ከዚህ ከልዩ ወገን በቀር እግዚአብሔርን ሊያከብሩ የተመለሱ አልተገኙም አለ። እርሱንም ተነሣና ሂድ፤ እምነትህ አድኖሃል አለው።” (ሉቃስ 17፡15-19)።

“ነገር ግን የካህናት አለቆችና ጻፎች ያደረገውን ድንቃ ድንቅ በመቅደስም ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ እያሉ የሚጮኹትን ልጆች ባዩ ጊዜ፣ ተቈጥተው እነዚህ የሚሉትን አትሰማምን? አሉት። ኢየሱስም፦ እሰማለሁ፤ ከሕፃናትና ከሚጠቡት አፍ ምስጋናን ለራስህ አዘጋጀህ የሚለውን ቃል ከቶ አላነበባችሁምን? አላቸው። ” (ማቴዎስ 21፡15-16)።

እግዚአብሔር በቅዱስ ቃሉ ውስጥ ክብሩን ለማንም እንደማይሰጥ በተደጋጋሚ ተናግሯል (ዘዳግም 5፡6-10፣ ኢሳይያስ 42፡8)። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የሰዎችን ስግደትና ምስጋና ተቀብሏል። ለአምላክ ብቻ የሚገባውን ክብር በመውሰድ አምላክ መሆኑን አሳይቷል።

ጌታ መሆኑን በመናገር:-

የሰዎች ጌታ መሆኑን:-

“እናንተ መምህርና ጌታ ትሉኛላችሁ፤ እንዲሁ ነኝና መልካም ትላላችሁ። እንግዲህ

እኔ ጌታና መምህር ስሆን እግራቻሁን ካጠብሁ፥ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳቻሁ እግራቻሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባቻኋል። እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻቻኋለሁና።" (ዮሐንስ 13፡13-15)።
የሰንበት ጌታ መሆኑን፡-
"እንዲሁም የሰው ልጅ ለሰንበት እንኳ ጌታዋ ነው አላቸው።" የማርቆስ ወንጌል 2፡28
ብዙ ሙስሊሞች ኢየሱስ ጌትነቱን በግልፅ መናገሩን ስለማያውቁ "ጌታ ነኝ ያለበትን ቦታ አሳዩን" በማለት ይጠይቃሉ። ነገር ግን ዮሐንስ 13፡13-15 ላይ የሚገኘውን ስናሳያቸው ትንሽ ደንገጥ በማለት ይቆዩና ሌላ ዘዴ ይፈጥራሉ። "በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰዎችም ጌታ ተብለዋል" ይላሉ። ነገር ግን ኢየሱስ ጌትነቱ ልክ ሐዋርያቱ የሚሉት ዓይነት ጌትነት መሆኑን ስለተናገረ ሐዋርያት በሚሉት ዓይነት መንገድ እንጂ በራሳቸን መንገድ ልንተረጉመው አንቻልም። በዚህ ርዕስ ስር በቀጣይነት እንደምንመለከተው ሐዋርያት የኢየሱስን አምላክነት ያምኑ ስለነበር "ጌታ" ሲሉት አምላክነቱን ለማመልከት እንጂ ከፍ ያለ ሥልጣን ያላቸው ሰዎች ጌታ በሚባሉበት መንገድ እየጠሩት አይደለም። ኢየሱስ ጌታ መሆኑን የተናገረበት ሌላው አጋጣሚ የሰንበት ጌታ መሆኑን ነው። ይህ ደግሞ በማያሻማ ሁኔታ አምላክነቱን ያሳያል፤ ምክንያቱም ሰንበት ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ቀን መሆኑ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ተነግሯልና (ዘጸአት 31:12-17)። እግዚአብሔር ለራሱ በቀደሰው ቀን ላይ ጌታ መሆን የሚቻል ራሱ እግዚአብሔር ብቻ ነው።
በዮሐንስ ራዕይ ውስጥ የሚገኙ ማስረጃዎቻ
በነዚህ ጥቅሶቻ ውስጥ የሚገኙት የኢየሱስ ንግግሮቻ ወደሰማይ ካረገ በኋላ የተናገራቸው ናቸው
(1) ፊተኛውና ኋለኛው
"አልፋና ዖሜጋ፥ ፊተኛውና ኋለኛው፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ።" የዮሐንስ ራእይ 22፡13
"ባየሁትም ጊዜ እንደ ሞተ ሰው ሆኜ ከእግሩበታቻ ወደቅሁ። ቀኝ እጁንም ጫነብኝ እንዲህም አለኝ፦ አትፍራ፤ ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ፥ ሞቼም ነበርሁ እነሆም፥ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ ሕያው ነኝ፥ የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ።" (ራእይ 1፡17-18)።
የሚከተለው የብሉይ ኪዳን ጥቅስ ይህንን ንግግር መናገር የሚቻለው አምላክ ብቻ መሆኑን ያሳያል፡-
"የእስራኤል ንጉሥ እግዚአብሔር፥ የሚቤዠም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እኔ ፊተኛ ነኝ እኔም ኋለኛ ነኝ፥ ከእኔ ሌላም አምላክ የለም። እንደ እኔ ያለ ማን ነው? ይነሣና ይጥራ ይናገርም፤ ከጥንት የፈጠርሁትን ሕዝብ ያዘጋጅልኝ፥ የሚመጣውም ነገር ሳይደርስ ይንገሩኝ።" (ኢሳይያስ 44፡6-7)።
(2) ኩላሊትንና ልብን የሚመረምር
"አብያተ ክርስቲያናትም ሁሉ ኩላሊትንና ልብን የምመረምር እኔ እንደ ሆንሁ ያውቃሉ" (ራእይ 2፡23)።
የሰዎቻን የተሰወረ የውስጥ ሐሳብ መርምሮ ማወቅ የሚቻለው ከአምላክ በስተቀር ማን ሊሆን ይቻላል? የሚከተለው የብሉይ ኪዳን ጥቅስ ይህንን ንግግር መናገር የሚቻለው አምላክ ብቻ መሆኑን ያሳያል፡-

“እኔ እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ እንደ መንገዱ፥ እንደ ሥራው ፍሬ እሰጥ ዘንድ ልብን እመረምራለሁ ኵላሊትንም እፈትናለሁ።” (ኤርምያስ 17፡10)።
(3) ለሁሉም እንደየስራው የሚከፍል
“እነሆ፣ በቶሎ እመጣለሁ፤ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ።” (ራእይ 22፡12)።
“ለእያንዳንዳችሁም እንደ ሥራችሁ እሰጣችኋለሁ።” (ራእይ 2፡23)።
በመጨረሻው የፍርድ ቀን ለሁሉም ሰው እንደየስራው መክፈል የሚችል ከአምላክ በስተቀር ማን ሊሆን ይችላል?
(4) አምላክ ነኝ ብሏል
“በዙፋንም የተቀመጠው። እነሆ፣ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ አለ። ለእኔም፤ እነዚህ ቃሎች የታመኑና እውነተኛዎች ናቸውና ጻፍ አለኝ። አለኝም ተፈጽሞአል። አልፋና ዖሜጋ፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ። ለተጠማ ከሕይወት ውኃ ምንጭ እንዲያው እኔ እሰጣለሁ። ድል የሚነሣ ይህን ይወርሳል አምላክም እሆነዋለሁ እርሱም ልጅ ይሆነኛል።” (ራእይ 21፡5-7)።
በዚህ ጥቅስ መሠረት አልፋና ኦሜጋ ፊተኛውና መጨረሻ የሆነው እርሱ አምላክ መሆኑን ይናገራል። በራዕይ 22፡12-13 ላይ ይህ አልፋና ኦሜጋ መጀመርያና መጨረሻ የሆነው በቶሎ እንደሚመጣ ይናገራል። ምዕራፍ 22፡20 ላይ ይህ በቶሎ የሚመጣው ራሱ ኢየሱስ እንደሆነ ተነግሮናል። ስለዚህ አልፋና ኦሜጋ የሆነው በቶሎ እንደሚመጣ የተናገረው በምዕራፍ 21፡7-8 ላይ አምላክ መሆኑን የተናገረው ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑ ግልፅ ነው።
እግዚአብሔር አብ ስለ እርሱ ምን አለ?
ሙስሊም ወገኖች በቁርኣን ውስጥ የሚገኙትን የአላህ ንግግሮች እንደሆኑ የሚያምኗቸውን ቃላት ያለምንም ቅድመሁኔታ ይቀበላሉ። ለምሳሌ ዒሳ ከድንግል ነው የተወለደው የሚለውን ትልቅ እምነት የሚጠይቀውን ንግግር የተቀበሉት ዒሳ በቁርኣን ውስጥ “እኔ ከድንግል ነው የተወለድኩ” በማለት ስለተናገረ ሳይሆን አላህ ራሱ ዒሳ ከድንግል እንደተወለደ ስለተናገረ ነው። ዒሳ ከድንግል መወለዱን ለማመን ለእነርሱ በቁርኣን ውስጥ የተጻፈው የአላህ ንግግር ብቻ በቂ ከሆነ ለኛም ኢየሱስ አምላክ መሆኑን ለመቀበል የእግዚአብሔር አብ ንግግር ብቻ በቂ የማይሆንበት ምንም ምክንያት የለም። ስለዚህ እግዚአብሔር አብ ስለልጁ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት ምን ብሎ እንደተናገረ የዕብራውያን መልዕክት ጸሐፊ መዝሙረ ዳዊት ውስጥ የተጻፈውን ትንቢት በመጥቀስ የተናገረውን እንመልከት።
“ከመላእክት ይልቅ እጅግ የሚበልጥ ስምን በወረሰ መጠን እንዲሁ ከእነርሱ አብዝቶ ይበልጣል። ከመላእክትስ። አንተ ልጄ ነህ፥ እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ፥ ደግሞም፦ እኔ አባት እሆነዋለሁ እርሱም ልጅ ይሆነኛል ያለው ከቶ ለማን ነው? ደግሞም በኵርን ወደ ዓለም ሲያገባ። የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉም ለእርሱ ይስገዱ ይላል። ስለ መላእክትም። መላእክቱን መናፍስት አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል የሚያደርግ ይላል፤ ስለ ልጁ ግን። አምላክ ሆይ፥ ዙፋንህ እስከ ዘለዓለም ድረስ ይኖራል፤ የመንግሥትህ በትር የቅንነት በትር ነው። ጽድቅን ወደድህ ዓመፅንም ጠላህ፤ ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክህ ከጓደኞችህ ይልቅ በደስታ ዘይት ቀባህ ይላል። ደግሞ ጌታ ሆይ፥ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ፥ ሰማዮችም የእጆችህ

ሥራ ናቸው፤ እነርሱም ይጠፋሉ አንተ ግን ጸንተህ ትኖራለህ፤ ሁሉም እንደ ልብስ ያረጃሉ፥ እንደ መጎናጸፊያም ትጠቀልላቸዋለህ ይለወጡማል፤ አንተ ግን አንተ ነህ፥ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም ይላል። ነገር ግን ከመላእክት ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ ከቶ ለማን ብሎአል? ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን?" (ዕብራውያን 1፡4-14)።

በዚህ ጥቅስ መሠረት እግዚአብሔር አብ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስን መላእክት የሚሰግዱለት፣ ጌታ፣ አምላክ፣ ዘለዓለማዊ ዙፋን ያለው፣ የሰማያት ፈጣሪ፣ ወዘተ. በማለት ይጠራዋል። ይህ ለክርስቲያኖች ኢየሱስ አምላክ መሆኑን ለመቀበል ብቻውን በቂ ማስረጃ ነው።

ሐዋርያት ምን አሉ?

የኢየሱስ ሐዋርያት ከእርሱ ጋር አብረው ስለነበሩ ስለማንነቱ ከማንም በላይ ያውቃሉ ስለዚህ የእነርሱ ምስክርነት ለኢየሱስ አምላክነት ትልቅ ማስረጃ ነው። ቀጥሎ እነዚህ ቅዱሳን ሰዎች ስለ እርሱ አምላክነት የተናገሯቸውን እንመለከታለን።

ስምዖን ጴጥሮስ

"የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያና ሐዋርያ የሆነ ስምዖን ጴጥሮስ፥ በአምላካችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ ካገኘነው ጋር የተካከለ የከብር እምነትን ላገኙ፤ የመለኮቱ ኃይል፥ በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን በማወቅ፥ ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚሆነውን ነገር ሁሉ ስለ ሰጠን፥ በእግዚአብሔርና በጌታችን በኢየሱስ እውቀት ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ።" (2ኛ ጴጥሮስ 1፡1-3)።

የዘብዴዎስ ልጅ ዮሐንስ

"በመጀመሪያው ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ። ሁሉ በእርሱ ሆነ፥ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም።" (ዮሐንስ 1፡1-3)።

"የእግዚአብሔርም ልጅ እንደ መጣ፥ እውነተኛም የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቡናን እንደ ሰጠን እናውቃለን፤ እውነተኛም በሆነው በእርሱ አለን፥ እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘለዓለም ሕይወትነው። " (1ኛ ዮሐንስ 5፡20)።

ቶማስ

"ቶማስም ጌታዬ አምላኬም ብሎ መለሰለት። ኢየሱስም፦ ስለ አየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው አለው።" (ዮሐንስ 20፡28-29)።

ቅዱስ ጳውሎስ

ጌታ ኢየሱስን ፊትለፊት በማየቱ ምክንያትና ከሐዋርያት ጋር እንዲማገልገሉ መጠን የሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ምስክርነት ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም። እርሱስ ስለ ኢየሱስ አምላክነት ምን አለ?

"አባቶችም ለእነርሱ ናቸውና፤ ከእነርሱም ክርስቶስ በሥጋ መጣ፥ እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘለዓለም የተባረከ አምላክ ነው፤ አሜን።" (ሮሜ 9፡5)።

"ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦአልና፤ ይህም ጸጋ፥ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊን ምኞት ክደን፥ የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ

እየጠበቅን፣ ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል፡፡” (ቲቶ ፡11-13)፡፡
ከላይ የተዘረዘሩትን ማስረጃዎች ካጤነ በኋላ ኢየሱስ ስለ አምላክነቱ መናገሩንና መጽሐፍ ቅዱስ አምላክነቱን ማረጋገጡን የሚክድ ለህሊናው ያደረ ሰው ይኖራል የሚል ግምት የለንም፡፡

## ኢንጂል ተበርዟልን?
## ስለ አዲስ ኪዳን እውነቱን ለማወቅ ያደረኩት ፍለጋ

ውድ አንባቢ
ፈጣሪ ይመስገን! አልሐምዱሊላህ!
ይህንን መጽሐፍ እንድጽፍ ኃይልን የሰጠኝ ፈጣሪ ነው፡፡ የዒሳ አል–መሲህ መጽሐፍ በሆነው በቅዱስ ኢንጂል ላይ ያደረኩትን ይህንን ጥናት ለናንተ አቀርባለሁ፡፡ እግዚአብሔር አል–ኢንጂልን የላከልን ፈቃዱንና ትዕዛዛቱን በማወቅ የእምነትን ሕይወት እንድንኖር ነው፡፡ በፈጣሪ (ሱበሃነ ወተዓላ) በማመን መኖር ታላቅ ሕይወት ነው፡፡ እምነት በዚህ ምድር ላይ ስኬታማ የሚያደርገንና ትርጉም የሚሰጠን ነዳጅ ነው፡፡ ከዚህም በመነሳት ይህንን መጽሐፍ ለኛ ኡማ አበረክታለሁ፡፡ በችግር ውስጥ ላለው ዓለማችን በረከት ይሁን፡፡
አብደላህ (የአላህ አገልጋይ)
ፉአድ መስሪ
ምዕራፍ 1
መግቢያ
“ኢንጂል ተበርዟል” ሲባል ሰምታችሁ ይሆናል፡፡ ምናልባት እናንተም ተናግራችሁት ይሆናል፡፡
በመካከለኛው ምስራቅ ባሳለፍኳቸው ዘመናት አስተማሪዎቼና ተማሪ ጓደኞቼ ኢንጂልን ሲያጣጥሉ መስማት የተለመደ ነበር፡፡ ክርስቲያኖች ስለቀየሩት በዘመናት መካከል ትክክለኛ ይዘቱን አጥቷል ይላሉ፡፡
የሃይስኩል ተማሪ ሳለሁ ከማል የተባለ ጓደኛዬ ክርስቲያኖች ኢንጂልን ስለለወጡት ላነበው እንደማይገባ ነግሮኝ ነበር፡፡
ከማልን “ወንጌልን አንብበህ ታውቃለህን?” ብዬ ጠየኩት፡፡
“አላውቅም” በማለት መለሰልኝ፡፡
“ካላነበብከው ታድያ እንደተበረዘ እንዴት አወክ?” ብዬ ጠየኩት፡፡
“አያቴና አጎቴ ነግረውኛል” በማለት መለሰልኝ፡፡
ጉዳዩን ሳጣራ ኢንጂል እንደተበረዘ የተናገሩት እርሱ የጠቀሳቸው ዘመዶቹም መጽሐፉን እንዳላነበቡት ተረዳሁ፡፡
ወንጌል በአስተማሪዎቼና በጓደኞቼ ለምን እንደተናቀ፣ እንደተደበቀና እንደነውር እንደተቆጠረ እንዳጠና ያነሳሳኝ ይህ ሁኔታ ነበር፡፡
አስገራሚው ነገር ሙስሊሞች ወንጌልን አግኝተው የማንበብና የማመን ግዴታ እንዳለባቸው መረዳት መቻሌ ነው፡፡ ክርስቲያኖችም የመናገር ግዴታ አለባቸው፡ ፡ ጓደኞቼ ወንጌልን እንደ መጥፎ ዜና የሚቆጥሩት ሲሆኔ ክርስቲያኖች ግን እንደ መልካም ዜና እንደሚቆጥሩት ማወቅ ችያለሁ፡፡

የፈጣሪ መልእክት

ኢንጂል የኢየሱስ መጽሐፍ የአረብኛ ስያሜ ነው። የመጽሐፉ የመጀመርያው ስያሜ የሆነው ኢዋንጌሊዮን የሚለው የግሪከኛ ቃል መልካም ዜና የሚል ትርጓሜ አለው። በአረብኛ መጽሐፉ ኢንጂል ተብሏል።

ኢንጂል ኢየሱስ ክርስቶስን ለሚከተሉት ሰዎች የተሰጠ የፈጣሪ መልእክት ነው። ኢንጂል እያንዳንዱን የክርስቲያን ሕይወትና እምነት ይመራል።

ኢንጂል ሙስሊሞች ሊያምኗቸው፣ ሊከተሏቸውና ሊታዘዟቸው ከሚገቡ አራት መጻሕፍት መካከል አንዱ መሆኑን ኢማሞች ያስተምራሉ። እንደርሱ ከሆነ በብዙ እስላማዊ የመጻሕፍት መደብር ውስጥ ኢንጂልን ለምን አናገኘውም? ሙስሊሞች በኢንጂል ማመን ካለባቸው አንዳንድ እስላማዊ መንግሥታት ዜጎቻቸው እንዳያነቡት ስለምን ይከለክላሉ?

የከማል አጎት እንደተናገረው ኢንጂል ተለውጦ ይሆን? ራሴን ጠየኩት።

ሙስሊሞች ቁርአን አል-ከሪምን ጨምሮ ፈጣሪ ለሰው ልጆች የላካቸውን አል-ተውራት (የሙሴ መጽሐፍ)፣ አዝ-ዘቡር (የዳዊት መጽሐፍ)፣ እንዲሁም አል-ኢንጂል (የኢየሱስ መጽሐፍ) ማመን ይጠበቅባቸዋል።

አንድ ሰው እንዲህ አለኝ "ሙስሊሞች እነዚህን ሁሉ መጻሕፍት ማክበር ይጠበቅባቸዋል ነገር ግን ቁርአንን ብቻ እንከተላለን"። ኢንጂል በብዙ ሙስሊም አገራት ውስጥ የማይገኝበት ምክንያት የፖለቲካና የሃይማኖት መሪዎች እንደተበረዘ በማመናቸው ምክንያት ነው። ታህሪፍ የተሰኘ አይሁድና ክርስቲያኖች ቅዱሳት መጻሕፍታቸውን በርዘውታል የሚል አስተሳሰብን ይከተላሉ።

የተለመደው ማብራርያ የሚከተለው ነው፡-

1. አል-ተውራት (የሙሴ መጽሐፍ) ስለተበረዘ ፈጣሪ አዝ-ዘቡር (የዳዊትን መጽሐፍ) ላከ።
2. አዝ-ዘቡር ሲበረዝ ፈጣሪ ኢንጂልን ላከ።
3. በመጨረሻም አል-ኢንጂል ሲበረዝ ፈጣሪ አል-ቁርአን ከሪምን ላከ።
4. ቁርአን የፈጣሪ ቃል ስለሆነ ሊበረዝ አይችልም።

ይህ ኢ-አመክንዮአዊ አስተሳሰብ ነበር ስለ ኢንጂል እንዳናውቅ የተከለከልነው ምን እንደሆነ እንድመረምር ያነሳሳኝ። ኢንጂል በእውነት ተበርዟልን? ክርስቲያኖች ኢንጂልን ለውጠውታልን?

ኢንጂልን በማጥናት በግሌ ብረዛውን ለማጋለጥ ተነሳሳሁ። ለራሴ እንዲህ አልኩት፡- እውነታዎቹን ሳልመረምር ለምን በማሕበረሰቤ ትውፊት ላይ ብቻ እመሠረታለሁ? አብዛኞቹ ኢንጂልን አላነበቡትም ነገር ግን ያጣጥሉታል። ብዙዎች ምድር ክብ መሆኗን እውነታዎችን በማጥናት ከማረጋገጣቸው በፊት ዝርግ እንደሆነች አስበው ነበር። ነገሮች ብዙ ጊዜ መስለው ከሚታዩን የተለዩ ናቸው።

በማስከተል የሚገኘው ለፈጣሪ የተገዙ ሰዎች በሚጠይቁት ወሳኝ ጥያቄ ላይ ያደረኩት ጥናት ጭማቂ ነው፤ ኢንጂል ተበርዟልን?

ምዕራፍ 2

የቁርአን ምስክርነት

ቁርአን ስለ ኢንጂል ምን ይላል?

አል-ኢንጂል ከፈጣሪ ዘንድ የተላከ ነው
(ቁርአን 3፡2-4)
ሙስሊሞች ኢንጂልን ማንበብና ማመን ይኖርባቸዋል
(ቁርአን 2፡136
(ቁርአን 57፡27)
(ቁርአን 5፡68)
ፈጣሪ ቃሉን ይጠብቃል
(ቁርአን 2፡148)
ብዙ ኢማሞች ቀደም ሲል ከተጠቀሱት የቁርአን ጥቅሶች በተቃራኒ እንደሚያስተምሩ ስደርስበት በጣም ተገረምኩኝ። እንዲህ ይላሉ፡- አል-ተውራት (የሙሴ መጽሐፍ) ስለተበረዘ ፈጣሪ አዝ-ዘቡር (የዳዊትን መጽሐፍ) ላከ። አዝ-ዘቡር ሲበረዝ ፈጣሪ ኢንጂልን ላከ። በመጨረሻም አል-ኢንጂል ሲበረዝ ፈጣሪ አል-ቁርአን ከሪምን ላከ። ቁርአን የፈጣሪ ቃል ስለሆነ ሊበረዝ አይችልም።
ነገር ግን የእስልምና ቅዱስ መጽሐፍ የሆነው ቁርአን እንዲህ ያለ ነገር አይናገርም፡
፡
ምዕራፍ 3
ፈጣሪ እውነተኛ ይሁን
ኢንጂል ስለ ራሱ ምን ይላል?
ቁርአን የኢንጂልን አስፈላጊነት ይጠቁማል ነገር ግን ኢንጂል ስለ ራሱ አስፈላጊነት የሚናገረውን መመልከት ወሳኝ ነው። እግዚአብሔር ለአይሁድ፣ ለክርስቲያኖችና ለመላው የሰው ልጆች በኢንጂል ውስጥ ያስቀመጠውን ምክር ስሙ፡-
ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ ምንጫቸው እግዚአብሔር ነው
“የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።” (2ጢሞቴዎስ 3፡16-17)
“ይህን በመጀመሪያ እወቁ፤ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም፤ ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፥ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ።” (2ጴጥሮስ 1፡20-21)
የእግዚአብሔር ቃል ፀንቶ በመኖር ይፈፀማል
“እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም። እውነት እላችኋለሁ፥ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ፥ ከሕግ አንዲት የውጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም፥ ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ።” (ማቴዎስ 5፡17-18)
“ሰማይና ምድር ያልፋሉ፥ ቃሌ ግን አያልፍም።” (ማቴዎስ 24፡35)
የእግዚአብሔር ቃል ፀንቶ የሚኖርና ሕይወት ሰጪ ነው
“ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም፥ በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ።” (1ጴጥሮስ 1፡23)
እግዚአብሔር ቃሉን ይጠብቃል
“በዚህ መጽሐፍ የተጻፈውን የትንቢት ቃል ለሚሰማ ሁሉ እኔ እመሰክራለሁ፤

ማንም በዚህ ላይ አንዳች ቢጨምር እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ የተጻፉትን መቅሠፍቶች ይጨምርበታል፤ ማንምም በዚህ በትንቢት መጽሐፍ ከተጻፉት ቃሎች አንዳች ቢያጎድል፥ በዚህ መጽሐፍ ከተጻፉት ከሕይወት ዛፍና ከቅድስቲቱ ከተማ እግዚአብሔር ዕድሉን ያጎድልበታል።" (ራዕይ 22፡18-19)

እግዚአብሔር ቃሉን እንደሚጠብቅ የሚናገረው ኢንጂል ብቻ ሳይሆን ዘቡርና ተውራትም ጭምር ናቸው።

ከተውራት

"ከእነርሱ ጋር ያለው ቃል ኪዳኔ ይህ ነው ይላል እግዚአብሔር፤ በአንተ ላይ ያለው መንፈሴ በአፍህም ውስጥ ያደረግሁት ቃሌ ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ ከአፍህ ከዘርህም አፍ ከዘር ዘርህም አፍ አያልፍም፥ ይላል እግዚአብሔር።" (ኢሳይያስ 59፡21)

በእርግጥ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ቃል ካለመታዘዝና ከመለወጥ ይልቅ ሞታቸውን ይመርጣሉ።

ከክርስቶስ ትንሣኤ በኋላ ተከታዮቹ ከቦታ ወደ ቦታ በመዞር እርሱ የሰው ልጆች ሁሉ አዳኝ እንደሆነ ያውጁ ነበር። የአይሁድ መሪዎች ቃላቸውን አልተቀበሉም፤ ሮማውያንና አረማውያን ነገሥታትም የኢየሱስ ተከታዮች በሚሰብኩት ስብከት ያላግጡ ነበር።

በክርስትና የመጀመርያዎቹ ሦስት መቶ ዓመታት ክርስቲያኖች በእምነታቸው ምክንያት ይጨፈጨፉ፣ ይጠቁና ይሠቃዩ ነበር። ሰላማዊያንና ንፁሃን ሰዎች ሆነው ሳሉ ክርስቶስ እንደ ዓለም አዳኝ በማመናቸው ብቻ ፍትሃዊ ያልሆነ ግፍ ይፈፀምባቸው ነበር። በብዙ ሁኔታዎች እነዚህ የክርስትና እምነት ሰማዕታት አሳዳጆቻቸው ክርስትናን እንዲቀበሉ ምክንያት ሆነው ነበር።

የመጀመርያዎቹ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ቃል እውነት እንደሆነ ያምኑ ነበር፤ ካለፉት ጥቅሶች በመነሳት እግዚአብሔር ሃያል የሆነ የአፅናፈ ዓለም ፈጣሪ በመሆኑ ኢንጂልን ለመጠበቅ የገባውን ቃል የመጠበቅ ኃይል እንዳለው ያምኑ ነበር።

ምዕራፍ 4

ከሃያሉ ፈጣሪ በላይ ኃይል ያለው የለም

ሥነ መለኮታዊ ምርመራ

በፈጣሪ እንሚያምን ሙዕሚን የፈጣሪ ቃል በሰዎች መለወጥ መቻሉ ሊገባኝ ያልቻለ ጉዳይ ነበር። ፈጣሪ ኢንጂልን ከገለጠ እርሱን የመጠበቅ ኃላፊነት የእርሱ አይደለምን? ብዬ ራሴን ጠይቄያለሁ። እግዚአብሔር የአፅናፈ ዓለም ፈጣሪ መሆኑን እናውቃለን፤ ጸሐይ፣ ከዋክብት፣ ጨረቃ፣ ሁሉም በእርሱ ተፈጥረዋል። እርሱ ሰዎችን፣ አእምሯቸውንና ዕውቀታቸውን ፈጥሯል። እግዚአብሔር ልብን የሚመረምር የሼኮችንና የዜጎችን፣ የነጋዴዎችንና የእረኞችን፣ የሳይንቲስቶችንና የአርቲስቶችን የልብ ሐሳብ የሚያውቅ አምላክ ነው። የእርሱ ዕውቀት የጊዜ ክፍሎችንና ዘመናትን ተሻጋሪ ነው። ያለፈውን፣ የአሁኑንና መፃዒውን የሚያውቅ አምላክ ነው። እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው!

ሰዎች ከፈጣሪ ይልቅ ሃያላን ናቸውን?

ፈጣሪ ቃሉን ለሰው ልጆች ከገለጠና የሰው ልጆች ቃሉን መበረዝ ከቻሉ ያ የሰው ልጆችን ከፈጣሪ በላይ ሃያላን አያደርጋቸውምን? የማይሆን ነው!

የፈጣሪ ቃልና መልእክት እንደተበረዘ ካመንኩኝ ሃያሉ ፈጣሪ (ሱብሃነ ወተዓላ) ሳይሆን እንደ እኔ ያለ ተራ ሰው የሁሉም ነገር መለኪያ ይሆናል ማለት ነው፡፡
ፈጣሪ ኢንጂልን የላከው ሰዎች እውነት እንዲበራላቸው ነው፤ ኢየሱስም እውነት ነፃ እንደሚያወጣን ተናግሯል፡፡ ሰዎች ከፈጣሪያቸው ይልቅ በምንም ተዓምር ብርቱዎች አይደሉም! ኢንጂል የፈጣሪ ቃል በመሆኑ በፍፁም ሊበርዙት አይችሉም፡፡
ኢየሱስ ስለ ፈጣሪ ቃል የነበረው እሳቤ
በእስልምና መሠረት ኢየሱስ ክርስቶስ የፈጣሪ ተወዳጅ ነቢይ ነው (ሐቢብ አላህ)፡፡
በእርግጥ እርሱ ከፍጥረት በፊት ዓለምን ይዋጅ ዘንድ (አል ፋዲ) የተመረጠ ነው (ሙስጠፋ አላህ)፡፡
በኢንጂል ውስጥ ኢየሱስ በቢሸረት ማርቆስ ምዕራፍ 13 አያ 31 ላይ እንዲህ አለ፡- “ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን አያልፍም፡፡”
በተጨማሪም በ 2ጢሞቴዎስ 3፡16 ላይ ኢንጂል ሁሉም ቅዱሳት መጻሕፍት የእግዚአብሔር መንፈስ እንዳለባቸው ይናገራል፡፡ እርሱ ነው የገለጣቸው ስለዚህ የእርሱ ናቸው፡፡
ኢንጂል ከየት እንደመጣ በግልፅ ይናገራል፡-“ይህን በመጀመሪያ እወቁ፤ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም፤ ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፣ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ፡፡” (2ጴጥሮስ 1፡20-21)
ፈጣሪን እንመን ሰውን እንጠራጠር
በሃያሉ ፈጣሪ ላይ ያለኝ እምነት ኢንጂል እንደተበረዘ የሚናገሩትን እነዚያን የሃይማኖት መምህራን እንድጠራጠር አድርጎኛል፡፡ አስቶፉሩላህ! የፈጣሪ ቃል እኔን በመሳሰሉ ፍጡራን ሰዎች ከመበረዝ የረቀ ነው፡፡
ኢንጂል እንደተበረዘ በተናገሩ ቁጥር ፈጣሪን እየተሳደቡ ነው፡፡ ፈጣሪ ኢንጂልን የላከ ሲሆን በሁሉም ላይ ሥልጣን አለው፤ ኢንጂልን በሰው ልጆች ሁሉ ላይ መስካሪ ይሆን ዘንድ ይጠብቀዋል፡፡
ፈጣሪ ፍትሃዊ ነው፤ ሰዎች ለኢንጂል መልእክት በሰጡት ምላሽ ላይ ተመሥርቶ ፍትሃዊ የሆነ ፍርድ ይሰጥ ዘንድ ቃሉን ይጠብቃል፡፡
ማንም ሊያበላሸው አይችልም፡፡ ፈጣሪ ሊጠብቀው ቃል ገብቷል፡፡ ማንም ሰው ደግሞ ከፈጣሪ በላይ ሃያል አደለም፡፡
ምዕራፍ 5
ምናባዊ አስተሳሰብና እውነታ
ሥነ አመክንዮአዊ ምርመራ
እውነት ሐሰትን ድል ነስታ ትቆማለች! እግዚአብሔር ለእርሱና ለተስፋዎቹ ባለን አክብሮት ላይ ብቻ ተመሥርተን ሳይሆን አመክንዮና የማሰብ ችሎታችንን በመጠቀም ጭምር እውነትን እንድናውቅ ይፈልጋል፡፡
እኛ የሰው ልጆች መረጃዎቻችን በምንሰበስብበት፣ በምናብላላበት፣ ድምዳሜ ላይ በምንደርስበትና ለሌሎች በምናስተላልፍበት መንገድ ከሌሎች ፍጡራን እንለያለን፡፡ የማሰብ ችሎታችን እውነትን የሚፃረር አይደለም፤ ይልቁኑ ያረጋግጠዋል፡፡ እግዚአብሔር ማሰብ የሚችል አእምሮ ከሰጠኝ የቃሉን እውነት

መሆን ለማረጋገጥ ይህንኑ የማሰብ ችሎታዬን መጠቀም ይችላል።
ከዚህ ሐሳብ በመነሳት የኢንጂልን መበረዝ ከአመክንዮ አንፃር ልመረምር ተነሳሁ፡፡ ምናልባት ፈጣሪ እኔ ያሰብኩትን ያህል ኃይል የሌለው ይሆን? (አስቶጉፍሩላህ)። ተከታዮቹ ወሳኝ ጥያቄዎችና መልሶቻቸው የጥናቴ ውጤቶች ናቸው። ፈጣሪ ቃሉ የሆነውን ኢንጂልን የመጠበቅ ችሎታውን በመጠራጠሬ አስቀድሜ ይቅርታ እጠይቃለሁ።
ሰባት ወሳኝ ጥያቄዎች
1. ኢንጂልን ማን ለወጠው?
ኢንጂል ይለወጥ ዘንድ ይህንን ሴራና ተንኮል የሚፈፅሙ ሰዎች በታሪክ ውስጥ መገኘት ይኖርባቸዋል።
ከፈጣሪ ዘንድ የተላከውን መገለጥ ለመለወጥ አልሞ ጊዜውንና ጉልበቱን ይህንን ለመሰለ ተግባር የሚያውል ሰው ማን ነው? በፈጣሪና በክርስቲያኖች ላይ ክህደትን በመፈፀም ኢንጂልን የሚበርዝ ሰው ምን ዓይነት ነው?
ይህ ብረዛ በእግዚአብሔር ፍትሃዊ ፍርድና በክርስቶስ አዳኝነት በሚያምን ክርስቲያን ተፈፅሞ ይሆን? ወይንስ ይህንን ተግባር የፈፀመው አረማዊ ወይንም አይሁድ ቀናተኛ ይሆን?
እንዲህ ያለ ከሃዲ ኖሮ ቢሆን ኖሮ በኢንጂል ላይ የጨመረውንና የቀነሰውን ይህንን ሰው ታሪክ ባጋለጠው ነበር።
2. ኢንጂል ስለምን ነበር የተለወጠው?
እንዲህ ያለ ሰው ኢንጂልን ስለምን ይለውጣል? ኢንጂል የፈጣሪን መኖር የሚገልጥና ፈጣሪ ለዓለም ያለውን ውብ ዕቅድ የያዘ መጽሐፍ ከሆነ አንድ ሰው ያንን የመሰለ መገለጥ ለመለወጥ ምን ያነሳሳዋል?
ኢንጂል ተለውጦ ቢሆን ኖሮ ፈጣሪ ጥንታዊያኑ ክርስቲያኖች ለስድስት መቶ ዓመታት ያህል የእርሱን ፈቃድ ባለማወቅ እንዲኖሩ ስለምን ፈቀደ? (ኢንጂል ተበረዘ በተባለበት ጊዜና በእስልምናው ነቢይ መምጣት መካከል ላለው ዘመን)። ሰዎች የፈጣሪን ፈቃድ ለማወቅ ሁሌም ፍለጋ እንዳደረጉ ነው። ይህንን የመሰለ አስተሳሰብ ዋጋ ማሳጣት ለምን አስፈለገ?
3. ኢንጂል የት ሀገር ነበር የተለወጠው?
በየትኛው ከተማ ወይንም በየትኛው ቦታ ነበር ኢንጂል የተለወጠው? ብረዛው የተፈፀመው በፖለቲካ ወይንስ በሃይማኖት ማዕከል? ኢንጂል ስጋት የሆነባቸው የትኞቹ መንግሥታት ናቸው?
ሮም፣ ቢዛንቲን፣ ኢየሩሳሌም፣ እነዚህ ሁሉ ከተሞች የሃይማኖት ማዕከላት ነበሩ፡፡ እነዚህ ሁሉ ከፈጣሪ በላይ ኃይል ኖሯቸው ይሆን? ኦሪጂናል ኢንጂልን አግኝተን ተበረዘ ከተባለው ጋር ማነፃፀር እንችል ይሆን?
4. ኢንጂል መቼ ነበር የተለወጠው?
በታሪክ በየትኛው ዘመን ነበር ኢንጂል የተለወጠው? በክርስትና ትውፊት መሠረት ክርስቶስ የተሰቀለው 30ኛ ዓመቱ አካባቢ ሲሆን ክስተቱ በ 29 ዓ.ም. እስከ 33 ዓ.ም. መካከል ነበር።
ከክርስቶስ በኋላ ለሦስት መቶ ዓመታት ያህል ክርስቲያኖች ክፉኛ ይሰደዱ ነበር። ይህ ደግሞ ቁልፍ ጥያቄ እንድናነሳ ያደርገናል።
5. የኢንጂል ብረዛ የተፈፀመው ከመሐመድ መምጣት በፊት ነው ወይንስ በኋላ?

ነቢዩ ሙሐመድ ሙስሊሞች ሁሉ ኢንጂልን እንዲያነቡ ስላዘዙ የተበረዘው ከእሳቸው ዘመን በኋላ መሆን አለበት። የተበረዘ መጽሐፍ እንድናነብ ስለምን ያዝዙን ነበር?
በሌላ ወገን ደግሞ ኢንጂል በእሳቸው ዘመን ወይንም ከእሳቸው ዘመን በፊት ተበርዞ ቢሆን ኖሮ ያንን በነገሩን ነበር። ከዚያ በኋላ ተበርዞ እንደሆን በታሪክ የኋሊት በመሄድ ማግኘት ይኖርብናል።
6. የትኞቹ ክፍሎች ናቸው የተበረዙት?
ብዙ ኢማሞች ኢንጂል መበረዙን ይናገራሉ ነገር ግን የትኞቹ የኢንጂል ክፍሎች እንደተበረዙ ሊነግሩኝ አልቻሉም።
ብረዛው የከፋ በመሆኑ ሁሉንም የኢንጂል ክፍሎች ለውጦ ይሆን? ከሆነ የወንጌልን መልእክት በማንበብ የሚገኝ ጥቅም ይኖራልን? ሁሉም ተበርዞ ከሆነ ቁርአን በእርሱ እንድናምንና እንድናነበው ስለምን ይናገራል?
ምናልባት የተወሰነ የኢንጂል ክፍል ብቻ ተለውጦ ይሆናል። እንደርሱ ከሆነ እውነቱን ከስህተት መለየት የምችለው እንዴት ነው? ፈጣሪ የተወሰነውን ክፍል ጠብቆ የተቀረውን መጠበቅ ተስኖት ይሆን?
7. ኦሪጅናል ጽሑፉ የት ነው የሚገኘው?
ይህ ለኔ ቁልፍ ጥያቄ ነበር። ሁሉም አሓዳውያን ሃይማኖታት የናዝሬቱ ኢየሱስን መምጣት ያረጋግጣሉ። ስለዚህ እውነተኛው ኢንጂል የት ነው የሚገኘው? ፈጣሪን እንደሚፈራ ሰው የፈጣሪን ትዕዛዝ በማክበር ኢንጂልን አግኝቼ ማጥናትና ማክበር ይኖርብኛል። ዋናው ኢንጂል ከጠፋ ፈጣሪዬን ታዝዤ ኢንጂልን ማንበብ የምችለው እንዴት ነው? ፈጣሪ እንዲህ ያለውን ውጥንቅጥ ይፈቅዳልን?
ፈጣሪ ኢየሱስንና ኢንጂልን ለሰው ልጆች በትውልዶች ሁሉ ብርሃን እንዲሆኑ ስለላካቸው ሃይማኖታዊ ግዴታዬን ለመወጣት ኦሪጅናሉን ኢንጂል አግኝቼ ማንበብ ይኖርብኛል።
የመጨረሻው መገለጥ
አንድ በተደጋጋሚ የሰማሁት ሙግት ትኩረትን ይስባል። አንዳንድ ሙስሊም ሊቃውንት እስልምና ኋላ ላይ የመጣ ሃይማኖት በመሆኑ በኢንጂል ውስጥ የሚገኙትን ስህተቶችና ስለ ፈጣሪ የሚያቀርባቸውን የተሳሳቱ አመለካከቶች እንዳረመ ይናገራሉ።
ይህንን ሐሳብ ለመደገፍ የሚጠቀሰው የቁርአን ጥቅስ 16፡101-102 ላይ የሚገኘው ነው።
የቁርአን መልእክት መጨረሻ ላይ የመጣ ቢሆንም መልእክቱ አረማውያንን ወደ አንዱ እውነተኛ አምላክ ይጠራ ከነበረው ከአብርሃም መልእክት ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ ተነግሯል።
ቁርአን ለሙሐመድ በተሰጠበት ጊዜ አንዱን አምላክ የሚያመልኩ ሰዎች ለሙሴ በተሰጠው ቃል (ተውራት)፣ ለዳዊት በተሰጠው ቃል (ዘቡር) እና ለዒሳ በተሰጠው ቃል (ኢንጂል) ተመርተዋል።
ነቢዩ አብርሃም (ኢብራሂም) የቤተሰቦቹን ጣዖታት በመተው ወደ አንዱና እውነተኛው አምላክ በመመለስ የመጀመርያው ነበር። ቤተሰቦቹን ከአረማውያን ምድር ፈጣሪ ወዳሳየው ምድር መርቶ ነበር።

ለሙሴ (ሙሳ)፣ ለዳዊት (ዳውድ) እና ለኢየሱስ (ዒሳ) የተሰጡት መልእክቶች ግን ለተለዩ አድማጮች የተሰጡ ነበሩ – አንዱንና እውነተኛውን አምላክ ለሚያመልኩ ሰዎች። ስለዚህ በተውራት፣ ዘቡርና ኢንጂል ውስጥ የሚገኘው የፈጣሪ መልእክት በአሓዳዊነት መልእክት ላይ የተገነባ ሲሆን የበለጠ ጥልቅ የሆኑ ነገረ መለኮታዊ ፅንሰ ሐሳቦችን፣ ስለ ፈጣሪ ይበልጥ የጠለቁ መረዳቶችንና ለኑሮ ተግባራዊ የሆኑ መመርያዎችን የያዘ ነው።

የፈጣሪ መገለጥ ወደ ድምዳሜ የመጣቸው የፈጣሪ ቃል በሆነው በኢየሱስ (ዒሳ ኢብን መርየም) ነው። የእርሱ መልእክት ሀገር፣ ዘርና ቋንቋ ሳይለይ ለሁሉም የሰው ልጆች የመጣ ነው።

“እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።” (ማቴዎስ 29፡19-20)

“እላችኋለሁም፡ ብዙዎች ከምሥራቅና ከምዕራብ ይመጣሉ ከአብርሃምና ከይስሐቅ ከያዕቆብም ጋር በመንግሥተ ሰማያት ይቀመጣሉ።” (ማቴዎስ 8፡11)

“አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፥ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፥ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና።” (ገላቲያ 3፡28)

ቁርአን የቀደሙትን መገለጦች እንደተካ አልተናገረም

በአንፃሩ ቁርአን አሓዳዊነትን በመካድ መድብለ አማልክትን ወደሚከተሉት አረቦች የመጣ መጽሐፍ ነው። ይህ አል-ጃህሊያ ወይንም የድንቁርና ዘመን በመባል የሚታወቀው ነው። ለአረብ ሰዎች እንደ ማንቂያ የመጣ መልእክት ነበር። ለዚህ ነው ቁርአን ቋንቋው አረብኛ የሆነው ለአረቦች እንዲገባቸው በማለም እንደሆነ የሚናገረው፡-

(አዝ-ዙክሩፍ 43፡3)

በተጫማሪም ቁርአን መልእክቱ የቀደሙትን መለእክቶች እንደሚያረጋግጥ በተደጋጋሚ ይናገራል፤ የቀደሙትን መልእክቶች እንደተካ አይናገርም።

(አል-ማዒዳህ 5፡48)

የፈጣሪን ቃላት መለወጥ?

አንዳንድ ሙስሊሞች ክርስቲያኖች የፈጣሪን ቃል እንደለወጡት ለማመልከት ተከታዩን የቁርአን ጥቅስ ይጠቅሳሉ፡-

(አል-በቀራ 2፡146)

(አል-ኢምራን 3፡71)

(አል-በቀራ 2፡159)

ከላይ የተጠቀሱት ጥቅሶች የፈጣሪን ቃል ስለለወጡ ሰዎች ሳይሆን ስለደበቁት ግለሰቦች የሚናገሩ ናቸው። ፈጣሪ ከሰዎች ይልቅ ሃያል ነው። ሰዎች ቃሉን ለመደበቅ ቢሞክሩም የእርሱ እውነት ውሸትን ድል ነስታ ትቆማለች።

እውነትን መፍራት

ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ጥናት ሳደርግ በማሕበረሰቤ ውስጥ የሚገኙት የሃይማኖት መሪዎች በእጅጉ ዕውቀት የጎደላቸው መሆኑን ተገንዝቤያለሁ። ጥያቄዎችን የሚፈሩ ይመስላሉ። እነዚህን ሐሳቦች መወያየት ክልክል ነው።

ጥያቄዎችን መጠየቅ ስጀምር ከሃይማኖቴ እንዳፈነገጥኩ ነበር የተቆጠርኩት፡
፡ ለምንድነው ኢንጂልን የማላነበው? ብዬ ራሴን ጠየኩት።
አንዳንድ የሃይማኖት መሪዎች ብረዛውን ዘመናትን፣ ክስተቶችንና ቦታዎችን በመጥቀስ ለማረጋገጥ ሲሞክሩ ሰምቻለሁ ነገር ግን ብሒሎቻቸውን በጥልቀት ሳጠና ስለ ኢየሱስ ሕይወትና ስለ ኢንጂል እንዲሁም ስለ ክርስትና ታሪክ የነበራቸውን የዕውቀት ጉድለት ማስተዋል ቻያለሁ።
ጓደኞቼ እውነትን ለመፈለግ አደርግ የነበረውን ጥረት ይቃወሙ ነበር። ከዲስ ኪዳንን ለምን እንደማጠና በተደጋጋሚ ጥያቄ ቀርቦብኝ ለጥቃት ተዳርጌያለሁ።
ይህ ሁሉ ተቃውሞ ለምን? ኢንጂልን በመመልከት ጥሩ አማኝ ለመሆን ጥረት እያደረኩ ብቻ ነበር። አመክንዮአቸው ከባሕርያቸው የከፋ ነበር። ፈጣሪያቸውን የሚጠሙ ሳይሆኑ ደም የሚጠሙ ነበሩ።
በዚህ ጊዜ ጥናቴ የአዲስ ኪዳንን ታሪካዊ ማስረጃና ክርስቲያኖች ለምን እንደሚከተሉት ወደ መመርመር መራኝ።

ምዕራፍ 6

የእጅ ጽሑፎች ይናገራሉ

ታሪካዊ ምርመራ

መልስ ለማግኘት ያደረኩት ጥረት የአዲስ ኪዳንን ታሪካዊ ዳራና የእጅ ጽሑፎች ወደማጥናት መራኝ።
ኢንጂል በክርስቲያኖች ዘንድ በእጅጉ እንደሚከበር ማወቅ ቻልኩኝ። ከብረዛ እርሱን ለመጠበቅ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል። የኢንጂል ታሪክ በሦስት ታሪካዊ ክፍሎች ሊከፈል ይችላል።
ሀ. የዐይን ምስክሮች ደረጃ
ለ. የስደት ደረጃ
ሐ. የትርጉም ደረጃ

ሀ. የዐይን ምስክሮች ደረጃ (0-100 ዓ.ም.)

ኢየሱስ ተዓምራዊ በሆነ ሁኔታ ከድንግል ማርያም ተወለደ። ልደቱ ኢሳይያስን በመሳሰሉት ነቢያት አስቀድሞ ተነግሮ ነበር።
ከድንግል ስለመወለዱ አስቀድሞ ተነግሯል
(ኢሳይያስ 7፡14)
የሚወለድበት ከተማ አስቀድሞ ተነግሯል
(ሚክያስ 5፡2)
ቀድም ሲል በተጠቀሱት ጥቅሶች ውስጥ እንደተመለከታችሁት የነቢዩ ዒሳ (ኢየሱስ የማርያም ልጅ) ልደት በመቶዎች ከሚቆጠሩት ዓመታት በፊት አስቀድሞ ተነግሯል። መሲሁ ሰዎችን ወደ ፈጣሪ እውነት ለመምራት እንደሚመጣ ተውራት በግልፅ ይናገራል።
(ዮሐንስ 1፡41)
ይህ ኢየሱስ ኃጢአት የሌለበትና የብዙ አማኞች መሪ ነበር። ሙታንን አስነስቷል የታመሙትን ፈውሷል። የእርሱ ትምህርትና ቃላት በአል ኢንጂል ውስጥ ተመስዝግበዋል።
አል ኢንጂል የሚለው ቃል ኢዋንጌሊዮን የሚለውን የግሪክ ስያሜ ተክቶ የገባ የአረብኛ ቃል ነው። ኢየሱስና ተከታዮቹ የሮማ ኢምፓየር መግባቢያ የነበረውን

ኮይኔ ግሪክ ይናገሩ ነበር። በተጨማሪም ምሁራን የተስማሙበት ነገር ቢኖር ኢየሱስ ኮይኔ ግሪክ፣ አረማክና እብራይስጥ ይናገር እንደነበር ነው።

የእጅ ጽሑፎች

በአሁ ወቅት የየትኛውንም ሃይማኖት ኦሪጅናል ጽሑፍ ያገኘ ሰው የለም። የቁርአን አል ከሪም ኦሪጅናል ጽሑፍ ኮፒ የለንም። የኡሥማን ቅጂም ቢሆን የለንም። እንደዚሁም የተውራት፣ ዘቡርና ኢንጂል ኦሪጅናል ጽሑፎች በእጃችን አይገኙም። ነገር ግን ኮፒ በማድረግ ከትውልድ ወደ ትውልድ ያስተላለፍናቸው ኮፒዎች አሉን።

ሊቃውንት ኢንጂል ለሰው ልጆች ብርሃን እንዲሆን የተላከ የፈጣሪ ቃል በመሆኑ በእጅ በመገልበጥ ሲጽፉ በታላቅ ጥንቃቄ ነበር።

(ራዕይ 22፡18-19)

በኢንጂል ውስጥ ለሚገኙት ክስተቶች የዐይን ምስክሮች

የኢየሱስን ልደት፣ ሞትና ትንሣኤ የተመለከቱ የዐይን መስክሮች ባሉበት ሁኔታ የኢየሱስን አስተምህሮም ሆነ ባሕርይ በተሳሳተ መንገድ ማቅረብ ተቀባይነትን ሊያገኝ አይችልም። እነዚህ ሰዎች እውነቱን ያውቃሉ።

(ሉቃስ 1፡1-3)

(2ጴጥሮስ 1፡16)

እነዚህ የዐይን ምስክሮች የተመለከቱትን ነገር በትክክል ስለመዘገባቸው እርግጠኞች መሆን እንችላለን። እነርሱ የጻፉት በጥርጣሬ ሊታይ አይችልም፤ ተሳስተው ቢሆን ኖሮ ክስተቶቹን የተመለከቱ ሌሎች ሰዎች ባረሟቸው ነበር። በተመሳሳይ፤ የክርስቶስ ተከታዮች ከመጀመርያው ጀምሮ ቃሉን በተሳሳተ መንገድ ጽፈውት ቢሆን ኖሮ ኢንጂልና ክርስትና ገና ከጅምሩ ባልኖሩም ነበር።

ፈጣሪ ኢንጂልን እንደላከ የምናምን ከሆነ፤ አስቀድሞ በትክክል እንዲጻፍና እንዲገለበጥ ማረጋገጡንም ማመን ያስፈልገናል። ይህ ባይሆን ኖሮ ሰዎች በውስጡ በተጻፈው ነገር ሊፈረድባቸው ባልቻለም ነበር። የእግዚአብሔር ፍርድ ትክክለኛና ፍትሃዊ ይሆን ዘንድ የእርሱ መገለጥ ትክክለኛና ከስህተት የጸዳ ሊሆን ይገባዋል።

በዐይን ምስክሮች ደረጃ መጽሐፍ ቅዱስን ለመበረዝ የሚያስችል ሁኔታ አልነበረም ምክንያቱም የዐይን ምስክሮች በሕይወት ነበሩና። በሕይወት የነበሩና ታሪኩን የሚያውቁ ሰዎች – አማኞች ቢሆኑም ባይሆኑም – በታሪኩ ላይ የተደረገ ለውጥ ቢኖር ኖሮ በተቃወሙ ነበር።

ለምሳሌ ያህል ጆን ኤፍ ኬኔዲ እንዳልተገደለ ወይንም ማርቲን ሉተር ኪንክ "ህልም አለኝ" የሚለውን ታዋቂ ንግግሩን አለማድረጉን ወይንም የአሜሪካ ጠፈርተኞች ጨረቃን አለመርገጣቸውን ብጽፍ፤ ሰዎች የተሳሳተ ታሪክ መጻፌን በመግለፅ ይቃወማሉ።

የጆን ኤፍ ኬኔዲን መገደል የተመለከቱ፣ የኪንግን ንግግር የሰሙ እንዲሁም ጨረቃን የረገጡት ምስክሮች አሁንም ድረስ አሉ። ከ50 እስከ 100 ዓመታት ባሉት መካከል ሰዎች መጽሐፌን ሊገዙ ይችላሉ ነገር ግን የዐይን ምስክሮች በሕይወት እስካሉ ድረስ ዋና ዋና ታሪካዊ ክስተቶችን መካድም ሆነ መፍጠር አይቻለኝም። በኢንጂል ውስጥ የሚገኙትም ዋና ዋና ክስተቶች ተመሳሳይ ናቸው። በዐይን ምስክሮች ዘመን ታሪካዊ ክስተቶችን አጨቃጫቂ ሊያደርግ የሚችል የለም።

የዐይንምስክሮችበሕይወትኖረውየአዲስኪዳንንተዓማኒነትከመመስከራቸውም በተጨማሪ ሌሎች ሁለት እውነታዎች የአዲስ ኪዳንን ተዓማኒነት ያረጋግጣሉ። እነርሱም ሰማዕታትና የክርስቶስ ትንሣኤ ማረጋገጫዎች ናቸው።

1. ራሱ ለፈጠረው ውሸት ሰማዕት የሚሆን የለም

ብዙ ጊዜ ሰዎች ለግል ጥቅም ሲሉ ወይንም አሳፋሪ ገጠመኞቻቸውን ለመደበቅ ሲሉ ሊዋሹ ይችላሉ። የነቢዩ ኢየሱስ ብዙ ተከታዮች ኢየሱስ ከሞት የተነሣ መሲሁ መሆኑን በመመስከር ሰማዕታት ሆነዋል።

2. ኢየሱስ በመቃብር ውስጥ መቅረቱን የሚያመለክት ምንም ዓይነት ማስረጃ የለም

ክርስቶስን ይቃወሙት የነበሩት የዓይን ምስክሮች ትንሣኤውን ውድቅ ለማድረግ የኢየሱስን አስከሬን ከመቃብሩ በማውጣት ማሳየት ይችሉ ነበር። ማድረግ ቢችሉ ኖሮ ያንን ማድረጋቸው ግድ ነበር!

የኢንጂል ሁኔታ ይህንን ይመስላል። የዓይን ምስክሮች ደረጃ ከኢየሱ ልደት አንስቶ 100ዓ.ም. ላይይጠናቀቃል።የኢየሱን ሕይወት፣ሞትናትንሣኤየተመለከተየዐይን ምስክር ከ100 ዓ.ም. በኋላ ሊኖር አይችልም። የዓይን ምስክሮች ማሕበረሰብ የኢየሱስ ተከታዮች ሆኑም አልሆኑም በ100 ዓ.ም. ላይ ሞተው አልቀዋል።

የመጨረሻው የዐይን ምስክ 100 ዓ.ም. አካባቢ ከሞተ በኋላ የፈጣሪን ቃል የመለወጥ የመጀመርያው አጋጣሚ ይፈጠር ነበር። አንድ ከሃዲ የፈጣሪን ቃል መለወጥ ቢፈልግ ዕድል ያገኛል።

ለ. የስደት ደረጃ (100 ዓ.ም. – 325 ዓ.ም.)

በዚህ ደረጃ ክርስቲያኖች በየቦታው ይሰደዱ ነበር። የአይሁድ መሪዎች በየቦታው ጥቃት ይፈፅሙባቸውና ይገድሏቸው ነበር። ሮማውያ በመድብለ አማልክቶቻቸው ስለማያምኑ እንደ አምላክ የለሾች ይቆጥሯቸው ነበር። ሮማውያን እንደ ስጋት ይቆጥሯቸው ስለነበር በየቦታው እንገደሉና ከነመጻሕፍታቸው እንዲቃጠሉ አዘዙ።

በዚህ የስደት ዘመን ለውጦች በኢንጂል ላይ መፈፀማቸው የማይሆን ነበር። በዚህ ወቅት የአዲስ ኪዳንን ተዓማኒነት የሚያረጋጡት አራቱ ነገሮች የሚከተሉት ናቸው:-

1. የእጅ ጽሑፎች
2. በአበው ጽሑፎች ውስጥ የተጠቀሱት ጥቅሶች
3. ቀዳሚያን ትርጉሞች
4. የቤተክርስቲያን አበው

እያንዳንዱን ማስረጃ አንድ በአንድ እንመልከት

1. የእጅ ጽሑፎች

የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በፓፒረስ ላይ በእጅ ይገለበጡ ነበር። ፓፒረስ በምድረ ግብፅ የሚበቅል እፅዋት ነበር። ግብፃውያን ወረቀትን ከፓፒሪ በፈጠሩ ጊዜ ሒሮግሊፊክስ ለመጻፍ የተለያዩ ቀለማት ጥቅም ላይ ይውሉ ነበር።

አጭር ታሪክ

ፊኒሻኖች የግብፃውያንን ግኝት በመቅዳት ፊደላትን ተጠቅመው በመጻሕፍት መልክ ዕውቀትን ለሌላው ዓለም ያሸጋግሩ ነበር። ቀዳሚያን ክርስቲያኖች የእጅ ጽሑፎች ሲያረጁ ወይንም አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት ሲመሠረቱ ኢንጂልን

በእጅ ይገለብጡ ነበር። የመጨረሻው ደቀ መዝሙር ወደ ፍጥሞ ደሴት በግዞት ተወስዶ ከሞተ በኋላ ክርስቲያኖች የኢንጂልን ጽሑፎች በታደሰ ስሜት በመገልበጥ ለአብያተ ክርስቲያናት ያሰራጩ ነበር።
የክርስቲያን ማሕበረሰብ አብዛኞቹ አባላት አጠቃላዩን አዲስ ኪዳን ኮፒ የማዘጋጀት አቅም አልነበራቸውም። ከዚህ የተነሳ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ገሚስ ቅጂዎች በመዘጋጀት ይሰራጩና ክርስቲያኖች ይቀባበሏቸው ነበር።
ሌሎች የገሚስ የእጅ ጽሑፎች ዓይነቶች በክርስቲያኖች ቤቶችና በአብያተ ክርስቲያናት ፍርስራሾች ውስጥ የተገኙት ናቸው። እነዚህ ገሚስ ቅጂዎች የተገመሱት በዕድሜ ወይንም በአደጋ ምክንያት እንጂ መጀመርያ እንደርሱ ስለነበሩ አይደለም።
ከ100 – 325 ዓ.ም. መካከል የሚገኙት ገሚስ ቅጂዎች አጠቃላይ የኢንጂል መጻሕፍት፣ የኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ ዘገባዎች፣ የኢየሱስ ልዩ መሆን ዘገባዎችና የቤዛነት ሞቱን የሚገልፁ ናቸው።
2. የቤተክርስቲያን ጥቅሶች (ሌክሽነሪዎች)
የቤተክርስቲያን ሌክሽነሪዎች መገኘት የአዲስ ኪዳንን ተዓማኒነት ከሚያረጋግጡ ታላላቅ ማስረጃዎች መካከል አንዱ ቢሆንም ጥልቅ ጥናቶች ካልተደረጉባቸው ጉዳዮችና በአነስተኛ ሁታ ጥቅም ላይ ከዋሉት ሙግቶች መካከል አንዱ ነው።
ሌክሽነሪዎች ለቤተክርስቲያን ዓመት እያንዳንዱ ቀን የተመደቡትን ጥቅሶች የያዙ ጽሑፎች ናቸው። ከዚህ የተነሳ ለአጥብያ አብያተ ክርስቲያናት በጣም ወሳኝ ነበሩ።
ብዙ ክርስቲያኖች የኢንጂል የግል ኮፒ ስላልነበራቸው በእግዚአብሔር ቃል ዕውቀት ለማደግ እነዚህን የአገልግሎት መጻሕፍት ይጠቀሙ ነበር።
አሁን የሚወቁት ሌክሽነሪዎች ኮፒ 2,300 ያህል ሆኗል። በተጨማሪም 3,200 የሚሆኑ ተከታታይነት ያላቸው ሌክሽሪዎች በመገኘት በዚያን ዘመን አዲስ ኪዳን በስፋት ስለመነበቡና በታማኝነት ስለመተላለፉ ምስክር ሆነዋል።
3. ቀዳሚያን ትርጉሞች
የአዲስ ኪዳንን ተዓማነት ለማረጋገጥ ወደ ሜድትራንያን ቋንቋዎች የተተረጎሙ የተሟሉ የአዲስ ኪዳን ትርጉሞች ወሳኝ ናቸው። ከነዚህ መካከል አንዱ ፔሺታ በመባል የሚታወቀው የአዲስ ኪዳን የሢርያክ ትርጉም ይገኝበታል። እንዲህ ያሉ ትርጉሞች የግሪክን ኦሪጅናል ጽሑፍ ይዘት ትክክለኛነት ለመገምገም እንደገና ወደ ግሪክ ሊተረጎሙ ይችላሉ።
4. የቤተክርስቲያን አበው
የክርስቶስ ሐዋርያት ተከታዮች የነበረው የክርስቲያን ማሕበረሰብ መሪዎች የቤተክርስቲያን አበው በመባል ይታወቃሉ። የሁለተኛው ትውልድ ደቀ መዛሙርት ብላችሁ ልትጠሯቸውም ትችላላችሁ።
በአሳቃቂ ስደት ውስጥ በማለፍ ማሕበረሰቦቻቸውን በክርስቶስ ባለው እምነት መምራት ችለዋል። በሜድትራንያን ባሕር የተለያዩ አካባቢዎች ይኖሩ የነበሩ ቢሆንም የተለያዩ ደብዳቤዎቻችንና ስብከቶችን በመጻጻፍ እርስ በርሳቸው ይገናኙ ነበር። የእነርሱ ጽሑፎች ከቀዳሚው የተሟላ የአዲስ ኪዳን ጽሑፍ (ኮዴክስ ሲናይቲከስ) ጋር ለማነፃፀርና ለማጥናት እንችል ዘንድ ዛሬም ድረስ ተጠብቀውልናል።

በእነዚህ ደብዳቤዎችና ስብከቶች ውስጥ የተጠቀሱት ጥቅሶች ከዛሬው ጽሑፍ ጋር ሙሉ በሙሉ ይስማማሉ።
ሐ. የትርጉም ደረጃ (ከ325 ዓ.ም. እስከ አሁን)
ክርስና በአውሮፓና በኢስያ ውስጥ እየተስፋፋ ሲመጣ ኢንጂል በተዓማኒነት ይተረጎም ነበር። ኢንጂል በሌሎች ቋንቋዎች ሲዘጋጅ ተርጓሚዎቹ ከዋናዎቹ የእጅ ጽሑፎች ጋር ያላቸውን ስምምነት ለማረጋገጥ ከፍተኛ የሆነ ጥንቃቄ ያደርጉ ነበር።
ሁሉም ቅጂዎች ወይንም የሌሎች ቋንቋዎች ትርጉሞች ከተከታዮቹ ቀዳሚያን ትርጉሞች ላይ የተዘጋጁ ናቸው፡-

1. ኮዴክስ ሲናይቲከስ
2. ኮዴክስ ቫቲካነስ
3. ኮዴክስ አሌክሳንድሪነስ

ቅጂዎች
አንዳንዶች እንደሚናገሩት ብዙ የሆኑት የኢንጂል ቅጂዎች ለብረዛ አጋልጠውታል፡፡ ቅጂ ማለት ትርጉም ማለት ነው። ታዋቂ የሆኑት ሙስሊም ተከራካሪዎች የኢንጂል ቅጂ ማለት የአንድ ታሪክ የተለየ ቅጂ ማለት እንደሆነ ሲናገሩ የቋንቋ እጥረት እንዳለባቸው እያሳዩ ነው።
አንዳንድ በክርስትና መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የጠለቀ ዕውቀት እንዳላቸው የሚናገሩ ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ዋና ቋንቋዎች የሆኑት የግሪክና የእብራይስጥ ቋንቋ መሠረታዊ ዕውቀት እንኳ የሌላቸው ናቸው።
አንድ በአረብኛ ምንም ሥልጠና የሌለው ሰው የቁርአን ሊቅ እንደሆነ ቢናገር ቂልነት እንደሚሆን ሁሉ የመጽሐፍ ቅዱስም ሊቅ ለመሆን ቋንቋዎቹን (እብራይስጥና ኮይኔ ግሪክ) ማጥናት አስፈላጊ ነው።
ታሪክ ይናገራል
ታሪክ ምን ይነግረናል? ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ አንስቶ እስከዚህ ዘመን ድረስ የሚገኘውን የክርስትና ታሪክ ስንመለከት የእግዚአብሔርን ቅዱስ ቃል ለመጠበቅ ያልተቋረጠ ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረጉን እንመለከታለን።
ከመጀመርያው ክፍለ ዘመን የዐይን ምስክሮች ዘገባዎች አንስቶ ስደተኛ በሆኑት ክርስቲያኖች መካከል እስከተላኩት ደብዳቤዎች ድረስ፤ ከዚያም ቀጥሎ ከ325 ዓ.ም. ጀምረው የሚገኙት ትርጉሞች መልእክት እያስተላለፉልን ነው። የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመታት ገደማ የተጻፉትን የኢየሱስ መልእክቶች በታማኝነት እያስተላለፉን ነው።
"ኢየሱስም የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ አለ" (ማርቆስ 4:9)
ምዕራፍ 7
የዚህ ሁሉ ትርጉም ምንድነው?
በዚህ ጥናት ኢንጂል ተበርዟል የሚለውን የጓደኞቼን መሠረት የለሽ ሐሳብ ለመረዳት ሞክሬያለሁ። ያገኘሁት ነገር ኢንጂል በፈጣሪ ተጠብቆ መቆየቱን ብቻ ሳይሆን እንዳምነውና ሕይወቴን በእርሱ ላይ እንድመሠርት አድርጎኛል።
ዛሬ የሚገኙት ትልቁ መሣፍርት የሌላቸው ማስረጃዎች ለኛ ከመናገር አልፈው እየጮኹ ነው! ማስረጃዎቹ የኢንጂልን እውነተኛነትና ንፅህና ያረጋግጣሉ። ዛሬ በእጃችን የያዝነው መጽሐፍ በኢየሱስ ተከታዮች ሲታመን የነበረው ያው ታሪክ

ነው። በዚያ እምነት በመፅናት ኖረው ሞተዋል።
ከአመክንዮ አንፃር አንድ ሰው እንጂል ተበርዟል ከማለቱ በፊት ወሳኝ ጥያቄዎችን መመለስ እንደሚገባው ተመልክተናል፡-

- ኢንጂል መቸ ነበር የተበረዘው?
- ማነው እንዲህ ያለ ተግባር የሚፈፅመው?
- አንድ ሰው ኢንጂልን እንዲለውጥ ምን ያነሳሳዋል?

በተጓዳኝ፣ ሐዋርያትና ተከታዮቻቸው እምነታቸው የውሸት መሆኑን እያወቁ ለውሸት ይሞታሉ ማለት የማይታሰብ ነው።
ኢንጂል እንደረተበረዘ የሚናገሩ ብዙ ሰዎች ስለ መነሻውና መልእክቱ ያላቸው ግንዛቤ የተሳሳተ ነው። ብሒላቸው በጥናትም ሆነ በአምክንዮአዊ ማስረጃ የተደገፈ አይደለም። ካለማወቃቸው የተነሳ ብዙዎችን ከእውነተኛ መንገድ ወደተሳሳተ መንገድ መርተዋል። ለፈጣሪ እንከራከራለን በሚል መነሻ ቃሉ የሆነውን ኢንጂልን መጠበቅ መቻሉን በመካድ ተገቢውን ክብር ነፍገውታል!
በመጨረሻም ቃሉን ጠባቂና ፍትሃዊ የሆነውን ሃያሉን ፈጣሪ ማመን ይቻል ዘንድ ይህ ፈጣሪያችን ቃሉ የሆነውን ኢየሱስን እንደላከልን ማመን ግድ ይላል። ለሰው ልጆች መመርያ ብርሃን ይሆን ዘንድ (ሊሁዳ አል-ዓለሚን) ኢንጂል በፈጣሪያችን እንደተጠበቀ ማመን አስፈላጊ ነው።
ሃያሉ ፈጣሪ ይህንን ጥናት ተጠቅሞ በእርሱና ቤዛችን በሆነው በመሲሁ ኢየሱስ ማመን እችል ዘንድ ረድቶኛል። ዛሬ ተከታዩን ጸሎት በመጸለይ ወደ ኢየሱስ ቤተሰብ ትቀላቀሉ ዘንድ እጋብዛችኋለሁ። ክርስቶስ ለእግዚአብሔር በመታዘዝ መኖር ትችሉ ዘንድ ኃይልን ይሰጣችኋል።
ጸሎት በየትኛውም ቦታ ሆናችሁ ከሃያሉ ፈጣሪያችሁ ጋር የምትነጋገሩበት መንገድ ነው።
ሁሉን ቻዩ አምላኬ ሆይ፣ አንተ ምሕረትን የተሞላህ አምላክ ነህ። ከኃጢአቴና ራስን ከማፅደቅ አመለካከቴ ንስሐ እገባለሁ። ባንተና ቃልህ በሆነው በመሲሁ ኢየሱስ አምናለሁ። እስከ መጨረሻዋ እስትንፋሴ ድረስ ያንተን ትምህርት ለመከተል ቃል እገባለሁ።
አሜን።

## የደህንነትን ማረጋገጫ መረዳት (ክፍል 1)
## መግቢያ

ለረጅም ጉዞ ከመውጣቴ በፊት የሚያስፈልገኝን ነገር ሁሉ መያዜን ለማረጋገጥ ዙርያ ገባውን እቃኛለሁ። የገንዘብ ቦርሳዬን ይዣለሁን? ለነዳጅና ለምግብ በቂ ገንዘብ አለኝ? የአውሮፕላን ቲኬቴን ይዣለሁን? የሆቴሎች አድራሻ የተጻፈበትን ወረቀት ይዣለሁን? እነዚህን ሁሉ ቁሳቁሶች መኪና ውስጥ መጨመሬን ባውቅም ለመጨረሻ ጊዜ መኖራቸውን አረጋግጣለሁ። ምክንያቱ ደግሞ አንድ አስፈላጊ ነገር ከረሳሁ ወደምፈልገው ቦታ መድረስ ስለማልችል ነው።
ልክ እንደዚሁ ክርስቶስን ለመከተል ከወሰንኩ በኋላ ሁሉንም ነገር በትክክል መፈፀሜን ለማረጋገጥ ዞር ብዬ ማየት ያስፈልገኛል። አንድን የደህንነት ወሳኝ ገፅታ በትክክል ካልተረዳሁ መድረስ ወደምፈልገው ቦታ (ሰማይ) መድረስ እንደማልችል

አውቃለሁ። ይህ የደህንነት ልምምድ ወሳኝ በመሆኑ አንዳንድ ሰዎች “በትክክል አድርጌዋለሁ ወይ?” ብለው መጠየቃቸው አያስገርምም። እግዚአብሔር ልጁ ዕዳችንን ይከፍል ዘንድ በመላክ የድርሻውን እንደተወጣ እናውቃለን። የኛ ስጋት የእርሱን ስጦታ ለመቀበል የድርሻችንን በትክክል አልተወጣን ይሆናል የሚል ነው። ይህ ጽሑፍ ይህንን ጉዳይ የተመለከተ ነው።

እግዚአብሔር ያደረገልንን መረዳት

መጀመርያ መረዳትና ማመን የሚገቡን የተወሰኑ ነገሮች አሉ። አንዳንድ ሰዎች እንዲህ ይላሉ፡- “እምነትህን አጥብቀህ እስከያዝክ ድረስ ምንም ብታምን ልዩነት የለውም።” ነገር ግን ሂትለር “ደካሞችን” በመግደል “ምርጥ” የሆነውን የአርያን ዘር ዓለምን እንዲቆጣጠር በማድረግ የሰው ልጆችን እየጠቀመ እንደሆነ አስቦ ነበር። ኦሳማ ቢን ላደን እርሱ የሚያምነውን የማያምኑትን ሰዎች እንዲገድል አላህ እንዳዘዘው ያምን ነበር። ሂትለርና ቢንላደን ያመኑበትን ነገር አጥብቀው የያዙ ሰዎች ነበሩ። ነገር ግን የተሳሳተ እምነት ወደተሳሳተ ተግባር ይመራል። ትክክለኛውን እምነት መያዝ በጣም ወሳኝ ነው። ለመዳን ምን ማመን አለብን?

መጥፎ ዜና፡- እኛ ኃጢአተኞች ነን። ይህ ኃጢአት ደግሞ ከእግዚአብሔር ይለያል። ከኃጢአት የተነሳ ከእግዚአብሔር ጋር በራሳችን ጥረት ሕብረት ሊኖረን አይችልም።

ለምሳሌ ያህል ሒሳብ እየተማራችሁ ነው እንበል። መምህራችሁ “አሁን እነዚህን የስሌቶች ቀመሮች ማወቅ ይጠበቅባችኋል። ለዚህ ፈጣን ፈተና የማለፍያ ነጥቡ መቶ ከመቶ ማምጣት ነው” አለ። ነገር ግን እየተፈተንክ እያለህ አንዳንድ ቀመሮችን መሳሳትህን ተረዳህ። ከዚህ በኋላ ሁሉንም ጥያቄዎች መመለስ ብትችል እንኳ ፈተናውን ማለፍ ትችላለህን? አትችልም። ምክንያቱም የማለፍያ ነጥቡ 100% ነውና። አንዴ ከተሳሳትክ ከዚህ በኋላ የፈለከውን ያህል ጥያቄ ብትመልስ 100% ልታገኝ አትችልም። ትወድቃለህ።

ልክ አንዱን ጥያቄ ከተሳሳትን በኋላ ያንን የሒሳብ ፈተና ማለፍ እንደማንችል ሁሉ አንዴ ኃጢአት ከሠራን (የእግዚአብሔርን ፍፁማዊ መመዘኛ ካላሟላን) ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባት አንችልም። ፍፅምና የጎደላቸው ሰዎች ፍፁም ወደሆነው ሰማይ በራሳቸው ችሎታ ሊገቡ አይችሉም። ማመን የሚገባን ቀዳሚው ነገር ይህ ነው።

መልካሙ ዜና፡-እግዚአብሔር አምላክ ራሳችንን ማዳን እንደማንችል ስለሚያውቅ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ያድነን ዘንድ ላከልን። ኢየሱስ ለአባቱ በመታዘዝ ፍፁም እንከን የለሽ ሕይወት ኖረ። በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ ስለ ራሱ ኃጢአት አልነበረም የሞተው ነገር ግን ስለኛ ኃጢአት ነበር። እኛ መክፈል የነበረብንን የቅጣት ዕዳ እርሱ ከፈለልን።

“ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶአልና።” (1ጴጥ. 3፡18)

“ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል።” (ሮሜ 8፡10)

ባለፈው ዓመት ቀጣሪዎችህ ተቋማቸውን ለሸሪኮቻቸው ጥሩ ለማስመሰል ሐሰተኛ የሆነ ትርፍ የጻፉበትን ሰነድ አገኘህ እንበል። ይህንን መረጃ አደባባይ የማውጣት የህሊና ግዴታ እንዳለብህ ብታውቅም ነገር ግን ከሥራ ተባረህ ቤተሰብህን አደጋ

ላይ ላለመጣል ብለህ ዝምታን መረጥክ። አሁን መረጃውን በመደበቅህ ምክንያት የወንጀሉ ተባባሪ ሆነህ ተከሰህ ፍርድቤት ዳኛ ፊት ቆመሃል። ዳኛው 100,000 ብር መክፈል አለብህ፤ አለበለዚያ ለ10 ዓመት ትታሰራለህ የሚል ውሳኔ አስተላለፈ። 100,000 ብር እንደሌለህ ነገርከው። እርሱም እንደ ፍትሃዊ ዳኛ ወንጀለኛ መሆንህን አረጋገጠብህ።
ዳኛው ያንተን ጭንቀትና የልጆችህን ጭንቀት በማየት አዘነ። ከዚያም እርሱ ብቻ ማየት የሚችለውን ጽሑፍ ጻፈ። ለፍርድ ቤቱ ተላላኪ አቀበለው፤ እርሱም ላንተ ሰጠው። ወረቀቱ ዕዳህን በሙሉ የሚከፍል በዳኛው እጅ 100,000 ብር የተጻፈበት ቼክ መሆኑን ስታውቅ በድንጋጤ ክው አልክ።
መጽሐፍ ቅዱስ “ጸጋ” ብሎ የሚጠራው እርሱን ነው። እግዚአብሔር ዕዳህን ከፍሎልሃል። ስለሚገባህ ሳይሆን ከታላቅ ፍቅሩ የተነሳ። እግዚአብሔር ዕዳችንን በልጁ ሞት መክፈሉ ምንኛ አስደናቂ ነው!
ነገር ግን እግዚአብሔር ይህንን ስጦታ መስጠቱ ብቻ በቂ አይደለም። መልካሙ ዳኛ የሰጠህን ቼክ አለመቀበል ትችላለህ። የእግዚአብሔርን ጸጋ የምንቀበለው እንዴት ነው? በእግዚአብሔር ማመንና ኢየሱስ እንደሞተልን ማመን በቂ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው ሰይጣን እንኳ በእግዚአብሔር ያምናል (ያዕ. 2፡19)። ይቅርታውን በንስሐና በእምነት መቀበል ይኖርብናል። እስኪ እነዚህን አንድ በአንድ እንመልከት።
እግዚአብሔር ምላሽ እንድንሰጥ በሚፈልግበት መንገድ ምላሽ መስጠት
ከኃጢአታችን ንስሐ መግባት፡- ንስሐ ለመጥፎው ዜና የምንሰጠው ምላሽ ነው፤ ኃጢአተኞች መሆናችንንና በእግዚአብሔር ላይ ማመፃችንን በማወቅ የምንሰጠው ምላሽ። የንስሐ ቀለል ያለ ትርጉም “ለመመለስ ፈቃደኛ መሆን” የሚል ነው። እዚህ ጋ ግራ እንዳይገባቸሁ! ራሳችንን ስንቀይር እግዚአብሔር ያድነናል እያልን አይደለም። እርሱ በሥራ የሚገኝ መዳን ነው የሚሆነው! በተጓዳኝ እግዚአብሔር እስኪያድሰንና አዲስን ሕይወት እንድንኖር አቅምን እስኪሰጠን ድረስ የረባ ለውጥ ልናደርግ አንችልም። ለራሳችን ከመገዛት ለእግዚአብሔር ወደ መገዛት የልቦና ለውጥ እናደርጋለን ማለት ነው። ንስሐ ስንገባ ለእግዚአብሔር “ለመለወጥ ፈቃደኛ ነኝ! ከኃጢአቴ በመመለስ ላገለግልህ እፈልጋለሁ!” ብለን እየነገርነው ነው።
“ከዚያ ዘመን ጀምሮ ኢየሱስ፦ መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ እያለ ይሰብክ ጀመር።” (ማቴ. 4፡17)
በኢየሱስ ማመን፡- በኢየሱስ ማመን ለሰማነው የምሥራች ወይም መልካም ዜና የምንሰጠው ምላሽ ነው።
“ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም።” (ኤፌ 2፡8-9)
“በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።” (ዮሐ. 3፡16)
ዝም ብለን በአእምሯችን “ኢየሱስ መኖሩን፣ ተዓምራትን ማድረጉንና ከሙታን መነሳቱን አምናለሁ” ብሎ መናገር አይደለም። በኢየሱስ ማመን ማለት እምነታችንን ሙሉ በሙሉ በእርሱ ላይ መጣል ማለት ነው። ሰዎች እስፖርት

በመሥራት እንደሚያምኑ ሲናገሩ እስፖርት የሚባል ነገር በዓለም ላይ የሆነ ቦታ አለ ብለው ማመናቸው አይደለም። እስፖርት ጠቃሚ መሆኑን ተቀብለው ለመሥራት ፈቃደኞች ናቸው ማለት ነው። አንዲት ሴት በኮካ አምናለሁ ብትል ኮካ ኮላ መኖሩን በሐሳቧ ከማመን ያለፈ ነገር ውስጧ አለ ማለት ነው። እንደ አዝናኝ መጠጥ ሙሉ በሙሉ ስለምትቀበለው ለመጠጣት ፈቃደኛ ናት ማለት ነው።

በተመሳሳይ በኢየሱስ ማመን እርሱ መኖሩን በአእምሮ ከመቀበል ያለፈ ነው። እንዲያድነን እምነታችንን በእርሱ ላይ መጣል ነው። ለእርሱ ራሳችንን አሳልፈን መስጠት ነው። እግዚአብሔር በልጁ በኩል አዳችንን በመክፈል ይቅርታን እንደሰጠን እናምናለን፤ የከፈለንንም ክፍያ እንቀበላለን ማለታችን ነው። ክርስቶስንም ለመከተል ፍቃደኝነታችንን እየገለፅን ነው።

ሁሉንም በአንድነት ማድረግ

ንስሐና እምነት በሁለት የተለያዩ ነገሮች ላይ ማለትም በኃጢአታችንና በክርስቶስ ላይ የሚያተኩሩ ቢሆንም ሁለቱም አንድ የአእምሮ ተግባር ናቸው። ከኃጢአታችን በተመለስንበት ቅፅበት ወደ ክርስቶስ እንመለሳለን። ኢየሱስ እንዳለው፡-

“ዘመኑ ተፈጸመ የእግዚአብሔርም መንግሥት ቀርባለች ንስሐ ግቡ በወንጌልም እመኑ” (ማር. 1፡15)

በዚህ ትምህርት መጀመርያ ላይ ወደጠቀስነው ወሳኝ ጉዞ እስኪ እንመለስ። ወደ መዳረሻዬ መድረስ መቻሌን ለማረጋገጥ እንዲህ ብዬ ራሴን እጠይቃለሁ፡ - “የአውሮፕላን ቲኬቴን ይዣለሁን? በቂ ገንዘብ ይዣለሁን?” በተመሳሳይ መንገድ በእውነት የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንንና ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባታችንን እርግጠኞች መሆን ከፈለግን “በእውነት ከልብ ንስሐ ገብቻለሁን? በኢየሱስ ከልቤ አምኛለሁን?” በማለት ራሳችንን መጠየቅ ያስፈልገናል። ያንን አለማድረግህን ካወክ ወይም ያንን ማድረግህን እርግጠኛ ካልሆንክ ውሳኔህን በጸሎት ለእግዚአብሔር በመግለፅ አሁኑኑ አረጋግጥ። የልብህን ቅንነት እንጂ የምትናገራቸውን ቃላት አይመለከትም። ተከታዩ የተጻፈ ጸሎት በልብህ ውስጥ ያለውን መሻት የሚገልፅልህ ከሆነ አሁኑኑ በእግዚአብሔር ፊት ለምን አትጸልይም?

“እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ በራሴ መንገድ በመሄዴ ተጸጽቻለሁ። ይቅር በለኝ፡ ፡ ከኃጢአቴ እመለሳለሁ። እንድከተልህ አቅምን ስጠኝ። በአንተ አምናለሁ፡ ፡ ከኃጢአቴ ታድነኝ ዘንድም በአንተ እደገፋለሁ። አዲስ ሰው አድርገህ ወደ መንግሥትህ አግባኝ። በጣም ስለወደድከኝና ኃጢአቴን ይቅር ስላልከኝ አመሠግንሃለሁ።”

ይህንን ጸሎት ከልብህ ከጸለይክ በእግዚአብሔር ቃል ሥልጣን መሠረት እነግርሃለሁ፤ አንተ ልጁ ሆነሃል፤ መዳረሻህ ወደ ሆነው ወደ መንግሥተ ሰማያትም በስኬት ጉዞ ጀምረሃል።

እውነታዎችና ስሜቶች

አለቃህ በጣም ስላቃለለህ ባለፈው ምሽት በቂ እንቅልፍ አልተኛህም። የሚያፅናና ቃል ፈልገህ ወደ ጸሎት ስብሰባ ሄደሃል። በዚህ ፋንታ እግዚአብሔር ችግሮቹን ሁሉ እንዴት እንደፈታለት በስሜት ተውጦ የሚናገር ክርስቲያን አጋጠመህ። “ችግሮቼ ሁሉ አልተቀረፉም” ብለህ አሰብክ። ከዚያም አንድ አዲስ ክርስቲያን

ተነስቶ ክርስቶስን ሲቀበል እንደ ኤሌክትሪክ ያለ ንዝረት በመላው አካሉ እንደተሰራጨ አስገራሚ ምስክርነት ሰጠ። "በዳንኩበት ሰዓት ምንም የተለየ ስሜት አልተሰማኝም" ብለህ አሰብክ። ከዚያም ክርስቲያን መሆንህን እንኳ መጠራጠር ጀመርክ።

በዚህ ጊዜ ስሜቶችህን ቦታ ልታሲዛቸው ይገባል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡- "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።" (ዮሐ. 3፡16) "ሁል ጊዜ ጥሩ ስሜት የሚሰማቸው" አላለም። "ልክ ሲያምኑ ድንገተኛ የሆነ ስሜት የሚሰማቸው" አላለም። "በእርሱ የሚያምን ሁሉ" ነው ያለው።

ስለዚህ በእውነት አምኜ ንስሐ ከገባሁ እና ካልዳንኩ ይህ ስለ እግዚአብሔር ምን ይነግረናል? (ሐሰተኛ ልንለው ነው! እርሱ ደግሞ ከዋሸ ምን ተስፋ ይኖረናል!) ስለዚህ ምንም ይሰማን ምን ንስሐ የገቡትና ያመኑት ሰዎች መዳን እንደ እግዚአብሔር ተስፋ ሁሉ እውነትና የጸና ነው። ምክንያቱም እርሱ ውሸት የማያውቀው እውነተኛና ታማኝ ነውና።

የደህንነትን ማረጋገጫ መረዳት (ክፍል 2)

ለተጠራጣሪዎች መድኃኒት

መግቢያ

ከአሜሪካ ወደ አውሮፓ በመርከብ ጉዞ ስለጀመረ አንድ ሰው ሰምቼ ነበር። ይህ ሰው ለቲኬት ብቻ የሚበቃ ገንዘብ ያዘጋጀ ሲሆን በመርከቢቱ ሬስቱራንት ላይ ምግብ ገዝቶ የሚመገብበት ገንዘብ አልነበረውም። ስለዚህ የራሱን ጥቂት ምግብ በማዘጋጀት ሰዎች በደስታ ከሚመገቡበት የመርከቢቱ ሬስቱራንት ራሱን አራቀ።

ከቀናት በኋላ የያዘው ምግብ አለቀበት። ከእርሱ ጋር ተጓዥ የነበረ አንድ ሰው ቀረብ ብሎ "ወዳጄ ሬስቱራንቱ ውስጥ አብረኸን ስትመገብ አላይህም፤ ካላስቸገርኩህ ምክንያቱን ልትነግረኝ ትችላለህ?" ብሎ ጠየቀው። ለቲኬቱ እንጂ ለምግቡ የሚከፍለው ገንዘብ እንደሌለው ገለጸለት። ከዚያም ያ ሰው መልሶ "ምን ነካህ ወዳጄ? ምግቡ እኮ ከትኬቱ ጋር አብሮ የመጣ ነው!" ብሎ መለሰለት። (1)

በሚያሳዝን ሁኔታ ብዙ ክርስቲያኖች ልክ እንደዚህ ሰው ናቸው። ሁሉም ነገር ወደሰማይ ከሚወስደው ትኬት ጋር አብሮ እንደመጣላቸው ወደማመን ብስለት አያድጉም። ራሳቸው ባዘጋጁት ድርቆሽ ላይ ጥገኛ በመሆን እግዚአብሔር ከደህንነታቸው ጋር እንደተሰጣቸው የተናገረውን ድግስ ሳይታደሙ ይቀራሉ።

እስኪ ዛሬ በድግሱ ውስጥ የሚገኙትን ጥቂት ነገሮችና ተጠራጣሪዎች ድግሱን እንዳይታደሙ የሚያደርጓቸውን አንዳንድ ነገሮች መመልከት እንጀምር።

የአሁን አዋጅ

ደህንነት ከሞት በኋላ ስላለ ሕይወት ጉዳይ ብቻ አይደለም። የዘላለምን ሕይወት ከብዙ ጥቅሞቹ ጋር አሁን እዚሁ አግኝተናል። ጥቂቶቹ እነሆ፡-

ይቅርታ – አንዳንድ ክርስቲያኖች ባለፈው ጊዜ በፈጸሙት ኃጢአት ምክንያት ውስጣቸው እየተወቀሰ ወደ መኝታቸው ይሄዳሉ። ነገር ግን በእግዚአብሔር ዕይታ ምስራቅ ከምዕራብ የራቀውን ያህል ኃጢአታቸው ከእነርሱ ርቋል። በምንም መንገድ ውስጣችን ሊከሰስ አይገባም! በናዚ የማሰቃያ ካምፕ ውስጥ የነበረችው ካሪ ቴን ቡም እንደተናገረችው "ኃጢአታችንን ስንናዘዝ እግዚአብሔር ለዘላለም

እንዲጠፋ ወደ ባሕር ይወረውረዋል። ከቃሉ ጥቅስ መጥቀስ ባልችልም እግዚአብሔር ‹እዚህ ቦታ አሣ ማጥመድ አይፈቀድም!› የሚል ምልክት እንዳስቀመጠበት አምናለሁ።” (2)
“በውድ ልጁም፣ እንደ ጸጋው ባለ ጠግነት መጠን፣ በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን እርሱም የበደላችን ስርየት።” (ኤፌ. 1፡7)
አዲስ ፍጥረት – አንዳንድ ሰዎች “ሕይወቴን እንዲህ አድርጌ ስላበለሻሸሁት ከታች መጀመር ያስፈልገኛል” ይላሉ። ለዚህ ነው እግዚአብሔር አሮጌውን ሕይወታችንን ከእንደገና ከማስተካከል ያለፈ ሥራ የሠራልን። በቤተሰቡ ውስጥ እንደገና እንድንወለድ በማድረግ አዲስ ሕይወት አስጀምሮናል። እንደ አዲስ ፍጥረት ከእግዚአብሔር ጋር አዲስ ሕብረት ጀምረናል። በዚያ ሕብረት ውስጥ የመኖር ፍላጎትም ተሰጥቶናል።
“ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፣ ሁሉም አዲስ ሆኖአል።” (2ቆሮ. 5፡17)
መንፈስ ቅዱስ – እግዚአብሔር ካዳነን በኋላ የተቀረው ሕይወታችንን በራሳችን እንድንኖር ለብቻችን አልተወንም። ስንድን መንፈስ ቅዱስ ወደኛ በመምጣት በውስጣችን መኖር ጀምሯል። ስኬታማ ክርስቲያናዊ ሕይወትም እንድንኖር ያስችለናል። ሁላችንም እንደምናውቀው ክርስቲያናዊ ሕይወት ከባድ አይደለም፤ ነገር ግን ሊኖሩት ፈፅሞ የማይቻል ነው! በራሳችን ኃይል ልንኖረው አንችልም፡ ፡ ስኬታማ ክርስቲያኖች ክርስቲያናዊውን ሕይወት መኖር እንዲችሉ በመንፈስ ቅዱስ ላይ መደገፍን ይማራሉ።
“ንስሐ ግቡ፥ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።” (ሐዋ. 2፡38)
የወደፊት ተስፋዎች
ከዓመታት በፊት ከአንድ ታዋቂ የእግር ኳስ ተጫዋች ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ አንብቤ ነበር። ሪኮርድ ያስመዘገበ፣ ግሩም ችሎታ የነበረው፣ ደጋፊዎች ለማምለክ የሚፈተኑበት ዓይነት ተጫዋች ነበር። በእግር ኳስ ሜዳ ውስጥ ከፍተኛ በራስ መተማመን የነበረው ይህ ተጫዋች በሕይወቱ ትልቅ ጉዳይ ላይ መተማመን አልነበረውም። ጋዜጠኛው ይህ ተጫዋች ምን እንደሚያስፈራው ጠየቀው። ወደ ሜዳ ሲገባ ተቀናቃኞቹን የሚያስፈራ ተጫዋች ለዚህ ጥያቄ የሚሰጠውን ምለሽ መስማት በጣም ያጓጓል። እንዲህ ሲል ነበር ምላሹን የሰጠው፡- “መሞትና ወደ ሲዖል መሄድ። ነገር ግን የምሄድ አይመስለኝም ምክንያቱም ጥሩ ሰው ሆኜ ኖሬያለሁና።”
ይህ ሰው በሙያው ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል ነገር ግን የዘላለም መኖርያው የት እንደሆነ በእርግጠኝነት ማወቅ ስላልቻለ ውስጡ ሰላም አላገኘም። ብዙ ሰዎች የዘላለም መኖርያቸውን ማወቅ የሚችሉ እንኳ አይመስላቸውም። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በግልፅ ይናገራል፡-
“ዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ።” (1ዮሐ. 5፡13)
ማወቅ እንጂ ተስፋ ማድረግ ወይም ምናልባት ይሆናል ብሎ ማሰብ አይደለም፡ ፡ እግዚአብሔር ስለ መጨረሻ መድረሻችን እርግጠኞች እንድንሆንና ሰላም እንዲኖረን ይፈልጋል። በሰማዩ ቤታችን ከእርሱ ጋር ለዘላለም ለመኖር ዝግጁዎች

ልንሆን ይገባናል!
እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ የሚከተሉትን ተስፋዎች ሰጥቶናል፡-
ከእግዚአብሔር ቁጣ እናመልጣለን፡- እግዚአብሔር ፍትሃዊ አምላክ በመሆኑ የኃጢአት ቅጣት መከፈል አለበት። ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ ምክንያት ኢየሱስ የኃጢአትን ቅጣት በሙሉ በራሱ ላይ ወሰደ።
“ይልቁንስ እንግዲህ አሁን በደሙ ከጸደቅን በእርሱ ከቍጣው እንድናለን።” (ሮሜ 5፡9)
በክርስቶስ ዳግም ምፅዓት ከሞት መነሳት፡- የሞቱትም ሆኑ በሕይወት ያሉት አማኞች ክርስቶስ ሲመለስ አዲስ የከበረ አካል ይለብሳሉ። ምድራዊው አካሌ በታመመና በተጎዳ ቁጥር ስለ ሰማያዊው አካሌ እያሰብኩ ደስ እሰኛለሁ!
“የሙታን ትንሣኤ ደግሞ እንዲሁ ነው። በመበስበስ ይዘራል፥ ባለመበስበስ ይነሣል፤ በውርደት ይዘራል፥ በክብር ይነሣል፤ በድካም ይዘራል፥ በኃይል ይነሣል፤ ፍጥረታዊ አካል ይዘራል፥ መንፈሳዊ አካል ይነሣል። ፍጥረታዊ አካል ካለ መንፈሳዊ አካል ደግሞ አለ።” (1ቆሮ. 15፡42-44)
የዘላለም ሕይወት ይኖረናል፡- ሁሉም አማኞች ለዘላለም ከክርስቶስ ጋር እንደሚኖሩ ተስፋ ተሰጥቷቸዋል። የዘላለምን ሕይወት እንዳገኘን ለማወቅ ጊዜ መጠበቅ የለብንም። አሁን እንኳ አግኝተነዋል!
“በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።” (ዮሐ. 3፡16)
ጥርጣሬን መቅረፍ
እግዚአብሔር ከቁጣው እንድናመልጥ፣ አዲስ ሰማያዊ አካል እንደምናገኝና ለዘላለም ከእርሱ ጋር እድንኖር ቃል ከገባልን ለምንድነው አንዳንድ ክርስቲያኖች ከጥርጣሬ ጋር የሚታገሉት? እናንተ ከጥርጣሬ ጋር ባትታገሉም እንኳ ይህ ችግር ያለባቸው ሰዎች ሊያጋጥሟችሁ ይችላሉ። እስኪ አንዳንድ የጥርጣሬ ምክንያቶችን እንመልከት።

1. “እግዚአብሔር ያለፈውን ኃጢአቴን ይቅር ይለኛል ብሎ ማመን ከባድ ነው።”

እስኪ የዚህን ታላቅ ኃጢአተኛ ሰው ምስክርነት ስሙ፡-
…አስቀድሞ ተሳዳቢና አሳዳጅ አንገላቺም ምንም ብሆን፥ ይህን አደረገልኝ፤ ነገር ግን ሳላውቅ ባለማመን ስላደረግሁት ምህረትን አገኘሁ፥የጌታችንም ጸጋ በክርስቶስ ኢየሱስ ካሉ ከእምነትና ከፍቅር ጋር አብልጦ በዛ። ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው፤ ከኃጢአተኞችም ዋና እኔ ነኝ፤ ስለዚህ ግን፥ የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት በእርሱ ያምኑ ዘንድ ላላቸው ሰዎች ምሳሌ እንድሆን፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ዋና በምሆን በእኔ ላይ ትዕግስቱን ሁሉ ያሳይ ዘንድ፥ ምህረትን አገኘሁ።
ይህንን ማን እንደጻፈው ታውቃለህ? እግዚአብሔር አብዛኞቹን የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ለመጻፍ የተጠቀመበት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ነው (1ጢሞ. 1፡13-16)። ክርስቲያን ከመሆኑ በፊት ምን ይመስል እንደነበር ታውቃለህ? የኢየሱስን መሲህነት ክዶ ነበር። በጣም ነውጠኛ ሰው ከመሆኑ የተነሳ በታላቅ ቁጣ ቤተ ክርስቲያንን አሳዷል፣ ክርስቲያኖችን አሳስሯል፣ እንዲገረፉና እንዲገደሉ አድርጓል

(1ጢሞ. 1፡13፣ ሐዋ. 7፡58፣ 8፡1፣ 9፡1-5፣ 22፡4-7፣ 19-20፣ 26፡9-11)። ነገር ግን ሐዋርያው ጳውሎስ እግዚአብሔር እርሱን ይቅር ካለው ይቅር የማይለው ሰው ሊኖር እንደማይችል ሊነግራችሁ ይወዳል። ምንም ብታደርጉ ይህንን አስታውሱ፡- "የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል።" (1ዮሐ 1፡7)
ከስንት ኃጢአት? "ከኃጢአት ሁሉ።" የዕፅ ሱሰኛና የዝሙት ኃጢአት የፈፀምን እንኳ ብንሆን? "ከኃጢአት ሁሉ።" ክርስቲያን የገደልን እንኳ ብንሆን? "ከኃጢአት ሁሉ።"

2. "እውነቱን ለመናገር ስለ እግዚአብሔር ብዙም ግድ የለኝም።"

አቤሴሎም የሃይስኩል ተማሪ እያለ ክርስቶስን ለመቀበል የንስሐ ጸሎት ጸልዮ ነበር። በወር አንድ ሁለት ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ብቅ ቢልም በዕለት ተዕለት ኑሮው ለእግዚአብሔር ያን ያህል ትኩረት አይሰጥም። ንግዱን እንዴት መምራት እንዳለበት፣ ልጆቹን እንዴት ማሳደግ እንዳለበትና ሚስቱን እንዴት መያዝ እንዳለበት ለማወቅ እንኳ መጽሐፍ ቅዱሱን ገልጦ አያነብም። ሕይወቱ በየቀኑ አብሯቸው ከሚሠራቸው ክርስቲያን ካልሆኑ ሰዎች የተለየ አይደለም። ስለ መዳኑ ጥርጣሬ ቢኖረውም የሃይስኩል ተማሪ ሳለ በጸለየው የንስሐ ጸሎት ይተማመናል።

አቤሴሎም የፈሩትን የሚያረጋጉ ጥቅሶችን ማንበብ እንዳለበት ሁሉ የተረጋጉትንም የሚያስፈሩ ጥቅሶችን ማንበብ ይኖርበታል። አቤሴሎም መፍራት አለበት። ቀደም ሲል የጠቀስነውን ጥቅስ ታስታውሳላችሁ?
"የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ።" (1ዮሐ. 5፡13)
ዮሐንስ ማረጋገጫ እንዲሆኗቸው የጻፈላቸው እነዚህ ነገሮች ምንድናቸው? የዮሐንስ መልዕክት ሁለት ዓይነት ሕይወቶችን ይጠቅሳል፤ የዘላለም ሕይወት ያላቸውና የሌላቸው ሰዎች ሕይወቶች። የያንዳንዱን ሕይወት ባሕርይ ተመልከቱ፡-
እውነተኛ ክርስቲያኖች የመዳናቸውን ማስረጃዎች በሚከተሉት መንገዶች ማሳየት አለባቸው፡-
መታዘዝ (1ዮሐ. 2፡3-4)
"ትእዛዛቱንም ብንጠብቅ በዚህ እንዳወቅነው እናውቃለን። አውቄዋለሁ የሚል ትእዛዛቱንም የማይጠብቅ ውሸተኛ ነው እውነትም በእርሱ ውስጥ የለም።"
እምነት (1ዮሐ. 5፡1)
"ክርስቶስ ነው ብሎ በኢየሱስ የሚያምን ሁሉ ከእግዚአብሔር ተወልዶአል፤ ወላጁንም የሚወድ ሁሉ ከእርሱ የተወለደውን ደግሞ ይወዳል።"
ፍቅር
ፍቅር ለእግዚአብሔር (1ዮሐ. 5፡1-2)
"ክርስቶስ ነው ብሎ በኢየሱስ የሚያምን ሁሉ ከእግዚአብሔር ተወልዶአል፤ ወላጁንም የሚወድ ሁሉ ከእርሱ የተወለደውን ደግሞ ይወዳል። እግዚአብሔርን ስንወድ ትእዛዛቱንም ስናደርግ የእግዚአብሔርን ልጆች እንድንወድ በዚህ እናውቃለን።"
ፍቅር ለእግዚአብሔር ሕዝብ (1ዮሐ. 3፡14-15)
"እኛ ወንድሞችን የምንወድ ስለ ሆንን ከሞት ወደ ሕይወት እንደ ተሻገርን

እናውቃለን፤ ወንድሙን የማይወድ በሞት ይኖራል። ወንድሙን የሚጠላ ሁሉ ነፍሰ ገዳይ ነው፥ ነፍሰ ገዳይም የሆነ ሁሉ የዘላለም ሕይወት በእርሱ እንዳይኖር ታውቃላችሁ።”
አንዳንዶቻችን ይህንን ዝርዝር በማየት ተስፋ ልንቆርጥ እንችላለን። ማናችንም እምነት፣ ፍቅርና መታዘዝን ሁል ጊዜ 100% አሟልተን አንገኝም። ይህ ማለት ክርስቲያኖች አይደለንም ማለት ነውን? በፍፁም! ዮሐንስ መልዕክቱን በጻፈበት የግሪክ ቋንቋ ተላምዶ መኖርን የሚያሳይ ቃል ተጠቅሟል። ዮሐንስ 1፡8 ስለ ፍፅምና እያወራን እንዳልሆነ ግልፅ ያደርጋል።
“ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፥ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም፡፡”
አንዳንድ ሰዎች ስሜታቸው በጣም ስስ ከመሆኑ የተነሳ በጸሎት በእግዚአብሔር ፊት የሚያሳልፉበትን ጊዜ ከዘለሉ መዳናቸውን ይጠራጠራሉ። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት መፈለግህና ካልተገናኘህ ቅር መሰኘትህ በራሱ መንፈስ ቅዱስ በሕይወትህ ውስጥ እየሠራ መሆኑን ያሳያል።
ክርስቶስን ስንቀበል በሕይወታችን ውስጥ ትልቅ ለውጥ ተደርጓል። ውሳኔዎችን ሁሉ “እኔ እኔ እኔ” ብለን በራሳችን ላይ አተኩረን ከማድረግ ይልቅ ሌሎችን ስለመውደድና ለእግዚአብሔር ስለመኖር እናስባለን።
በ1ዮሐንስ መሠረት ማረጋገጫዬ ያረፈው በሃይማኖታዊ ሥርኣት ወቅት በሚሰማኝ ስሜት ላይ ሳይሆን አሁንና እዚህ አጠቃላዩ ሕይወቴ በሚይዘው አቅጣጫ ላይ ነው።
አሁን በኢየሱስ ታምናለህን? አሁን ኢየሱስን እየተከተልክ ነውን? በክርስቶስ ያሉትን ወንድሞችህንና እህቶችህን አሁን ትወዳቸዋለህን? ራስህን ከመከተል ይልቅ እግዚአብሔርን እየተከተልክ ነውን? በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ክርስቲያን ነህ፤ የዘላለም ሕይወት አለህ።
ማስጠንቀቂያ! የኑሮ ዘይቤያችን ለደህንነታችን ምልክት ቢሆንም የደህንነታችን ምክንያት ወይም ጠባቂ አይደለም። ደህንነታችን በእምነት በሆነ ጸጋ እንጂ እኛ ሠርተን ያገኘነው አይደለም (ኤፌ. 2፡8-9)።

3. “ደህንነቴን ለመጠበቅ በጣም ደካማ በመሆኔ እፈራለሁ።”

ላንተ የምሥራች አለኝ! መጀመርያ በእግዚአብሔር ዘንድ የዘላለም ሕይወት እንዳለህ ለማወቅ እስከ ዕለተ ሞትህ ድረስ መጠበቅ የለብህም። የዘላለምን ሕይወት አግኝተሃል።
“የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ።” (1ዮሐ. 5፡13)
እስኪ አስበው። የዘላለም ሕይወትህን የምታጣ ከሆነ ሲጀመር የዘላለም ሕይወት አይደለም! እንደማታገኘው የምትፈራውን የዘላለምን ሕይወት አግኝተኸዋል፤ በእጅህ ነው!
ሁለተኛ እግዚአብሔር እንደሚጠብቅህ ተስፋን ሰጥቷል። ደህንነታችን በኛ የመጠበቅ ችሎታ ላይ ሳይሆን በእግዚአብሔር ችሎታና የመጠበቅ ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ነው። ኢየሱስ እንዲህ አለ፡-
“ከሰጠኝም ሁሉ አንድን ስንኳ እንዳላጠፋ በመጨረሻው ቀን እንዳስነሣው እንጂ የላከኝ የአብ ፈቃድ ይህ ነው። ልጅንም አይቶ በእርሱ የሚያምን ሁሉ

የዘላለም ሕይወትን እንዲያገኝ የአባቴ ፈቃድ ይህ ነው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።” (1ዮሐ. 6፡39-40)

“በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ እኔም አውቃቸዋለሁ ይከተሉኝማል፤ እኔም የዘላለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ፥ ለዘላለምም አይጠፉም፥ ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም። የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል፥ ከአባቴም እጅ ሊነጥቃቸው ማንም አይችልም። እኔና አብ አንድ ነን።” (ዮሐ. 10፡27-30)

እነዚህ ጥቅሶች በኢየሱስና በእግዚአብሔር አብ እጆች ውስጥ አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ መያዛችንን በግልፅ ይስላሉ። ያ ምስል ከአእምሮህ እንዲጠፋ አትፍቀድ። እንወድቃለን እርሱም ዴግሞ ይጥለናል ብለን በእግዚአብሔር እጆች ላይ ተንጠልጥለን እየተፍጨረጨርን የምንኖር ሰዎች አይደለንም። የእርሱ ሃያል እጅ አጥብቆ ስለያዘን ምንም ነገር ከእጁ ፈልቅቆ ሊያወጣን አይችልም። የኛ ደህንነት አጥብቆ የያዘንን የእግዚአብሔርን እጅ ያህል አስተማማኝና ጠንካራ ነው።

ማስታወሻዎች

- Found in Bill Bright’s Transferable Concepts (Campus Crusade for Christ). Worded by Steve Miller.
- Corrie ten Boom with Jamie Buckingham, Tramp for the Lord (Fort Washington, PA: CLC Publications, 1974), 53.

የኢየሱስና የአብ አንድነት የዓላማ ብቻ ወይንስ የባሕርይም ጭምር?

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ 10:30 ላይ “እኔ እና አብ አንድ ነን” በማለት ተናግሯል። ማናችንም እንደምናውቀው በሰው ልጆች ታሪክ እንዲህ ብሎ የተናገረ ነቢይ የለም። ሙስሊሞች እንደ መጨረሻው ነቢይ የሚቆጥሩት ሙሐመድ አንድም ጊዜ “እኔና አላህ አንድ ነን” ብሎ ተናግሮ አያውቅም። እንዲህ ያለው ንግግር አንድ አካል አምላክነቱን እያወጀ ስለመሆኑ ግልፅ ማስረጃ ነው። ታድያ ሙስሊም ወገኖቻችን ይህን ግልፅ የኢየሱስ ንግግር ለማስተባበል የተለያዩ ሙከራዎችን አድርገዋል። በመደበኛነት የሚጠቀሙት ሙግት ኢየሱስ ስለ ዓላማ አንድነት እንጂ ስለ ባሕርይ አንድነት እየተናገረ አይደለም የሚል ነው። በዚህ ጽሑፍ ኦሪጅናሉን የግሪክ ንባብ በማጣቀስ ይህንን ማስረጃ ለማጣጣል ጥረት ያደረገውን የአንድ ሙስሊም ሰባኪ ሙግት የምንመለከት ይሆናል። ይህ አብዱል የተለያዩ ኑፋቄ ቡድኖችን ሙግቶች በመቅዳት የሚታወቅ ሲሆን የሙግቶቹን ምንጭ ባለመጥቀስ የገዛ ራሱ ሙግት በማስመሰል ያቀርባል። ምንም ዓይነት የግሪክ ቋንቋ ዕውቀት ሳይኖረው ልክ ግሪክ እንደሚችል ሰው በራስ በመተማመን ትንታኔዎችን ይሰጣል። እንዲህ ሲል ይጀምራል፦

መንደርደርያ

አንድ ጊዜ አንዱን ሰው፦ ”ኢየሱስ እኔ አምላክ ነኝ አምልኩኝ” ያለበትን ጥቅስ አሳየን ብዬ ስጠይቀው፣ አንተም፦ ኢየሱስ ”እኔ አምላክ አይደለሁም አታምልኩኝ” ያለበትን ጥቅስ አሳየን ብሎ አረፈው። እኔም በመቀጠል፦ ኢየሱስ እኔ አምላክ አይደለሁም አታምልኩኝ ያለበትን ጥቅስ ባይገኝ ኢየሱስ አምላክ መሆኑንና መመለኩን ያሳያልን? ብዬ ጠየኩት፣ እርሱም አዎ አለ፣ እኔም በመቀጠል፦ ስለዚህ የእምነት አባት አብርሐም ”እኔ አምላክ አይደለሁም አታምልኩኝ” አላለም፣

አለማለቱ ግን አምላክ ለመሆንና ለመመለክ መስፈርት አይደለም፣ ይህ ከስነ–ኣመክኖ ኣንፃር ፉርሽ የሆነ ሙግት ነው።
ከሥነ አመክንዮ አንጻር ፉርሽ የሆነው ያንተ ጥያቄ እንጂ የእርሱ ምላሽ አይደለም። አንድ አካል አምላክ የሚሆነው የአምላክ ባሕርያት ካሉት ብቻ እንጂ አምላክ ነኝ ስላለ አምላክ አይሆንም። ከግብፅ ፈርዖኖችና ከሮማውያን ነገሥታት ጀምሮ እስከ ዘመናችን ሐሰተኛ ክርስቶሶች ድረስ "አምላክ ነን" ያሉ ብዙ ሰዎች ሊጠቀሱ ይችላሉ ነገር ግን እንደርሱ ማለታቸው አምላክ አላደረጋቸውም፡፡ አምላክ መሆናቸውን በማወጅ ያጭበረበሩ ሰዎች በሰው ልጆች ታሪክ በተደጋጋሚ ከመታየታቸው አንፃር እንዲህ ያለው ንግግር ለአምላክነት መስፈርት ሊውል አይገባውም። ትክክለኛው መስፈርት አንድ አካል አምላካዊ ባሕርያትን አንጸባርቋል ወይ? የሚል እንጂ አምላክ ነኝ ብሏል ወይ? የሚል አይደለም።
በአንፃሩ ኢየሱስ አምላክ አለመሆኑን አለመናገሩ የአምላክነቱ ማረጋገጫ በመሆኑ አምላክ አይደለሁም ያለበትን ቦታ እንድታሳየው መጠየቁም ትክክል ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰዎች ለሰዎች ለአምላክ ብቻ የሚገባውን ክብር ሲሰጡ ሰው እንጂ አምላክ አለመሆናቸውን ሲገልፁ እንመለከታለን (ሐዋ. 14፡ 11-18)። ኢየሱስ ግን ሰዎች ሥራውን ተመልክተው ሲሰግዱለት፣ ሲያመሰግኑትና "አምላኬ" ብለው ሲጠሩት ተቃውሞ ከማሰማት ይልቅ ተግባራቸውንና ንግግራቸውን ሲያጸድቅ እንመለከታለን። ስለዚህ አምላክ አለመሆኑን አለመናገሩ የአምላክነቱ ማረጋገጫ ነው።
ሌላው የጥያቄው ችግር ለክርክር እንጂ እውነትን ለማወቅ የተጠየቀ አለመሆኑ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኢየሱስ "እኔ አምላክ ነኝ" ያለበት ቦታ ቢኖር የእውነት ትቀበላለህ ወይንስ "መጽሐፍ ቅዱስ ተበርዟል" ትላለህ? ለምሳሌ ያህል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኢየሱስ የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ስለመኾኑ፣ ስለስቅለቱ፣ ስለሞቱና ስለትንሣኤው የተናገረባቸው በርካታ ቦታዎች ይገኛሉ፡፡ እነዚህን እውነታዎች አለመቀበልህ "አምላክ ነኝ" ብሎ የተናገረበትን ቦታ ብናሳይህ ላለመቀበልህ ማረጋገጫ አይደለምን? ስለዚህ ጥያቄው ሲጀመር በቅንነት የተጠየቀ ሳይሆን ፍሬ ለሌለው ክርክር የተጠየቀ በመሆኑ የጥያቄውን ከንቱነት በሚያሳይ ሌላ ጥያቄ ሊመለስ እንጂ ቦታ ሊሰጠው የሚገባ አይደለም።
ፈጣሪማ "እኔ አምላክ ነኝ አምልኩኝ" ይላል፦ ዘዳ.32:39፤ "አሁንም እኔ ብቻዬን እኔ እንደ ሆንሁ፥ ከእኔም በቀር አምላክ እንደሌለ እዩ፤"
ቁርአን 21:92 "እኔም ጌታቸሁ ነኝና ተገዙኝ።"
ዘመነ ብሉይና ዘመነ ሐዲስ ልዩነት ስላላቸው እግዚአብሔር በኹሉም ዘመናት በተመሳሳይ መንገድና ኹኔታ ራሱን መግለጥ የግድ አያስፈልገውም። ጥያቄያችን ሊሆን የሚገባው ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነቱን በምን ዓይነት መንገድ ነው የገለጠው? የሚል እንጂ እኛ በምንፈልገው መንገድ ስላልተናገረ አምላክ አይደለም ብሎ ማለት ትክክል አይደለም።
በቁርአን ውስጥ አላህ "እኔ አምላክ ነኝና አምልኩኝ" ብሎ የተናገረበትን ጥቅስ አላሳየኸንም። የምድር ንጉሥ እንኳ "እኔ ጌታቸሁ ነኝና ተገዙኝ" ብሎ ሊናገር ይችላል።
ኢየሱስ ግን አንድም ገዜ "ኢየሱስ እኔ አምላክ ነኝ አምልኩኝ" አላለም፣ ስለው ልጁ ቀጠል አረገና፦ ዮሐ10:30 ጠቀሰልኝ፣ ደስ የሚለው ነገር ክርስቲኣኖች

ለኢየሱስ ኣምላክነት ብለው የሚጠቅሳቸው ጥቅሶቸ ለእኔ ኢየሱስ ኣምላክ አለመሆን የሚያሳዩ ናቸው፦
ዮሐ.10:30 እኔ እና አብ አንድ ነን።
የጥቅሱ አውድ ኢየሱስ በትክክል አምላክ መሆኑን እየተናገረ እንደሆነ ያሳያል። ይህንንም ከአፍታ በኋላ የምናየው ይሆናል።
ነጥብ አንድ እኔ እና አብ እኔ *i* የሚለው ባለቤት ተውላጠ–ስምና አብ*father* የሚለው የማእረግ ስም እና*and* በሚል አያያዝ መስተጻምር* coplative conjuction* እንደተለየ አስተውል። በስነ–ሰዋሰው ጥናት ከማእረግ ስም በፊት *the* የሚል ጠቃሽ አመልካቸ መስተኣምር*definite article* ካለና ተውላጠ–ስሙ በመስተጻምር ከተለየ ሁለት የተለያየ ማንነቶቸን*persons* ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ነው። ታዲያ ይህ ጥቅስ ኢየሱስ አብ አሊያም አምላክ ሊሆን ይቅርና ከአብ አሊያም ከአምላክ የተለየ መሆኑን ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው።
[coplative conjuction ያለው copulative conjunction ለማለት ፈልጎ ነው፡ ፡ አጻጻፉ ግድፈት አለበት ለማለት ያህል ነው።] ይህ ሰው ገና ከጅምሩ Straw man fallacy የተሰኘውን የሥነ አመክንዮ ተፋልሶ ፈፅሟል። ይህ ተፋልሶ ሞጋቻቸሁ ያልተናገረውን ደካማ ሙግት በመፍጠር ማፈራረስ ማለት ነው። በሥላሴ አስተምህሮ መሠረት አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በአካል ልዩ ሲሆኑ አንድነታቸው በመለኮት ነው። ስለዚህ አብና ወልድ ሁለት ማንነቶቸ ናቸው ነገር ግን በምንነት አንድ ናቸው። ስለዚህ ክርስቲያናዊው አስተምህሮ ከጥቅሱ ጋር የሚስማማ ሆኖ ሳለ ክርስቲያናዊውን አስተምህሮ የሚጻረር ነጥብ ያገኘ ማስመሰሉ ግራ የሚገባ ጉዳይ ነው። ደግሞስ ኢየሱስ አምላክ ለመሆን “አብ” መሆን አለበት ብሎ የሚያምን ሥላሴያዊ ክርስቲያን የለም። በትምህርተ ሥላሴ መሠረት ሦስቱም የሥሉስ ቅዱስ አካላት የአንዱ መለኮታዊ ባሕርይ ተካፋዮቸ በመሆናቸው አንድነታቸው በመለኮት (በምንነት) እንጂ በአካል (በማንነት) አይደለም። ይህ አብዱል ወይ የሥላሴን አስተምህሮ አልተረዳም አለበለዚያም ለሙግት እንዲያመቸው ሲል ትክክለኛውን ነጥብ እያጣመመ ነው።
ነጥብ ሁለት ነን በመቀጠል ነን*are* የሚል የብዜት አያያዝ ግስ*linking verb* ተጠቀመ እንጂ ነኝ *am* አሊያም ነው *is* የሚል አልተጠቀመም ይህም በስነ–ሰዋሰው ጥናት ሁለት የተለያየ ማንነቶቸን *persons* መሆናቸውን ቁልጭ ኣድርጎ ያሳያል።
አሁንም ጸሐፊው የቀደመውን ተፋልሶ ደግሞታል። ክርስቲያኖቸ አብና ወልድ ሁለት አካላት እንደሆኑ እንጂ አንድ አካል እንደሆኑ አያምኑም።
ነጥብ ሶስት አንድ እዚህ ጋር የሚነሳ ትልቁ ነጥብ አብና ወልድ የምን አንድነት ነው ያላቸው? የአላማ? የማንነት? የህላዌ ? ይህን ለማወቅ አንድ የሚለውን ቃል በስነ–ቋንቋ ሙግት ይፈታል፦ A.የማንነት አንድነት *heis* የማንነት አንድነት ማለት የአንድ ቀዋሚ–ማንነት*person* የግሪኩ የሚጠቀምበት ሄእስ ሲሆን በስነ–ሰዋስው ተባታይ ጾታ ነው ይህንን ለአንድ ቀዋሚ–ማንነት*person* ብቻ ነው፦
ማር 12:29 ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው። ከትእዛዛቱ ሁሉ ፊተኛይቱ። እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ ጌታ አምላካቸን አንድ ጌታ ነው፤
ማር 12:32 አንድ ነው ከእርሱም በቀር ሌላ የለም ብለህ በእውነት ተናገርህ፤

1ቆሮ 8:4 ከአንዱም  በቀር ማንም አምላክ እንዴሌለ እናውቃለን።
1ቆሮ 8:6 ለእኛስ ነገር ሁሉ ከእርሱ የሆነ እኛም ለእርሱ የሆንን አንድ  አምላክ አብ አለን፥
ኤፌ 4:6 ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ።
1ጢሞ 2:5 አንድ  እግዚአብሔር አለና፥ ገላ 3:20 መካከለኛውም ለአንድ ብቻ አይደለም እግዚአብሔር ግን አንድ  ነው።
ያዕ 4:12 ሕግን የሚሰጥና የሚፈርድ አንድ  ነው፤
ማር 10:18 ኢየሱስም። ስለ ምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ  ከእግዚአብሔር በቀር ቸር ማንም የለም።
ያዕ2:19 እግዚአብሔር አንድ  እንደ ሆነ አንተ ታምናለህ፤ መልካም ታደርጋለህ፤ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል።
ስለዚህ ካንዱ አምላክ አንድ ቀዋሚ–ማንነት*person* ነው ማለት ነው፣ ምክንያቱም የሚጠቀምበት አያያዥ ግስ ነው*is* እንጂ ናቸው*are* አይደለም። ይህ ጸሐፊ አስተምህሮተ ሥላሴንም ሆነ ሥነ አመክንዮን አያውቅም። በሥላሴ አስተምህሮት መሠረት እግዚአብሔር በሦስት አካላት የሚኖር አንድ መለኮት ነው፡ ፡ ሦስቱም የሥላሴ አካላት የአንዱ ግፃዌ መለኮት አካላት እንጂ ሦስት የተለያዩ አማልክት ስላልሆኑ በተናጠል “አንድ አምላክ” “አንድ ጌታ” “አንድ ፈጣሪ” ወዘተ. ተብለው ሊጠሩ ይችላሉ። ለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አብን “አንድ አምላክ” ባለበት በዚያው ቦታ ወልድን “አንድ ጌታ” ብሎ የጠራው፡- “ለእኛስ ነገር ሁሉ ከእርሱ የሆነ እኛም ለእርሱ የሆንን አንድ አምላክ አብ አለን፥ ነገር ሁሉም በእርሱ በኩል የሆነ እኛም በእርሱ በኩል የሆንን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን።” (1ቆሮ. 8፡6)። በዚህ ቦታ ሐዋርያው የተጠቀመው “ኩሪዮስ” የሚለው የግሪክ ቃል ሰብዓ ሊቃናት ብሉይ ኪዳንን ከእብራይስጥ ወደ ግሪክ ሲተረጉሙ ስመ እግዚአብሔርን እንዲወክል የመረጡት ቃል ነው። በርግጥ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ ክፍል የብሉይ ኪዳንን የአይሁድ “ሼማ” እያብራራ ነው፡- “እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው” (ማር. 12፡29)። ሐዋርያው በአይሁድ ሼማ ውስጥ አንድ አምላክ ለሚለው አብን የጠቀሰ ሲሆን አንድ ጌታ ለሚለው ደግሞ ኢየሱስን ጠቅሷል። ይህም በተለያዩ ሁለት ቃላት አብም ኢየሱስም መለኮት መሆናቸውን የገለጸበት መንገድ ነው። ሐዋርያው ይሁዳም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶን “ብቻውን ያለ ጌታ” በማለት ይጠራዋል፡- “ንጉሣችንንና ጌታችንንም ብቻውን ያለውን ኢየሱስ ክርስቶስን ይክዳሉ” (ይሁዳ 4)። እንዲህ ያሉ የተናጠል አገላለፆች ከሥላሴ አስተምህሮ መሠረታዊ ግንዛቤ ጋር የሚስማሙ እንጂ የሚጣረሱ አይደሉም።
ሌላው የጸሐፊው ችግር የአዲስ ኪዳንን ግሪክ አለማወቁ ነው። በርግጥ አንድ ሰው አዲስ ኪዳንን ለመረዳት የግድ ግሪክ ማወቅ አለበት የሚል ሕግ የለም። ነገር ግን ሌሎችን ለማስተማር እንዲህ ያሉ ጽሑፎችን የሚጽፍ ሰው ቋንቋውን የሚያውቁትን መጠየቅ አለበለዚያም በዘርፉ ምሑራን የተጻፉ መጻሕፍትን ማንበብ ይኖርበታል። ነገር ግን ይህ ጸሐፊ እንዳደረገው ዝም ብሎ ከራሱ እየፈለሰፈ ቢጽፍ ለራሱም ተሳስቶ ሌሎችንም ያሳስታል።
ግሪኩ የአንድ ቀዋሚ-ማንነትን (person) ለማመልከት  (ሄይስ) የሚል ቃል

እንደሚጠቀምና ይህንንም ቃል ለአንድ ቅዋሜ-ማንነት ብቻ እንደሚጠቀም ገልጿል። ይህ ግን ትክክል አይደለም። ቃሉ ነጠላ አንድነትንም ሆነ ብዝሃ አንድነትን ለማመልከት በአዲስ ኪዳን ውስጥ ጥቅም ላይ ውሏል፡- "አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፤ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፤ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ (ሄይስ) ሰው ናችሁና" (ገላ. 3፡28)። ይህ ማለት አማኞች በክርስቶስ ባላቸው ሕብረት አንድ ይሆናሉ ማለት እንጂ ተጨፍልቀው ነጠላ አንድነት ይኖራቸዋል ማለት አይደለም። ስለዚህ "ሄይስ" የሚለው ቃል የማንነት አንድነትን እንደሚገልፀው ሁሉ የሕብረት አንድነትንም ይገልፃል። እናም ከዚህ ቃል በመነሳት እግዚአብሔር በአካል ነጠላ እንደሆነ መናገር አይቻልም።
የህላዌ አንድነት*mia* የህላዌ አንድነት ማለት የአንድ ተፈጥሮ *essence* የግሪኩ የሚጠቀምበት ሚአ µ ሲሆን በስነ ሰዋስው ኣንስታይ ጾታ ነው ይህንን ለተፈጥሮ አንድነት ነው፦ ማቴ 19:5 አለም፦– ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፥ ሁለቱም አንድ µ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን?
ማቴ 19:6 ስለዚህ አንድ µ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደ ፊት ሁለት አይደሉም። እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው።
"ሚኣን" የሚለው የግሪክ ቃል ጸሐፊው በጠቀሳቸው ጥቅሶች ውስጥ የህላዌ አንድነትን ለማሳየት የዋለ ቢሆንም በሌሎች ብዙ ቦታዎች የቁጥርና የዓላማ አንድነትን ለማመልከት ስለዋለ ጸሐፊው ቃሉን በዚህ መወሰኑ ጥናት አለማድረጉን ያመለክታል። ጥቂት ምሳሌዎችን ለመጥቀስ ያህል፡-
ነጠላ ቁጥርን ለማመልከት፡- "ጴጥሮስም መልሶ ኢየሱስን፦ ጌታ ሆይ፥ በዚህ መሆን ለእኛ መልካም ነው፤ ብትወድስ፥ በዚህ ሦስት ዳስ አንዱን (ሚኣን) ለአንተ አንዱንም (ሚኣን) ለሙሴ አንዱንም (ሚኣን) ለኤልያስ እንሥራ አለ።" (ማቴ. 17፡ 4)
አንድ ማንነትን ለማመልከት፡- "እንግዲህ ኤጲስ ቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባዋል፤ የማይነቀፍ፥የአንዲት(ሚኣስ µ )ሚስት ባል፥ልከኛ፥ራሱን የሚገዛ፥እንደሚገባው የሚሰራ፥ እንግዳ ተቀባይ፥ ለማስተማር የሚበቃ" (1ጢሞ. 3፡2)። "ሁለት ሴቶች በወፍጮ ይፈጫሉ፤ አንዲቱ (ሚኣ µ ) ትወሰዳለች አንዲቱም (ሚኣ µ ) ትቀራለች።" (ማቴ. 24፡41)
የዓላማ አንድነትን ለማመልከት፡- "እግዚአብሔር አሳቡን እንዲያደርጉ አንድንም (ሚኣን) አሳብ እንዲያደርጉ የእግዚአብሔርም ቃል እስኪፈጸም ድረስ መንግሥታቸውን ለአውሬው እንዲሰጡ በልባቸው አግብቶአልና።" (ራዕይ 17፡ 17)
የሕብረት አንድነትን ለማመልከት፡- "ከዚህም በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ፤ እነርሱን ደግሞ ላመጣ ይገባኛል ድምፄንም ይሰማሉ፥ አንድም መንጋ (ሚኣን ፖይሜን) ይሆናሉ እረኛውም አንድ (ሄይስ)" (ዮሐ. 10፡16)።
የአላማ አንድነት*hen* የአላማ አንድነት የግሪኩ የሚጠቀምበት ሄን ሲሆን በስነ–ሰዋስው ግዑዝ ጾታ ነው ይህንን ለአላማ የሚጠቀምበት አንድነት ነው፦
1ቆሮ 3:6 እኔ ተከልሁ አጵሎስም አጠጣ ነገር ግን እግዚአብሔር ያሳድግ ነበር፤
1ቆሮ 3:8 የሚተክልና የሚያጠጣ አንድ ናቸው፥
በተመሳሳይ "ሄን" የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥርን፣ የዓላማ አንድነትንም ሆነ

የሕብረት አንድነትን ለማመልከት ጥቅም ላይ ውሏል።
ነጠላ ቁጥር፡- “እርሱ ግን፦ ከእናንተ አንድ (ሄን ) በግ ያለው በሰንበት በጕድጓድ ቢወድቅበት፥ ይዞ የማያወጣው ሰው ማን ነው?” (ማቴ. 12፡11)
አንድ ማንነት፡- “እንደዚህም ያለውን አንድ (ሄን ) ሕፃን በስሜ የሚቀበል ሁሉ እኔን ይቀበላል” (ማቴ. 18፡5)። “አካልም አንድ (ሄን) እንደ ሆነ ብዙም ብልቶች እንዳሉበት ነገር ግን የአካል ብልቶች ሁሉ ብዙዎች ሳሉ አንድ (ሄን) አካል እንደ ሆኑ፥ ክርስቶስ ደግሞ እንዲሁ ነው” (1ቆሮ. 12፡12)
አንድ ሕብረትን፡- “እንዲሁ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ (ሄን ) አካል ነን፥ እርስ በርሳችንም እያንዳንዳችን የሌላው ብልቶች ነን።” (ሮሜ 12፡5)
ታዲያ የአብና የወልድ የምን አንድነት ነው የሚጠቀምበት? ስንል ሄን የሚለውን ነው፤ ይህም የአላማ አንድነት እንጂ ሥላሴአውያን እንደሚሉት የህላዌ አሊያም አፖስተሊኮች እንደሚሉት የአካል አይደለም።
በአዲስ ኪዳን ውስጥ አንድነትን ለመግለፅ ጥቅም ላይ የዋሉት ሁሉም ቃላት የተለያዩ ትርጉሞች እንዳላቸው ተመልክተናል። ስለዚህ የቃላቱን ትርጉም የሚወስነው የተጠቀሱበት አውድ እንጂ ወጥ የሆነ ትርጉም ኖሯቸው እንዲህ ብቻ ነው ብለን የምናስቀምጠው ምንም ነገር የለም። ስለዚህ ኢየሱስ በዮሐንስ 10፡30 ላይ ምን እያለ እንደሆነ አውዱን በመመልከት መረዳት ይኖርብናል። ጥቅሱን በአውድ ውስጥ እናንብበው፡-
“በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ እኔም አውቃቸዋለሁ ይከተሉኝማል፤ እኔም የዘለዓለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ፥ ለዘለዓለምም አይጠፉም፥ ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም። የሰጠኝ አባቴ ከኹሉ ይበልጣል፥ ከአባቴም እጅ ሊነጥቃቸው ማንም አይችልም። እኔና አብ አንድ ነን። አይሁድ ሊወግሩት ደግመው ድንጋይ አነሡ።” (ዮሐ. 10፡27-31)።
በዚህ ክፍል ጌታችን ኢየሱስ የሚከተሉትን ነጥቦች ግልፅ አድርጓል፡-

- የዘለዓለምን ሕይወት ይሰጣል (ቁ. 28)
- በጎቹን (ምዕመናንን) ማንም ከእጁ መንጠቅ አይችልም (ቁ. 28)
- እነርሱን የሰጠው አባቱ ከነጣቂዎቹ ኹሉ ይበልጣል፤ እርሱና አብ ደግሞ አንድ በመሆናቸው ከአብ እጅ መንጠቅ እንደማይችሉት ሁሉ ከእርሱም እጅ መንጠቅ አይችሉም (ቁ. 29 እና 30)

ከእርሱም ሆነ ከአብ እጅ በጎቹን ማንም መንጠቅ እንደማይችል ከተናገረ በኋላ እርሱና አብ አንድ እንደሆኑ በማሳወቅ በባሕርይ የተካከሉ መሆናቸውን ግልፅ አድርጓል (ዮሐ. 10፡30)። ይህ አንድነት የኃይል አንድነትን የሚገልፅ ነው። አብና ኢየሱስ በኃይል አንድ ናቸው። ለዚህ ነው ማንም በጎቹን ከአብ እጅ መንጠቅ እንደማይችል ኹሉ ከኢየሱስም እጅ መንጠቅ የማይችለው። በተጨማሪም በዚሁ ቦታ ላይ ለበጎቹ የዘለዓለምን ሕይወት እንደሚሰጥ በመናገር አምላክነቱን የበለጠ ግልፅ አድርጓል (ቁ.28)። ከአምላክ በስተቀር የዘለዓለምን ሕይወት መስጠት የሚችል አለን? ከዚህ ንግግር በኋላ አይሁድ ሊወግሩት ድንጋይ ያነሱት ኢየሱስ አምላክ መኾኑን እየተናገረ መኾኑ ስለገባቸው ነበር፡-
“አይሁድም፦ ስለ መልካም ሥራ አንወግርህም፤ ስለ ስድብ፤ አንተም ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ስለ ማድረግህ ነው እንጂ ብለው መለሱለት” (ቁ.31-33)።
ስለዚህ ከአውዱ ግልፅ ሆኖ እንደሚታየው የአብና የኢየሱስ አንድነት የመለኮት

ነው።
ዮሐ 17:11 ከዚህም በኋላ በዓለም አይደለሁም፥ እነርሱም በዓለም ናቸው፥ እኔም ወደ አንተ እመጣለሁ። ቅዱስ አባት ሆይ፥ እነዚህን የሰጠኸኝን እንደ እኛ አንድ እንዲሆኑ በስምህ ጠብቃቸው። ዮሐ 17:22-23 እኛም አንድ*hen* እንደ ሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ፤
ሃዋርያት ከሌላው ማህበረሰብ በተለየ መልኩ ያላቸው ኣንድነት እንደ ኣብና ወልድ የአላማ ኣንድነት ነው *እንደ እኛ አንድ እንዲሆኑ* የሚል መመሳሰል ኢየሱስ ይጠቀማል።
ኢየሱስ ዮሐንስ 10፡30 ላይ “እኔና አብ አንድ ነን” ብሎ የተናገረው ስለ ኃይል አንድነት እንጂ ስለ ዓላማ አንድነት እየተናገረ ባለመኾኑ በዮሐንስ 17 ላይ ለሐዋርያቱ ከተነገረው አንድነት ጋር ማመሳሰል ትክክለኛውን የሥነ ፍታቴ ሥርኣት የጠበቀ አይደለም። የሁለቱ አውድ ለየቅል ናቸው።
መደምደሚያ ሰውና አምላክ ሁለት የተለያዩ ህልውናዎች እና ማንነቶች ናቸው። ኢየሱስና እግዚአብሔር ደግሞ የህላዌ ሆነ የማንነት ልዩነት እንዳላቸው ከኢየሱስና ከመፅሐፉ ኣንደበት ይደመጣል፦ ዮሐ 7:16-17 ስለዚህ ኢየሱስ መለሰ እንዲህም አላቸው። ትምህርቴስ ከላከኝ ነው እንጂ ከእኔ*myself* አይደለም፤ ፈቃዱን ሊያደርግ የሚወድ ቢኖር፥ እርሱ ይህ ትምህርት ከእግዚአብሔር ቢሆን ወይም እኔ ከራሴ*myself* የምናገር ብሆን ያውቃል።
ጌታችን ኢየሱስ መለኮታዊ ክብሩን በመተው ሰው ሆኖ ወደ ምድር እንደመጣ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል። በማንነቱ አምላክ ቢሆንም ነገር ግን ሰብዓዊ ባሕርይን በመላበስ ወደ ምድር መጥቷል። ስለዚህ ይህንን ጥቅስ ኢየሱስ መለኮታዊ ክብሩን በመተው ራሱን ባዶ አድርጎ የባርያን መልክ ይዞ መምጣቱን በሚናገረው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምሕርት አውድ መረዳት አስፈላጊ ነው (ፊልጵስዩስ 2፡5-11)፡ ፡ ኢየሱስ ራሱን ለማክበርና ከፍ ከፍ ለማድረግ ስላልመጣ በአምላካዊ ባሕርዩ ሳይኾን በሰብዓዊነቱ በሰዎች ፊት ለመታየትና ለማገልገል በመወሰኑ ምክንያት ፍጹም ሰው ኾኖ ተመላልሷል። ይህንንም በቀጣዩ ቁጥር ላይ አስታውቋል፡-
“ከራሱ የሚናገር የራሱን ክብር ይፈልጋል፤ የላከውን ክብር የሚፈልግ ግን እርሱ እውነተኛ ነው በእርሱም ዓመፃ የለበትም።” (ቁ.18)።
ኢየሱስ የራሱን ክብር ለመፈለግ አለመምጣቱን ከአብ የሰማውን ብቻ በመናገር አሳይቷል። ይህ አምላክነቱን ለማስተባበል የሚበቃ ሙግት አይደለም።
ዮሐ 14:1 ልባችሁ አይታወክ፤ በእግዚአብሔር እመኑ፥ በእኔም ደግሞ እመኑ።
በአዲስ ኪዳን ውስጥ አውዱ ካላመለከተ በስተቀር “እግዚአብሔር” ከተባለ የተጠቀሰው የሥላሴ አካል አብ ነው። ስለዚህ በዚህ ቦታ ላይ ኢየሱስ ሐዋርያቱ በእርሱና በአብ እንዲያምኑ መጠየቁ አምላክነቱን የሚያሳይ እንጂ የሚፃረር አይደለም።
ዮሐ 5:31-32 እኔ ስለ እኔ ስለ ራሴ*myself* ብመሰክር ምስክሬ እውነት አይደለም፤ ስለ እኔ የሚመሰክር ሌላ ነው፥ እርሱም*HE* ስለ እኔ የሚመሰክረው ምስክር እውነት እንደ ሆነ አውቃለሁ።
በአይሁድ ሕግ መሠረት አንድ ሰው ብቻውን ስለ ራሱ መመስከር አይችልም። እውነተኛነቱን ለማረጋገጥ ሁለተኛ ወገን ያስፈልገዋል። ስለዚህ ኢየሱስ ይህንን የተናገረው ከአይሁድ ሕግ አኳያ ነው እንጂ ዮሐንስ 8፡18 ላይ ስለ ራሱ መመስከር

እንደሚችል ተናግሯል። አብ በተለያዩ መንገዶች ስለ ማንነቱ ስለመሰከረለት የኢየሱስ ምስክርነት የአይሁድን ሕግ ያሟላል። እናም በዘመኑ የነበሩት አይሁድ የኢየሱስ ምስክር ራሱ ኢየሱስ ብቻ ነው የሚል ማመካኛ የላቸውም። የሆነው ሆኖ አብ ሥጋ ለብሶ ወደ ምድር ስላልመጣ አንድያ ልጁ መመስከሩ ልጁን ከአምላክነት ደረጃ ዝቅ አያደርገውም።

ዮሐ 8:18 ስለ ራሴ የምመሰክር እኔ ነኝ፣ የላከኝም አብ ስለ እኔ ይመሰክራል።

አብና ኢየሱስ በአካል ልዩ በመለኮት ግን አንድ ናቸው። ኢየሱስ ለአብ መመስከሩና አብም ለኢየሱስ መመስከሩ የአብና የኢየሱስን ማንነት የሚደባልቁ የኑፋቄ አስተምህሮዎችን ውድቅ የሚያደርግና የሥላሴን አስተምህሮ የሚያጸና እንጂ የኢየሱስን አምላክነት የሚጻረር አይደለም።

ስለዚህ መደምደሚያችን ይህ ከሆነ ዮሐ 10:30 እኔና አብ አንድ ነን። የሚለው ንግግር የኢየሱስ ኣምላክነት አሊያም አብ መሆን የሚያሳይ ኣይደለም በቂ መረጃ ይዛችሁ ኑ።

መጽሐፍ ቅዱሳቸውን የሚያውቁ አማኞች ኢየሱስ አብ ነው አይሉም። አንተ እንዳደረከው ጥቅሶችን ከአውድ ነጥሎ በማውጣትና ትርጉም አልባ የቃላት ስንጠቃ ውስጥ በመግባትም የኢየሱስን አምላክነት አይክዱም። የኢየሱስን አምላክነት በማወጅ ከሚጀምረውና ከሚደመድመው ወንጌል ውስጥ አምላክነቱን የሚጻረር ሐሳብ መፈለግህ በራሱ ምን ያህል ግራ እንደገባህ አመላካች ነው። በአንድ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙትን ሐሳቦች መገንዘብ ያለብን በመግቢያውና ማጠቃለያው ላይ በተገለጸው ጭብጥ መሠረት እንጂ በዘፈቀደ አይደለም። ዮሐንስ የኢየሱስን አምላክነት በማወጅ ይጀምራል፦

“በመጀመሪያው ቃል ነበረ፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፣ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ። ሁሉ በእርሱ ሆነ፣ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም።” (ዮሐ. 1፡1-2)

መቋጫውንም ያደረገው አምላክነቱን በማረጋገጥ ነው፦

“ቶማስም ጌታዬ አምላኬም ብሎ መለሰለት። ኢየሱስም፦ ስለ አየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው አለው።” (ዮሐ. 20፡28-29)።

ሙስሊሙ ወገኔ ዛሬ አምላክነቱን ለመካድ ራስህን የምታደክመው ኢየሱስ ክርስቶስ ፈጣሪህና የእስትንፋስህ ምንጭ ቢሆንስ? ዛሬ አምላኬ አይደለም ብለህ የካድከው ኢየሱስ ለፍርድ ተመልሶ ቢመጣና በፊቱ ብትቆምስ?

“እነሆ፣ በቶሎ እመጣለሁ፣ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ። አልፋና ዖሜጋ፣ ፊተኛውና ኋለኛው፣ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ።” (ራዕይ 22፡12-13)

ሙስሊሙ ወገኔ እስኪ ላንድ አፍታ ቆም በልና እውነቱን እንዲገልጥልህ በትህትና ጠይቀው። ግድ የለም “ፈጣሪዬ ከሆንክ የልብ ዓይኔን አብራልኝና ልወቅህ” ብለህ ጠይቀው፡

## የሴቶች ምስክርነት በእስልምና
## እውን የሴት ምስክርነት የወንድ ግማሽ አይደለምን?

የሙስሊሞች ቅዱስ መጽሐፍ የሆነው ቁርኣን የሴቶች ምስክርነት የወንዶችን ምስክርነት ግማሽ ያህል ዋጋ እንዳለው ይናገራል፦

“እናንተ ያመናችሁ ሆይ! እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ በዕዳ በተዋዋላችሁ ጊዜ ጻፉት። ጸሐፊም በመካከላችሁ በትክክል ይጻፍ። ጸሐፊም አላህ እንደ አሳወቀው መጻፍን እንቢ አይበል። ይጻፍም። ያም በርሱ ላይ ዕዳው ያለበት ሰው በቃሉ ያስጽፍ። አላህንም ጌታውን ይፍራ። ከእርሱም (ካለበት ዕዳ) ምንንም አያጉድል። ያም በርሱ ላይ ዕዳው ያለበት ቂል፣ ወይም ደካማ፣ ወይም በቃሉ ማስጻፍን የማይችል ቢኾን ዋቢው በትክክል ያስጽፍለት። ከወንዶቻችሁም ሁለትን ምስክሮች አስመስክሩ። ሁለትም ወንዶች ባይኾኑ ከምስክሮች ሲኾኑ ከምትወዱዋቸው የኾኑን አንድ ወንድና አንደኛዋ ስትረሳ አንደኛይቱ ሌላዋን ታስታውሳት ዘንድ ሁለት ሴቶች (ይመስክሩ)። ምስክሮችም በተጠሩ ጊዜ እንቢ አይበሉ።(ዕዳው) ትንሽ ወይም ትልቅ ቢኾንም እስከ ጊዜው ድረስ የምትጽፉት ከመኾን አትሰልቹ። እንዲህ ማድረጋችሁ አላህ ዘንድ በጣም ትክክል ለምስክርነትም አረጋጋጭ ላለመጠራጠራችሁም በጣም ቅርብ ነው። ግን በመካከላችሁ እጅ በጅ የምትቀባበሏት ንግድ ብትኾን ባትጽፉዋት በናንተ ላይ ኃጢኣት የለባችሁም። በተሻሻጣችሁም ጊዜ አስመስክሩ። ጸሐፊም ምስክርም (ባለ ጉዳዩ ጋር) አይጎዳዱ። (ይህንን) ብትሠሩም እርሱ በእናንተ (የሚጠጋ) አመጽ ነው። አላህንም ፍሩ። አላህም ያሳውቃችኋል። አላህም ነገሩን ሁሉ ዐዋቂ ነው።” ሱረቱ አል በቀራ (የላም ምዕራፍ) 2፡282

ከቁርኣን ረጃጅም አንቀፆች መካከል አንዱ በሆነው በዚህ አንቀፅ ውስጥ በግልፅ እንደተቀመጠው የሁለት ሴቶች ምስክርነት ከአንድ ወንድ ምስክርነት ጋር እኩል ነው። ለዚህ ደግሞ እንደ ምክንያት የተቀመጠው የሴቶች የማስታወስ ችሎታ ነው። የዓለም ሕዝቦች የሴትን ልጅ የከበረ ተፈጥሯዊ ዋጋ በመረዳት ለእኩልነቷ እየታገሉ በሚገኙበት በዚህ የሰለጠነ ዘመን እንዲህ ያለው አስተሳሰብ ተቀባይነት የለውም። በዚህም ምክንያት እስልምና በዘመናዊው ዓለም ውስጥ ተቀባይነት እንዲኖረው ጥረት እያደረጉ የሚገኙት ሙስሊም ሰባኪያን ይህንን ቁርአናዊ አስተምሕሮ በማድበስበስ እስልምና የሴትን ልጅ እኩልነት የተገነዘበና የተቀበለ ሃይማኖት ለማስመሰል ሲታትሩ ይስተዋላሉ። ከላይ የሚገኘውን የቁርኣን አንቀፅ በተለየ መንገድ ለመተረጎም ሲሞክሩና በእስልምና የሴቶች ምስክርነት ከወንዶች እኩል መሆኑን “ማስረጃዎችን” በመስጠት ለማሳመን ሲውተረተሩ ማየትም የተለመደ ነው።

እነዚህ ወገኖች ገና ከጅምሩ በጥቅሱ ውስጥ “አንደኛዋ ስትረሳ” ተብሎ የተተረጎመው (ተዲላ) የሚለው የአረብኛ ቃል መርሳትን ሳይሆን መሳሳትን የሚያመለክት በመሆኑ ከሴት ልጅ የማስታወስ ችሎታ ጋር እንደማይያያዝ ይናገራሉ። የእነዚህ ወገኖች ስህተት ቀጥሎ የተቀመጠውንና ለቃሉ አውድ ሰጪ የሆነውን “ፈቱዘኪረ” የሚለውን ቃል ልብ አለማለታቸው ነው። “ፈቱዘኪረ” “እንድታስታውሳት” የሚል ትርጉም ያለው ሲሆን በመርሳት ሰበብ የሚፈጠረውን ስህተት ለማረም ማስታወስን የተመለከተ ነው። ስለዚህ የሴቷ ስህተት ከመርሳት የሚመነጭ በመሆኑ አንቀፁ እየተናገረ ያለው ስለ ሴት ልጅ የማስታወስ ችሎታ ነው። ኢብን ከሢር የተሰኘው የቁርኣን ሐታቾ ይህንን አንቀፅ በዚሁ መንገድ አብራርቶታል።[1]

በሁለተኛ ደረጃ እነዚህ ወገኖች ከላይ የተቀመጠው አንቀፅ ገንዘብ ነክ ጉዳዮችን የተመለከተ በመሆኑ በእስልምና የሴቶች ምስክርነት ከወንዶች በእጥፍ የሚያንሰው በገንዘብ ነክ ጉዳዮች ረገድ ብቻ እንደሆነ ይናገራሉ። ሴቶች በገንዘብ

ነክ ጉዳዮች ከወንዶች ያነሰ ዕውቀት ስላላቸው በዚህ ሁኔታ ለምስክርነት ተመራጭ አይደሉም ይላሉ። በመጀመርያ ደረጃ ሁለት ቡድኖች የገንዘብ ብድር ውል ሲፈፅሙ አይቶ መመስከር የፋይናንስ ሊቅ መሆንን አይጠይቅም። መሠረታዊ የሰው ልጅ የማስታወስ ችሎታ በቂ በመሆኑ ይህንን አይረቤ ምክንያት በመጥቀስ ሴትን ልጅ በሕግ ፊት የእኩልነትን ደረጃ መንፈግ ትክክል አይደለም። ይህ ሙግት ተቀባይነት የማያገኝበት ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ ሙሐመድ ለጥቅሱ የሰጠው ማብራርያ ነው። በሙሐመድ እምነት መሠረት የሴት ልጅ ምስክርነት ከወንድ በእጥፍ የሚያንስበት ምክንያት የሴት ልጅ የማሰብ ችሎታ ከወንዶች በእጥፍ ያነሰ በመሆኑ ነው። ሳሂህ አል-ቡኻሪ ውስጥ ሙሐመድ እንዲህ ማለቱ ተነግሯል፡-

“ሴቶች ሆይ ምፅዋት ስጡ የገሃነም አብዛኞቹ ነዋሪዎች ሴቶች መሆናቸውን አይቻለሁና። ‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ ለምንድነው?› ብለው ጠየቁት። ‹ብዙ ጊዜ ትሳደባላችሁ፤ ለባሎቻችሁም ምስጋና ትነፍጋላችሁ። በዕውቀትና በሃይማኖት ከእናንተ በከፋ ሁኔታ ጎዶሎ የሆነ አላየሁም›... ሴቶቹም እንዲህ ብለው ጠየቁ፡- ‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ በዕውቀትና በሃይማኖት ጎዶሎዎች የሆንነው እንዴት ነው?› እርሱም ‹የሁለት ሴቶች ምስክርነት ከአንድ ወንድ ምስክርነት ጋር እኩል አይደለምን?› በማለት ጠየቃቸው። እነርሱም በአዎንታ መለሱ። ‹ይህ በዕውቀት ጎዶሎዎች መሆናችሁን ያሳያል። ሴት በወር አበባ ጊዜዋ መጸለይም ሆነ መፆም አለመቻሏ እውነት አይደለምን?› ብሎ ጠየቃቸው። ሴቶቹም በአዎንታ መለሱ። ‹ይህ በሃይማኖት ጎዶሎ መሆናችሁን ያሳያል› በማለት መለሱላቸው።”[2]

በሙሐመድ መረዳት መሠረት የሴት ልጅ ምስክርነት ከወንድ በእጥፍ ያነሰው የአስተሳሰብ ጉድለት ስላለባት ነው። ይህ ሐዲስ በአጠቃላይ ጉዳዮች የሴት ምስክርነት ከወንድ በእጥፍ ያነሰ መሆኑንም ያስረዳል። ስለዚህ የቁርአኑ አንቀፅ በገንዘብ ነክ ጉዳዮች ብቻ የተወሰነ መሆኑንና የሴትን ልጅ የማስታወስ ችሎታ እንደማይመለከት የሚነግሩን ሙስሊም ሰባኪያን ከሙሐመድ የላቀ ቁርኣንን የመተንተን ሥልጣንና ዕውቀት ኖሯቸው እንደሆን ይንገሩን። የሙስሊም ሰባኪያን ሙግቶች ሁሉ የእምቧይ ካብ ሆነው ጫወታው እዚህ ጋ ያከተመ ቢሆንም ሌሎች የሙግት ነጥቦቻቸው እስከ ምን እንደሚያስኬዷቸው እንመልከት።

እነዚህ ወገኖች የሚያነሱት ሦስተኛው ነጥብ ቁርኣን የአንዲት ሴት ምስክር ከአንድ ወንድ ምስክርነት ጋር እኩል መሆኑን የገለጸበት ቦታ አለ የሚል ነው። ለዚህም ተከታዩን ጥቅስ ይጠቅሳሉ፡-

“እነዚያም ሚስቶቻቸውን (በዝሙት) የሚሰድቡ ለእነሱም ከነፍሶቻቸው በስተቀር ምስክሮች የሌሏቸው የኾኑ የአንዳቸው ምስክርነት እርሱ ከውነተኞች ለመኾኑ በአላህ ስም አራት ጊዜ ምሎ መመስከር ነው።” (ሱራ 24፡6)

ይህ ጥቅስ ባል ሚስቱን በምንዝርና በመጠርጠር ቢከሳትና ለጉዳዩ ምስክር ባይኖር እርሷም እርሱም እውነት መናገራቸውን አራት ጊዜ በመማል መመስከር እንደሚችሉ ይናገራል። ይህ ትዕዛዝ የሴቷ የማሰብ ችሎታ ከወንዱ እኩል መሆኑን በመቀበል ላይ የተመሠረተ ሳይሆን የአስገዳጅ ሁኔታ ትዕዛዝ ነው። ምስክር ከሌለ የተገኘውን ምስክር እንደ በቂ በመቁጠር አስገዳጁን ሁኔታ ከመዳኘት ውጪ አማራጭ የለም። ስለዚህ ከዚህ ጥቅስ በመነሳት ቁርኣን የሴትና የወንድ ምስክርነት እኩል እንደሆነ እንደሚያስተምር መናገር አይቻልም።

እነዚህ ወገኖች የሚያቀርቡት አራተኛው ሙግት አይሻ የዘገበቻቸው 2250 የሚሆኑ ሐዲሳት ተቀባይነት ማግኘታቸው የሴት ልጅ ምስክርነት ከወንድ እኩል ተቀባይነት እንዳለው ያመለክታል የሚል ነው። ይህ ሙግት በሦስት ምክንያቶች ውድቅ ነው። የመጀመርያው የአይሻ ምስክርነት ተቀባይነትን እንዲያገኝ ሙሐመድ በልዩ ሁኔታ ማዘዙ ነው። እንዲያውም መገለጥ የሚወርድለት በአይሻ ልብስ ውስጥ ሲሆን እንደሆነ እስከመናገር ደርሷል።[3] ይህም ሙሐመድ ለእርሱ ለቀረቡት ሴቶች አድልዎ ማድረጉን እንጂ በእስልምና ሴት ልጅ ከወንድ ጋር እኩል መታየቷን አያመለክትም። ሙሐመድ ለእርሱ ቅርበት ለነበራቸው ሴቶች ሲያደላ የመጀመርያው አይደለም። ልጁ ፋጢማ ላይ ድርብ ጋብቻ እንዳይፈፅም ለአሊ ፅኑ ማስጠንቀቂያ ሲሰጥ እንመለከታለን።[4] ይህ እስከ አራት ማግባትን የሚፈቅደውን ቁርአናዊ ትዕዛዝ ከመጣስም ባለፈ የሙሐመድን አድሎአዊ አመለካከት በግልፅ የሚያሳይ ነው። በመሆኑም አይሻ ብዙ ሐዲሳትን መዘገቧ የሙሐመድ ሚስት በመሆኗ ምክንያት አድሎ እንደተደረገላት የሚያሳይ እንጂ ሙስሊም ሴቶችን የሚወክልና በእስልምና ሴቶች ከወንዶች የተስተካከለ ደረጃ እንዳላቸው የሚያሳይ አይደለም።

ይህ ሙግት ውድቅ የሚሆንበት ሁለተኛው ምክንያት በሴቶች የተዘገቡት ሐዲሳት መጠን በወንዶች ከተዘገቡት ጋር ሲስተያይ ኢምንት መሆኑ ነው። አይሻን ብቻ ነጥለን ባንመለከትና በሴቶች የተዘገቡትን በወንዶች ከተዘገቡት ጋር ብናነፃፅር የምናገኘው ቁጥር የወንዶችን ፍፁማዊ የበላይነት የሚያሳይ በመሆኑ ሙግቱን ውድቅ ያደርገዋል።

ሦስተኛው ምክንያት ደግሞ የአይሻ ትውስታ ከፍተኛ መሆኑና ይህን ያህል የሚበዙ ታሪኮችን ማስተላለፍ መቻሏ ሴት ልጅ ዕድሉን ብታገኝ ምን ያህል ታላላቅ ሥራዎችን መሥራት እንደምትችል በማረጋገጥ የሴትን ልጅ አእምሯዊ ብቃት ዝቅ አድርጎ የሚመለከተውን እስላማዊ አስተሳሰብ ፉርሽ ማድረጉ ነው። በሙሐመድ አድሎ ዕድሉን በማግኘቷ ምክንያት ብዙ ተግባራትን መፈፀም የቻለችው አይሻ ሴቶች የማሰብ አቅማቸው ከወንዶች እንደማያንስ ጥሩ ምሳሌ ናት። ስለዚህ ይህ ሙግት በቁርኣንም ሆነ በሌሎች እስላማዊ መጻሕፍት ውስጥ የሰፈሩት የሴትን ልጅ ችሎታና ሚና ዝቅ አድርገው የሚያሳዩት ሐሳቦች ሁሉ ስህተት መሆናቸውን ከማሳየት በዘለለ እስልምና ሴት ልጅ ያላትን የላቀ ዋጋ መቀበሉን የሚያሳይ ሙግት ሊሆን አይችልም።

እነዚህ ወገኖች እንደ መጨረሻ የሙግት ሐሳብ የሚያነሱት በእስልምና ሴቶች የረመዳን ፆም መግባቱንና መውጣቱን የምታበስረዋ ጨረቃ መታየቷን ቢመሰክሩ ምስክርነታቸው ተቀባይነት አለው የሚል ነው። የአንዲት ሴት ምስክርነት ከእስልምና መሠረቶች በአንዱ ላይ ተቀባይነት አግኝቶ የዓለም ህዝብ ፆሙን እንደሚጀምርና እንደሚፈፅምም በመናገር ሁኔታውን አግዝፈው ለማሳየት ይሞክራሉ።

የነዚህ ወገኖች ትልቁ ስህተት በዚህ ጉዳይ ላይ ሙስሊም ሊቃውንት ከስምምነት የደረሱ በማስመሰል መናገራቸው ነው። ሴት ልጅ የጨረቃን መውጣት መመስከር እንደምትችል የሚቀበሉት የሀነፊና ሐንበሊ ቤተ እምነቶች ሊቃውንት በደመናማ ቀን ምስክርነቷ ተቀባይነት እንዳለውና በሌላ ቀን ግን ተቀባይነት እንደማይኖረው ይናገራሉ። የሻፊ ቤተ እምነት ሊቃውንት በደመናማ ቀን መመስከር መቻሏን

እንደ አንድ አመለካከት ዕውቅና በመስጠት ነገር ግን ትክክለኛው አመለካከት መመስከር አትችልም የሚለው እንደሆነ ያስተምራሉ፡፡ የሀነፊ ቤተ እምነት ሊቃውንት እንዲያውም በደመናማ ቀን የሁለት ወንዶች ወይንም የአንድ ወንድና የሁለት ሴቶች ምስክርነት ብቻ ተቀባይነት ያለው መሆኑን፤ በጠራ ሰማይ ግን ብዙ ሰዎች ምስክርነታቸውን መስጠታቸው ግዴታ መሆኑን ያስተምራሉ፡፡
የማሊኪ ቤተ እምነት ሊቃውንት ግን በዚህ ረገድ የሴት ልጅ ምስክርነት ተቀባይነት ሊኖረው እንደማይችል የሚያስተምሩ ሲሆን በሻፊዎች አስተምሕሮ መሠረት ትክክለኛው አመለካከት እርሱ ነው፡፡
ፆም ፍቺ መድረሱን ወይንም የሸዋል ወር መግባቱን የምታበስረዋን ጨረቃ አይቶ በመመስከር ረገድ ግን የሴት ምስክርነት በምንም ዓይነት መንገድ ተቀባይነት እንደሌለውና ወንዶች ብቻ መመስከር እንደሚችሉ ሁሉም የእስልምና ቤተ እምነቶች ሊቃውንት ይስማማሉ፡፡ በዚህ ላይ ያለውን አጠቃላይ እስላማዊ ድንጋጌ ከታች በተቀመጠው ኢፊሴላዊ የእስልምና የፋትዋ ድረገፅ ላይ ማየት ይቻላል፡፡[5]
ፆምን ለመጀመር የአንዲት ሴት ምስክርነት ተቀባይነት እንዳለው የሚያምኑ ጥቂት ሊቃውንት ጨረቃ መታየቷን መመስከር መረጃ መስጠት እንጂ ሃይማኖታዊ ትዕዛዝን ማስተላለፍ ባለመሆኑ የሴቷን ምስክርነት መስማት ችግር የለውም ከሚል አመለካከት በመነሳት እንጂ የሴትን ልጅ እኩልነት ከመቀበል አይደለም፡፡[6]
የዚህ ሙግት ሌላው ችግር በእስላማዊ ሐዲሳት ውስጥ ከሚገኙት ከ 25 በላይ ዘገባዎች መካከል ሴት ልጅ የረመዳንን ጨረቃ ዐይታ መመስከር እንደምትችል የሚጠቁም አንድም ዘገባ አለመኖሩ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የሴትን ልጅ ምስክርነት የሚቀበሉት ሊቃውንት ከሙሐመድ የተገኘ ማስረጃ የላቸውም፡፡
እንግዲህ በዝርዝር እንደተመለከትነው በእስልምና የሴት ልጅ ምስክርነት ከወንድ ልጅ ምስክርነት ጋር እኩል መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ የለም፡፡ ከሙሐመድና ከብዙ ሙስሊም ሊቃውንት የተገኙት ማስረጃዎች በሙሉ የሴት ልጅ ምስክርነት ከወንድ በእጥፍ ያነሰ መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ ሙሐመድ የሴቶች አእምሯዊ ብቃት ከወንዶች ያነሰ መሆኑን ማመኑ ነው፡፡ ለዚህ ነው ሙስሊም ሊቃውንት የሁለት ሴቶች አእምሯዊ ብቃትና የትውስታ አቅም የአንድ ወንድ ያህል እንደሆነ ያለ ምንም ማቅማማት የሚናገሩት፡፡[7]
ወንዶች በሴቶች ላይ ተፈጥሯዊ ብልጫ እንዳላቸው ቁርኣን እንዲህ ሲል ይናገራል፡-
“ወንዶች በሴቶች ላይ ቋሚዎች (አሳዳሪዎች) ናቸው፤ አላህ ከፊላቸውን በከፊሉ ላይ በማብለጡና (ወንዶች) ከገንዘቦቻቸው (ለሴቶች) በመስጠታቸው ነው፡፡ መልካሞቹም ሴቶች (ለባሎቻቸው) ታዛዦች አላህ ባስጠበቀው ነገር ሩቅን ጠባቂዎች ናቸው፡፡ እነዚያንም ማመጣቸውን የምትፈሩትን ገሥጹዋቸው፤ በመኝታዎችም ተለዩዋቸው፣ (ሳካ ሳታደርሱ) ምቱዋቸውም፡፡ ቢታዘዙዋችሁም (ለመጨቆን) በነርሱ ላይ መንገድን አትፈልጉ፡፡ አላህ የበላይ ታላቅ ነውና፡፡” (ሱራ 4፡34)
የእስልምና አስተምሕሮ ይህ ነው፡፡ የሴቶች ሰብኣዊ ዋጋ ከወንዶች ያነሰ ነው፡፡ ስለዚህም ባሎች ሚስቶቻቸውን እስከ መምታት ድረስ በእነርሱ ላይ የበላይነት

አላቸው። ለምስክርነት ከወንድ እኩል መቆም አለመቻላቸው ተፈጥሯቸውን በማሳነስ ከሚመለከተው እስላማዊ አስተምሕሮ የመነጨ ነው። ዘመናንኛ ሙስሊም ሰባኪያን ይህንን እውነታ አድበስብሰው እስልምናን ለሰዎች ኅሊና ምቹ ለማድረግ ጥረት ቢያደርጉም እስላማዊ መጻሕፍት በተገለጡ ቁጥር ከዚህ መራራ ሃቅ ጋር ለመጋፈጥ ይገደዳሉ።

[1] Tafseer Ibn Katheer, part 1, p. 724
[2] Sahih Al-Bukhari vol.1 no.301 p.181. See also Sahih Muslim vol.2 book 4 no.1982,1983 p.432
[3] Sahih al-Bukhari, Hadith Number 2393
[4] Sahih al-Bukhari, Volume 4, Book 53, Number 342; Aisha Bewley, The Sahih Collection of al-Bukhari, Chapter 66. Book of the Virtues of the Companions; source
[5] https://islamqa.info/en/98154
[6] Hidayah v.1 p. 215
[7] I’laam al-Muwaqqa’een, part 1, p. 75

## ኢየሱስ ያሕዌ ነው!
## ቅዱሳት መጻሕፍት ይመሰክራሉ

“የመጠበቂያ ግንብ” (Watchtower) የተሰኘው የሐሳውያን ማሕበር “ኢየሱስ ያሕዌ አይደለም” የሚል አቋም አለው። ይህ አቋሙም ከቅዱሳት መጻሕፍት የተወሰደ ስለመሆኑና የሰዎች ፈጠራ ስላለመሆኑ በአፅንዖት ይናገራል፡፡ በዘመናችን የሚገኙት ብዙ ሙስሊም ሰባኪያን ከዚህ ማሕበር የተቀዱ የሙግት ሐሳቦችን ተጠቅመው ክርስቲያኖችን ሲገዳደሩ ማየት የተለመደ ነው፡፡ ነገር ግን ቅዱሳት መጻሕፍትን በጥልቀት የመረመርን እንደሆን ኢየሱስ ያሕዌ እግዚአብሔር መሆኑ በማያጠራጥርና በማያሻማ ሁኔታ ተጽፎ እንመለከታለን፡፡ በዚህ ጽሑፍ ኢየሱስ ያሕዌ መኾኑን የሚመሰክሩ የቅዱሳት መጻሕፍት ምንባባትን እናቀርባለን። አንባቢያንም የቅዱሳት መጻሕፍቱን ምስክርነት በማገናዘብ የኢየሱስን ማንነት በተመለከተ ትክክለኛውን አቋም ይወስዱ ዘንድ እናበረታታለን።
እንደሚታወቀው “ያሕዌ” የሚለው ቃል የዕብራይስጥ ቃል እንደመሆኑ በግሪክ አዲስ ኪዳን ውስጥ ተጠቅሶ አናገኘውም። ስለዚህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ “ያሕዌ” ተብሎ መጠራቱን ለማረጋገጥ ቃሉ የተጠቀሰባቸውን የብሉይ ኪዳን ምንባባት ከአዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ጋር ማመሳከር ያስፈልገናል። በዚህ አግባብ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያሕዌ መሆኑን የሚያረጋግጡ የብሉይና የአዲስ ኪዳን ምንባባትን መሳ ለመሳ እናቀርባለን፡-

1. “አሕዛብ በአንድነት በተሰበሰቡ ጊዜ መንግሥታትም ለእግዚአብሔር (ያሕዌ) ይገዙ ዘንድ … አቤቱ፥ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ፥ ሰማያትም የእጅህ ሥራ ናቸው። እነርሱ ይጠፋሉ፥ አንተ ግን ትኖራለህ፤ ሁላቸው እንደ ልብስ

ያረጃሉ፣ እንደ መጐናጸፊያም ትለውጣቸዋለህ፣ ይለወጡማል፤ አንተ ግን ያው አንተ ነህ፣ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም።” (መዝ 102፡22-25)
መዝሙረኛው ይህንን ቅኔ እየተቀኘ ያለው ለያሕዌ ነው። በእብራይስጡ ንባብ ውስጥም “ያሕዌ” የሚለው ስም በተደጋጋሚ ተጠቅሶ የምናገኝ ሲሆን እርሱ “ያሕዌ” በማለት የሚቀኝለት አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደነበር የዕብራውያን ጻሐፊ እንዲህ ያረጋግጥልናል፡-
“ደግሞ፦ጌታ ሆይ [ኢየሱስ]፣ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ፣ ሰማዮችም የእጆችህ ሥራ ናቸው፤ እነርሱም ይጠፋሉ አንተ ግን ጸንተህ ትኖራለህ፤ ሁሉም እንደ ልብስ ያረጃሉ፣ እንደ መጎናጸፊያም ትጠቀልላቸዋለህ ይለወጡማል፤ አንተ ግን አንተ ነህ፣ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም ይላል።” (ዕብ 1፡10-12)።

2. “ይናገሩ ይቅረቡም በአንድነትም ይማከሩ፤ ከጥንቱ ይህን ያሳየ ከቀድሞስ የተናገረ ማን ነው? ያሳየሁም የተናገርሁም እኔ እግዚአብሔር (ያሕዌ) አይደለሁምን? ከእኔም በቀር ሌላ አምላክ የለም፤ እኔ ጻድቅ አምላክና መድኃኒት ነኝ፣ ከእኔም በቀር ማንም የለም። እናንተ የምድር ዳርቻ ሁሉ፣ እኔ አምላክ ነኝና፣ ከእኔም በቀር ሌላ የለምና ወደ እኔ ዘወር በሉ ትድኑማላችሁ። ቃሌ ከአፌ በጽድቅ ወጥታለች፣ አትመለስም፦ ጕልበት ሁሉ ለእኔ ይንበረከካል፣ ምላስም ሁሉ በእኔ ይምላል ብዬ በራሴ ምያለሁ።” (ኢሳ 45፡21-23)
ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በፊልጵስዩስ መልእክቱ ይህንኑ ቃል ለኢየሱስ ክርስቶስ በመጠቀም ያሕዌ መኾኑን ያጸናልናል፡-
“ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ፣ መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው።” (ፊል 2፡10-11)

3. “እንግዲህ አምላካችሁ እግዚአብሔር (ያሕዌ) የአማልክት አምላክ የጌቶችም ጌታ፣ ታላቅ አምላክ ኃያልም የሚያስፈራም፣ በፍርድ የማያደላ፣ መማለጃም የማይቀበል ነውና እናንተ የልባችሁን ሸለፈት ግረዙ፣ ክእንግዲህ ወዲህም አንገተ ደንዳና አትሁኑ።” (ዘዳ 10፡16-17)
ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ በራዕይ መጽሐፉ ይህኑን ቃል ለክርስቶስ በማዋል ጌታችን ኢየሱስ ያሕዌ መኾኑን አረጋግጦልናል፡-
“እነዚህ በጉን ይወጋሉ፤ በጉም የጌቶች ጌታና የነገሥታት ንጉሥ ስለ ሆነ እነርሱን ድል ይነሣል፣ ከእርሱም ጋር ያሉ የተጠሩና የተመረጡ የታመኑም ደግሞ ድል ይነሣሉ።” (ራዕይ 17፡14)

4. “የእስራኤል ንጉሥ እግዚአብሔር፣ የሚቤዠም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር (ያሕዌ) እንዲህ ይላል፦ እኔ ፊተኛ ነኝ እኔም ኋለኛ ነኝ፣ ከእኔ ሌላም አምላክ የለም። እንደ እኔ ያለ ማን ነው? ይነሣና ይጥራ ይናገርም፤ ከጥንት የፈጠርሁትን ሕዝብ ያዘጋጅልኝ፣ የሚመጣውም ነገር ሳይደርስ ይንገሩኝ።” (ኢሳ 44፡6)
ነብዩ ኢሳያስ በትንቢት መጽሐፉ የጻፈው ያሕዌ ስለኾነው ኢየሱስ ክርስቶስ መኾኑን ዮሐንስ በራዕይ መጽሐፉ እንዲህ ያረጋግጥልናል፡-
“እነሆ፣ በቶሎ እመጣለሁ፣ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ። አልፋና ዖሜጋ፣ ፊተኛውና ኋለኛው፣ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ።” (ራዕይ 22፡- 12 -13)

5. “ከእግዚአብሔር (ያሕዌ) ዘንድ ምሕረት፥ በእርሱም ዘንድ ብዙ ማዳን ነውና እስራኤል በእግዚአብሔር ይታመን። እርሱም እስራኤልን ከኃጢአቱ ሁሉ ያድነዋል።” (መዝ 130፡7-8)

መዝሙረኛው የተቀኘለት ሕዝቡን ከኃጢአታቸው የሚያድናቸው ያሕዌ ራሱ ጌታቸን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑ በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ እንዲህ ተጽፏል፡-

“እርሱ ግን ይህን ሲያስብ፥ እነሆ የጌታ መልአክ በሕልም ታየው፥ እንዲህም አለ፦ የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ፥ ከእርስዋ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ። ልጅም ትወልዳለች፤ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ።” (ማቴ. 20-21)

6. “በዳዊትም ቤት ላይ፥ በኢየሩሳሌምም በሚኖሩት ላይ፥ የሞገስንና የልመናን መንፈስ አፈስሳለሁ ወደ እርሱም ወደ ወጉት ይመለከታሉ ሰውም ለአንድያ ልጁ እንደሚያለቅስ ያለቅሱለታል፥ ሰውም ለበኵር ልጁ እንደሚያዝን በመራራ ኀዘን ያዝኑለታል።” (ዘካ 12፡10)

ለግልፅነት ያህል ይህንን ጥቅስ በአዲሱ መደበኛ ትርጉም እናንብበው፡- “በዳዊት ቤትና በኢየሩሳሌም ነዋሪዎቸ ላይ የርኅራኄና የልመና መንፈስ አፈሳለሁ፤ ወደ ወጉኝ ወደ እኔም ይመለከታሉ፤ እነርሱም ለአንድያ ልጅ እንደሚለቀስ ያለቅሱለታል፤ ለበኵር ልጅ ምርር ተብሎ እንደሚለቀስም አምርረው ያለቅሱለታል።”

አዲሱ መደበኛ ትርጉምና ብዙ የእንግሊዘኛ ትርጉሞች የተወጋው ያሕዌ እግዚአብሔር ራሱ መሆኑን በሚገልፅ ሁኔታ ተርጉመውታል። በ1954 ዕትም “ወደ ወጉት ወደ እርሱ” ተብሎ የተተረጎመው መጠነኛ የትርጉም ስህተት እንዳለበት ልብ ሊባል ይገባል።

በገዛ ወገኖቹ የተወጋው ያሕዌ ራሱ ጌታቸን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን የራዕይ መጽሐፍ እንዲህ ያረጋግጥልናል፡-

“እነሆ፥ ከደመና ጋር ይመጣል፤ ዓይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል፥ የምድርም ወገኖቸ ሁሉ ስለ እርሱዋይ ዋይ ይላሉ። አዎን፥ አሜን።” ራእይ 1፡- 7።

7. “እንዲህም ይሆናል፤ የእግዚአብሔር (ያሕዌ) ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል እግዚአብሔርም እንደ ተናገረ፥ በጽዮን ተራራና በኢየሩሳሌም መድኃኒት ይገኛል። ደግሞም እግዚአብሔር የጠራቸው፥ የምስራች የሚሰበክላቸው ይገኛሉ።” (ኢዩ 2፡32)

ስሙን ስንጠራ የሚያድነን ያሕዌ ራሱ ጌታቸን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለመሆኑ በሮሜ መጽሐፍ እንዲህ ተጽፏል፡-

“የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና” (ሮሜ 10፡13)

8. “እግዚአብሔር (ያሕዌ) እረኛዬ ነው፥ የሚያሳጣኝም የለም። በለመለመ መስክ ያሳድረኛል በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል።” (መዝ 23፡1-2)

መዝሙረኛው ያሕዌ ሲል የተቀኘለት እረኛቸን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡-

“በዙፋኑ መካከል ያለው በግ (ኢየሱስ) እረኛቸው ይሆናልና፥ ወደ ሕይወትም ውኃ ምንጭ ይመራቸዋልና፤ እግዚአብሔርም እንባዎቸን ሁሉ ከዓይናቸው ያብሳል።” (ራእይ 7፡17)

9. “እነሆ፥ ጌታ እግዚአብሔር (ያሕዌ) እንደ ኃያል ይመጣል ክንዱም ስለ እርሱ ይገዛል እነሆ፥ ዋጋው ከእርሱ ጋር ደመወዙም በፊቱ ነው።” (ኢሳ 40፡10)

በተመሳሳይ መልኩ፤ በዚህ ክፍል “ያሕዌ” የተባለው ጌታቸን ኢየሱስ ክርስቶስ

መኾኑን ቅዱስ ዮሐንስ መስክሯል፡-
“እነሆ፣ በቶሎ እመጣለሁ፤ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ። አልፋና ዖሜጋ፥ ፊተኛውና ኋለኛው፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ። ወደ ሕይወት ዛፍ ለመድረስ ሥልጣን እንዲኖራቸው በደጆቹዋም ወደ ከተማይቱም እንዲገቡ ልብሳቸውን የሚያጥቡ ብፁዓን ናቸው። ውሻዎችና አስማተኞች ሴሰኞዎችም ነፍሰ ገዳዮችም ጣዖትንም የሚያመልኩት ውሸትንም የሚወዱና የሚያደርጉ ሁሉ በውጭ አሉ። እኔ ኢየሱስ በአብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ይህን እንዲመሰክርላችሁ መልአኬን ላክሁ። እኔ የዳዊት ሥርና ዘር ነኝ፥ የሚያበራም የንጋት ኮከብ ነኝ።” (ራዕይ 22፡12-16)

10. “የእስራኤል ንጉሥ እግዚአብሔር (ያሕዌ)፥ የሚቤዠም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር (ያሕዌ) እንዲህ ይላል፦ እኔ ፊተኛ ነኝ እኔም ኋለኛ ነኝ፥ ከእኔ ሌላም አምላክ የለም።” (ኢሳ 44፡6)

በዚህ ክፍል “ፊተኛውና ኋለኛው” በማለት የሚናገረው ያሕዌ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፦
“... እንዲህም አለኝ፦ አትፍራ፤ ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ፥ ሞቼም (ኢየሱስ) ነበርሁ እነሆም፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ፥ የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ።” (ራእይ 1፡17-18)

11. “ንጉሡ ዖዝያን በሞተበት ዓመት እግዚአብሔርን በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ አየሁት፥ የልብሱም ዘርፍ መቅደሱን ሞልቶት ነበር። ሱራፌልም ከእርሱ በላይ ቆመው ነበር፥ ለእያንዳንዱም ስድስት ክንፍ ነበረው በሁለት ክንፍ ፊቱን ይሸፍን ነበር፥ በሁለቱም ክንፍ እግሮቹን ይሸፍን ነበር፥ በሁለቱም ክንፍ ይበር ነበር። አንዱም ለአንዱ። ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር (ያሕዌ) ምድር ሁሉ ከክብሩ ተሞልታለች እያለ ይጮኽ ነበር።” (ኢሳ 6፡1-3)

ኢሳይያስ ረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ተቀምጦ ያየው ያሕዌ እግዚአብሔር ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደነበር ቅዱስ ዮሐንስ በወንጌሉ አረጋግጦልናል፡-
“ኢሳይያስ ደግሞ። በዓይኖቻቸው እንዳያዩ፥ በልባቸውም እንዳያስተውሉ፥ እንዳይመለሱም፥ እኔም እንዳልፈውሳቸው፥ ዓይኖቻቸውን አሳወረ ልባቸውንም አደነደነ ብሎአልና ስለዚህ ማመን አቃታቸው። ክብሩን ስለ አየ ኢሳይያስ ይህን አለ፥ ስለ እርሱም ተናገረ።” (ዮሐ 12፡39-41)

12. አንቺ ከባቢሎን ሴት ልጅ ጋር የምትኖሪ ጽዮን ሆይ፥ኰብልዪ። የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፦ ከክብሩ በኋላ ወደ በዘበዙአችሁ አሕዛብ ልኮኛል፤ የሚነካችሁ የዓይኑን ብሌን የሚነካ ነውና። እነሆ፥ እጄን በላያቸው አወዛውዛለሁ፥ ተገዝተው ለነበሩት ብዝበዛ ይሆናሉ፤ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርም እንደ ላከኝ ታውቃላችሁ። የጽዮን ልጅ ሆይ፥ እነሆ፥ መጥቼ በመካከልሽ እኖራለሁና ዘምሪ ደስም ይበልሽ፥ ይላል እግዚአብሔር። በዚያም ቀን ብዙ አሕዛብ ወደ እግዚአብሔር ይጠጋሉ፥ ሕዝብም ይሆኑኛል፤ በመካከልሽም እኖራለሁ፥ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርም ወደ አንቺ እንደ ላከኝ ታውቂአለሽ።” (ዘካ 2፡8-10)

ይህንን ጥቅስ ልብ ብለን ያነበብን እንደሆን “ያሕዌ” ተብለው የተጠሩ ሁለት አካላትን እናስተውላለን። ያሕዌ ተብሎ የተጠራው አንዱ አካል ላኪ ሲሆን

በሕዝቡ መካከል እንዲኖር የተላከውም ሁለተኛው አካል ያሕዌ ተብሎ ተጠርቷል፡ ፡ ቅዱስ ዮሐንስ በወንጌሉ ከያሕዌ ዘንድ የተላከው “ያሕዌ” ክርስቶስ መኾኑን ይመሰክርልናል፡-

“ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ፥ አንድ ልጅም (ኢየሱስ) ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነው ክብሩን አየን።” (ዮሐ 1፡14)

13. “ያዕቆብ ሆይ፥ የጠራሁህም እስራኤል ሆይ፥ ስማኝ እኔ (ያሕዌ) ነኝ እኔ ፊተኛው ነኝ እኔም ኋለኛው ነኝ።” (ኢሳ 48፡12)

በተከታዩ የአዲስ ኪዳን ጥቅስ መሠረት ያኔ በብሉይ እኔ “ፊተኛው ነኝ እኔም ኋለኛው ነኝ” ይለን የነበረው አምላክ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፦

“በሰምርኔስም ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፡፡ ሞቶ የነበረው (ኢየሱስ) ሕያውም የሆነው ፊተኛውና መጨረሻው እንዲህ ይላል፡፡” ራእይ 2፡- 8፡፡

14. “አላወቅህምን? አልሰማህምን? እግዚአብሔር የዘላለም አምላክ፥ የምድርም ዳርቻ ፈጣሪ ነው አይደክምም፥ አይታክትም፥ ማስተዋሉም አይመረመርም፡፡” ኢሳ 40፡- 28፡፡

በክፍሉ እንደተጻፈው ምድርንና ዳርቻዋን የፈጠረው ያሕዌ ጌታ ኢየሱስ ነው፡-

“ሁሉ በእርሱ ሆነ፥ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም።” (ዮሐ 1፡3)

15. “የአዋጅ ነጋሪ ቃል። የእግዚአብሔርን (ያሕዌ) መንገድ በምድረ በዳ ጥረጉ፥ ለአምላካችንም ጐዳና በበረሀ አስተካክሉ።” (ኢሳ 40፡3)

ኢሳይያስ በትንቢቱ የያሕዌን መንገድ ጥረጉ ሲል የጻፈው ስለ ኢየሱስ መኾኑን ወንጌላዊው ቅዱስ ማርቆስ በሚገባ ዘግቦልናል፡-

“እነሆ፥ መንገድህን የሚጠርግ መልክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ የጌታን (የኢየሱስን) መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ ተብሎ በነቢዩ በኢሳይያስ እንደ ተጻፈ” (የማርቆስ ወንጌል 1፡2-3)

16. “እኔ እግዚአብሔር (ያሕዌ) ለሰው ሁሉ እንደ መንገዱ፥ እንደ ሥራው ፍሬ እሰጥ ዘንድ ልብን እመረምራለሁ ኵላሊትንም እፈትናለሁ።” (ኤርምያስ 17፡ 10)፡፡

በራዕይ መጽሐፍ ውስጥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ በማለት ተናግሯል፡-

“አብያተ ክርስቲያናትም ሁሉ ኵላሊትንና ልብን የምመረምር እኔ እንደ ሆንሁ ያውቃሉ” (ራእይ 2፡23)

ከላይ ከቀረቡት ጥቅሶች በተጨማሪ ሊመጣ ያለው መሲህ ያሕዌ መሆኑን ቅዱሳን ነቢያት በብዙ መንገዶች ተናግረዋል። ለምሳሌ ያሕል ነቢዩ ኤርሚያስ እስራኤልን ለማዳን የሚመጣው አዳኝ “ያሕዌ ጽድቄኑ” (እግዚአብሔር ጽድቃችን) በሚል ስም እንደሚታወቅ እንዲህ ተናግሯል፡-

“እነሆ፥ ለዳዊት ጻድቅ ቍጥቋጥ የማስነሣበት ዘመን ይመጣል፥ ይላል እግዚአብሔር፥ እርሱም እንደ ንጉሥ ይነግሣል፥ ይከናወንለታልም፥ በምድርም ፍርድንና ጽድቅን ያደርጋል። በዘመኑም ይሁዳ ይድናል እስራኤልም ተዘልሎ ይቀመጣል፥ የሚጠራበትም ስም፦ እግዚአብሔር ጽድቃችን ተብሎ ነው።” (ኤር 23፡5-6)

ነቢዩ ሚክያስ በትንቢቱ ሊመጣ ያለው መሲህ ዘላለማዊ መሆኑን እንዲህ ይናገራል፡-

“አንቺም ቤተ ልሔም ኤፍራታ ሆይ፥ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ፤ ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ፥ በእስራኤልም ላይ ገዥ የሚሆን ይወጣልኛል።” (ሚክ 5፡2)
ነቢዩ ኢሳይያስም ስለ ኢየሱስ ዘላለማዊነት ተመሳሳይ ነገር ተናግሯል፤ አማላክነቱንም እንዲህ ያውጃል፡-
“ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።” (ኢሳ 9፡6)
ነቢዩ ዳንኤልም ስለ ኢየሱስ አምላክነት እንዲህ ሲል መስክሯል፡-
“በሌሊት ራዕይ አየሁ እነሆም፥ የሰው ልጅ የሚመስል ከሰማይ ደመናት ጋር መጣ በዘመናት ወደ ሸመገለውም ደረሰ ወደ ፊቱም አቀረቡት። ወገኖችና አሕዛብ በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገሩ ሁሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትና ክብር መንግሥትም ተሰጠው ግዛቱም የማያልፍ የዘለዓለም ግዛት ነው፥ መንግሥቱም የማይጠፋ ነው።” (ዳን 7፡13-14)
በዚህ ጥቅስ መሠረት ይህ የሰው ልጅ የተባለው አካል ህዝቦችን ሁሉ የሚገዛ፤ የማያልፍ የዘለዓለም ግዛት ያለውና የማይጠፋ መንግሥት ያለው ነው። ከአምላክ በስተቀር ህዝቦች ሁሉ ሊገዙት የሚገባ፣ ዘለዓለማዊ ግዛትና መንግሥት ሊኖረው የሚችል ማነው? በዚህ ጥቅስ ውስጥ መገዛትን ለማመልከት ጥቅም ላይ የዋለው “ፕላኽ” የሚለው የአረማይክ ቃል ለፈጣሪ ብቻ የሚሆን አምልኮን የሚያመለክት መሆኑ ልብ ሊባል ይገባል። ኢየሱስ “የሰው ልጅ” የሚለውን ማዕርግ በተደጋጋሚ በመጠቀም ሥጋን ለብሶ የመጣ አምላክ መሆኑን ግልፅ አድርጓል (ማርቆስ 13፡ 23-27፤ 14፡60-64)።
ስለዚህ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያሕዌ እግዚአብሔር ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት ይህንን ያረጋግጣሉ!

## እግዚአብሔር በብዙ ቁጥር የተገለጸባቸው ጥቅሶች
## አምላካችን ሥላሴ ስለመሆኑ የማይታበሉ ማስረጃዎች

በክርስትና አስተምሕሮ መሠረት እግዚአብሔር ሥላሴ ነው። ይህም ማለት አንዱ መለኮት አብ፣ ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ በተሰኙ ሦስት አካላት ይኖራል ማለት ነው። ይህ አስተምህሮ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ጠልቶ የተመሠረተ አስደናቂ አስተምህሮ ነው። የእግዚአብሔር ሥሉስ አሓዳዊነት በአዲስ ኪዳን ይበልጥ የተገለጠ ቢሆንም ከዘመነ ብሉይ ጀምሮ በተለያዩ መንገዶች ታይቷል። ከእነዚህ መንገዶች መካከል አንዱ እግዚአብሔር አምላክ በነጠላ ቁጥር ብቻ ሳይሆን በብዙ ቁጥርም ጭምር መገለጹ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች በተወሰኑ አጋጣሚዎች እነዚህን ጥቅሶች በትክክለኛው መንገድ ቢተረጉሙም (ዘፍ. 1፡ 26፤ 3፡5፤ 22፤ 11፡7፤ ኢሳ. 6፡8፤ 48፡16) በብዙ አጋጣሚዎች ይህንን ብዝኅነት በትክክለኛው መንገድ ከመተርጎም ይልቅ በነጠላ ቁጥሮች በመተርጎማቸው ሳብያ ከብዙ ወገኖች የተሰወረ ሆኗል። በዚህ ጽሑፍ በዋናው የእብራይስጥ ንባብ በብዙ ቁጥር የተነገሩ ሆነው ሳሉ ተርጓሚዎች በነጠላ ቁጥር የተረጎሟቸውን ጥቅሶች እናቀርባለን። በእግዚአብሔር ሥላሴነት ላይ ጥርጣሬ ያላቸው ወገኖች

መጽሐፍ ቅዱሳችን ለሥላሴ አስተምህሮ የሚሰጠውን የማያወላዳ ምስክርነት በማስተዋል እውነትን ወደ ማወቅ ይመጡ ዘንድ ጸሎታችን ነው፡-

ማሳሰብያ፡- የእብራይስጥ አጻጻፍ እንደ አረብኛ ከቀኝ ወደ ግራ ቢሆንም የኔ ኮምፒውተር ግን የቃላቱን አደራደር ከግራ ወደ ቀኝ አስቀምጧል፡፡

ማሳያ አንድ

ዘፍጥረት 20፡13 "እግዚአብሔርም ከአባቴ ቤት ባወጣኝ ጊዜ አልኋት..."

በዚህ ጥቅስ ውስጥ (ካዓሼር ሂትዑ ኦቲ ኤሎሂም) ማለት በአማርኛ እንደተተረጎመው ሳይሆን "ኤሎሂም ... ባወጡኝ ጊዜ" ማለት ነው፡፡ "ሂትዑ" የ (ታህ) ሦስተኛ መደብ ብዙ ቁጥር ሲሆን "አስኬዱኝ"፣ "አወጡኝ" ወይም "አንከራተቱኝ" (they caused me to wander) ተብሎ በብዙ ቁጥር ይተረጎማል፡፡

ማሳያ ሁለት

ዘፍጥረት 35፡7 "በዚያም መሰውያውን ሠራ፡ የዚያንም ቦታ ስም ኤልቤቴል ብሎ ጠራው፤ እርሱ ከወንድሙ ፊት በሸሸበት ጊዜ እግዚአብሔር በዚያ ተገልጦለት ነበርና፡፡"

ይህ ጥቅስ በእብራይስጥ "ሻም ኒግሉ ኢላው ሀኤሎሂም" ይላል፡፡ (ኒግሉ) የሚለው ቃል የ "ጋላህ" ሦስተኛ መደብ ብዙ ቁጥር ሲሆን ቀጥተኛ ትርጉሙ "ተገለጡለት" የሚል ነው፡፡ ስለዚህ በቀጥታ ጥቅሱ ሲተረጎም "ኤሎሂም በዚያ ተገለጡለት" የሚል ይሆናል፡፡

ማሳያ ሦስት

ዘዳግም 4፡7 "በምንጠራው ጊዜ ሁሉ አምላካችን እግዚአብሔር ለእኛ ቅርብ እንደሆነ አማልክቱ የሚቀርቡት ሌላ ታላቅ ሕዝብ ማነው?"

በዚህ ጥቅስ ውስጥ "ቅርብ" የሚለው ቃል በእብራይስጥ "ቃሩቢም" የሚል ሲሆን "የቃሮብ" ብዙ ቁጥር ነው፡፡ ጥቅሱ በቀጥታ ሲተረጎም "ኤሎሂም ለእኛ ቅርብ እንደሆኑ" የሚል ትርጉም ይሰጣል፡፡

ማሳያ አራት

ዘዳግም 10፡16–17 "እንግዲህ አምላካችሁ እግዚአብሔር የአማልክት አምላክ የጌቶችም ጌታ፥ ታላቅ አምላክ ኃያልም የሚያስፈራም፥ በፍርድ የማያደላ፥ መማለጃም የማይቀበል ነውና እናንተ የልባችሁን ሸለፈት ግረዙ፥ ከእንግዲህ ወዲህም አንገተ ደንዳና አትሁኑ፡፡"

የእብራይስጡ ንባብ (ያሕዌ ኤሎሂከም ሁ ኤሎሄይ ሃኤሎሂም ወ አዶኔይ ሃአዶኒም) የሚል ሲሆን ቃል በቃል ሲተረጎም "ያሕዌ አምላኮቻችሁ የአማልክት አምላኮች እና የጌቶች ጌታዎች ነው" የሚል ትርጉም ይሰጣል፡፡ በዚህ ጥቅስ ውስጥ "ኤሎሂከም" (አምላኮቻችሁ)፣ "ኤሎሄይ" (አምላኮች)፣ "አዶኔይ" (ጌታዎች) የሚሉት ቃላት ሁሉ ለያሕዌ ጥቅም ላይ የዋሉ ቢሆኑም ብዙ ቁጥር ናቸው፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች መሰል ቃላትን በቀጥተኛ ትርጉማቸው ማስቀመጥ ከተለመደው የሰዎች መረዳት አንጻር ወደ መድብለ አማልክትነት የተሳሳተ ድምዳሜ ሊመራ እንደሚችል ስላሰቡ በነጠላ ቢተረጉሟቸውም እውነታው ግን ብዙ ቁጥር አመልካች መሆናቸው ነው፡፡ የሥላሴን ትምህርት ለተረዳ ሰው ግን ጥያቄ የሚፈጥሩ አይደሉም፡፡ እግዚአብሔር በመለኮቱ አንድ ቢሆንም በአካል ግን ሦስት ነው፡፡

ማሳያ አምስት
2ኛ ሳሙኤል7፡23 "ለእርሱ ለራሱ እንዲሆን ሕዝብን ይቤዥ ዘንድ ለእርሱ ለራሱም ስም ያደርግ ዘንድ፡ በአሕዛብና በአምላኮቻቸውም ፊት ከግብጽ በተቤዠው ሕዝብ ፊት ተአምራትንና ድንቅን ያደርግ ዘንድ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) እንደ ሄደለት እንደ ሕዝብህ እንደ እስራኤል ያለ በምድር ላይ ምን ሕዝብ አለ?"
ጥቅሱ (ሐለኩኤለሂም)የሚለውየአማርኛተርጎሚዎችእንዳስቀመጡት ሳይሆን "ኤሎሂም እንደ ሄዱለት" የሚል ነው ምክንያቱም የ (ሐለከ) ሦስተኛ መደብ ብዜት ነውና።
ማሳያ ስድስት
ዘጸአት 33፡14-15 "እግዚአብሔርም፦ እኔ ከአንተ ጋር እሄዳለሁ፥ አሳርፍህማለሁ አለው። እርሱም፦ አንተ ከእኛ ጋር ካልወጣህስ፥ ከዚህ አታውጣን።"
በዚህ ጥቅስ ውስጥ "እኔ ከአንተ ጋር እሄዳለሁ" ተብሎ የተተረጎመው በእብራይስጥ (ፓነይ ይልኩ) የሚል ሲሆን በቀጥታ ሲተረጎም "ኃልዎቴ [ከአንተ ጋር] ይሄዳሉ" የሚል ነው። "ይልኩ" የሚለው ቃል ነጠላ ሳይሆን ብዙ ቁጥር ነው። እንዲሁም "አንተ ከእኛ ጋር ካልወጣህስ" የሚለውም (ዒም ዒን ፓኔካ ሆለኪም) ተብሎ የሚነበብ ሲሆን "ሆለኪም" የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር በመሆኑ "ኃልዎትህ ከኛ ጋር ካልሄዱ" የሚል ትርጉም ይሰጣል።
ማሳያ ሰባት
ኢዮብ 35፡10 "ነገር ግን፦ በሌሊት መዝሙርን የሚሰጥ፥ ከምድርም እንስሶች ይልቅ የሚያስተምረን ከሰማይም ወፎች ይልቅ ጥበበኞች የሚያደርገን፤ ፈጣሪዬ እግዚአብሔር ወዴት ነው? የሚል የለም።"
በዚህ ጥቅስ ውስጥ "ፈጣሪዬ እግዚአብሔር" የሚለው በእብራይስጥ (ኤሎሃ ዖሼይ) የሚል ሲሆን "ዖሼይ" የሚለው ቃል ብዙ ቁጥር በመሆኑ ቃል በቃል ሲተረጎም "ኤሎሂም ፈጣሪዎቼ" የሚል ትርጉም ይሰጣል።
ማሳያ ስምንት
መዝሙር 58፡11 "ሰውም፦ በእውነት ለጻድቅ ፍሬ አለው፤ በእውነት በምድር ላይ የሚፈርድ አምላክ አለ ይላል።"
መዝሙረኛው ዳዊት "ኤሎሂም ሾፌጢይም" የሚል ብዙ ቁጥር የተጠቀመ ሲሆን ፣ ቃል በቃል ብንተረጉመው "በምድር ላይ የሚፈርዱ ኤሎሂም" ማለት ነው።
ማሳያ ዘጠኝ
ዘዳግም 5፡26 "ከሥጋ ለባሽ ሁሉ እኛ እንደ ሰማን በእሳት ውስጥ ሆኖ ሲናገር የሕያው አምላክን ድምፅ ሰምቶ በሕይወቱ የኖረ ማን ነው?"
"የሕያው አምላክን ድምፅ" ተብሎ የተተረጎመው በእብራይስጡ (ቆል ኤሎሂም ሐይም) የሚል ሲሆን በቀጥታ ሲተረጎም "የሕያዋን ኤሎሂም ድምፅ" የሚል ነው፤ ምክንያቱም "ሐይም" የሚለው ቅፅል የ (ኸይ) ተባዕታይ ብዙ ቁጥር ነውና።
ማሳያ አሥር
ኢያሱ 24፡19 "ኢያሱም ሕዝቡን፦ እርሱ ቅዱስ አምላክ ነውና፡ እርሱም ቀናተኛ አምላክ ነውና እግዚአብሔርን ማምለክ አትችሉም፤ መተላለፋችሁንና

ኃጢአታችሁን ይቅር አይልም።”
“ቅዱስ” ተብሎ የተተረጎመው የዕብራይስጥ ቃል “ቃዶሺም” የሚል ሲሆን “ቅዱሳን” ተብሎ ሊተረጎም የሚችል የብዜት ቅፅል ነው። ስለዚህ ምንባቡ “እርሱ ቅዱሳን አምላክ ነው” ተብሎ ቢተረጎም የዕብራይስጡን ሐሳብ ይበልጥ ይገልጻል።

ማጠቃለያ

ከላይ በተመለከትናቸው ጥቅሶች ውስጥ የነጠላና የብዜት ስሞች፣ ቅፅሎች፣ ግሦች፣ ወዘተ. ተሰባጥረው መምጣታቸው እግዚአብሔር በባሕርዩው አንድ ቢሆንም ነገር ግን በአካል ከአንድ በላይ መሆኑን የሚያረጋግጥ ስለሆነ የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት የሚያጠናክር የማይታበል ማስረጃ ነው። በእርግጥ እነዚህ ጥቅሶች በብዙ ቁጥር ቢናገሩም የቁጥሩን መጠን አይገልጹም። ስለ እግዚአብሔር ሥላሴነት የሚናገሩ መሆናቸውን ለመረዳት ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማገናዘብ አስፈላጊ ነው። ትምህርተ ሥላሴን የማይቀበሉ ወገኖች በብዙ ቁጥር የተቀመጡትን እነዚህን ቃላት ከእግዚአብሔር አንድነት አኳያ በበቂ ሁኔታ ማብራራት ይጠበቅባቸዋል። ነገር ግን ቃላቱ ከትምሕርተ ሥላሴ ውጪ ሊብራሩ የሚችሉበት ምንም ዓይነት መንገድ የለም።